1· የኢትዮጵያ ነገ [illegible] ቸው በተለይ [illegible] ስለነበር ይህ [illegible] ምንም እን [illegible] ስመቀበል [illegible] ሰው [illegible] ማለት [illegible] (Sacre Ecclesiae) [illegible] በ [illegible] ቤ ተ [illegible] ሥርዓት (caesaro-papismus) [illegible][27]

[illegible]

21· [illegible]

22· [illegible]

23· [illegible]

24· [illegible]

25· [illegible]

26· [illegible]

27· [illegible] 227

28. Paulos Tzadua, The Fetha Nagast in the practice of the Ethiopian church Wien 1973 [illegible]

ጉዳዮችን የሚመለከተው የመጀመሪያው ክፍል ድንጋጌዎች በሲኖዶስ አማካይነት ገብተው ይታወቁ ስለነበር አዲስ የነበረውን ሥጋዊ ክፍሉን አስመልክቶ ፍትሐ ነገሥት የሚለው ስያሜ-ርእስ ሊሰጠው እንደቻለ የሚያመለክተው አስተሳሰብ ነው[29] ።

ፍትሐ ነገሥት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተመለሰውና በሥራ ላይ የዋለው በንጉሠ ነገሥቱ አፄ ዘርዐያዕቆብ (1444 – 1468) ጥያቄና ፍላጎት ስለ ነበር ለዚሁ ጥያቄና ፍላጎት ባለቤት ንጉሠ ነገሥት አፄ ዘርዐያዕቆብ ክብር ሲባል የተሰጠ ይሆናል ብሎም መገመት ይቻላል ።

ሆኖም ምክንያቶቹ እንደተጠበቁ ሁነው "ፍትሐ ነገሥት" የሚለው ስያሜ ሁለተኛውን ክፍል – ሥጋዊ ክፍልን ብቻ የሚመለከት ሁኖ ከመገኘቱ የተነሳ ከመጽሐፉ ሙሉ ይዘትና ቅርጽ አንፃር ሲታይ የዐረብኛው ሰነድ ርእስ "ጉባኤ ቀኖናት" በታየበት መልኩ ይህም ተቀባይነት ማግኘቱ አስቸጋሪ ነው ። ነገር ግን ይህ "ጉባኤ ቀኖናት" ዘአብን አል አሳል (ፍትሐ ነገሥት) "ብሔረ ሕጊ ወቀኖና" (Nomocanon) ዘኢብን አል አሳል" ተብሎም ይጠራል[30] ።

ስለዚህ ይህን ርእስንና ሌሎችንም ተዛማጅ ርእሶች መመልከቱ ሌላው ምንአልባት የተሻለውን አማራጭ ርእስ በማግኘት ይረዳል የሚል እምነት ስለአለን የሚከተሉትንም ርእሶች ማገናዘብ ይቻላል ።

4· ምእላደ — ብሔረ ሕግ መንፈሳዊ ወሕግ ሥጋዊ Corpus-Codex Iuris Canonici Ft Civilis

ፍትሐ ነገሥት አሁንም በአንድ ክፍል ከቤተክርስቲያን ሕገጋት

[29]. I. I. Guidi: IL Fetha Nagast ገጽ VIII

[30]. 2. P.Dib: "Lequel des Ibn al-'Assal est L'Auteur du Nomocanon"? in R.O.C.T. 20/1915-1917 ገጽ104። D'Emilia la compravendita nel capitolo XXXIII del Nomocanone di ibn al-Assal, (Milano 1938) D' Emilia, Influssi di diritto Mussulmano nel capitolo XVIII2. del Nomocanone di ibn al-Assal R.S.D.T. 19/1940 Fasc.1. ገጽ 1–15፡ P.Tzadua, Fetha Nagest.. ገጽ XV Riedel. Die kirchenrechtsquellen Des patriarchats Alexandrien Oder nomocanon des Ibn Al-Assal-Fetha Negest) Leipzig 1906 ገጽ 115–119።

Νευοδίου Λέμπης: Ο Χριστιανισμός καί ο Ιουδαϊσμός εν Αιθιοπία, Νουβία καί Μερόη Μέρος Α: ΑΘΗΝΑΙ 1979 ገጽ 164–169

ቀኖናውያት በይበልጥ መንፈሳዊ ክፍሉን በሚመለከት በአንጻሩም ሥጋዊ ክፍሉን በሚመለከት ከሮማ ቢዛንቲን ነገሥታት ሕገጋት ተማእልዖ የተቀረጸ እንደመሆኑ መጠን ከአንጻራውያን ሥራዎች ጋር ሲነጻጸር ምእላደ ሕግ መንፈሳዊ ወሕግ ሥጋዊ ወይም ብሔረ ሕግ መንፈሳዊው ሥጋዊ - Corpus ወይም Codex Iuris Canonici Et Civilis ተብሎ መሰየም እንደነበረበት ሌላው አማራጭ ነበር ማለትም ፍትሐ ነገሥት ወይም ብሔረ ሕግወቀኖና ዘአብን አል አሳል ከይዘቱና ከቅርጹ የተነሳ (አንጻር) ሲመረመር ይህ ርእስ ተገቢም ሆኖ ይሰማል ።

ሆኖም በአጭሩ Corpus Iuris Canonici ወይም Codex Iuris Civilis የሚሉት ሐረጎች ማለትም የታወቁት አርእስተ ነገሮች ምን ማለት እንደሆኑ መመልከት እንችላለን ።

4·1·ሀ ምእላደ ሕግ ቀኖናዊ – Corpus Iuris canonici

በቤተክርስቲያን ሥርዐተ ሕግ ቀኖናዊ "Corpus Iuris Canonici በሚባል የሚታወቀው ምዕላደ ሕግ ቀኖናዊ ከተለያዩ የገልና የቤተክርስቲያን ጉባዔያተ ቀኖናት ፥ ሊቃነ ጳጳሳት (ፓፓዎች) ውሳኔዎችና ድንጋጌዎች የተቀነባበረው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ቀኖናዊ ሕግ ነው ። የግል ጉባኤያት 1) Concordia Discordantium Canonum (Decretum gratiani) 1140.2) Extravagantes Constituiones Johannis XXII (1316-1334) 3) Extravagantes Communes – Jean Chapuis 1500.

– የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት – አሌፃል ጉባኤያት 1) Decretales Gregorianac ወይም Liber Extravagantium (Decretalium Extra vagantium Decretum ከግርጎርዮስ 9ኛ (1234) 2) Liber Sextus Boniphatius 7ኛ (12[illegible]) 3), Clementinae Constitutiones ከ ቀለሜንጦስ 5ኛ ተዘጋጅቶና ቀይቶ በዮሐንስ 22ኛ የታወጀ 1317

4·1·ለ ብሔረ ሕግ ቀኖናዊ Codex Iuris Canonici

ከላይ የተመለከተው እየተሻሻለና በፓፓዎች ድንጋጌዎች እየተጨላ መጥቶ የተቀነባበረው የአሁኑ Corpus Inris Canonici የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ቀኖናዊ ሕግ ነው ። Codex Iuris Canonici በፒዮስ 10ኛ (1904)

ተጀቁም በካርዲናል ጴጥሮስ (Pietro Casp.) በሚመራ ኮሚቴ[31] ተዘጋጅቶና በበነዲክቶስ 15ኛ ጳጳሳት ግንቦት 27/1917 ታውጆ በዓመቱ ግንቦት 19/1918 በሥራ ላይ የዋለ[32] ቀኖናዊ ሕግ ነው ። Codex Iuris Canonici 2414 አንቀጾች (ቀኖናት) ሲኖሩት በሚከተሉት መጻሕፍት ወይም አርእስት ተከፍሎ ይገኛል ።

1. Normae Generales 2. De personis
3. De Rebus 4. De processibus 5. De Poenis

እንግዲህ ይህ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን Codex Iuris Canonici ከቤተክርስቲያን [illegible] — ትእዛዞችና ከመንግሥታት ጋር በሚደረጉ ስምምነቶች (Concordacin) [illegible] በሥራ ላይ የሚገኘው ቀኖናዊ ሕግ (Lex Lata) ነው ።

4·2 <u>[illegible] ሕግ ሥጋዊ — Corpus iuris civilis</u>

Corpus Iuris Civilis የቢዛንታይን ንጉሠ ነገሥት ዩስጢኒያኖስ ሕግ [illegible] ነው ። ይህ [illegible] ቃል — ስያሜ ግን የተቀረጸው በ1604 [illegible] Denis Gothoredus ነው ።

Iuris Civilis [illegible] ሥርዐተ ሕግ በሰፊ ዕንስ ሕባቡ [illegible] ሕግ (ius Naturale) ጋር ከሚመስለው ዓለም አቀፍ ዓይነት ሕግ (ius Gentium) ወይም ከሰዎች ልጆች የጋራ ሥነ አእምሮአዊ [illegible] ጋር Naturalis Ratio[33] በተቃራኒ የእየአንድ አንዱ አገር ሕግ [illegible][34] [illegible] ነገሥት በአንድ በኩል መንፈሳዊ ሕግንና ሥጋዊ ሕግንና [illegible] የያዘ — መድበለ ሕግ ሕጋዊ ወሕግ መንፈሳዊ [illegible] በኩል ፍትሐ ነገሥት ሕግ ሥጋዊ ወሕግ [illegible] ርእስ ስለሚታወቅ በላቲን የሚታወቀው — Corpus Iuris Canonici et Civilis ወይም Codex Iuris Canonici Et Civilis አምሳያ ርእስ ሆኖ ይታያል ።

ነገር ግን [illegible] ሕግ ወቀኖና — Nomocanon የተሻለው [illegible]

31. Motu Proprio: Arduum Sane munus (ቅእዘዝ)
32. Const. Providentissima Mater Ecclesia (አዋጅ)
33. Gaius 1.1.9
34. Gaius 1.1.10

5· ብሒረ ሕግ ወቀኖና

5·1 የቃሉ ጥምርነት ትርጉም

“ፍትሐ ነገሥት” በሌላ በኩል [illegible] (Nomocanon) ዘእብን እል አሳል በመባል ይታወቃል ። [illegible] መጽሐፍ — ፍትሐ ነገሥት ይዘትና [illegible] አይደለም? የሚለውን አስተሳሰብ [illegible] Nomocanon ምን ማለት [illegible] ።

በግሪክ ድርብ ቃላት (Compound Words) [illegible] መሠረት ለምሳሌ ፍልስፍና (Philosophy —) [illegible] (Philosopher) [illegible] : [illegible] (Theologos) [illegible] መለኮት : ፊላታዎስ (Philotheos) [illegible] : ቴዎፍሎስ (Theophilos) [illegible] Nomocanon ሲባል ሊገባን የሚለችበው ሕግ ቀኖናዊ ወይም ቀኖናዊነት [illegible] ሕግ ማለት መሆኑ ነው [illegible] Nomocanon [illegible] Nomos (ሕግ) እና Canon (ቀኖና) ጥምር [illegible] ቃል : [illegible] የተመለከተውን ትርጉም [illegible] ትርጉምን ይዞ ይገኛል ። ነገር ግን Nomocanon [illegible] ሕግ ቀኖናዊ ወይም ወደፊት [illegible] ሕግ ወቀኖና [illegible] ብሒረ ሕግ ወቀኖና እንዴት [illegible]? [illegible] መንሻና ይህንስ ትርጉም [illegible] ትርጉም ብሒረ ሕግ ወቀኖና እንዴት ያዘ? [illegible] የሚከተሉትን [illegible] መመልከት አስፈላጊ ሆኖ [illegible] ።

በሕገ ቤተክርስቲያን [illegible] ዓይነት ጉባዔያተ ሕጋጋት እንደተከፈሉ ይታወቃል ።

ሀ/ <u>ጉባዔያተ ቀኖናተ ቤተክርስቲያን</u>፡ የቤተክርስቲያንን ቀኖናተ ሕጋጋት የያዙ ጉባዔያት ፤

ለ/ <u>ጉባዔያተ ሕጋጋት</u>፡ የቤተክርስቲያን [illegible] የሚመለከቱ የሮማ—ቢዛን ታይን ነገሥታት ሕጋጋትን የያዙ ጉባዔያት ፤

ሐ/ <u>ጉባዔያተ ጥምር ሕጋጋት</u>፡ የቤተክርስቲያን ቀኖናትንና የሮማ—ቢዛንታይን ነገሥታት ሕጋጋትን [illegible] ሆነ እና [illegible] ያዙ ጉባዔያት ።

ሀ· በመጀመሪያው ተራ ቁጥር የሚታቀፉት ጉባዔያት — ጉባዔያተ ቀኖናት ቤተ ክርስቲያንያውያት የሚከተሉት ናቸው ።

1/ በአራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ – ሲኖዶስ (451) ቃለ ጉባኤ የተጠቀሰው ጉባኤ ቀኖናት ሲሆን ፣ ጉባዔው በውስጡ የተሰበሰቡት ቀኖናት እንደ ሲኖዶሱቱ ተከፋፍለው ሳይሆን በይዘት ተከታትለው የሚገኙበት ጉባኤ ነው [35]

2/ ሌላው የሲኖዶሶትን ቅደም ተከተል በመያዝ ቀኖናተ ቤተክርስቲያን የተሰበሰቡበት ጉባኤ ቀኖናት ዘ እስጢፋኖስ ኤፌሶናዊ (አምስተኛ ውና ስድስተኛው ምዕተ ዓመት) ሲሆን ይህም ጉባኤ ቀኖናት በአሥረኛው ምዕተ ዓመት በነበረና ስሙ ስምኦን በተሰኘ ምሁር በተከተሉት ዘመናት የተገኙት ቀኖናት ተጨምረውበት የሚገኝ ጉባኤ ነው [36]

3/ ሌላው ሦስተኛው ጉባኤ ቀኖናተ ቤተክርስቲያን በይዘት ተቀነባብሮና በአምሳት አርእስት ተከፍሎ በአምስተኛው ምዕተ ዓመት የተዘጋጀው የዮሐንስ መተርጉም – የሊቅ ዮሐንስ (Scholastique) ምክራብ ቀኖናት – የመጀመሪያው ብሔረ ሕግና ወቀኖና ዘአምሳቱ አርእስቲሁ Synagoga LTitlorum ተቀርጾ ሲገኝ በውስጡ የፍትሐ ብሔር ሕጎች ተጨምረውበት ይገኛል [37]

ለ· በሁለተኛው ተራ ቁጥር የሚመለከቱት ጉባኤያት የሚከተሉት ናቸው።

1/ **Collectio LXXXVII Capitulorum**

ይህ "ጉባኤ ዘ 87ቱ ምዕራፍቲሁ" የተሰኘው ጉባኤ ሕገጋት አሁንም በዮሐንስ መተርጉም የተዘጋጀ መሆኑ ሲረዳ ይዘቱ የተወሰደው ከቢዛንታይን ንጉሥ ዩስጢኒያኖስ "ሐዲሳት ሕገጋት" (Novellen) የቤተክርስቲያን ጉዳዮች ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች ነው ። በ87

35· ከዚሁ ገጽ 252–261

36· የሰነዱ ሕትመት Voelli Et Justelli , Bibliothecae Iuris Canonici Veteris: Thomus secundus Lutetiae Parisiorum 1661 T.II ገጽ 710

37· ሕትመት Voelli Et Justelli: T.II ገጽ 499–602 A.F. Bienner: Geschichte Der Novellen Justinianus, Berlin 1824 ገጽ 608፣ G.E.Heimbach, Anecdota T.II Cap. III ገጽ LVI–LVII

ምዕራፎች ተከፍሎ የተቀረጸ በመሆኑ በላቲን በJ. Bienner ይህን ስያሜ ሊይዝ ችሏል[38] ። በተቀረጸበት ግሪክ ቋንቋ "የቤተክርስቲያን ሕግ ከሚመለከቱ የአጼ ዩስጢኒያኖስ ሐዲሰት ሕገጋት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች … የመነጨ ጉባኤ" የሚል ዝርዝር ርእስን ይዞ ይገኛል[39]

2/ **<u>Collecto</u> XXV Capitulorum**

ሌላው ተመሳሳይ ጉባኤ በ7ኛው ምዕተ ዓመት በነበረ አንድ ባለታወቀ ሰው የተዘጋጀ መሆኑ ሲነገር አሁንም በ J. Bienner የተሰጠው "ጉባኤ ዘ25ቱ ምዕራፍቲሁ" የሚለው ላቲን ርእስ[40] እንደሚያመለክተው በ25 ምዕራፎች ተከፍሎ የቤተክርስቲያንን ጉዳዮች ከሚመለከቱ የዩስጢኒያኖስ ሕገጋት ማለትም አራቱ ምዕራፎች ከሐዲሳት ሕገጋት እና 21 ምዕራፎች ከCodex- ምእላደ ሕግ የተወሰዱበት ጉባኤ ነው ።

ሙሉ ርእሱ በተቀረጸበት ግሪክ ቋንቋ "የቅዱሳን አባቶችን ቀኖናተ ቤተክርስቲያን ከሚያጸድቁና ከሚጠብቁ የአጼ ዩስጢኒያኖስ ሐዲሳት ሕገጋት የፍትሐብሔር ትእዛዛት" [41]

3/ **Collectio Constitutionum Ecclesiasticarum**

መበል ሦስተኛ ጉባዔ ቀኖናት አሁን ከንጉሥ ዩስጢኒያኖስ ሕገጋት Codex pandects et novellem የቤተክርስቲያንን ጉዳዮች ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተወስዶ የተዘጋጀ ሲሆን ፡ የዚህ ላቲን ርእስ እንደሌሎችም በ

38. J. Bienner: Geschichte Der Novellen Justinianus ገጽ 167

39. "Ek των μετά τόν Κώδικα Θείων Νεαρών Διατάξεων του της Ευσεβούς λήξεως Ιουστινιανού διάφοροι διατάξεις συνάδουσαι εξαιρέτως τοις θείοις καί Ιεροίς Κανόσι" Α. Χριστοφιλόπουλου: Ελληνικόν Εκκλησιαστικόν Δίκαιον ገጽ 50 Anecdota T II ገጽ 206—234 J.Pitra: Juris Ecclesiastici Graecorum:Historia Et Monumenta T II ገጽ 385–405

40. J. Bienner: Geschichte Der Novellen Justinianus ገጽ 173

41. ሕትመት Eimbach: Anecdota T.II ገጽ 145 201 J. Pitra Juris Ecclesiastici Graecorum Historia et Munumenta IIT.I ገጽ 407

F.Bienner የተሰጠም መሆኑ ይታወቃል [42]. በሌላም በኩል ከነዚህ ሦስት ሕጋጋት የተዋጣ ዘመሆኑ[43] ዘሠለስቱ አርስቲሁ (collectio Tripartita ወይም Triparatitla በመባልም ይታወቃል ።

የተጻፈበት ግሪክ ቋንቋ ሙሉ ርእስ "ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ፣ ካህናት ፣ መነኮሳት፣ ትዱላት ንዋያት ፣ ስለአይሁድና መናፍቃን ከሚደነግጉ (codex Pandects እና Novelle የተወሰዱ ድንጋጌዎች ምኩራብ - ምኩራባተ ትእዛዛት ከንጉሥ ዩስጢኒያኖስ ነው የሚል ነው [44]

ሐ/ የጉባኤያተ ሦስተኛ ዓይነት

በሁ· ቀኖናተ ቤተ ክርስቲያንን እና በሉ· የፍትሐ ብሔር ግን የቤተክርስቲያንን ጉዳዮች የሚመለከቱ ሕጎች ይዘው የሚገኙ ጉባኤያተ ቀኖናተ ቤተክርስቲያንና ጉባዔያተ ሕጋጋትን (ለመመልከት ለንችል ሦስተኛው የጉባኤያት ዓይነት እንዚህ ሁለቱ ይዘቶች ተጣምረው ሁኖም ለመጀመሪያዎቹ የበለጠ ኃይልን በመስጠት [45] ተተነባበር የሚታዩ

42. Διατάξεις Νόμων Πολιτικών εκ Νεαρών του Ιουστινιανού Βασιλέως Συνηγορούσαι καί Επικυραύσαι των Αγίων Πατέρων Εκκλησιαστικούς Κανόνας 42· ሕትመት Voelli Et Justelli: Bibliothecae Iuris Canonici Veteris Tomus secumdus lutotiae parisiorum T.II. ገጽ 1223-1263, Pitra, juris ecclesiastici Graecorum T.II. ገጽ 410-416

J. Bienner: Geschichte Der Novellen Justinianus ገጽ 197 Zachariae Von Lingenthal. Historia Iuris Graecoromani delineatio... Heidelberg 1889 ገጽ 34· Heimbach: Griechisch– Römishes Recht. Im Mittelalter and in der Neuzeit A.E.W.K. T 86/1868 ገጽ 295·

43 Leunclavius: Paratitlorum Libri Tres Antique De Graccis Latini Facti Et Notarum Libri Duo 1895.

44· Νόμος του Ιουστινιανού Βασιλέως Συναγωγή των Ειρημένων εν τω Κώδικι καί τοις Διεγέοτοις καί ταις Νεαραίς Διατάξεων περί Επισκόπων καί Κληρικών καί Μοναχών καί Πραγμάτων Ευαγών έτι δέ Ιουδαίων καί Αιρετικών, MILASCH-Αποστολοπούλου; Εκκλησιαστικόν Δίκαιον της Ορθοδόξου Ανατολικής Εκκλησίας ገጽ 245-247

45· Οι τοίς Κανόσιν εναντιουμενοι πραγματικοί τύποι άκυροι εισίν: ΡΑΛΛΗ: Νομοκάνων εις ΙΔ' Τίτλους, Σύνταγμα Θείων καί Ιερών Κανόνων Τ.Α-Σ' ΑΘΗΝΑΙ 1852-1859 Τ.Α' ገጽ 36

ጉባኤ መስል የሥራ ውጤት ነው ።

ይህም ተቀለን ከትርጉም ሆነ ይዘቱ አንፃር የምንመለከተው Nomocanon- ብሔረ ሕግ ወቀኖና ተብሎ የሚጠራው ቅርጽ ነው።

5·2 ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘቁስጥንጥንያ Byzantine Nomocanon

በቁስጥንጥንያ – ቢዛንታይን ልማድ ብሔረ ሕግ ወቀኖና (Nomocanon) ሲባል ከላይ እሁን እንደተመለከተው የቤተክርስቲያን ቀኖናትንና ከፍትሐ ብሔር ሕጎች የቤተክርስቲያን ጉዳዮችን የሚመለከቱ ትእዛዛትን አጣምሮ ይዞ የሚገኝ ቅንብር–ጥምር ሥራ ማለትም ሥርዐተ ሕግ ምእላይ ሕግ ወቀኖና ነው ።[46]

1/ በቁስጥንጥንያ – ቢዛንታይን በሕገ ቤተክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው ብሔረ ሕግ ወቀኖና ብሔረ ወቀኖና ዘ50 አርእስቲሁ (Nomocanon eis 50 Titlous) ሲሆን በይዘቱ ከዮሐንስ መተርጉም Collectio coostitutionum Ecclesiasticarum-Collectio Tripartita ወይም Triparatitla ላይ የፍትሐ ብሔር ሕጎች ተጨምረውበት ይገኛል ። [47]

2/ ሌላው በ7ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ የተዘጋጀ ዘ14 አርእስቲሁ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘፎትዮስ እዋልድ ዘፎትዮስ ነው [48]

46· Είπου δέ χρειώθη πρός τάς τοιαύτας Κανονικάς Συγγραφάς τήν Πολιτικήν Νομοθεσίαν Υπείληφα ταύτης, βραχέα τέ καί συντετμημένα τοίς συγγενεύσι κεφάλοις προσήρμοσα εν ιδιάζοντι μέρει δέ της Βίβλου, των είς Εκκλησιαστικήν ανηκόντων ευταξίαν έν ταίς βιβλικαίς θεσπίσμασιν έν τέ ταίς τών Σοφών ερμηνίαις σύντομον έν Συναγωγή ποιησάμενος έκθεσιν, Ράλλη-Ποτλή: Σύνταγμα Τ.Α. ገጽ 7

47· ሕትመት Voelli et Justelli: Bibliothecae Juris Canonici Veteris T.II ገጽ 603· J. Pitra: Juris Ecclesiastici Graccorum T.II ገጽ 416.

48· የሰንዱ ሕትመት Voelli et Justelli Bibliothecae T.II 789. Zachariae Von Lingenthal: Die Griechischen Nomocanon M.A.I.S.P Ser. VII T. 23Ar 7 Zachariae: Über den Verfasser und Die Quellen des (Pseudophotianischen, Nomokanon in XIV. Titlen. M.A.I.S.P Ser. VII T. 32 Ar 16. Pitra: Juris Ecclesiastici Graecorum T.II 431 640. Κ. Πέτροβιτζ, Ο Νομοκάνων είς ΙΔ' τίτλούς καί οι Βυζαντινοί Σχολάσται - ΑΘΗΝΑΙ 1970.

ይህ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘ14 አርእስቲሁ የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ፎትዮስ (9ኛው ምዕመ ዓመት) ሥራ እንደሆነ ቢነገርም በሌላ በኩል ተቀባይነት ያለው ከላይ እንደተመለከተው በ7ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ስሙ በውል ባልታወቀ ሰው ወይም በአንዳንዶቹ ዘንድ ይህ ሰው ተርጓሚ Pandects እስጢፋኖስ በሌሎች ዘንድ ደግሞ አኖኒሞስ የተባለ ሰው ሥራ እንደሆ ሲሆን ስለዚህም ነው Pseudophotitian Nomocanon የሚባለው ይሆናል ።

3/ ቀጥሎም መታወስ የሚገባው በ1516 ዓ.ም የተዘጋጀው ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘማኑኤል ማላክሲስ የሚባለው ነው [49]

ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘማኑኤል ማላክሲስ እስከ አሁን በተመለከቱት ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት ከታየው ይዘትና ይዘት ውጪ ሁኖ ይገኛል ምክንያቱም ከቀኖናተ ቤተክርስቲያንና ከላይ የተጠቀሰው ይዘት ከእላቸው ሕገጋት በስተቀር ከቤተክርስቲያን አቋም ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሌሎች ነገሮችን ለምሳሌም የዓየር መቆጣጠሪያ መረጃን (Meteorology) መልክዐ ምድርን (Geography) ፍልስፍናን (Philosophy) እና የመሳሰሉትን ልዩ ልዩ ነገሮችን ይዞ ይገኛል ።

ስለሆነም ቀደቶ የተዘጋጀ በመሆኑ በምንም ዓይነት እስከአሁን የተመለከተውን ዕንስ ሐሳብና ይዘት ፡ የተሰጠውንም አስተያየት ሊሰውጥ አይችልም 2 "

5·3 ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘ ምሥራቅ (Oriental Nomocanon)

በምሥራቅ ወይም በተሻለ አጠራር በመካከለኛው ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ብሔረ ሕግ ወቀኖና (Nomocanon) ሲባል በአንድ በኩል ቀኖናተ ቤተክርስቲያንንና የፍትሐ ብሔር ሕግንትን ይዞ የሚገኝ መጽሐፍ code ምእላድ ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እንዚህ ከላይ እንደጠቀስነው ብሔረ ሕግ ወቀኖና የሚይዛቸው የፍትሐ ብሔር ሕጎች የቤተክርስቲያንን ጉዳዮች የሚመለከቱ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ይዘት ያላቸው ትእዛዛትን ጭምር ያቀፈ ስንድ ማለትም ነው ።

49፡ P.M. Ράλλη: Νομοκάνων έν Ελληνικη εγκυκλοπαιδέια Τ. ΙΗ ገጽ 179, Δ. Γκίνη κείμενα Βυζαντινού καί Μεταβυζαντι- νού Δικαίου, ΑΘΗΝΑΙ: 1963 ገጽ 11

ንዘሔበረ ሕግ ወቀኖና Nomocanon ቅርጽና ይዘት ቀነዛበ · Beck. Kirche und [illegible]ologischen Literatur in Byzantinischen Reich. München 1959 ገጽ 145 ተመልከት

ይህም ዓይነቱ የይዘት ልዩነት ሊፈጠር የቻለው በሁለት ምክንያቶች ነው ።

1/ በመካከለኛው ምሥራቅ (ግብጽ ፡ ሶርያ ፡ ፍልስጥኤም ፡ ወዘተ) የሚኖሩ ሕዝቦች መጀመሪያ ከግሪኮች ቀጥሎም ከሮማውያን ገዥዎቻቸው ከወረሱአቸው የአኗኗር ዘዴ ተልዕኖ ለመላቀቅና የራሳቸውን ታሪክና ልማድ ለማስከበር ስለዚህም ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር የሚያስችሏቸው ደግሞ ለዚህ ብሔራዊነት ንክ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገው በዚሁ አካባቢ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተፈጠረው የሃይማኖት ልዩነት ነበር።
በዚህም ልዩነት በግንባር ቀደምትነት ተሰልፈው ይገኙ የነበሩት የአንጾኪያ (ንስጥሮሳውያን) ፡ የቁስጥንጥንያ (ኬልቄዶናውያን) እና የእስክንድርያ (ኢ ኬልቄዶናውያን መሪዎች ሊቃነ ጳጳሳት ነበሩ ።

2/ ቀጥሎም የዚህ ቀበሌ — አካባቢ ፈጽሞ የተለየ የኑሮ ዘዴና የሕግ አመለካከት በሚከተል የእስልምና እጅ መውደቅና በቁስጥንጥንያና በመካከለኛው ምሥራቅ (ግብጽ ፡ ሶርያ ፡ ሌሎችም ክፍላተ ሀገራት) መካከል ቢላላም ቅሉ የነበረው ግንኙነት አንደኛውን ሊቋረጥ ቻለ ።

ስለዚህ በእነዚህ ቀበሌዎቹ በእስልምና እምነት ሥር ወድቀው ያሚገኙ ክርስቲያኖች በመካከላቸው የሚፈጠረውን ልዩነት ለማስወገድ ልዩ ጠባይና ይዘት ያለውን ሕግ የሚከተሉ የእስልምና ፍርድ ቤቶች ጥፅቃ ለመሻት ከመገደድ ተቆጥበው ለመኖር ከእምነታቸውም ፡ ከሥነ ሥርዐታቸውና ሥነ ምግባራቸው ጋር የተዛመዱ ሕገጋት መኖር አስፈላጊ መሆኑን ያመኑበት የአብያተክርስቲያናት መሪዎች ፣ የሃይማኖትና የሕግ ሊቃውንት የዚህ ዓይነቱን ብሔረ ሕግ ወቀኖና ለማዘጋጀት ስራ ቀረት አድርገዋል ምክንያቱም ከላይ በተጠቀሱት ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት ዘቁስጥንጥንያ (ቢዛንቲን) ውስጥ የነበሩት ሕገጋት የቤተክርስቲያን ጉዳዮች ብቻ የሚመለከቱት ሳይሆን ጠቅላላ ማኅበራዊ ኑሮ ይዘት ያላቸው ሕገጋት ናቸው (ነበሩ) ።

5·3·1 ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘሶርያ (Syriac Nomocanon)

5·3·1·1 ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘጎርጎርዮስ አቡልፋርጊዮስ ባር ሄብሬውስ Nomocanon Gregorii Abulphargii Bar Hebraei.

ዕውቅ የሥነ ጽሑፍና የሃይማኖት ሊቅ ሶርያዊ ያዕቆባዊ ሊቀጳጳሳት)[51] መጥሮጲሊጣን (1226) ጎርጎርዮስ አዱልፋርጊዮስ ባርሄብሬውስ -Gregorius Abulphargius Bar Hebraeus በጻፋቸው የሥነ ጽሑፍና የሃይማኖት ይዘቶች ከአሏቸው ሥራዎች መካከል ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው ብሔረ ሕግ ወቀኖና (Nomocanon Gregorii Abulphargii Bar Hebraei) ነው።

ጎርጎርዮስ አቡልፋርጊዮስ ባር ሄብሬውስ በራሱ ጠባቂነት ሥር ትገኝ ስለነበረችው ቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በወቅላላ የአመራር (ሕጋዊ) እና የአስተዳደር (ቀኖናዊ) ችግርን ለማስወገድ የሚቻልበትን ዘዴ ለማግኘት ይቻል ዘንድ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በተለየ በሶርያ ቤተክርስቲያንና በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ከሚገኙት ቀኖናተ ቤተክርስቲያንና ከሮማ ቢዛንታይን የፍትሐ ብሔር ሕጋጋት ለዓላማው አስፈላጊ ሆነው የተገኙትን ድንጋጌዎች ከማሰባሰቡ ጋር ይህ የታወቀውን ብሔረ ሕግ ወቀኖና "Liber Directionum Sev Epitome Canonum Ecclesiasticorum et Regum Saecularium) [52] ማዘጋጀቱ ነው ። ከላይ የተመለከቱትን ቀኖናተ ቤተክርስቲያን በማሰባሰብ የተጀመረው ከ4ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ስለነበር ይህን ብሔረ ሕግ ወቀኖና ለማዘጋጀት – ለማቀነባበር በቂና ያለብዙ ድካም የሚገኙ ምንጮች ነበሩ።

እንግዲህ ይህ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘጎርጎርዮስ ባር ሄብሬውስ (Liber Directorum - CKTâbâ Dhudâye በመባል የሚታወቀው ብሔረ ሕግ ወቀኖና ከቀኖናት ሲኖዶሳይያት (ሲኖዶሳውያት) በተለየ ቀኖናዊ ይዘት ከአላቸው የአባቶች ጽሑፎች ፣ ከሃይማኖትና ሕግ መምህራን (ሊቃውንት) (Responsa prudentium et doctorum Ecclesiae) በአንድ በኩል በሌላም በኩል ከቢዛንታይን ክርስቲያኖች ነገሥታት ሕጋጋት ፣ ከዩስጢኒያኖስ ሕጎችና ቀኖናተ ነገሥት ላይ

51. "ሶርያዊ" "ያዕቆባዊ" "ሶርያዊውያን" "ያዕቆባውያን" ስለሚለው ስያሜ ቅጽል ከቢሁ ገጽ 119–120 ተመልከት

52. Duval Rubens: anciennes chrétiennes Litteratures: I Litteratur Syriaque, Paris 1973 ገጽ 168 Fortenscue: the Lesser churches of the East: London 1813 T.I. ገጽ፣ 742 የግርጌ ማስታወሻ ፣ 1

ተመርኩዞ ነው የተዘጋጀው ።

ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘባር ሄብሬውስ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ በቅድሚያ [illegible] Aloysius Assemanus ወደ ላቲን [illegible] ።)[53] [illegible] ማዮ (Angelo Maio) [illegible] ።[54] [illegible] ሰኑዮ ግን በሊፕ በድጃም (Lep Bodjam) [illegible] ።[55] ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘባር ሄብሬውስ [illegible] (De Ecclesiae)[56] ጀምሮ እስከ ፍርድ [illegible] (Acusione Generatim)[57] የፍትሐ ብሔር [illegible] (De testamentis)[58] የውርስ ሕግ (De Hereditate)[59] [illegible] (De Gravibus Flinoribus, Quae Poenam Capitalem Merentur)[60] በሚመለከቱ ድንጋጌ [illegible] ።

[illegible] ኢየሱስ Nomocanon Ebediesus

[illegible] ሶርያዊ ንስጥሮሳዊ ኢቢድ ኢየሱስ [illegible] ቀኖና ወሕግ ለማዘጋጀት ጎርጎርዮስ ባር [illegible] ችግር በመነሳት ነበር አሁን በስመ [illegible] ለማሰባሰብ የወሰነው ። ይህንም ብሔረ [illegible] ለማዘጋጀት የተጠቀመባቸውም ምንጮች [illegible] በተለየ የራሱ ቤተክርስቲያን–ንስጥሮሳ

53. [illegible] mani Bibliothecae orientalis. A. Maio: Ecclesiae [illegible] nomocanon

54. [illegible] hargio Bar-Hebraeo Syrice compositus et A. Iosephi [illegible] Latin Linguam conversus, scriptorum veterum nova [illegible] 1838 T.X.II ገጽ 3-268 I ገጽ XIII-XXI.

55. [illegible] Nomocanon Gregorii Bar-Hebraei, Paris 1898.

56. [illegible] A. Maio scriptorum... T.X.II ገጽ፣ 3–60።

57. [illegible] A. Maio scriptorum T.X.II ገጽ 258–268።

58. [illegible] A. Maio scriptorum T.X.II ገጽ 83 – 87።

59. [illegible] A. Maio scriptorum T.X.II ገጽ 87 – 94።

60. [illegible] A. Maio scriptrum T.A.II ገጽ 215–229።

ዊት ጉባዔያተ ቀኖናት እና የሮማ–ቢዛንቲን ነገሥታት ሕጎች ናቸው[61]

ፍትሐ ነገሥት ወቀኖና ዘ ኢቢድኢየሱስ ወደ ላቲን በዮሴፍ አሎሲዩስ አሴማኖስ Iosephus Aloysius Assemanus ተተርጉሞ[62] እና በአንጀሎ ማዩ Angelo Maio ታትሞ ይገኛል[63]

ሶርያውያን በኋላም በዚሁ በአንጀሎ ማዮ ሲታተም ችሏል ።[64] እንደሚታየው ፍትሐ ነገሥት ወቀኖና ዘኢቢድኢየሱስ በሁለቱ ክፍሎቹ ተከፍሎ ሲገኝ ከነዚህም አንዱ ክፍል 5 ሌላው ክፍል 4 (Tractata) ምዕራፎች ይዘው ይገኛሉ ።

ከመጀመሪያው ክፍል እየአንዳንዱ (Tractus) ምዕራፍ ከመጀመሪያ (Tractus) የመጀመሪያው ክፍል በስተቀር[65] ከሮማ – ቢዛንቲን ነገሥታት የፍትሐ ብሔር ሕጎች የተወሰዱ ድንጋጌዎች ("Codex Imperatorum Graecorum Hocest Statuta Quae Constantino, Theodosio ac Leonis Tribuntur Quaeque a Sobenis ad Ambrosius referntur") ማለትም ስለ ጋብቻ De Matrimoniis Canonibus, ac ritibus Sponsalium Christifideles[66], ስለ ውርስ ክፍፍል De-Divisione Hereditatum)[67] ስለ ሌሎችም ክርስቲያኖች እማኞችን የሚመለከቱ አርእስት Deiudicis Et Saecularibus Quae inter Christifideles Contigunt[68] የሚደነግጉ ትእዛዛትን ይዞ ሲገኝ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የቤተክርስቲያን የውስጥ ሕይወትን የሚመለከት ትእዛዛት ቀኖናውያትን ያሰባሰበ ክፍል ነው[69]

61.Duval Rubens: Anciennes chrétiennes ... I.La litterature Syriaque... ገጽ ፡ 166– 167·

62. Iosephi Aloysii Assemani: Bibliothecae ... III Part I ገጽ 332 ...

6... A. Maio ,, Ebediesus Mitropolitae Sorae et Armeniae collectio canonum synodicorum... et in latinam Linguam Ab. Iosepho Aloysio Assemano: scriptorum ... T.X.I ገጽ ፡ VI–XI: 23–168

64. A. Maio: Scriptorum T.X. I ገጽ ፡ 168 – 332·

65. A. Maio : Scriptorum... T.X.I ገጽ X

66. Tractatius 2: A.Maio: Scriptorum... T.X.I ገጽ 40 53

67. Tractatus 3: A. Maio: Scriptorum... T.X.I ገጽ 54–64

68. : A. Maio 4 : Scriptorum ... T.X.II ገጽ 65–93

9/01. : a. Maio: Scriptorum... T.X.I ገጽ 95–168

ሆኖም ፍትሐ ነገሥት ወቀኖና ዘኢቢድኢየሱስ ከፍትሐ ነገሥት ወቀኖና ዘንርጎርዮስ ባር ሄብሬዎስ ጋር ሲመዛዘን ይዘቱንና ምልዓቱን በሚመለከት ሁለቱም አንድ ዓይነት ገጽታ ያላቸው ከተመሳሳይ ምንጮች የተቀነባበሩ ቢሆንም ይህ ፍትሐ ነገሥት ወቀኖና በጣም ወደ ኋላ የቀረ መሆኑ ይታያል ።

ትርጓሜውን በተመለከተ ሁለቱም የአብያተ ክርስቲያናት ሲኖዶሳት ቀኖናትን ፣ ወዘተ· የያዙ ጉባዔያት ...እይደሉም ነገር ግን እንደ አቡልፋርድ ፍትሐ ነገሥት ወቀኖና ፎትዮስ ዘ14 አርእስቲሁ የመጀመሪያው ክፍል[70] እና እንደ ፍትሐ ነገሥት ወቀኖና ዘሚካኤል ዘደማያጥ ሁለተኛው ክፍል አርእስተ ነገሮችን በመከተል የተዘጋጁ ጥንቅሮች (codex) ናቸው ።

5·3·2 ፍትሐ ነገሥት ወቀኖና ዘእስክንድርያ – Coptic Nomocanon

በግብጽ ከላይ ስተመለከተው ችግር ተመሳሳይ መፍትሔ ለመስጠት ሲባል ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ጸሐፊት ቀኖናትና ውሳኔዎች ፣ ከሕግና ሃይማኖት ሊቃውንት ትምህርቶች ፣ ከሕግ ድንጋጌዎች ፣ መሰል ፍትሐ ነገሥት ሕጎች ወቀኖናት ሲዘጋጁ ችለዋል[71] ።

ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ፍትሐ ነገሥት ሕጎች ወቀኖናት ናቸው ።

5·3·2·1 ፍትሐ ነገሥት ወቀኖና ዘወልደ ጠይብ – Nomocanon Ibn-At Tayyib

አብን አል–አሳል የፍትሐ ነገሥት ምንጮች በመቅድሙ ሁለተኛ ክፍል ሲዘረዝርና መሪ ምልክቶችን (ትእምርቶችን) ሲያመለክት የምንጮች አንድ አንድ ልዩነቶች መኖራቸውንም ያሳያል ።

ከዚህ አንጻር ከሐዋርያውያት ቀኖናት አንዱ "ረስጠአ" ዘውእቱ ቀሌምንጦስ ቀዳማዊ በንስጥሮሳውያንና መለካውያን ከጽርእ – ግሪክ ቋንቋ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ ትርጉም ቀጥሎ በመለካውያን ዘንድ እንደ ያዕቆባውያን ሶርያውያን 83 ሲሆን በንስጥሮሳውያን ዘንድ ግን ወልደ ጠይብ (ንስጥሮሳዊ) በ1643 በአሰባሰበው "መጽሐፈ ኩሉ ክርስቲያን

70· ከዚሁ ገጽ 40 49

71· ከዚሁ ገጽ 283

– ብሒረ ሕግ ወቀኖና (Nomocanon) 82 እንደሆነ ተመልክቷል [72]።
እንግዲህ በዚ ይዘቱና ግድንቱ በቂ መረጃ ባናገኝም ከዚሁ መቅድመ ፍትሐ ነገሥቱ በንጽባ ለውጦም ክርስቲያኖች የሚያገለግለን ብሒረ ሕግ ወቀኖና እንደሆነ ነው ።

5·3·2·2 ብሒረ ሕግ ወቀኖና ዘገብርኤል ኢብን ቱራይክ – Nomocanon Gabriel Ibn Turaik

በቁጥር 70ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ገብርኤል ኢብን ቱራይክ የጻፈው የውርስ ሕግ (Epitome Iudiciorum 'De Hereditatibus) ለክርስቲያኖች የውርስ ሥርዐት ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል[73]

ይህን የውርስ ሕግ ለማዘጋጀት ከቀኖናተ ቤተክርስቲያን ድንጋጌዎች በተጨማሪ ቀኖናተ ነገሥታት በመባል ከሚታወቁት በተለየ "መጽ" በሚባል ምኅጻረ ቃል ከሚታወቀው ሁለተኛው ቀኖናተ ነገሥት [74] (Canones Basilicorum — Canones Imperatorum) ተመርኩዞ ያዘጋጀው ብሒረ ሕግ ወቀኖናት የመጀመሪያው ነው ።

5·3·2·3 ብሒረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድምያጥ Nomocanon Michaelis Mitropolitae Damitae.

ሊቀ ጳጳሳት ዘድምያጥ ሚካኤል በስሙ የሚጠራውን ዝነኛውን ብሒረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድምያጥ[75] ወይም በአንድ አንድ የእጅ ጽሑፎች መጽሐፈ ሕግ ወእምልኮት (Liber Legum Et Ritum) በመባል የሚታወቀውን ሰነድ እንደ አዘጋጀ ለመረዳት ተችሏል ።

ብሒረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድምያጥ እንደ ፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ አብነ እል አሳል አነጋገር – አገላለጥ የተለያዩ ቀኖናተ ቤተክርስቲያንን በተለየ በቅድሚያ ቀኖናተ ሐዋርያትን ፣ ረስጠአ [76] ረስጠብ [77] ረስጠጅ [78]።

72. መቅድም ፍትሐ ነገሥት ክፍል 2·1 Guidi: Il Fetha Nagast... ገጽ 102···
73. ፍትሐነገሥት መቅድም ክፍል 2
74. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ – 42
75· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
76· ቀለሚንጦስ ቀዳማዊ ከዚሁ ገጽ 137-167
77· ቀለሚንጦስ ዳግም ከዚሁ ገጽ 168-196
78· ቀለሚንጦስ ሣልስ ከዚሁ ገጽ 197

እና ረስጠጅ [79]
ይዞ እንደሚገኝ ተመልክቷል[79] ። ተብሕለ ከመ አባ ሚካኤል ዘሀገረ ድምያጥ ሊቀ ጳጳሳት እሎንተ ሕፁረ ቀኖናተ አስተጋብአ ዘውእቶሙ 3ቱ መጻሕፍተ እመክሉ ዘተጽሕፈ እምኒሆሙ ለለአሐዱ በኋልቆሙ...[80] ።

ይህም ተመሳሳይ የሌለው ከእሱ በፊት ተጽፎ የማያውቅ ሥራ እንደሆነም ተገምቷል··· ወኢከነ አሐዱ ዘተከሥተ እምካልዕ ክፍል ውእቱ ባሕቲቱ ክሡቶሙ··· አንድ እንኳ በሌላ የተገለጠ አይደለም እርሱ ብቻ ገለጣቸው እንጅ [81]

በእርግጥ እንደተባለው ይህ ብሐረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድምያጥ ለግብጽ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ዋጋ ያለው መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕግን አጠቃሎ የያዘ መጽሐፈ ሕግ ነው ። ከዚህም የተነሳ ለአብነ እል አሳል ሥራ (ፍትሐ ነገሥት) መሠረታዊ ምንጭ መሆኑ አላጠራጠረም [82]

ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድምያጥ በመጀመሪያ ጉባዔ ቀኖናትን
ሀ· ዲድስቅልያ ዘሐዋርያት ዘ39 አርእስቲሁ[83]
ለ· ቀኖናተ ሐዋርያት [84]
1· 81 ቀኖናት[85]
2· 71 ቀኖናት[86]
3· 56 ቀኖናት[87]
ሐ· የአብያተ ክርስቲያናት ሲኖዶሳት (የሦስት ዐበይት እና የስድስት ሌሎች ንዑሳን ሲኖዶሳት) ቀኖናት ፣
1· 20 ቀኖናት ዘዕንቆራ[88]

79· የድምያጡ ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤል ቀኖናትን አስጥሮ እንደአሰባሰባቸው ተነገረ እነሱም አያንዳንዳቸው በየቁጥራቸው ከተጻፉት ወገኖች የሆኑ ሦስት መጻሕፍት ናቸው ። ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
80· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
81· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
82· Sentence Lxxiv Du Nomocanon De Michael De Damette Ms, Arabe 472 F 177 - (Nomocanon Michaelis) Mitropolitae Damitae
83· ከዚሁ ገጽ 219–242
84· ከዚሁ ገጽ 102–251
85· ከዚሁ ገጽ 152–164
86· ከዚሁ ገጽ 167–197
87· ከዚሁ ገጽ 198
88· ከዚሁ ገጽ 252–253

2· 14 ቀኖናት ዘቅርጣግና[89]
3· 1,220 ቀኖናት ዘኒቅያ[90]
4· 2,84 ቀኖናት ዘኒቅያ[91]
5· 20 ቀኖናት ዘጋንግራ[92]
6· 25 ቀኖናት ዘአንጾኪያ[93]
7· 59 ቀኖናት ዘላኦዶቅያ[94]
8· 21 ቀኖናት ዘሰርድቅያ[95]
9· 4 ቀኖናት ዘቁስጥንጥንያ[96]
10 · 1 ቀኖና ዘኤፌሶን[97]

መ· ቀኖናት ዘአበው – የቤተክርስቲያን አባቶች ቀኖናት
1· 30 ቀኖናት ዘአቡሊዲስ [98]
2· 106 ቀኖናት ዘባስልዮስ [99]
3· 7 ቀኖናት ዘጎሐንስ አፈወርቅ [100]

ሠ· ቀኖናትና ውሳኔያት ዘሊቃነ ጳጳሳት ዘእለእስክንድርያ
1· ቀኖናት ዘ ክርስቶዱሎስ [101]
2· የሌሎችም ሊቃነ ጳጳሳት ቀኖናት [102]

ረ· ቀጥሎም ይህ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ሊቀ ጳጳሳት ዘድምያጥ አርእስተ ነገሮችን – ፍሬ ነገሮችን መሠረት በማድረግ በተቀነባበሩ 149 ንዑሳን አንቀጾች የተከፈሉ 72 አንቀጾችን (ምዕራፎችን) የያዘ የሕግ ቤተክርስቲያንንና የፍትሐ ብሔርን ሕጎች ድንጋጌዎች ይዞ ይገኛል ።

89· ከዚሁ ገጽ 251–254
90· ከዚሁ ገጽ 265
91· ከዚሁ ገጽ 255–259
92· ከዚሁ ገጽ 254
93· ከዚሁ ገጽ 254
94· ከዚሁ ገጽ 259
95· ከዚሁ ገጽ 260
96· A. Αλιβιζάτου; Οἱ Ἱεροὶ Κανόνες ገጽ 34 – 39
97· A. Αλιβιζάτου: Οι Ἱεροί Κανόνες ገጽ 40–46
98· ከዚሁ ገጽ 262–268
99· ከዚሁ ገጽ 269–272
100· ከዚሁ ገጽ 270–278
101· ከዚሁ ገጽ 280–282
102· ከዚሁ ገጽ 282–298

1· 1–61 አንቀጾች (ምዕራፎች) የቤተክርስቲያን ውስጣዊ ሕይወትን የሚመለከቱ ትእዛዛትን ማለትም ለምሳሌ ስለ ሥጋ ወደሙ [103] ፡ ጾም 104 የእ.ጳ.ስ ቀጸሳት [105] እና ካህናት (ቀሳውስትና ዲያቆናት [106] ምርጫና ሲመት የሚደነግጉ ቀኖናውያትን ትእዛዛት ይዘው ይገኛሉ ።
2· 62 – 72 አንቀጾች (ምዕራፎች) የሚይዟቸው ትእዛዛት ከቤተክርስቲያን አስተዳደር ሕግና የቤተክርስቲያን ጉዳዮችን ከሚመለከት ውጪ ያልሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ ትእዛዛት ናቸው[107]

በዚህ ብሔረ ሕግ ወቀኖና በዚህ ክፍሉ ስፍረው የሚገኙት ድንጋጌዎች የሚመለከቷቸው ነገሮች ለምሳሌ ጋብቻ፡ ውርስ [108] ወዘተ፤ ማለትም በአንድ በኩል የቤተክርስቲያን ሕግ -የቤተክርስቲያን አስተዳደር ሕግና የፍትሐ ድንጋጌዎች ጥምር ይዘቶች ያሏቸው ትእዛዛት ሲሆኑ በሌላ በኩል ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድምያጥ በሮማ-ቢዘንታይን ሕጎጋት ደንጋጌዎች መሠረትና እነዚህም ደንጋጌዎች በብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘገብርኤል ኢብን ቱራይቅ እንደተቀነባበሩ [109] ለምሳሌ የንግድ ልውውጥን [110] ወዘተ፡ የሚመለከቱ ትእዛዛትን ይዞ ይገኛል።

እነዚህ ትእዛዛት በምንጭነት የሚጠቀሙበት የሮማ-ቢዘንታይን ሕግ በአንድ በኩል በG.Sachau ሕትመት [111] በሌላ በኩል በፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘኢብን አል አሰል በምሕፃረ ቃል "መክ" ተብሎ[112] በሚታቀው የቀኖናተ ነገሥት ክፍል ሁለት (Canones Basilicorum ወይም Canones Imperatorum) እንደሆነ ይታሰባል።

103· ምዕራፍ 49 — I ቀኖና ሐዋርያት ·64፤ II ቀኖና ሐዋርያት 4፤ III ቀኖናተ ሐዋርያት ፤ 40.49.50. 60, ቀኖናተ አቡሊዲስ 20,22,38 ፤ ቀኖናተ ባስልዮስ 29,30 ዲድስቅልያ 18,31።
104· ምዕራፍ 50 — የሐንስ 6፡53 ፤ ማቴዎስ 5·24 ፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 11·23 31፡ ዲድስቅልያ 14.15.96. 16።
105· ምዕራፍ 35,38 — ቀኖናተ ሐዋርያት 19,44, ቀኖናተ አቡሊዲስ 28,29,30, ቀኖናተ ባስልዮስ 79
106· ምዕራፍ 11·33፣
107· ምዕራፍ 62 ከቅዱሳት መጽሐፍትና ቀኖናተ ቤተክርስቲያን በስተቀር ቀኖናተ ነገሥት – Canones Basilicorum 82,83,85,86, ወይም እንደ G.Sachau ሕትመት Syrisch–Römisches Rechtsbuch 83,84,86, 87 W.Riedel. Die KirchenrechtsQuellen... des Nomocanon der Ibn al-Assal–Fetha Nagast. Leipzig 1980.
108· ምዕራፍ 72 Canones Basilicorum 22-25, 35,36,42,43,27,28,40,41:
109· ከዚሁ ገጽ - W.Riedel:die Kirchenrechtsquellen... ገጽ 95
110· ምዕራፍ Canones Basilicorum 29, 33, 12,
111· C. Sachau, Syrisch- Römisches Rechtsbuch ገጽ 114
112· መቅድመ ፍትሐ ነገሥት ክፍል 2

ስለዚህ ለሶርያ ቤተክርስቲያን ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘጎርጎርዮስ ባር ሄብሬዎስ [113] በአንድ በኩል በሌላ በኩል ለንስጥሮሳዊት ቤተክርስቲያን (በዚያው አካባቢ) ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘኢቤድኢየሱስ [114] መሠረታውያን ሰነዶች እንደሆኑ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድም ያጥም ለግብጽ ቤተክርስቲያን መሠረታዊ የመተዳደሪያ ሰነድ መሆኑ ይታወቃል።

5·3·2·3 ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘመቃርዮስ ካህን ወመነኩስ (Nomocanon Macarius Presbyter et Monachus)

የዮሐንስን ንዑስ ገዳም ካህንና መነኮስ መቃርዮስ (940 ዓመተ በግዕታት 1233 ዓ·ም ወይም 1080 ዓመተ በግዕታት 1372 ዓ·ም) የዝነኛው ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘመቃርዮስ መነኮስ አዘጋጅ መሆኑ ይታወቃል።

ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘመቃርዮስ በአንድ በኩል ቀኖናተ ቤተክርስቲያንን በሌላ በኩልም ከዚያ በፊት የነበሩትን ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት ከያዚቸው የፍትሐ ብሔር ሕጎች ድንጋጌዎች ብልጫ ያላቸውን የሕግ ትእዛዛት ይዞ ይገኛል። (macarius presbyter et monachus coptita auctor collectionis canonum ecclesiae Alexandrinae [115]

ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘመቃርዮስ መነኩስ (nomocanon ecclesiae Alexandrinae coptitarum) በአንድ በኩል ቀኖናት ሐዋርያውያትን፣ ቀኖናት ሲኖዶሳይያትን፣ የቤተክርስቲያናት አባቶች ቀኖናትንና የሊቃነ ጳጳሳት ውሳኔዎችን በሌላም በኩል ቀኖናተ ነገሥት በመባል የሚታወቁትን የፍትሐ ብሔር ሕጎች (canones basilicorum sev statuta imperatorum, ius complectentia christianorum orientalium, ex canonibus consiliorum .responsis patrum. et constitutionibus imperatorum, eti conflatum, quotum ecclesiae cumcivilis causae definiuntur

እንደሚከተለው ይዞ ይገኛል።

1· Liber primus titulorum a Constantino imperatore presentibus patribus cccviii editorum, qui in quadraginta capita dividuotur [116]
2. Liber secundus basilicorum sev statutorum imperatoribus adtributorum sistens canones centum et triginta

113· ከዚው ገጽ 53 55

114· ከዚው ገጽ 55 57

115· A. MAIO. Scriptorum T.IV. ገጽ 275, 570።

116. A.Maio. scriptorum T.IV ገጽ 275

ይህም ከ LXXII የእስክንድርያ ፓትርያርክ ማርቆስ Filius Zaraa ዐረብኛ Codex የመጣ ነበር [117]
3 Liber tertius basicilicorum sisten quae patres cccviii ይህም ከ version doctoris saphi ben Assal መምጣቱ ይታወቃል [118]
4, Liber quartus basicilicorum in cap. XI. divisus sed. ex calligrapbi oscitantia postpriorem constitutionum apostolorum per clementum liberum positus [119]

ስለዚህም ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘመቃርዮስ መነኮስ የተሟላ ጉባኤ ቀኖናተ ቤተክርስያን ወሕገጋት (የፍትሐ ብሔር ሕገጋት) ሆና ታይቷል።

ነገር ግን በሮማ — ቢዛንታይን ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት እና በአንድ በኩል በሱርስጥ (ሶርያ) እና በዐረብ (ግብጥ) ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት መካከል ልዩነት መኖሩ ይታወቃል።

ይህም ልዩነት ሊከሰት የቻለበት ምክንያት የሮማ— ቢዘንታይን ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት ቀኖናተ ቤተክርስቲያንንና የቤተክርስቲያን ጉዳዮችን የሚመለከት የሕግ ድንጋጌዎችን ይዘው ቢገኙ የሱርስጥ እና ዐረብ ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት ግን ቀኖናተ ቤተክርስቲያንንና ጠቅላላ ይዘት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ሆኖም በምንም ዓይነት ከቤተክርስቲያን ቀኖናትና ማኅበራዊ ሥነ ምግባር ጋር የማይጋጩ ሆነው የተገኙትን ድንጋጌዎች እያያዙ መገኘታቸው ነው።

እስከ አሁን ከተመለከቱት መሠረተ ሐሳቦች በመነሳት ብሔረ ሕግ ወቀኖና ማለት:—

1· የቤተክርስቲያን ቀኖናትና የቤተክርስቲያንን ጉዳዮች የሚመለከቱ የፍትሐ ብሔር ሕጎች ትእዛዛት የተሰበሰቡበት መደብለ ሕግ ወቀኖና ማለት ነው (በቢዛንታይን)

2· የቤተክርስቲያን ቀኖናትና ጠቅላላ ይዘት ያላቸው የፍትሐ ብሔር ሕጎች ትእዛዛት የተሰበሰቡበት መደብለ ሕግ ወቀኖና ማለት ነው (በምሥራቅ ሶርያና ግብፅ)

3· ቀኖናተ ቤተክርስቲያን ብቻ የተሰበሰቡበት መድብለ ቀኖናት ማለት ነው።

117. A.Maio, scriptotum T.IV ገጽ 275 570

118. A.Maio, scriptorum T.IV ገጽ 278

119. A.Maio, scriptorum T.IV ገጽ 278

ስለዚህ ፍትሐ ነገሥት እንደ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘእብነ እል አላል መታየቱ— መቆጠሩ ከይዘቱ በመነሳት ከቢዛንታይን ብሔራት ሕገጋት ወቀኖናት ጋር ተነጻጽሮ ሳይሆን ከሱርስጥ (ሶርያ) እና ዐረብ (ግብጥ) ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት ይዘቶች አንጻር ሲታይ ትክክል ነው ለማለት ይቻላል ምክንያቱም ከለይ እንደተመለከተው [120] በክፉል አንድ መንፈሳዊ ሕግን ሲይዝ በክፍል ሁለት ጠቅላላ ይዘት ያለውን ሥጋዊ ሕግን ይዞ ይገኛል።

ነገር ግን በአንድ በኩል ከቤተክርስቲያን ሕግ (መንፈሳዊ ሕግ) የተወሰዱ አንዳንድ ትእዛዛት የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን የሚደነግጉ [121] በሌላም በኩል ከፍትሐ ብሔር ሕግ (ቀኖናት ነገሥት) የተወሰዱ ድንጋጌዎች የቤተክርስቲያን ጉዳዮችን ሲደነግጉ ይገኛል[122]

5·3·2·4 ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘዮሐንስ ጸዋሚ

እስከ አሁን እንደተመለከትነው ብሔራተ ሕገጋትና ወቀኖናት ቀኖናተ ቤተክርስቲያንንና አንድም የቤተክርስቲያን ጉዳዮችን የሚመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎችን ወይም ቀኖናትንና ጠቅላላ ይዘት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን እየያዙ የሚገኙ ጉባዔያት ዓይነት ሥራዎች ሲሆኑ ነገር ግን በሌላ በኩል በአንድ ወይም በሌላ መልክ ቢሆንም የሕግ ድንጋጌዎችን ሳይጨምሩ ቀኖናተ ቤተክርስቲያንን ብቻ ይዘውም የሚገኙም ሌሎቹ ናቸው።

እነዚህም በጠባብ ትርጉማቸው ብሔራተ ሕገጋት ወቀኖናት ይባላሉ። የቤተክርስቲያን ውስጣዊ ሕይወትን የሚመለከቱ ነገሮችን ለምሳሌ አንቀጸ ንስሐን የያዘው የዮሐንስ ጸዋሚ ቀኖናዊ ሕግ "ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘዮሐንስ ጸዋሚ" ተብሎ ይጠራል" ሕግ ቀኖናዊ ዘዮሐንስ ጸዋሚ" ወይም " ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘአቡነ ዮሐንስ ቅዱስ ንዑድ በእንተ አንቀጸ ንስሐ" [123] ወዘተ

120· ምሳሌ አንቀጽ 33

121· ምሳሌ አንቀጽ 45

122· ምሳሌ አንቀጽ 46

123. MILASCH-Αποστολοπούλου; Τό Εκκλησιαστικόν Δίκαιον, τής Ανατολικής Ορθοδόξου Εκκλησίας ገጽ 152. የግርጌ ማስታወሻ 6ን፣

124. Τρωϊάννου Σ., Νομοκάνων πάν ωφέλιμον καί πλούσιον ΑΘΗΝΑΙ: 1969

ምዕራፍ ሁለት

የፍትሐ ነገሥት ዝግጅት — ቅንብርና ዓላማ

1· የፍትሐ ነገሥት ቅንብር ዓላማ

የፍትሐ ነገሥት ዝግጅት—ቅንብር ዓላማ ምን ወይም ለምን እንደሆነ ሁለት ክፍሎችን ይዞ በሚገኘው መቅድሙ የመጀመሪያው ክፍል ተመልክቷል።

ከነዚህም የመቅድሙ ሁለት ክፍሎች አንዱ የመጀመሪያው ክፍል በጠቅላላ ፍትሐ ነገሥቱ የተቀነባበረባቸውን ምንጮችና መሠረታዊ ዓላማውን ይዞ ሲገኝ [125] ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በአንደኛው ክፍል የተመለከቱትን ምንጮች ዝርዝር [126] እና ስያሜያቸውን ወይም ምልክቶቻቸውን[127] ያሳያል ማለትም ፣ ትእምርታተ ጥቅሶቻቸውን የፍትሐ ነገሥት መቅድም እንደተመለከተው ሀሁለት ክፍሎች ተከፍሎ የመጀመሪያው ክፍል የምንጮችን ዓይነትና የተቀነባበረበትን ዓላማ ሲያመለክት ሁለተኛው ክፍል በአጠቃላይ የተመሠረተባቸውን ምንጮች የተወሰኑትንም ቢሆን በዝርዝር ይገልጣል ይህም ጠቅላላና ልዩ ክፍል በመባል ሊከፈሉ የሚችሉ ሁለት ክፍሎችን ይዟል ማለት ነው።

ሀ· <u>ፍትሐ ነገሥት ያስፈለገበት ዓላማ</u> የፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓትን ለማቅለል እንዲቻል መሆኑ በመቅድሙ ሲመለከት ምክንያቱም ተመልክተዋል።

የፍትሐ ነገሥት መኖር አስፈላጊነት ሕግ ተርጓሚ አካል አግባብ በአለው የሕግ ደንጋጌ ተመሥርቶና ሁኔታዎችን መርምሮ ተገቢውን ፍትሕ ለመስጠት ማስቻል ነው። ስለዚህም ፍትሕ ሰጪውን — ሕግ ተርጓሚው አካል— ፍርድ ቤት ሊኖረው የማይችል ጊዜን ከማባከን አልፎ የጥድፊያና ያልበሰለ ውሳኔን ከመስጠት መጠበቅ ነው።[128]

በሌላም በኩል እያንዳንዱ ፍትሕ ሰጪ— ሕግ ተረጓሚ አካል ለሚያጋጥመው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሕግ ካልኖረ በራስ ኅሊና ብቻ

125· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 1

126· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

127· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

128. Guidi, Fetha Nagast ... ገጽ 2 P.Tzadua:Fetha Nagast, ገጽ 3 የግርጌ ማስታወሻ 3

በመመርኮዝ ወይም በሥነ አእምሮ ብቻ በመመራት የሚሰጠው የሚያሳልፈው ውሳኔ ትክክለኛ ፍትሕን ሳይከተል ይችላል።

ስለዚህ ፍትሐ ነገሥትን የመሰለ ሰነድ መኖር ከዚህ ችግር ይጠብቃል ።

በሥነ ሕግና በሕግ ትርጉም ሂደት ንዑስ ነጥብ የታቀፈበት ፀቢይ ነጥብ ቀኖና ሕግ ራሱ ግልጥ ካልሆነ ወይም ላይኖር ሲችል የሚተላለፍ ውሳኔ ከግላዊ ጥራዝ ዘለልነትና ከወል ጥርጣሬ ያልተላቀቀ ሁኖ ብዙ ጊዜ ስለሚገኝ በሥነ ሥርዓት ሕጐች መሠረት ውድቅ መሆኑ አያጠራጥርም።[129]

ስለዚህ ምንም ጊዜ ቢሆን በፍትሐ ነገሥት መሠረት የሚሰጥ ፍርድ ይህን ከመሰለው ሁኔታ የተጠበቀ ይሆናል። እንደዚህም በመሆን በባለጉዳዮች መካከል እውነትን የመቀበል መንፈስ ሊሰፍን ይችላል።

ቀጥሎም ፍትሐ ነገሥት በሌሎች አገሮች የፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች የሚመሠረቱባቸውና የሚመሩባቸው ሥርዐተ ሕገጋትና ዘዴዎች ሊገናዘቡበት እንደቻለ ይታወቃል።

በሕግ ለመመሥረት ወይም ለሕግ ለመገዛት ካልተቻለ በአንድ በቀረበ ጉዳይ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ በሐሳብ አየር ላይ በመንጠልጠል— በማውጣትና በማውረድ ሊሆን ስለሚችል ከስሕተት ላይ መውደቅ ግዴ ሊሆን ይችላል ።

ከዚህም በስተቀር በፍትሐ ነገሥቱ ከሰፈሩ ጉዳዮች አያንዳንዱን ጉዳይ የሚመለከቱ ግን በልዩ ልዩ ሰነዶች — ምንጮች ተበታትነው የሚገኙ ቀኖናውያን ሕገጋትን በአንድ ሰነድ ማሰባሰቡና ማቀነባበሩ አስፈላጊ ሁኖ መገኘቱ ነው ሌላው የፍትሐ ነገሥቱ ዝግጅት ዓላማ፣

ስለዚህም አንድ ዳኛ በአንድ ጉዳይ ላይ አንድ ውሳኔን ለመስጠት አግባብነት ያላቸውን ሕጐች ከተለያዩ ሰነዶች ፍለጋ ከመሄድ ይልቅ በቀላሉ በአንድ ሰነድ እንዲገኙ ማድረጉ ጊዜንና ጉልበትን ከመቆጠብና ምንጭን ከመዝለል ሊያድን ይችላል [130] ይህም የቤተክርስቲያንን ሕግ ይመለከታል። ሁለተኛው ክፍል— መቅድመ ፍትሐ ነገሥት ክፍል ሁለት ማለትም ሥጋዊ ክፍል እንደአዘጋጁ አብንአል አሳል

129- P/Stamler: Lehrbuch des Rechtsphilosophie Berlin und Leipzig 1928 ግሪክ ትርጉም Κοσμοπούλους Εγχειρίδιον Φιλοσοφίας Δικαίου, ΑΘΗΝΑΙ 1964 ገጽ 395.

130- ፍትሐ ነገሥት መቅድም ቀኖናተ ሐዋርያት ፣ 30 ፣ 35 ፣ 47 ፣ ዲድስቅልያ ምዕራፍ 4 ሊጠየቁ ይችላሉ

አገላለጥ በግብጽ አገር የነበረውን የሕግ ባዶነት vacuum of law ለመሸፈን እንዲረዳ የተቀነባበረ ክፍል ነው። ምክንያቱም የቤተክርስቲያን ሕጐች—ቀኖናት የተወሰኑት እንደተጠበቀው ሁነው ዓለማዊ /ማኅበራዊ ነክ ጉዳዮችን በዝርዝር አለመመልከታቸው ይታሆል። ሐዋርያት ዓላማዊ ሕይወትን በሚመለከት የሙሴ ሕገ-ብሔረ ኦሪት በቂ መሆኑን በማመን ለዚህ ጉዳይ ዝርዝር ሕግን—ቀኖናን አልሰሩም።

ስለዚህም ለምሳሌ በእምነትና ግብረ ገብነት ትምህርት ወሰነው ከዚሀም የተነሳ ሰዎችን ይህን ዓለምና በውስጡ ያሉትን ነገሮች ፍቅር እንዲተው— እንዲንቁ በመጥራት ስለብድርና ትርፍ አልደነገጉም፣ የምንኩስና ሕይወትን በማወጅ ስለጋብቻ ሕግ አልሰሩም።

ስለዚህ በሐዋርያት ትምህርት ለዓላማዊ ማኅበራዊ ኑሮ ባዶ /ክፍት ሁኖ የተገኘውን ለማሟላት ለመሸፈን የፍትሐ ነገሥት ዝግጅት አስፈላጊነት ታመነበት [131] ይህ የመቅድሙ ጠቅላላ መልክ ነው።

ሉ ልዩ ክፍል ፣ የፍትሐ ነገሥት መቅድም ልዩ ክፍል ሁኖ የሚታየው ክፍል ዳኞች በቀና ሙንፈሳቸውና ሥነ ምግባራቸው ብቁ ሁነው ቢገኙም የፍትሕ አሰጣጥ ተግባራቸውን በሚወጡበት ጊዜ ከሚያጋጥማቸው ጉዳይ ጋር በተዛመደ ሁኔታ ተገቢ ዕውቀት የሌላቸውንና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ያዳገታቸውን ዳኞችን ለመርዳት ለማገዝ—እንደተዘጋጀ ይነገራል።

በመጨረሻ አብን አል አሳል የፍትሐ ነገሥት ሁለቱን ክፍሎች/ሥጋዊ ሕግንና መንፈሳዊ ሕግን ያንጸጽራል[132]

በመጀመሪያው ክፍል መረጬሻ ላይ አብን አል አሳል ፍትሐ ነገሥት አምላካዊ ሕግ በመሆኑ ታላቅ አክብሮትን ይጠይቃል። ስለዚህም ይህን አምላካዊ ሕግ መተላለፍ የአምላክን ትእዛዝ መተላለፍ መሆኑን ያመለክታል [133]

ሁኖም ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ በማጠቃለያ ይህን የፍትሐ ነገሥት መቅድም ለማጥናት የሚፈልግ ማንም በው ጠቅላላ ፍትሐ ነገሥቱን

131 ፍትሐ ነገሥት መቅድም

132 ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

133 ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

ለመረዳት ችግር እንደሚያጋጥመው አስቀድሞ መገንዘብ ይችላል። ምክንያቱም መቅድሙን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ጠቅላላ— የሁሉንም ይዘት ለመረዳት የፅንስ ሐሳብ አቀነባበሩና የይዘት አቀራረጹ — አመዳደቡ ሥርዓትና ዘዴ የጐደለው መሆኑ በግልጥ የሚታይ ጉዳይ ነው።

2· የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ

የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ (አዘጋጅ—አቀነባባሪ) በመጀመሪያው የኒቅያ ዐቢይ ሲኖዶስ (Ecumenical Synode) 318 አባቶች ጋር ጊዜ ገጠም ሰው እንደነበር በፍትሐ ነገሥቱ መግቢያ መቅድም—ቅድመ መግቢያ ወይም ቅድመ መቅድም — ቅድመ መቅድመ ፍትሐ ነገሥት በፈጠረው መስመ ታሪክ ታትቷል ።

በዚህም ቅድመ መቅድመ ፍትሐ ነገሥት ወይም ተውሳከ መቅ ድመ ፍትሐ ነገሥት — የተፈጠረ ታሪክ በሮማ—ቢዘንታይን ንጉሥ ትልቁ ቆስጠንጢኖስና በ318 የኒቅያ ሲኖዶስ አባቶች መካከል ግንኙነት ተደርጎ ስለሥርዐተ መንግሥቱ ውይይት እንደተካሄደ ሁኖ ተመልክ ቷል።

በዚህም ውይይት ከተነሱት ፍሬ ነገሮች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል ።

ትልቁ ቆስጠንጢኖስ በመጀመሪያ በዓመተ ስግዕታት[134] መጨረሻ ላይ በ318 አባቶች ተቀብቶ እንደ ነገሠ ከዚያም በቅባቱና በንግሡ ወቅት የዚህ ዓለም መንገድ ከእምላክ መንገድ የተለየ በመሆኑ የዚህን ዓለም መንግሥት እንደማይፈልግ ከመናዘዝ ጋር በተጨማሪ በአምላክ ሕግና በዘመኑ በነበረው በሮማ—ቢዘንታይን ሕግ መካከል ልዩነት እንደ አለ በማሳየት ስለዚህም አምላካዊ ሕግ የፍቅር ፣ የርኅራኄ ፣ የትእግሥት ሕግ[135] በአጠቃላይም የቀደሙ ሕጎችን የመሻር ኃይል ያለው ፍጹምና ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር ሕግ (Lex Lata) [136]

ከዚህ የተነሳ ከእሱ በኋላ በሚደነገግ ሕግ መሻር የማይችል ሕግ መሆኑን ከመግለጥ ጋር ምክንያቱን ሲሰጥ እንደዚህ ያለውን ኃይል ይዞ የሚገኝ ሕግ ሌላ ፍጹም ሕግ ሊገኝ የማይችል መሆኑን ያስተምራል ። ይህም ቀዳማይ ሕግ ዳኅራይ ሕግን ይሽራል Lex prior derogat legi

134· የግብጽ ቤተክርስቲያን ዘመን አቆጣጠር ዓመተ ሰማዕታት (Sanata Ash Shahada ዐረብኛ) ነሐሴ 29 (MESIORI) 284 ይጀምራል ።

135· ማቴዎስ 5·44 ሉቃስ 6· 27—28 ፣ 35

136· ይህ ከሕግ ፅንሰ ሐሳብ አንጻር "ዳኅራይ ሕግ ቀዳማይ ሕግን ይሽራል" (Lex Posterior Derogat Legi Priori) ከሚለው የሮማ ሕግ ጋር ይመሳሰላል ።

posteriori ከሚለው ከአቴና ሕግ መርሕ ጋር ይነጻጸራል ። ይህ ዓይነቱ መርሕ ዛሬም በሕግ ትርጓሜ በስፋት መሠረትነት አለው ።

ሆኖም በሁለቱ ሕጋጋት — አምላካዊ ሕግና ሮማዊ ሕግ መካከል የተደረገውን ንጽጽር ሥርዐተ ሕግን ለማሳየት ካልሆነ በስተቀር ከይዘት አንጻር አልነበረም ። በእንጻሩ ግን የሮማውያን ሕግ ሕገ በቀል (መስተበቀል) መሆኑን ይግልጣል ። በፍትሐ ነገሥት ቅድመ—ተወሳከ መቅድም ጸሐፊ ገለጣ ይህ ዓይነቱ የሮማዊ ሕግ ጠባይ—ባሕርይ ሮማዊ ፍትሕን በማጕናጸፍ ሂደት ይገለጣል —Suum Jus Cuique Tribuere ይህም መርሕ መኖር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚያን የሮማውያን ሕግ ድክመት በታየበት ወቅት የሮማ መንግሥት ፍትሕ አሰጣጥ በይበልጥ በሌተጸፉ ቀኖናተ ሕግ ማለትም ከመልካም ሥነ ምግባር፡ (Bona Mores)፥ ራኅራኄ — ቸርነት (Aequitas) ፥ በቅን እምነት (Bona Fides) ወዘተ መሠረትነት ላይ ነበር ።

ሆኖም በይበልጥ የሮማውያን ሕግ ፀንሰ ሐሳብ በሚቀጥለው መልክ ተጠቃሎ እንደሚታየው ሥነ ምግባራዊ ይዘት ነበረው፥ (Ars Boni et Aequi) የእኩልነት ፍትሕ ሥነ ሥርዓት (Kelson 2nd Century), Honeste Livere የከበረ ሕይወት መኖር) (Alterum non laedere) ጕረቤትህ አትስቸግር (Suum Cuique Tribuere) ለሁሉም እንደ ሥራው (Ulpianus) ነገር ግን የፍትሐ ነገሥት ቅድመ መቅድም የተወለደ ታሪክ የሮማውያን ሕግ የሥነ ምግባር ትእግሥትና ርኅራኄ ጠባይ የነበረውም መሆኑን በመዘንጋቱ ርሑቅ ታሪክ ሆኖ ይገኛል ።

የዚህም ቅድመ—ተወሳከ መቅድመ ፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በወንጌል ቃልና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር Christian Ethics) ላይ በመመርኮዝ የመንግሥት ሕግ እንዲቀርጹለት 318 አበቶችን እንደጠየቀ አድርጐ ያሳያል ።

ምክንያቱም 318 አባቶች የቈስጠንጢኖስ ፍላጎት እንዲሟላ አምላ ክን እንደ ለመኑና እምላክም የአባቶችን ልመና ሰምቶ ከብሉይና ከሐዲስ የተውጣጣ መጽሐፈ ሕገጋትን አዘጋጅተው እንዲሰጡት እንደ እዘዛቸው ገለጣው ይቀጥላል ።

ስለዚህም እብነ እል አሰል (በ318 አባቶች ትእዛዝ) ይህን መጽሐፈ ሕግ—ፍትሐ ነገሥት አዘጋጅቶ ቀጥሎም 318 አባቶች ለቈስጠንጢኖስ ይህን መጽሐፈ ሕግ እንደ ሰጡት ይተረካል ።

መስመ ታሪኩም እንደሚከተለው ይጠቃለላል ፥ እብነ እል አሰል ይህን መጽሐፈ ሕግ—ፍትሐ ነገሥት ጻፈ ። እነዚህም 318 አባቶች በሀገረ ዩናኒ (ግሪክ አገር) ለነገሠው የንግሥት እሌኒ ልጅ ቈስጠንጢኖስ ሰጡት [137] በዚህ ቅድመ መቅድም የፍትሐ ነገሥትን ዝግጅት አስመልክቶ የተተረከው ታሪክ—መስመ ታሪክ (Pseudography) መሆኑን መመልከት ይቻላል ምክንያቱም

1· 318 አባቶች ትልቁ ቈስጠንጢኖስን ቀብተው ስማንገሣቸው በታሪክ አልተደገፈም[138]

2· ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ 318 አባቶችን ከክርስትና ትምህርት ላይ የተመሠረተ ሕግን አዘጋጅተው — አውጥተው እንዲሰጡት መጠየቁ ምንጊዜም ሊረጋገጥ አልቻለም[139]

3· እቡል—ፋዳኢል እብነ እል—ዓሳል የ318 አባቶች 4ኛው ምዕተ ዓመት ጊዜ ገጠም አልነበረም[140] ። ሆኖም የዚህ ታሪክ ምንጭ ሁኖ የሚታየው የግእዙ ቅድመ መቅድመ ፍትሐ ነገሥት በዐረብኛው ፍትሐ ነገሥት (ጉባኤ ቀኖናት) አይገኝም[141] ነገር ግን ምንጓልባት ፍትሐ

137· ቅድመ፥ መቅድመ ፍትሐ ነገሥት ክፍል 2

138· የሮማ ነገሥታት ሥርዐተ ንግሥ እስከ 5ኛው ምዕተ ዓመት ይፈፀም የነበረው በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት (Senate) ነበር ። ነገር ግን የሮማ ቢዘንታይን ንጉሥ ሥርዐተ ንግሥ በቈስጥንጥንያ ፓትርያርክ መፈጸም የጀመረው በዚህ 5ኛው ምዕተ ዓመት ማለትም ለመጀመሪያ ጊዜ በ457 ሊዮን ቀዳማዊ በቈስጥንጥንያ ፓትርያርክ መርቈያኖስ ተቀብቶ ከነገሠበት ጊዜ ጀምሮ ነው ። B. Στεφανίδους Εκκλησιαστική Ιστορία 1962 ገጽ 152 K. Κολιας Εκκλησία καί ο Αυτοκράτωρ είς το Βυζάντιον 1959 ገጽ 38. በኢትዮጵያ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በእምልከተ ጣእት ላይ ድልን ከተጐናጸፈ በኋላ በኒቅያ ሲኖዶስ 318 አባቶች ተቀብቶ እንደነገሠ ይተረካል ። ስንክሣር ሐምሌ 4 ።

139· እስከምናውቀው ድረስ በሮማውያን ሕግ ታሪክ ስለዚህ ምንም ጊዜ ተጠቅሶ አይገኝም በአጠቃላይ ግን ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ የኒቅያ ሲኖዶስ ውሳኔዎችን እንደ አጸደቀና በአዋጅ ከሮማ መንግሥት ሕግ ጋር እኩል የሕግ ኃይል እንደ ሰጠ ይታወቃል ። B. Στεφανίδους 'Ερευνα περί τών έν Βυζαντίω κράτει σχέσεων Εκκλησίας καί Πολιτείας έν τώ καθορισμώ Δογματικής Διδασκαλίας ΑΘΗΝΑΙ: 1952 25.

140· ከዚሁ ገጽ 252

141· Guidi, Il Fetha Nagast...ገጽ 2 የግርጌ ማስታወሻ 2።
p. Tzadua, Fetha Nagast ገጽ 3 የግርጌ ማስታወሻ 3 ።

ነገሥትን ወደ ግእዝ የተረጐመው ሰው) ጴጥሮስ ወልደ አብደል ስይድ) ወይም የኋላ ተማራማሪዎች — መተርጐማን ጭማሪ እንደሆነ ይታሰ ባል።

ስለዚህ ይህ የፍትሐ ነገሥቱ ቅድመ መቅድም ቆይቶ የተጨመረ መሆኑ ከታወቀ ስለ ጸሐፊው — አዘጋጁ ማንነት የውስጥ — ሰነዳዊ ምስክር የለም ።

የፍትሐ ነገሥቱ አጥኝዎች — ተማራማሪዎች የዚህ ፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ በቅድመ መቅድሙ የተመለከተው እብነ እል እ[illegible] መሆኑን ሲቀበሉ ግን የነበረበትን ጊዜና ሥራውን በሚመለከት በጣም ቆይቶ ማለትም በ13ኛው ምዕተ ዓመት እንደነበረ ያሳያሉ[142]።

ነገር ግን በዚያን ውቅት እብነ እል አሳል በመባል የሚታወቁ ምን አልባት ቢያንስ አራት በተለያዩ ሦስቱ ጸሐፍት ግ/ቅ) ብጣውያን ወንድምአማቾች እንደነበሩ ታውቋል[143] ።

ከነዚህ ማንኛው እንደነበር ፍትሐ ነገሥቱን የጻፈው ጥያቄ ይነሳል ይህንንም ጥያቄ ለመመለስ ሰዎቹን አንድ በአንድ መመልከት ይረዳል ።

አንዱ እብነ እል ዓሳል ፣ አል አሳድ አቡል ፈራግ ሄባታላህ ኢብን አል—አሳል (al – Assad Abu – L Farag Hibatallah Ibn al – 'Assal) የሚባል ሲሆን ትርጓሜ ወንጌላትን እንደ ጻፈ ይነገራል ። በሌላም በኩል የውርስ ሕግን (Compendium on the Law of Succession) እንደፈ ጸመ ታውቋል[144]

---

142. P. Dib "Lequel des Ibn al-Assal est L'Auteur Du Nomocanon? E.O.C.T. 20/1915-1917 ገጽ 104 G. Graf: Geschichte Der Christlichen Arabischen Literatur. Roma 1947 .7.2 ገጽ 387...A.C. Nallino: Libri Giuridici Byzantini in Versione Arabe Cristiane De Secoli XII. E. XII: R.R.L. SER. VI VOL. 1/ 1925 ገጽ 102 የግርጌ ማስታወሻ 4 Conti Rossini: IL Synodos Ethiopico : R.R.A.L. SER VII VOL. III 1934 ገጽ 41 - 48

143. G.Grat: Koptischen Gelehrtenfamilie Der Aulad Al-Assal Und Ihr Schriftum. Orientalia (N.S.) 129 (1932)

144. Compendium on the law of succession በአንድ አንድ ጽሑፎች እንደ ተመለከተው ከፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 42 በአንተ ርስት ስለ ርስት ጋር አስከተወሰነ መጠን ተመሳሳይነት እንዳለው ይነገራል ። P. Peter sand : Roman Origins of the Ethiopian law of Kings: J.E.L.T.3 ገጽ 75 የግርጌ ማስታወሻ 43

ሌላው ሁለተኛው እብነ እል ዓሳል፣ አል ሙታማን (አድ—ዳውላ) አቡል ኢ(ይ) ስሐቅ አብራሂም ኢብን አል ዓሳል (Al Mutaman Ad Duala Abu – L Ishaq Ibrahim Ibn al – Assal ሲሆን ይህም ሰው መድበለ መሠረታተ ሃይማኖትን Collectio Fundamentorum Fidei እንደ አቀነባበረ ሲታመን

በዚህም ሥራ ታቃሪኒን የመዋጋት የፍልስፍና ዘዴዎችን በመጠቀም አይሁዳዊነትንና ዓረሚኔነትን ተዋግተዋል ።

Collectio Fundamentorum Fidei አምስት ክፍሎች ሲኖሩት በ91 ምዕራፎች ተከፍሎ ፤

1) ስለ ግ/ቅ/ብጥ ቤተክርቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት (ምዕራፎች 25)

2) ስለ አንድነትና ሦስትነት (ምሥጢረ ሥላሴ) ምዕራፎች 15)

3) ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ (ምዕራፎች 26)

4) ስለ ቅድስት ማርያም ፣ ቅዱሳን ፣ ሐዋርያት ፣ ወዘተ (ምዕራፎች 14)

5) ስለ አሳዊ መሲሕ (ምዕራፎች 11) ይናገራል ።

2· ሌላው የዚህ ሰው ሥራ

Margarita Pretiosa-Liber dogmaticus ሲሆን[145] ይሀም በነቢያት ሐዋርያት ፣ አባቶችና ፓትርያርኮች ትምህርት ላይ ተመሥርቶ የተጻፈ ስለ አንድነትና ሦስትነት ምሥጢር የሚናገር መጽሐፈ እምነት ነው ።

3) ሦስተኛው መጽሐፈ መሠረታውያን እምኖቶች ስብስብ — ወይም ጉባኤ መሠረታውያን እምነቶች — Persicuitas compendiaria ወይም Epitome Collectionis Fundamentorum Fidei ሲሆን[146] ይህም ጉባኤ መሠረታውያን እምነቶች በ16 ምዕራፎች ተከፍሎ የተዘጋጀ ነው ። ይዘቱም ከላይ ከተጠቀሰው de Fundamentis Fidei 1259 የተቀዳ ወይም የእሱ ማሟያ ነው ።

ሦስተኛው እብነ እል ዓሳል ፣ በተለያዩ ቅጽል ስሞች ፣ አል ሳፊ አል ሐኪም አል አሳድ አቢ አፍራጊ አቢ አላሀ ኢስሐቅ ቤን አል ዓሳል al–Safi al–Hakim 'al – As-ad Abi' Ifgraghi Abi allha' Ishaq

---

145. A-Mai: Scriptorum...T.IV. . ገጽ 210

146. A.Mai. Scriptorum...T.IV. ገጽ 212

ben al – assal [147] ወይም አል ሙታማን አቡ ይስሐቅ ቤን አቡ ኢሙ ፋዳል ቤን ይስሐቅ ቤን አል አሳል al – Mutaman Abu' Ishaq Ben AL – Imu-faddal Ben al – Assal[148]

ወይም አል ቢልም አል ሙጋኒ አል—ሳፊ አቡ—ፋዳኢል ኢብን አል ዓሳል al – Silm Al – Muganni Al – Safi Abu – l Fadail Ibn Al – Ass-al [149] ዘወትር አል—ሰፊ አቡ ፋዳኢል ቤን አል—ዓሳል (al—Safi. ዘወትር ግን አል—ሳፊ አቡ ፋዳኢል ቤን አል—ዓሳል (al — Safi. Abu—lfadail Ben al-Asal[150] ከዚህም አልፎ በ[illegible]ም ባጭሩ ኢብን አል—አሳል Ibn Al—Assal[151] በመባል የሚታወቀው ሰው ነው። ኢብን አል—አሳል ልዩ ልዩ የሃይማኖት መጻሕፍትን እንደጻፈ ይነገራል — ስለ አምላክ አንድነትና ሦስት (ምሥጢረ ሥላሴ) ስለ ሃይማኖት ልዩነቶች ፡ ስለ ቤተክርስቲያን የአስተዳደር ሥነ ሥርህት [152]

እንግዲህ ከእነዚህ እብን አል አሳል በሚል የወል ቅጽል ስም ከሚታወቁ ሦስት ጸሐፍት — ደራሲያን ፍትሐ ነገሥትን የጻፈው ማንኛውም እብን አል አሳል ነው ? ለሚለው ጥያቄ ልዩ አመለካከቶች ነበሩ ። ስለዚህ በመጀመሪያ ፍትሐ ነገሥቱን የጻፈው ታናሹ አል ሙታማን (አድ ዳውላ) አቡ—ል ኢሳቅ (ይስሐቅ) ኢብራሂም ቤን አል አባል (Al-Mutaman ad-Daula) Abu-L Ishaq Ibrabim Ibn

147. Bibliothecae Bodleianae codicum Mss. Orientalium catalogus A. Joanne Uri Confectus oxonii: 1787 No. 74 ገጽ 32

148. Bibliothecae Mediceae Laurentianae Et Platinae Codicum Mss. Orientalium Catalogues. Stephanus Evodius Assemanus Florentiae 1742. ገጽ 100። supplement to the catalogue of Arabic manucripts in the British Museum by Riey Charles No. 23 ገጽ 18 A. Maio: Scriptorum...T.IV ገጽ 211

149. W. Riedel: Die Kirchenrechtsquellen... ገጽ 115...

150. Nomocanon Macarius No. 38, 48, W. Riedel, Die Kirchenrechtsquell-en... ገጽ 125፣ 127፣ A. Maio: Scriptorum...T. IV. ገጽ 219፣ 245።

151. Cardilio Maurico : Compendium Theologie Orientalis. Rome. ምዕራፍ 9 No.4 ገጽ 256 ። A.King: The Rights of the Eastern Christendom T I. Rome 1947. ገጽ 372 1965 ገጽ 106

al-Assal) እንደነበር ይታመን ነበር ማለት ይቻላል[153]

2) ፍትሐ ነገሥትን ለመጀመሪያ ጊዜ በቁሙ ግእዝ ሰነድነቱ ያሳተመውና ቀጥሎም ወደ ጣሊያንኛ ተርጉሞ ያሳተመው I. Guidi ፍትሐ ነገሥትን ያቀነባበረው አል አሳድ እብን አል አሳል Al— Assad Ibn Al—Assal እንደነበር አስቀድሞ የተቀበለ እንደነበር ቢታወቅም [154] ቆይቶ ሐሳቡን በመሻሻል (በመለወጥ) የዚህ ፍትሐ ነገሥት መአልድ አል አሳፊ አቡ—ል ኢብን ፋዳኢል አል አሳል (Al-Assafi Abu-l Fadail Ibn Al-Assal መሆኑን አምኗል[155] ስለዚህ ከሦስቱ ወንድአማቾች ፡—

1· አል አሳድ አቡል ፋራግ ሂባታላሕ ኢብን አል አሳል
Al Assad Abu-l Farag Hibatallah Ibn Al-Assal

2. ኢብን አል አሳል አል ሙታማንአድ ደውላ አቡ—ል ይስሐቅ ኢብራሂም ኢብን አል አባል (Al Mu'taman Ad-Daula Abu-l Lshaq Ibrahim Ibn Al–Assal

3· ኢብን አል አሳል አል ሳፊ አል ሐኪም አል አሳድ አቢ ኢፍራጊ አላሕ ይስሐቅ ቢን አል አሳል al-Safi Al–hakim al-Assd Ifragh Al-Assad abi Allah Ishaq Ben al-Assal

ፍትሐ ነገሥቱን የጻፈው ያዘጋጀው እብን አል አሳል al-Assafi Abu-l Fadail IBN al-Assal መሆኑ ተቀባይነትን አግኝቷል[156] በአጭሩም እብን አል አሳል በመባል ይታወቃል

3· ዐረብኛው ፍትሐ ነገሥት የተጻፈበት ዘመንና ቋንቋ

ፍትሐ ነገሥት የተመሠረተባቸውን ምንጮች መሠረት በማድረግ

153. P.H Sand: Roman Orgins of the Ethiopian Law of Kings (Fetha Nagast). J. E. L. ገጽ 75 ። Girgis Filutaus Awad al-Magmu as-safawi Cairo, 1980. መግቢያ G. Graf: Geschichte der Christlichen Arabischen Literature Vol. 1947 ገጽ 398—402 ፣ 407—414

154· Guidi: Storia Della Literatura Ethiopica, Roma 10, 1992 ገጽ 18 ።

155 p. Tzadua: Fetha Nagast... ገጽ XV የግርጌ ማስታወሻ . 18 A Mallon: Ibn al-Assal. Les Trois Ecrivains De le Nom. 6 Journal Asiatique (Ser 10/609/1905 p. Dib. Liquel Des Ibn Al Assal Est L'Autuer Du Nomocanon? 20. R.O.C. 104 (1915-1917 A.J. Higgins: Ibn L-Assal 44. Journal of theological studies 13, 1943.

156· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 1።

የተጻፈበት ዘመን በ13ኛው ምዕተ ዓመት በፊት አለመሆኑን የመረዳት ግንዛቤ ተግኝቷል ። ከነዚህም ምንጮች መካከል ፦

ሀ) እስከ 13ኛው ምዕተ ዓመት የነበሩ የሚከተሉት የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ክርስቶዱሎስ (1048—1077)[157] ፤ ገብርኤል ኢብን ቱራይቅ (1131—1145) [158] ፤ ሚካኤል ዘድምያጥ (1180) [159] — ቄርሎስ 3ኛ ኢብን ላቅላቅ (1235—1243)[160] ቀኖናትና ውሳኔዎች ፤

ለ) እስከ 10ኛው ዓመት የተነሱ የሮማ—ቢዛንታይን ነገሥታት ሕገጋተ ይገኙባቸዋል ። በተለየ የመጨረሻውን አንቀጽ (አንቀጽ 52) በንመለከት ይህ አንቀጽ የተጻፈበት ዘመን958ዓመተ ሰማዕታት ማለትም 1241 ዓመተ መሕረት መሆኑን ያስገነዝባል ።

እንግዲህ ይህ ጊዜ የፍትሐ ነገሥትት ዐረብኛው ሰነድ የተጻፈበትን—ዘመን (Terminus ad Quem) ያመለክታል ። ነገር ግን ይህ የመጨረሻ አንቀጽ 52 የራሱ የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ እብነ አል አሳል ሥራ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ጥያቄ ይነሳል ።

ይህ የፍትሐ ነገሥት መጨረሻ አንቀጽ ሁኖ የሚገኘው አንቀጽ 52 የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ ኢብን አል አሳል ሥራ አይደለም ግን ቆይቶ የተጨመረና የአንቀጽ 42 ተቀጽላ ነው የሚለው መልስ ተቀባይነትን ቢያገኝ በፍትሐ ነገሥት መቅድም ላይ የተጠቀሰው ሚካኤል ዘድምያጥ የነበረበት ዘመን 1180 [161] ፍትሐ ነገሥቱ የተጻፈበትን ዘመን (Terminus ad Quem) ይይዛል ።

ሁኖም ፍትሐ ነገሥት የተዘጋጀበት ዘመን ፍትሐ ነገሥት የሕግ ሰነድ ባለመኖሩ የነበረውን እጥረት ምክንያት በማድረግ በሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ 3ኛ ኢብን ላቅላቅ (1235—1243) ሊቀ መንበርነት በተጠራው የግብጽ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ትእዛዝ እብነ አል አሳል Asafi Abul Fadail Ibn 'Al Assal የጻፈበት ዘመን የፍትሐ ነገሥት Terminus ad Quem ነው ነገር ግን ይህን የመሰለ የሕግ ሰነድ ፍጹም አልነበረም ማለት አይቻልም ። ምክንያቱም ከፍትሐ ነገሥት ድንጋጌ ዎች ጋር ተመሳሳይ ድንጋጌዎች የነበሩት ዝነኛው ብሔረ ሕግ ወቀኖና

157· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል ሁለት አንቀጽ 12 ፡ 13 ፡ 15 ፤ (ቁጥር 496 ፡ 527 ፡ 599)

158· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል ሁለት አንቀጽ 42 (ቁጥር 1337 ፡ 1340)

159· ፍትሐ ነገሥት ክፍል 2

160· አባሪ (አንቀጽ 52) ከዚሁ ገጽ

W.Riedel : Kirchenrechtsquellen das Patriarchats Alexandrien ገጽ 118

ዘሚካኤል ዘድምያጥ ነበር ። እንደ Conti Rossini የግብጽን ቤተክርስቲያን ተከታዎች የሚመለከቱ የሲኖዶሳት ውሳኔዎችን ቀኖናውያንና የሲቪል ሕጋጋትን የያዘውና በ14ኛው ምዕተ ዓመት ወደ ግእዝ የተተረጐመው ፍትሐ ነገሥት በኢብን አል አሳል Asafi Ibn al Assal የተጻፈው 1238[162] ነው ። እብነ አል አሳል ይህን ፍትሐ ነገሥት በሚያዘጋጅበት ጊዜ በቆቱ ቀኖናት ነገሥት ላልተመለከቱ ጉዳዮች እስከዚያ ጊዜ በሥራ ላይ የነበረን የእነ Malicite Madhhar) የሕግ ሰነድ ከማምት አስገብቶ ነበር ቢሆንም ማለት ግን የሚቻለው ብሔረ ሕግ ወቀኖና በሚካኤል ዘድምያጥ የፍትሐ ነገሥትን ያህል ሰፋትና መልዓት አልነበረውም ነው [163] እስከ ዚህ ጊዜ ድረስ በፍትሐ ነገሥት የሰፈሩትን ምንጮች መነሻ ጊዜ ለማመልከት ተሞክሯል ።

962.II Synodos Etiopico Ser. VII. III 1943 ገጽ 41 48 W. Reidel: Die

163. A Nallino Raccolta Di Scrittit IV 371–374, D'emilia Influssi Di Diritto Musulmano Capitolo XVII. 2 Del Nomocanone Arabo Christiano di Ibn al Assal. R.S.O.T. XII 1941 – 1942 T.I. (1 – 15)

Kirchenrechtsquellen ገጽ 116

4· የፍትሐ ነገሥት ወደ ግእዝ መመለስ

4·1 ፍትሐ ነገሥት ወደ ግእዝ የተተረጐመበት (የተመለሰበት) ዘመን

ፍትሐ ነገሥት ወደ ግእዝ ቋንቋ የተተረጐመበት ዘመን በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ (1444—1468) መጀመሪያ ዘመነ ንግሥ መሆኑ ይታመናል [164] ።

በትውፊት ኢትዮጵያ በ9ኛው ምዕተ ዓመት ቅድመ ክርስቶስ በንግሥተ ሰባና በልጅዋ ምኒልክ ገብቶ እስከ 15ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ እንደተጻፈ ሕግ ሁኖ ሲሰራበት በነበረው የሙሴ ሕግ (ኦሪት ሙሴ) ትተዳደር እንደነበር ይተረካል ። በትውፊትና በሌሎችም ታሪካውያን ምንጮች መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ እንኳን ለማለት ባይቻልም አብዛኛው ክፍል ለብዙ ዘመናት (9ኛው ቅ·ክ· — 15ኛው ድ·ክ) በእናት ንግሥቱ ሳባና በልጅ ምኒልክ አማካይነት በገባው የሙሴ ሕግ ሲተዳደር ኖሮአል ። ከዚህም በመነሳት የኢትዮጵያ ዙፋን መሥራች ምኒልክ እንደሆነ በመቁጠርና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የዚህ ዙፋን ሕልውና መቀጠል በመጽሐፍ ቅዱስ "በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም ፣ የገዥም ዘንግ ከአግሮቹ መካከል" (ዘፍጥረት 49·10) በሚለው መሠረት የእስራኤል መለኮታዊ አልጋ ወራሽና ቀጣይ እንደሆነ ሲነገርለት ቆይቷል ።

አፄ ዘርዐ ያቆብ በኢትዮጵያ የመንግሥቱን ፖለቲካዊ አስተዳደር ለመለወጥና የቤተክርስቲያንን ሕይወት ለማሻሻል ከተነሱት ነገሥታት አንዱና ከፍተኛ ድርሻ የነበረው ንጉሠ ነገሥት አንደ ነበረ ይነገራል [165] ።

ይህን የሙሴ ሕግ ለመተካት ፍትሐ ነገሥት ወደ ግእዝ ተተርጕሞ የአገሪቱ ሕግ ሁኖ ያገለግል ዘንድ የሐሳቡ ባለቤት ወይም የሐሳቡ እመንጪ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ መሆኑ አላጠራጠረም ።

164. Dillmann: Über die regierung Insbesondere die Kirchenordnung des Könige Zara Iacob, Rerlinne 1884.

165. ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው (OFFSET) ሕትመት ገጽ 8 ዐምድ 1 P. Tzadua The Fetha Nagast...ገጽ XVII.

አፄ ዘርዐ ያቆብ አገራቸው የክርስትናን ትምህርት ተቀብላ ብዙ ዘመናት ስታሳልፍ ነገር ግን የምትተዳደረው በኦሪት ሕግ መሆኑን ያሳዝነው ስለ ነበር ብሉይ ሕግ በሐዲስ ሕግ መተካት እንደነበረበት ምኞት ነበረው ።

ሁናም በእጠገቡ ይገኝ የነበረ ጴጥሮስ አብደል ሰይድ የተባለ ሰው ኀዘኑን ተመልክቶ ስለምን እንደሚያዝን ቢጠይቀው አገሬ በክርስትና እምነት ሐዲስ ኪዳንን ተቀብላ የምትገኝ አገር ስትሆን ዘብሉይ ኪዳን ሕግ እየተዳደረች መገኘቷ የሚል መልስ ሰጠው ።

በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ በክርስትና ትምህርት ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕግ በግብጽ አገር እንደሚገኝ በማስረዳት ይህን ሕግ አስመጥቶ በሥራ ላይ ያውለው ዘንድ መከረው ። በዚህ ጊዜ አፄ ዘርያዕቆብ "ይህን የመሰለ መጽሐፈ ሕግ የሚገኝ ከሆነ አንተ ዐረብኛ ቋንቋን ታውቃለህ ሂድና አምጥተህ ተርጉምልኝ" በማለት 30 ወቄት ወርቅ ሰጥቶ ወደ ግብጽ ላከው ።

ጴጥሮስ አብደል ሰይድም በንጉሡ ነገሥቱ ጥያቄ መሠረት ወደ ግብጽ አገር ሂዶና ይህን መጽሐፈ ሕግ አምጥቶ ወደ ግእዝ ቋንቋ ተርጉሞ ሰጠው ።

ይህ ትውፊታዊ ታሪክ ሲያያዝ የመጣው ታሪክ ነው ። ነገር ግን በሥራ ላይ ለመተርጐም የመጀመሪያው ምንጭ—መረጃ የተገኘው በአፄ ሠርጸ ድንግል (1563—1597) ዘመነ መንግሥት ነው [166] ።

ዛሬ በአውሮፓ ልዩ ልዩ አብያተ መጻሕፍት ከሚገኙ የፍትሐ ነገሥት የእጅ ጽሑፎች መካከል በአፄ ዮሐንስ ተጻማዊ ዘመነ መንግሥት (1667—1682) የተጻፈ ቅጅ ይገኛል [167] ።

ስለዚህ በወል ግንዛቤ ፍትሐ ነገሥት በ15ኛው ምዕተ ዓመት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጕሞ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕግ (የመንግሥትና የሃይማኖት ሕግ) በተሻለው አግራጭ ግን ብሔረ ሕግ ወቀኖና (Corpus

166. C. conti Rossini: Historia Regis sarsa-dengel (MELAK Seged) Paris-Leipzrg 1807) ክፍል አንድ (ግእዝ) ገጽ 76 እና ክፍል 2 (ፈረንሣይኛ ትርጉም) ገጽ 87፡ Κεφάλεβ Σ., θερί τής Ανεξαρτησίας τής Αιθιοπικής Εκκλησίας ገጽ 46

167. I Gnidi: Il Fetha Nagast... ገጽ VII-VIII

iuris canonici et civilis) ሆኖ በሥራ ሲውል እንደቻለ ነው[168]

4·2 ፍትሐ ነገሥትን ወደ ግእዝ የተረጐመው — የመለሰው ሰው

ፍትሐ ነገሥትን ወደ ግእዝ ቋንቋ ስለተረጐመው ሰው ማንነት በመዝጊያው – መደምደሚያው ክፍል ከሰፈረው መግለጫ ለመረዳት ይቻላል ።

በዚህ መዝጊያ—መደምደሚያ ሁለት ሰዎች ጴጥሮስ ወልደ አብደ ሰይድ እና ቀሲስ አብርሃም ወልደ ሐናናጥያን ይገኛሉ[169] ።

ከነዚህም ሰዎች የመጀመሪያው ጴጥሮስ ወልደ አብደል ሰይድ ፍትሐ ነገሥትን ከዐረብኛ ወደ ግእዝ እንደተረጐመ ሲመለከት ሁለተኛው ቀሲስ አብርሃም ወልደ ሐና ናጥያን የፍትሐ ነገሥት ትርጉም በቀና ሂደት እንዲከናወን ተገቢውን ጥንቃቄ ያደረገ ሰው ሆኖ ይታያል ።

ሀ) ስለ ጴጥሮስ ወልደ አብደ—አብደል ሰይድ ማንና ምን ዓይነት ሰው መሆንን በሚመለከት ስዚህ መዝጊያ ላይ እንደሰፈረው ይህን ፍትሐ ነገሥት ለመተርጐም ተመጣጣኝ ዕውቀት ካለመኖሩ የተነሳ ይህን ሥራ—ትርጉም ለማከናወን አቅመ ቢስ ሁኖ መገኘቱን በማመልከት ስለዚህም ምንዓልባት ለሚፈጠሩ (ለተፈጠሩ) ስሕተቶች ከአንባቢያን ይቅርታንና ትእግሥትን መጠየቁን መመልከት ቢቻልም ሌላ ትርጉም ሊሰጠው ይችላል ።

በርግጥ የፍትሐ ነገሥት የግእዙ ትርጉም ከዐረብኛው ጋር ሲተያይ — ሲነጻጸር ስሕተቶችና የአለመጣጣም ሁኔታዎች ያጋጥማሉ ይከሰታሉ ። ከነዚህም ሁኔታዎች እንደ I. Guidi[170] አስተሳሰብ የሀረብኛው ፍትሐ ነገሥት ወደ ግእዝ በደንብ ባለመተርጐሙ ሁኗል ። Guidi የመግቢያ ሐተታ ፍትሐ ነገሥትን ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተርጓሚው ሰው በአንድ በኩል ግብጻዊ እንደነበር ቢታመንበትም ዐረብኛ ቋንቋን በደንብ (አጣርቶ) ካለማወቁ በመነጩ የተፈጠሩ ስሕተቶችና

168. Conti: Rossini Il Synodos Etiopico Ser VII T' III
169. ፍትሐ ነገሥት መዝጊያ —መደምደሚያ
170. I. Guidli, Fetha Nagast ... ገጽ XIX Κεφέλεβ Ζ., Περί της Ανεξαρτησίας τής Αιθιοπικής Εκκλησίας ገጽ 45

የሁለቱ ሰነዶች የአለመጣጣም ሁኔታዎች ተመልክተዋል ። ሁኖም ግብጻዊ ነበር የሚለው አስተሳሰብ ከአባቱ ስም "አብደልሰይድ" በመነሳት ነው ። ነገር ግን ከአባት ስም ብቻ በመመርኮዝ ይሀ ሰው ጴጥሮስ ወልዶ አብደል ሰይድ ግብጻዊ — ቅብጣዊ ነበር ማለት አይቻልም ። ኢትዮጵያዊም የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም ምክንያቱም አብደልሰይድ ለጴጥሮስ የጡት አባት ወይም በተለየ በግብፅ በነበረበት ጊዜ አስተማሪው ኑሮ ይሆናል ። በኢትዮጵያ ልማድ ብዙ ጊዜ ተማሪዎች በአስተማሪዎቻቸው ስም (እንደ አባት ስም) እንደሚጠሩ ይታወቃል ለምሳሌ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፡ ደስታ ኪዳነ ወልድ ።

ይህም ሲሆን የቻለበት ምክንያት ተርጓሚው ዐረብኛውን ወደ ግእዝ ሲመልስ ብዙዎችን ፍሬ ነገሮች በትክክል ለማስተላለፍ ባለመቻሉ መሆኑ ይታሰባል ምክንያቱም ለተራ አንባቢ ብቻ ሳይሆን ዐረብኛውን ተመልክቶ ሊረዳ ያልቻለ ካልሆነ ለምሁርም ቢሆን ሊረዱ ሊገቡ የማይችሉ ብዙ ዐረፍተ ነገሮች ይገኛሉ ። ስለዚህም አንድ ሰው የፍትሐ ነገሥት ብዙ ክፍሎችን ለመረዳት የሚቻለው በግምት ከአጠቃላይ ስሜቱ በመርኮዝ (Ad Sensum) ነው ።

426. G. Philippos: The Doctrine of Addai the Apostle, London ..... ገጽ 76

427. W Cureton: Ancient Syriac Documents, London 1864 .... ገጽ 1፡23

428. B.P. Pratten: The Teaching of Addaieus the Apostle A:N:Fገጽ 68.165

429. L. Abishian: Letter D'Abgar ou Histoire de la conversion Edessenes Viènnie 1868

430. Langlois Collect des Historiens anciennes Et Modernes De l Armanie 1867 H.G Youtie: The Coptic Version of the Letter to Abgar H.T.A. 24/1831 .... ገጽ 61

ሆኖም ይህ መጽሐፍ–ትምህርት ዘአዱዎስ ከ30 ቀኖናት—ሥርዓተ ጽዮን ወይም "ትምህርተ ፲ወ፪ቱ ሐዋርያት" ጋር ግንኙነት የለውም[431] በመጨረሻ የኤዴሳ ቤተክርስቲያን መሥራች ሐዋርያ የግብረ ሐዋርያት ታዴዎስና የአቡሊዱስ ታዴዎስ ከሰብዓ አርድእት አንዱ ታዴዎስ እንዶሆን የተጠቀሰው ፉዛዛቤን ለአገረ ገዥ አብጋርን ሰጠ አልሰጥም እንደ ተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን የመጀመሪያው ፊደል በታዴዎስ ፈንታ አዴዎስ ሊባል እንደቻለ እሱም 30 ቀኖናተ ሐዋርያት የመነጨበት መጽሐፈ ትምህርትን የጻፈ መሆኑን ለማገናዘብ ይቻላል ።

ከዚህም በላይ የታወቀ የሱርስጥ ልምድ በኤዴሳ ቤተክርስቲያን ሰዎች (አባቶች) መካከል ትድሚያ ቦታን ይዞ እንደሚገኝ ይነገራል[432] አንድ ሰው ወደ እነዚህ ቀኖናተ (ሥርዓተ ጽዮን ችግርተ ተመልሰና በራሳቸው መግቢያ በተዘረዘሩት ነገሮች ላይ ተመሥርቶ ለመመልከት ቢሞክርም በመጀመሪያ እነዚህ ቀኖናት በሐዋርያው ርድኡ አዴዎስ ተዘጋጅተው በሐዋርያት እንደ ታወጁ ወደ መደምደሚያ ሊደርስ ይችላል። ነገር ግን ከብዙዎቹ ቀኖናት ድንጋጌዎች በመነሳት ቀደም ብሎ እንደተመለከተው ከጊዜም አንጻር ሆነ ከተገኙበት ምንጭ አንጻር ከዘመነ ሐዋርያት በኋላ እንደ ተዘጋጁ በአንድ በኩል በሌላ በኩል የጸሐፊው ስም አዴዎስ ስውር ስም መሆኑን መረዳት አያዳግትም ቢሆንም እነዚህ ቀኖናት ቀደም ብለው ከተገኙት ቀኖናት መካከል መሆናቸው ከጥርጣሬ ውስጥ አይገባም[423] ምክንያቱም እነዚሁ ቀኖናት በአንድ ወይም በሌላው መልካቸው በጥንት ቤተ ክርስቲያን በተለይም ከ432 ከሦስተኛው የቁስጥንጥያ ዐቢይ ሲኖዶስ በፊት እንደ ነበሩ ይታወቃል ። ይህም በልዩ ልዩ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናተ (በንስጥርሳውያትና መለካውያተ አብያተ ክርስቲያናት) እንደዚሁም በሱርጥና ግብጽ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተተርጉመውም ይገኙ እንደነበረ ስለሚታወቅ ይህ ማስረጃ ነው ።

እንደሚታወቀው የመጀመሪያው የጥንት አብያተ ክርስቲያናት

431. Acheus, Apostolischen Kirchenordnung R F E. ገጽ 237 Nau. Canons des apotes. D.T.C.ገ III አምድ 1612

432. Ruvens Duval, Anciennes litteratures Chretiennes. II litterature Syriaque Paris 1900፤ ገጽ 100. 118

433. A Harnack: Ueberieferung

ገጽ 433 H. Leclerq. Canons Apostoliques D.A.I. I. t. 22 .... ገጽ 1938

መለያየት የተፈጠረው በአጼ መርቅያኖስ በ451 በተጠራው አራተኛው የኬልቄዶን ዐቢይ ሲኖዶስ ነው ።

ከአጼ መርቅያኖስ የተላለፈውን ውሳኔ ሲኖዶሱ እንዲያሳልፍ ተፅዕኖና ግፊት ያደርግ ስለነበር የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ዲዮስቆርስና ሌሎች አንድ አንድ የምሥራቅ ኤጲስ ቆጶሳት ይህን የመርቅያኖስንና የሲኖዶስን አቋም ቢቃወሙም ትሱ የመርቅያኖስ ፍላጐት በሲኖዶሱ ተካፋዮች የድምጽ ብልጫ አለፈ ፤ የሲኖዶሱም ውሳኔ ሁኖም ጸደቀ ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፡ ስለዚህም የአጼ መርቅያኖስን የንጉሡን ሐሳብ ደግፈው ውሳኔውን ያስተላለፉት ወይም በውሳኔው የተካፈሉት ክፍሎች "መለካውያን" "ንጉሣውያን ተብለው ተሰየሙ ። በዐረብኛ መለከ ማለት ንጉሥ ማለት ስለሆነ የንጉሡ ደጋፊዎች ለማለት ነው ። ተቃዋሚዎቹ "ያዕቆባውያን" ተብለው ተሰየሙ—ተጠሩ[434] "መለካዊያን" የሚለው ስያሜ ጥያቄ ባያስነሳም "ያዕቆባውያን" የሚለው ስያሜ አመጣጥ ግን የተለያዩ አመለካከቶችን ጋብዟል ።

1. ዲዮስቆርስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ከመሆኑ በፊት ያዕቆብ ይባል ነበር ። በልምድ እንደሚታወቀው ዲዮስቆሮስ በስደት በነበረበት ጊዜ አንድ ደብዳቤ ያዕቆብ በሚል ስም ጽፎና ከዚህ ደብዳቤም ጋር ከጥርሶቹ አንዱን ጥርስና ከጢሞቹ ሦስት ጠጉሮችን ነቅሎ በእስክንድርያ ለሚገኙ ክርስቲያኖች የፍሬ ሃይማኖት ምስል አድርጐ እንደ ላከላቸው ሲታመን የእሱን ትምህርት የተከተሉት ሁሉ "ያዕቆባውያን" ተብለው ተጠሩ ይባላል ።

2. የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ሳዊሮስ አንድ መፍትሬ ዲዮስቆርስ የነበረ ተማሪ ነበረው ። ይህም ተማሪ የዲዮስቆርስን ትምህርት በማጠናከር በክርስቲያኖች ዘንድ መልካም ውጤትን አሳየ—አስመዘገበ ። ስለዚህ ትምህርት ታማኝ ሁነው የተገኙት ክርስቲያኖች "ያዕቆብያውያን" ተብለው እንደተሰየሙ ይነገራል ።

3. አንድ ከደግነቱና ጽናቱ የተነሳ ድሪቶ ለባሽ ባሕታዊ የነበረ የኤዴሳ ኤጲስ ቆጶስ (543.548) ስለዚህም Ya' Qub El–Baradai

434. Iaqi-ed-din et waqrit.. A Short History of the Copts and Their Churchs ትርጉም Malan Solomon London 1873 .... ገጽ 15
Renaudotius, Historia patriarchum Alexandrinorum Iacobitarum ab Marcousque Ad Finem Saeculi XIII. Paris 1713.

ወይም በግእዝ ያዕቆብ ዘእል በረዳይ በግሪክኛ ያቆቦስ (ያዕቆብ) Bara Datos በመባል የሚጠራ ኤጲስ ቆጶስ ነበር ።

ይህ ሰው ክርስቲያኖችን የበለጠ ወደ ዲዮስቆሮስ ትምህርት እንዲሳቡ ለማድረግ ከክልል ወደ ክልል በመዘዋወር ይሰብክ ነበር ። ስለዚህም በኃለ ቅናቱ ተግባሩን ፈጸመ ። የሶርያና የግብጽ አብያተ ክርስቲያናት "ያዕቆባውያን" ክርስቲያኖችም" "ያዕቆባውያን" ተብለው ይጠሩ ዘንድ አበቃ ይባላል ።

ስለዚህ ያዕቆብያውያን ፣ ያዕቆብያውያት የሚለው ኃይለ ቃል በመጀመሪያ የአራተኛውን ዐቢይ ሲኖዶስ ውሳኔ ውድቅ ላደረጉ የምሥራቅ አውራጃዎች ክርስቲያኖችና አብያተ ክርስቲያናት ይሰጥ ነበር [435]

ይህ የመጨረሻው ሦስተኛው አስተሳሰብ ትርጉም ቢያንስ "በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊጸና የቻለ ይመስላል ። ቆይቶ ያዕቆብያውያን የሚለው ቅጽል በሶርያ ብቻ ሲወሰን ለግብጾች ክርስቲያኖች ግብጦች" (ቅብጦች) የሚለው ስያሜ ተፈጠረ) ጸና ።

ስለዚህ የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብነ እል አሳል በሶርያ ክርስቲያን "ያዕቆብያውያን" በግብጽ ክርስቲያኖች "ግብጣውያን" (ቅብጣውያን እንደሚባሉ ማለትም የስያሜ ልዩነት መኖሩን አሳየ [436]

በሌላም በኩል እነዚህ የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት በሚገኙበት ምሥራቅ ክልል ቀኖናተ ቤተ ክርስቲያን በአጭሩ ሦስት ክፍሎች ይዘው እንደሚገኙ ይታወቃል ። ሲያያዝ በመጣው ልምድ መሠረት ፤

1. በጥንት አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት የነበራቸው ቀኖናት ማለትም አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ወደ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበረሰባት ከመከፋፈሏ በፊት የታወጁና በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ተጠብቀው የሚኖሩት ቀኖናት ለምሳሌ የኒቅያ ጉባኤ 20 ቀኖናት [437]

2. ቀኖናት አንድም የበለጠ በተቀነባበረ አዲስ መልክ የተቀረጹ ወይም ከጊዜያት በኋላ በእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ሕይወትና ትምህርት በተፈጠሩ አዳዲስ ሁኔታዎች ጋር ለማዛመድ/ለማስማማት አንድ

435.M.. Solomon: Jaqi-ed-din el waqrit: A Short History OF The Copts And Their Churches .... ገጽ 15

436. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2. አንቀጽ 51 ቁጥር 1812

437· ከዚሁ ገጽ 255,211

አንድ ድንጋጌዎች ተጨምረውባቸው የተዘጋጁ ቀኖናት ናቸው ለምሳሌ በበታው የሚመረመሩት የኒቅያው አንደኛ ሲኖዶስ 84 ቀኖናት [438] አንድ አንድ ቀኖናትን ብንመለከት ለምሳሌ ቀኖናት 7 — [439] 19 [440] 24 [441]፡ 38 [442]፤ 45 [443] ፡ 47 [444] ፡ 51 [446] ፡ 77 [447] ፡ 81 [448] 56 ቀኖናት [449]

3 ቀኖናት በዚሁ ምሥራቅ ክልል ከሥር መሠረቱ የተቀረጹ ግን ለታላላቅ አባቶችና ጸሐፍት የተሰጡ ቀኖናት ለምሳሌ ለትልቁ ባስልዮስ 106 ቀኖናት [450] ለትልቁ አትናቴዎስ 107 ቀኖናት [451] ከሥር ከመሠረቱ ሲባል ግን ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ቀኖናት ጋር ግንኙነት የሏቸውም ማለት አይደለም እንዲያውም የበለጠ ከእነሱ ላይ ተመርኩዘው እንደተቀረጹ ነው ለመናገር የሚቻለው ምክንያቱም በእነዚህ ሦስት ቀኖናት መካከል ያለው መታሰርና መያያዝ ግልጥ በመሆኑ የበለጠ ማብራራት አስፈላጊ ሆኖ አልታየም ። ስለዚህ እነዚህ ቀኖናት የተጻፉበት ዘመን ዘመነ ሐዋርያት አለመሆኑን መቀበል ግድ ሲሆን ከ"ሐዋርያውያት ትእዛዛት" ከ85 ቀኖናት ጋር ያሏቸው ግንኙነቶች (ዝምድናዎች) የተሰሩበትን ዘመን ያሳያሉ ። የተነሱበትንም እንኳን ባይሆን የቀሙበትን ዘመን Termimus Ad Quem ግን Terminnus a Quo አይደለም ነገር ግን የትኞቹ ይቀድማሉ? ወይስ የትኞቹ ይከተላሉ? የሚለው ጥያቄ ይነሳል።

ስለዚህ ከይዘታቸው የመነጨ 30 ቀኖናት በጊዜ እንደሚቀድሙና ትእዛዛተ ሐዋርያትና 85 ቀኖናት ሐዋርያት የ4ኛው ምዕተ ዓመት

ከዚሁ ገጽ 255.211

439. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 157

440. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 193

441. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 206

442. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 206

443. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 182

444. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 197

445. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 154

446. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 148

447. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 158

438· ከዚሁ ገጽ 255–259

448· ከዚሁ ገጽ 1–237

449· ከዚሁ ገጽ 297

450· ለምሳሌ 7·45· 59· ከዚሁ ገጽ 269–272

451· ከዚሁ ገጽ 270

መጨረሻ ወይም የ5ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ሥራዎች እንደነበሩ ይታሰባል። ቢሆንም በርግጥ ይህም ሲባል ፍጹምነት አለው ማለት አይደለም በተጨባጭ ይኸ ነው ምክንያቱ ብሎ ለማስረዳት ያዳግታልና ሆኖም በትክክል እንኳን ባይሆን በተቃረበ ሁኔታ ርግጠኛ ለመሆን የሚቻለው እነዚህ ሁለት ክፍላተ ቀኖናት በአንድ በኩል 30 ቀኖናት በሌላ በኩል ትእዛዛተ ሐዋርያት 85 ቀኖናተ ሐዋርያትን ጨምሮ በተጠቀሰው 4ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ወይም በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ክልል ውስጥ እንደተጻፉ ነው።

በተቃራኒው የ30 ሐዋርያውያት ቀኖናት የተጻፉበትን መድረሻ ዘመን Terminus Ad Quem በሚመለከት የእነዚህ ቀኖናት የተጻፉበት ዘመን መነሻ Termimus a Quo ከቀኖናቱ በአንዱ ቀኖና ሊወሰን ይችላል ይህም ቀኖና ስለ አስተርዮት በዓል "በዓለ አስተርዮ" የሚደነግገው ቀኖና ነው።

ስለ "በዓለ አስተርዮ"[452] የተጻፈ ቀኖናን ለመጥቀስ ባይቻልም በጣም ቀደም ብሎ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ልምድ መሠረት እስከ 4ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ይጠቀም ነበር።[453]

---

452. በመጀመሪያ "አስተርእዮተ እግዚአብሔር" የሚለው ኃይለ ቃል ልደተ ክርስቶስ ከሚለው ኃይለ ቃል ጋር ይማታ ነበር ። ስለአስተርእዮና ልደተ ክርስቶስ መመሳሰል ቴርቱርዮስ በእንግሊዝኛው ስለ ልደተ ክርስቶስ "አስተርእዮት" ወይም "ልደት" የሚሉ ቃላትን ሲጠቀም ስለ "በዓለ ጥምቀተ ክርስቶስ ግን" ኤጲፋንያ የሚለውን ኃይለ ቃል ይጠቀም ነበር ።
ስለዚህ በዓለ ጥምቀተ ክርስቶስን ለመግለጥ በተለዋጭ ሁለት ቃላትን ይጠቀሙ ነበር።
"አስተርእዮ" ከቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ የተፈጠረ ኃይለ ቃል ነው (ጢሞቴዎስ 1ኛ·3·16·2) "ኤጲፋንያ" አሁንም ከቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ የተወሰደ ኃይለ ቃል ነው (ቲቶ 2·11·13)

453· ብርሃን ክርስቶስ በተጠመቀበት ተን የንውሳን ክርስቲያን የመጠበቅ ልምድ ስለነበረ ከዚህ የመነጨ ኃይለ ቃል "በዓለ ብርሃን" ቴርቱርዮስ በእንግሊዝኛ ቃል 39 ለቅዱሳት ብርሃናት P. G.T. 36 ዐምድ 336። ነገር ግን ዛሬ የበለጠ እንቶ የሚገኘው ኃይለ ቃል ኤጲፋንያ ነው ስለዚህ ይህን የመሳሰለውን መግታት ለማስወገድ ወደፊት "ኤጲፋንያ" የሚለውን ኃይለ ቃል መጠቀምም በዓለ ጥምቀት ማለት መሆኑን መረዳቱ ተገቢ ይሆናል።
በዓለ ኤጲፋንያ ከቀለሚንጦስ በመጣ ምስክርነት መሠረት አንድ ዕለተ ጥምቀተ ክርስቶስ ተቀጥር በታወቁ የባሲሊዲስ ተከታዮች ተጀምሮ ጥር 6 ቀን ይከበር ከነበረው የፋሲካ በዓል ቀጥሎ ጥንታዊ ክርስቲያናዊ በዓል ነው በሌላ በኩል በዚያን ዕለት በግብጽና በዐረቢያ አሕዛብ የክረምት ቁመተ ፀሐይን ያከብሩ ነበር። Ηλιοστάσιον በርም ታህሣሥ 25 ቀን ይኸው ዓይነት በዓልና ሆኖ የማይሸነፈው ፀሐይ ልደት Natalis Solis Invici ይከበር እንደነበረ እናውቃለን ።

ስለዚህ በምሥራቅም ሆነ በምዕራብ አንድ ጊዜ እነዚህ የእምልኮተ ጣዖት በዓላት በክርስቲያን በዓል መተካታቸው ይታወቃል።

ይህም በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቴዎፍሎስ (385—412) ቀኖና አንድ ሊወጣ ይችላል። ልምድና ሥርዓት ሁሉንም እሁድን እንድናከብር ይጠይቀናል በዚያችም ዕለት ክብረ በዓል እንድናደርግ ምክንያቱም በዚያች ዕለት ጌታችን ከሙታን መነሳትን እውጀልናል...የቅድስት አስተርእዮ የጾም ዕለት እንጠብቃለን....[454]

ቢሆንም ቀኖናው ግልጥ አይደለም ስለዚህ ከመጨረሻው ሐረግ ለጾም ቀን የሚገባውን እናደርጋለን፣ የማታውን ስብሰባ እንጠብቃለን... የበዓለ ኤጶፋንያንና ልደት ዋዜማ እሁድ ቀን በሚሆንበት ጊዜ ይህ እሁድ ቀር እንዲጾም ይናገራል ።[455]

ከቴዎፍሎስ በፊት የነበረው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ጢሞቴዎስ (381— 385) የበዓለ ኤጲፋንያ ዋዜማ ጾም ቀን መሆን እንደነበረበት ያስተምር ነበር። በጊዜው የነበረውና ተከራካሪው የነበረው ዮሐንስ አፈወርቅ ኤጲፋንያ ከክርስትና ዋና ዋናዎቹ በዓላት የመጀመሪያው በዓል እንደሆነ ይናገራል።[456]

በምዕራብ በዓለ ኤጲፋንያ Epiphania,Festum Epiphaniae, Dies Epiphanionum, Dies manefestationis Domini: በ4ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ አጋማሽ ላይ ይከበር እንደነበረ እናገኛለን ምክንያቱም ዮልያኖስ ዐላዊ ሕግ በ360 በፈረንሳይ አገር ተገኝቶ ጥር 6 ቀን በዓለ ኤጲፋንያ ሲከበር በቪዬና ቤተክርስቲያን መገኘቱን ከሚያሳየው የታሪክ ጸሐፊ አሞያኖስ ማርቄሊኖስ ምስክርነት ለመረዳት ይቻላል።[457]

454· በአጋጲዮስና ኒቆዲሞስ የተናናውን Πήδαλιον ትርጉም ተመልከት ገጽ 47
455· Πήδαλιον ገጽ 472 የግርጌ ማስታወሻ 1
456· በዓለ ኤጲፋንያ አምላክ በምድር የተገለጠበትና ከሰዎች ጋር አብሮ የታየበት ስለ በጸንጠቆስጤ ንግግሩ የ·G.T. 56 ዐምድ 452
457· Ammjan Marcelin: Hist.1. XX1.c.2. Rerum Gestarum xx 2.5.

የበዓለ ኤጲፋንያ ዋዜማ[458] እና የበዓለ ልደት ዋዜማ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን እንዲያውም ጥብቅ አጽዋማት እንደሚባሉት ተቆጥረው የጾም ቀናት ሆነው ይጠበቃሉ[459] ማለትም የእነዚህ በዓላት ዋዜማዎች ቀን ዐርብና ረቡዕ ካልሆኑ ይጾማሉ። በልምድ የበዓለ ልደትና የበዓለ ጥምቀት ዋዜማዎች በመጀመሪያ ማለትም።

ቢሆንም እግረ መንገዳችን ለማውሳት ቢሞከርም ትክክለኛው አቀማመር ይህ ነው ብሎ ማመን ግን አይደለም። ልደትና ኤጲፋንያ ጥምቀት ረቡዕና ዓርብ የሚውሉ ከሆነ ማለትም በዐርብ ፈንታ ሐሙስ

458· "ቴዎፋንያ" ΘΕΟΦΑΝΙΑ የሚለው ንዩስ ቃል በኢትዮጵያ አይታወቅም፤ ቃሉ አልተወሰደም፤ አልተገለበጠም ሆኖም ግን "ኤጲፋንያ" የታወቀ ንዩስ ቃል ነው። ቴዎፋንያ ማለት አስተርዮተ እግዚአብሔር ማለት ቢሆን ኤጲፋንያም ΕΠΙΦΑΝΙΑ ማለት አስተርዮት ማለት ነው ልዩነቱ በቴዎፋንያ እግዚአብሔር የሚለው ቃል ስላለበት ነው። ከበዓለ ጥምቀት ጀምሮ እስከ ዐቢይ ጾም ጾመ ሕርቃልን ጨምሮ ያለው ጊዜ በኢትዮጵያ አንድ ጊዜ "ኤጲፋንያ" ሌላ ጊዜ "አስተርዮ" ይባላል።

459 በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም ሆነ በግብጽ ቤተክርስቲያን ልዩ ልዩ አጽዋማት(ጥብቅና ቀላል) ይጠበቃሉ፤ ስለዚህ የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ "በእንተ ኩሎሙ አጽዋማት" በሚል ርእስ አንድ ሙሉ አንቀጽን— 15ኛ አንቀጽን ሲያበረክት የአጽዋማቱ ቀመሮች ሰባት መሆናቸውን ይገልጻል።

ሆኖም እነዚህ ሰባት አጽዋማት ቁጥራቸው እንደተጠበቀ ሁኖ በተለያየ አቀማመር ይገለጻሉ።

ሀ· 1· ጾመ ዓ (ዐቢይ ጾም)
2· ሕማማት ሰሙነ ስቅለት
3· ጾመ ልደት (ስብከት)
4· ጾመ ሐዋርያት
5· ረቡዕ
6· ዓርብ እና
7· ገሀድ ድራረ ልደትና ድራረ ጥምቀት ተለያይተው የሚቆጠሩ ሲሆን ረቡዕና ዓርብ አንድ ሁነው ይቆጠራሉ።

ለ. 1. ጾመ ዓ (ዐቢይ ጾም)
2. ጾመ ልደት (ስብከት)
3. ገሀድ (ድራረ ልደትና ድራረ ጥምቀት)
4. ረቡዕና ዓርብ
5. ነነዌ
6. ጾመ ሐዋርያት እና
7. ፍልሰታ ፡ ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ገጽ 216

በረቡዕ ምትክ ግክለኛ የጾም ቀናት ይሆናሉ ምክንያቱም በእነዚህ ቅዱሳትና ክቡራት ቀናች ልደትና ኤጲፋንያ (ጥምቀት) ጾም ሊዋልባ ቸው አይፈቀድም (ቀኖና 64) ነገረ ግን ቀስ በቀስ ይህ ልምድ ልደትና ጥምቀት በሳምንቱ ማንኛውም ቀን ቢወድቁ የእነዚህ በዓላት ዋዜማ ቀናት ይጾማሉ። ሰኞ ቀን እንኳን እነዚህ በዓላት ቢውሉ እሁድና ቅዳሜ ለሦስትና ለአራት ሰዓታት እንደሚጾሙ እንደ ትውፊታዊ ቀኖና ሆኖ ሊታይ ችሏል። ስለዚህ በዚሁ በሊቀ ጳጳሳት ቴዎፍሎስ ቀኖና ላይ ተመርኩዞ ምርምርን የሚያካሂድ ሰው እነዚህ ቀኖናት በ400 ድኅረ ክርስቶስ እንደተዘገጁ ማለትም ይህ ጊዜ የእነዚህ ቀኖናት ዝግጅት መነሻ ዘመንን(Termimus a quo መያዝ እንደ አለበት ሊደመድም ይችላል በተቃራኒው ክላይ እንደተባለው [460] የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ንስጥሮስን ያወገዘው 3ኛው የኤፌሶን ዐቢይ ሲኖዶስ የተሰበሰበበት) የተጠራበት 431 የእነዚህን ቀኖናት ዝግጅት መዳረሻ ዘመን Termimus Adquem እንደሚወስን ያመለክታል ምክንያቱም በተወገዘው ሊቀ ጳጳሳት ንስጥሮስ ሥር የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ቀኖናት ልትጠቀም ችላለች። እንደዚሁም ምክንያቱም ይህች ቤተክር ስቲያን እንደ እሷ እምነት በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ወይም ጳጳሳት በተደነገጉ ቀኖናት ትጠቀም ነበር ማለት ያጠራጥር ይሆን ይሆናል ለሌሎችም ተመሳሳይ ቀኖናት ይህ ዓይነቱ ችግርም ሊፈጠር ይችላል።

እንግዲህ "ዓይን" በሚል ምኅፃረ ቃል የተመለከተው ሥርዓተ ጾምን (30 ቀኖና ሐዋርያት) የተጻፉበት ዘመን በግሪኮች ዘመነ መንግሥት ቀመር ሐምሌ 14 ቀን 342 መሆኑ ማለትም ክርስቶስ የተወለደው በዚህ ቀመረ ዘመን 309 [461] ስለሆነ 342 309 = 33

---

460. ከዚሁ ገጽ 117 225 ግን M. Achelis Geschichte Der Kirechenordnung RE. AOT. 1. ገጽ 740 A. Harnack, Die Älchristlichen Literature, die Ueberlieferung ገጽ 5331 F, Nau; Les 27/30/ Canones appostolici D.C.T. 22 አምድ 1618–1619 ።

bung ገጽ 533፣ F.Nau, Lcs 27/30/ Canones appostolici D.C.T. 22 አምድ 1618-1619

461· በግሪኮች ዘመነ መንግሥት ቀመር ሐምሌ 14 ቀን 342 እሑድ በዓለ ጰንጠቆስጤ በዋለበት ዕለት ሐዋርያትና አርድእት የክርስቶስ መያዝ ከተሰበከበት ገሊላ ናዝሬት ወደ ይብሪ ሀይት ተራራ የወጡበትና የመጀመሪያ ሐዋርያዊ ስብሰባ ሲኖዶስ ያደረጉበት ቀን ነበር ተብሎ ይታመናል P.de. Lagarde, Reliquiae... Graec ገጽ 9

በእንጠቀስጤ ዕለት እሑድ ማግሥት ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን በገኑት በአደረጉት የመጀመሪያ ስብሰባ (ተዳግሮ ሐዋርያዊ ጉባኤ ሲኖዶስ) የተጻፈ ግብረ ሐዋርያት ሁኖ በሰሚቀጠር ይህ ሥርዓተ ጽዮን (30 ቀኖናተ ሐዋርያት) የተጻፈበት ጊዜ ይህ የሐዋርያት የመጀመሪያ ስብሰባ ዕለት ነው የሚለው ታሪክ ቀደም ብሎ ተወስቷል።
ነገር ግን ሥርዓተ ጽዮን ወይም የሚመረመሩትን ቀኖናት ግብረ ሐዋርያት ናቸውን ወይስ አይደሉም? የሚሉት ጥያቄዎች እነዚህን ቀኖናት ብቻ ሳይሆን ወደፊት በምንመለከቻው ሌሎች ልዩ ልዩ ቀኖናትም ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው። ሁኖም ሲታመን እንደመጣም ከመጻሕፍተ ቀኖናት የመጀመሪያው ሐዋርያዊ ቀኖናዊ መጽሐፍ ከዕርገትና ርደተ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ሐዋርያት ለስብከት ከመበተናቸው አስቀድሞ በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው የሠሯቸውን ቀኖናት የያዘው ሥርዓተ ጽዮን መሆኑ ነው።

2.2. ሥርዐተ ጽዮን የተጻፈበት ቋንቋ፤

ከፍትሐ ነገሥት መቅድም ላይ ለመረዳት እንደሚቻለው ሥርዐተ ጽዮን ቀኖናተ ሐዋርያት ጥንት በግሪክ ቋንቋ (በጽርእ ቋንቋ) ነው የተጻፈው ምክንያቱም የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ አብነ አል አሳል በመቅድሙ እንደ ጻፈው መለካውያንና ንስጥሮሳውያን ይህን ሥርዓተ ጽዮን ከግሪክ ቋንቋ (ከልሳነ ጽርእ) ወደ ዐረብኛ (ዐረቢ) በመተርጎም ጽሑፍ ይህም በያዕቆብያውያን ሶርያውያን ዘንድም ይገኛል።

የእነዚህ ቀኖናት ቁጥሮች እንደ አብነ አል አሳል በመለካውያን ዘንድ 30 ቀኖናት ሲሆኑ [462] በንስጥሮሳውያንና ያዕቆብያውያን ዘንድ ግን በንት እንደሆኑ አላመለከተም በሌላም በኩል እነዚህ ቀኖናት – ሥርዐተ ጽዮን በግብጻውያን ዘንድ ስለመኖራቸው አልጠቀሰም ቢሆንም በዝምታ ማለፍ ግብጻውያን በመለካውያንና በንስጥሮሳውያንም ቢሆን የተመሰሰውን በዐረብኛ ሰነድ ተቀብለው ቢሆን ነው የሚል ግምት ይሰጣል።

2.3. የሥርዓተ ጽዮን የሌሎች ቋንቋዎች ትርጓሜዎች

462· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2 Bechmann: Corpus Iuris Abessinorum, Ius Connubii Berlin 1890. ገጽ XXXIII

ከላይ እንደ ተባለው ሥርዐተ ጽዮን 30 ወይም 27 ቀኖናተ ሐዋርያት በምሥራቅ ቋንቋዎች ሱርስጥ፣ ዐረብኛና ግእዝ ትርጉሞች ይገኛሉ።

(2.3.1. የሥርዐተ ጽዮን ሱርስጥ ትርጉም

የ30 ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም ምንአልባት በ5ኛው ምዕተ ዓመት ግን ከ6ኛው ምዕተ ዓመት በፊት የተደረገ ሁኖ ከሌሎች ትርጉሞች ቅድሚያ የሚኖረው ትርጉም ነው ምክንያቱም Cureton የተጠቀመበት የእነዚህ ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም የእጅ ጽሑፍ የ6ኛው ምዕተ ዓመት እንደሆነ ይገመታል [463] M.land ደግሞ ይህን የእጅ ጽሑፍ የ5ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ዘመን አድርጐ ይቆጥራል[464]። የሥርዐተ ጽዮን ሱርስጥ ትርጉም (30 ቀኖናት) በንስጥሮሳውያንና በያዕቆብያውያን – በሶርያውያን ዘንድ ተጠብቆ ይገኛል ።

1· በንስጥሮሳውያን ዘንድ በአገልግሎት ላይ የሚገኙ የ30 ቀኖናት – ሐዋርያውያት ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም Canones Apostolici ወይም ቀዳሚ ሲኖዶስ ዘሐዋርያት በሚል ርእስ በ1838 በAngelo Maio ከላቲን/ሮማይስጥ ትርጉም ጋር ታትሞ ተሰራጭቷል [465] በያዕቆብያውያን— ሶርያውያን ዘንድ የሚገኘው ይኸው ሰነድ ሱርስጥ ትርጉም በ1856 በP.DE Lagarde [466] በዚሁ ሰው ምላሽ የግሪክ ቋንቋ ሰነድ መጽሐፈ ትምህርት ዘአዱምስ በሚል ርእስ ታትሟል [467]። ሥርዓተ ጽዮን (30 ቀኖናት) ቀይተው The Teaching of Apostles በሚል ርእስ ከእንግሊዝኛ ትርጉም ጋር በw.curetou ታትሞ ይገኛል። [468] በመጨረሻ ሐዋርያት ወንጌልን ለመስበክ የተበተኑባቸውን ቦታዎች የሚዘረዝረው የቀኖናቱ የመጨረሻው ክፍል ከአንድ ከቆየ የእጅ ጽሑፍ በBachman ታትሟል[469]

463· Cureton, Aniennes Syriac Documents. London... 1864 ገጽ 149
464· M.Land, Anecdota Syriaca, 1862 ገጽ 65-66. 94
465. Gregorius Bar Hebraeus Nonocanon Ecclesiae Antiochenae (Syrorum) Latin Interprete Alyosio Assemano ገጽ 1—268 ሕትመት A. Maio Scriptorum...T.X. ገጽ 3—5 169—173።
466· P.De Lagarde, Reliquiae. Syriac ገጽ 32-34
467· P.De Lagarde, Reliquiae Graec ገጽ 89-95
468. ዝ. 463
469· MSS. 234 እና 235 Catalogue des Melchits Arabes de Paris ገጽ 58

2.3.2 የ30 ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም

ከላይ እንደተባለው እንደ ፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብን እልአሳል እነዚህ 30 ቀኖናት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት (መለካውያትና ንስጥሮሳውያት አብያተ ክርስቲያናት) በኩል ከግሪክ ቋንቋ (ልሳነ ጽርእ) ወደ ፀረብኛ — ዐረቢ ተተርጉመዋል ።

ሀ) የመለካውያን የቀኖናቱ ዐረብኛ ትርጉም በብዙ የእጅ ጽሑፎች ለምሳሌ Histoire de acts des Apôtres et indications des Canons et des Réglements Qu ils Ont Etablis. Le Tout extrait des Livres de clément[470] በሚል ርእስ በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ አንድ የእጅ ጽሑፍ

ለ· የያዕቆብያውያን 30 ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም በልዩ ልዩ የእጅ ጽሑፎች ለምሳሌ እሁንም Les Trente Canons des Saint Apôtres-[471] በሚል መለያ በፓሪስ የሚገኝ አንድ የእጅ ጽሑፍ ሊጠቀሱ ይችላሉ ።

ሐ) የእነዚህ ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም በግብጻውያን ዘንድም እንደሚገኝ የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብን እል እሳል ሲያሳይ በምንጩነት እንደተጠቀመባቸውም ያመለክታል ። በዚህም ጊዜ ሐዋርያት በሠራቸው ቀኖናት የመጀመሪያዎቹ እንደሆኑ ይጽፋል ። አንድ አንድ ጊዜ በግብጻውያን ዘንድ "ቲትላሳት" ተብለው ይጠራሉ[472]

መ· M.Vansleb በ1677 የእነዚህን ቀኖናት አርእስት በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኝ ዐረብኛ ትርጉም Trente et un canons des Apôtres fait au Cencal de Sion[473] በሚል ርእስ ወደ ፈረንሳይኛ ተርጉሚቸዋል ። እነዚህን አርእስተ ቀኖናት ቆይቶ Bickell በ1843 ስፋ ካለ ሐተታ ጋር እንደገና አሳተማቸው ።[474]

2·3·3 የሥርዓተ ጽዮን (የ30 ቀኖናት) ግእዝ ትርጉም

ከዐረብኛ ትርጉም ምን አልባት የተደረገው የእነዚህ ቀኖናት የግእዝ ትርጉም "ሥርዐተ ጽዮን" ቀኖናት ዘጽዮን" በሚል ርእስ

470. MSS 234 — 235 Catalogue des MSS. Melchits Arabes de Paris ገጽ 58
471. MSS. Jacobits Arabes de Paris 243 FOL 1—17 MSS. 252 ገጽ 1—10
472. Bibliotheque Nationale De paris MSS. 252 ስለ ዐረብኛ ቲትላሳት ወይም ስለ ግእዙ ተጥላሳት ሥርዐ አመጣጥ ከላይ ገጽ 150 ተመልከት ።
473. W. Vansleb: Histoire de Alexandrie Paris ገጽ 1677 ገጽ 239 341
474. J.W. Bickell Geschichte des Kirchenrechts...Giessen 1843 ገጽ 178—180

በ"ሲኖዶስ" ሲታወቅ "መጽሐፈ ዜናሆሙ ለሐዋርያት..." በሚል ቅርጽ ተይዟል ።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዝነኛው ቀኖናዊ መድበል "ሲኖዶስ" ይባላል ። የዚህ "የሲኖዶስ" የመጀመሪያው ክፍል ሐዋርያውያት ቀኖናትን[475] ማለት በተለያዩ ርእሶች ተቀርጸውና በአንጸራቸውም በተለያዩ አሐዞች ተመድበው የሚገኙ ቀኖናትን ይይዛል ።

ስለዚህ በ"ሲኖዶስ" የታቀፉት "ሐዋርያውያት ቀኖናት" የሚባሉት ቀኖናት ቁጥር (ብዛት) 8 መጻሕፍት ሲሆን ከነዚህ 8 መጻሕፍተ ቀኖናት አራቱ እብን እል እሳል ፍትሐ ነገሥትን ሲያዘጋጅ የተጠቀመባቸው ናቸው ። ስለዚህ ምክንያት የሚደረገው ምርምር ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባላቸው በእነዚህ ቀኖናት ብቻ ይወሰናል ። ምክንያቱም ስለ ሌሎቹ ቀኖናት መመርመሩ የጥናቱን ዓላማ ወሰን ስለሚያልፍ ነው ። እንደተነገረው ምንም እንኳን ሁሉም ቀኖናውያት "ሐዋርያውያት" ቢባሉም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መድበለ ቀኖናት "ሲኖዶስ" በተለያዩ ተጨማሪ እርእስት ተይዘዋል ። ስለዚህም አሁን በጥናት ላይ የሚገኙት ቀኖናት በሚከተሉት እርእስት መነሻነት ግን ሁል ጊዜ ርእስ — እርእስት "ሲኖዶስ[476]" በማድረግ ተመዝግበው ይገኛል ።

2.3.3 የሥርዓተ ጽዮን (የ30 ቀኖናት) ግእዝ ትርጉም

2· "ሲኖዶስ" ቀኖናት ዘቤተክርስቲያን[478]

3· "ሲኖዶስ" አብጠሊሳት ዘሐዋርያት[479]

475· "ሲኖዶስ" ከግሪክ ቃል ΣΥΝΟΔΟΣ በቀጥታ የተወሰደ ኀይለ ቃል ነው ልዩነቱ በግሪክ ቋንቋ "ሲ" ላይ ሲረገጥ/ሲነሳ ሲ'ኖዶስ Σύνοδος በግእዝ ግልባጩ ግን "ዶ" መሆኑ አለመነሳቱ ሲኖዶ'ስ ማለትም ተብሎ መነበቡ ነው ነገር ግን በግሪክ ቋንቋ "ዶ" ላይ የሚረገጥ ሲኖዶስ ሲኖዶ'ስ Συνοδός ግን ሌላ ትርጉምን ይዞ የሚገኝ ቃልም ነው ። ተዘታይ እስተናጋጅ ማለት ስለሆነ ከላይኛው ሲኖዶስ ጋር አይጋጭም ።
476· እዚህ ላይ "ሲኖዶስ" የሚለው ኀይለ ቃል ራሱን ሲኖዶሱን ይሁን መድበለ ቀኖናት እሙራት ቀኖናት በእቀነባበረው ሰው እንደተሰጠው ትርጉም ቀኖና ከሚለው ኀይለ ቃል ጋር ተመሳሳይ ሁኖ ይገኛል ።
477· MS. Borgio Etiopico ገጽ 48
478. MS. Borgio Etiopico ገጽ 49—61
479. MS Borgio Etiopico ገጽ 74—83

4. "ሲኖዶስ" ቀኖናት ዘጽዮን መጽሐፈ ዜናሆሙ ለሐዋርያት [480] ሌላው አንዱ ክፍል የኒቅያን 84 መበግተ ቀኖናትንና 20 ቀኖናትን ጨምሮ የታወቁ ሰባት የአካባቢዎች ንዑሳን ሲኖዶሳትና ሦስት ዐበይት ሲኖዶሳት ቀኖናት ተመዝግበው የሚገኙበት ክፍል ነው[481] ። የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ አብን አል አሳል የአካባቢዎቹ ንዑሳን ሲኖዶሳት ቀኖናትንና ከዐበይት ሲኖዶሳት ቀኖናት የመጀመሪያው የኒቅያ ሲኖዶስ የታወቁትን 20 ቀኖናትና እነዚያንም 84 መስግተ ቀኖናት መጠቀሙ ይታያል[482]

የሚቀጥለው ክፍል 13 ንዑሳን ክፍሎች ሲኖሩት ልዩ ልዩ የአብያተ ክርስቲያናትና የአብያተ ክርስቲያናት አባቶች (አፈወርቅ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ወዘተ·) ሥነ መለኮታዊ ፡ ሥነ ቅዳሴያዊና ሥነ ሥርዓት ይዘት ያላቸውን ቀኖናት ይይዛል[483] ።

ችግሩ ጥያቄው ሲኖዶስ ዛሬ በአለበት መልኩ ማለትም ከያዛቸው ቀኖናትና ሌሎች የአብያተ ክርስቲያናት ትእዛዛት የተቀነባበረ — የተቀረጸ ነው ወይስ ምን አልባት አስቀድሞ በዐረብኛ ወይም ከግብጽ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች በአንዱ ተዘጋጅቶ ተቀነባብሮ ከነበረ መሰል መድበለ ቀኖናት ተተርጉሞ — ተመልሶ ነው? የሚለው ነው ።

"ሲኖዶስ = በዐረብ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ወይም በግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት እንደተተረጐመ የሚገመት ንድፈ ሐሳብም ይገኛል[484] ። ነገ. ግን ይህ ንድፈ ሐሳብ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም ምክንያቱም በዐረብኛው ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት[485] ወይም በግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት[486]

480. Ms. Borgio. ctiopico ገጽ 84
481. Ms. Borgio Etiopico ገጽ 115
482. Ms. Borgio Etiopico ገጽ 123 144
483- ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፡ ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ፡ ገጽ 225–26 L.Stan L' èglise de. Ethiopie. Nouveau Patriarchat. Abba Selam T. II ገጽ 130 W. Riedel Die Kirchenrechtsquellen des Partiarchats Alexandrien.. . ገጽ 159። Pankhurst. Cultural History of Ethiopia London 1949 ገጽ "274 W. Pell. Canones Apostolorum 1871
484. I. Guidi, Die Äthiopische Synodos. ZDMG 1901 T. LV
485- ስለ ዐረብ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ከዚሁ ገጽ 207–209
486- ስለ ግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ከዚሁ ገጽ 209–216

ይህም ኪዳን ዘእግዚእነ (የጌታን ኪዳን) ሳይጨምር[487] በ8 ክፍሎች እንደሚከፈሉ ከተመለከቱት ቀኖናት የመጀመሪያወቱን ብቻ ይዞ እንደ መገኘቱ መጠን ከይዘቱ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ ተቀባይነት አያገኝም ። ሁኖም የሚቻለው ሙከራ ቢደረግም በግብጥ ቤተክርስቲያን ይፁ "ሲኖዶስ" ከዐረብ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ወይም ከግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት መምጣቱን (መመለሱን ውድቅ ለማድረግ ተመሳሳይ መድበለ ቀኖናት መገኘቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል።

ስለዚህ ሲኖዶስ በመሠረቱ አሁን በአለበት መልኩ በግእዝ ቋንቋ የተሰበሰበ መድበለ ቀኖናት ነው ።

እነዚህ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትርጉም ቀኖናት በአውሮፓም በሚገኙ ብዙ አብያተ መጻሕፍት በሚገኙ ልዩ ልዩ የእጅ ጽሑፎች ለምሳሌ Bibliotheque Nationale de Paris Decreta Alia Apostolorum per clementem Tradita au Nombre De 30[488] እና British Museum British Library [489] መገኘቱ ይታወቃል ። በሌላም በኩል Ludolphus የእነዚህን ቀኖናት አርእስት ወደ ላቲን ሮማይስጥ ቋንቋ ተርጉሟቸው ይገኛሉ[490]

2.3.4 የቀኖናቱ ቁጥር አሐዝ

በፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ አብን አል አሳል አነጋገር — አገላለጥ የነዚህ ቀኖናት ቁጥር አሐዝ 'በሱርስጥ ትርጉማቸው 27 ቀኖናት ሲሆን ወይም ማለት ከሱርስጥ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ በIbn al-Taib በተተረጐመበት መልኩ ማለት ነው ። ነገር ግን እንደ Abu-L Bar-kat የእነዚህ ቀኖናት ቁጥር 30 ነው ።[491] W. Vansleb ደግሞ አርእስቶችን ወደ ፈረንሳይኛ ቋንቋ የተረጐመበት የዐረብኛ ትርጉም ቁጥር — አሐዝ 31 ሲደርስ [492] በግእዝ ትርጉማቸው ግን ይህ ቁጥር 30 ነው [493]

487· ስለ ኪዳን ዘእግዚእ ከዚሁ ገጽ 240–246
488· [illegible] Ethiopien De Paris No. 121 FOL. 41—45 Catalogue ገጽ 141 Funk. Die Apostolischen Konstitutionen 1891 ገጽ 246 የግርጌ ማስታወሻ 5
489. Mss. Orient. 793 ገጽ 43 45
490. Ludolphus : Commentarius...T.I ገጽ 330
491. Riedel. die Kirchenrechtsquellen...ገጽ 279–341
492. W. Vansleb: Histoire de L'èglise... ገጽ 239 241 F. FUNK: Die Aoostolischen Kontitutionen ገጽ 246 የግርጌ ማስታወሻ 249
493 Ludolphus: Commentarius...320 I. Guidi: Gli Atti Apocrypha Copti Arabi E Etiopici: G.S.L.I.T. II ገጽ 2

2.3.5 የሥርዐተ ጽዮን—30 ቀኖናት ይዘት

“ቀኖናተ ሐዋርያት” ከተመለከተው ታሪካዊ መቅድም በስተቀር የሥነ ቀዳሴ ይዘትና ቤተ ክርስቲያናዊ ሥነ ሥርዐት ትዛዛትን ፤

1· የሥነ ቅዳሴ ይዘት ትእዛዝ

— ፊትን ወደ ምሥራቅ አዙሮ መጸለይ [494]
— በእሁድ ቀን የሚደረግ ጸሎት[495]
— ረቡዕ ቀን ስለሚደረግ ጸሎት[496]
— ዐርብ ቀን ስለሚደረግ ጸሎት[497]
— ስለ በዓለ ልደት[498]
— ስለ በዓለ ኤጲፋንያ (ጥምቀት)[499]
— ስለ ጾመ 40 ቅድመ ፋሲካ[500]
— ስለ በዓለ ዕርገት[501]
— ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ[502]
— ስለ ሰማዕታት መታሰቢያ[503]
— ስለ ዘወትር ጸሎት[504]
— ስለ ቅዱስ ቁርባን[505]

2· ስለ ክርስቲያን አገልግሎት ሥነ ሥርዐት ድንጋጌዎች

— የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ማዕርጋት
— ቀዳማዊ በኩረ ማኅበራት ሊቀ ጳጳሳት ፤ ኢጲስ ቆጶሳት ... [506]
— ዳግማዊ በኩረ ማኅበራት ቄስ ፡ ዲያቆን ... [507]

494· ቀኖና 1
495· ቀኖና 2
496· ቀኖና 3
497· ቀኖና 4
498· ቀኖና 8
499· ቀኖና 9·6
500· ቀኖና 10·7
501· ቀኖና 11·9
502· ቀኖና 12·8
503· ቀኖና 21·18
504· ቀኖና 22·19
505· ቀኖና 30·27
506· ቀኖና 5
507· ቀኖና 7·13·5

3· ስለ ቤተ ክርስቲያን አባል ካህንም ሆነ ምዕመን ሥነ ባሕርይ[508]

ስለ መሪዎች ቦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ[509]

በመጨረሻ ጸሐፊው ለአሕዛብ ወንጌልን ለመስበክ የክርስቶስ ሐዋርያትና አርድእት የተሠማሩባቸውን ቦታዎች ይቆጠራል /ይዘረዘራል ነገር ግን የአቡሊዲስ ስም ዝርዝር ከነዚህ ቦታዎች ስም ዝርዝር ይለያል [510]

የሱርስጥና የግእዝ ስንዱም የተገለበጠበት የዐረብኛ ትርጉም ቀኖናት ቁጥር አስጣጥ ልዩነት ሊታይ የሚችለው በሱርስጥ ትርጉሙ አንድ ቀኖና በዐረብኛ ትርጉሙ ወደ ሁለት ወይም ወደ ብዙ ቀኖናት በመባዛት ነው ለምሳሌ በሱርስጥ ትርጉሙ 9ኛው ቀኖና[511] ከእነዚህ ቀኖናት የተወሰኑትን ትእዛዛት — ድንጋጌዎች የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ እብነ አል አሳል ተጠቅሞባቸዋል ። ነገር ግን እነዚህ ቀኖናት በሚቀጥሉት የሐዋርያት ቀኖናት

508· ቀኖና 14·20 ፡ 23·26 ፡ 29
409. ቀኖና 27 — 28
510· አቡሊዲስ ስስ 12 ሐዋርያት P.G.T.X...ዐምድ 951—854 ስለ ሰብዓ አርድእት P.G.T.X. ዐምድ 454 — 958

511 የሱርስጥ ትርጉም ቀኖናት	የግእዝ እና የዐረብኛ ትርጉሞች ቀኖናት
1	1
2	2
3	3
4	4
5	5 — 7
6	8 — 9 ኛው ቀኖና ጥር 11 ቀን ስለሚከበረው በዓለ ጥምቀትና ታህሣሥ 29 ቀን ስለሚከበረው በዓለ ልደት ሲናገር በተቃራኒው ሱርስጡ ትርጉም 6ኛው ቀኖና እንደ ግሪክ አቆጣጠር ጥር 6 ቀን ስለሚከበረው ስለዚሁ በዓለ ልደት ይናገራል
7	10 — 11
8	12
9	11
10	—
11	13 14

— ረስጠአ[512]
— ረስጠአ[513]
— ረስጠጅ[514]
— መልእክተ ጴጥሮስ[515]
— ወዘተ ···

1. ለጢትና ማታ ስለታዘዘው ጸሎት የታዘዘው ድንጋጌ ረስጠአ ሆኖ ሲጠቀስ[516] ግን ይህ ድንጋጌ የተጠቀሱት 30 ቀኖናት—ሥርዐተ ጽዮን የ22ኛው ቀኖና ይዘት ነው[517] በእንጸሩ የግሪኩ ሰነድ 19ኛው ቀኖና ነው[518]

2· ስለ ቁርባን ሕብስት ዕለታዊ መሆን እንደአለበት የሚመለከተው ድንጋጌ ረስጠአ 30 ሆኖ ይጠቀሳል[519] ነገር ግን ይህ ድንጋጌ የንዐ

12	15
13	16
14	17
15	18
16	19
17	20
18	21
19	22
20	23 — ለውጥ አለበት
21	24
22	24 ልዩነት አለበት
23	25
24	26
25	27 28
26	29
27	30

512· ከዚሁ ገጽ 137 166,212 213
513· ከዚሁ ገጽ 167–169,211
514· ከዚሁ ገጽ 197–211
515· ከዚሁ ገጽ 247–251
516· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14 ቁ· 542 P. Tzadua. Fetha Nagast ገጽ 89
517· British Library Mss. Orient 793 .... ገጽ 43
518· P. DE Lagarde Reliquiae... Graec .... ገጽ 92
419· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13 ቁ· 508 P. Tzadua Fetha Nagast............ ገጽ 43

ቀኖናት— ሥርዓተ ጽዮን 30ኛው ቀኖና[520] እና በግሪኩ ሰነድ 27 ቀኖና[521] ሁኖ ይገኛል ።

3 ካህኑ ወይም ኤጲስ ቆጶሱ በምዕመናን ፊት ስለሚኖረው ሥነ ባሕርይ ያለው ድንጋጌ በረስጠብ ይጠቀሳል[522] ነገር ግን ይህ ድንጋጌ በ30 ቀኖናት ሥርዓተ ጽዮን 24ኛውን ቀኖና[523] እና በተቃረበው 21ኛውን የግሪኩ ሰነድ ቀኖና[524] ይዞ ይገኛል ።

4 በክርስቶስ ስም ስለተሰው ቅዱሳን መታሰቢያ ድንጋጌ ረስጠጅ 21 ቀኖና ሁኖ ሊጠቀስ[525] ነገር ግን ድንጋጌው የ30 ቀኖናት—ሥርዐተ ጽዮን 21ኛው ቀኖና[526] እና የግሪኩ ሰነድ ቀኖናት 18 ቀኖና[527] ሆኖ ይገኛል።

5 ስለ ሐሳዊ ቀሲስ (ካህን) የሚናገረው ትእዛዝ በመልዕክተ ጴጥሮስ ቀኖና ይጠቀሳል[528] ነገር ግን ይህ ደንጋጌ በሚመረመሩትም 30 ቀኖናት ሥርዐተ ጽዮን 13ኛውን ቀኖና[529] እና በግሪኩ ሰነድ 12ኛውን ቀኖና[530] ይዞ ይገኛል ።

6 ስለ ካህን ኮከብ ቆጠራ መከልከል ደንጋጌ በመልዕክተ ጴጥሮስ ቀኖና 10 ሲጠቀስ[531] ግን ይህ ድንጋጌ የእነዚህን 30 ቀኖናት— ሥርዐተ ጽዮን 15ኛውን ቀኖና[532] እና 12ኛውን የግሪኩን ቀኖና[533] ይዞ ይገኛል

ቢሆንምየተመለከቱትም ሆኑ ያልተመለከቱት ትእዛዛት በፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ ተጠቅሰው መመልከት ባይታይም ሥርዐተ ጽዮን (30 ቀኖናት) የፍትሐ ነገሥት ምንጭነትን መያዛቸው ርግጠኛ ነው ።

520· British Library Mss Orienit 793 .... ገጽ 43
521· P. DE Lagarde, Religuiac ... Graec .... ገጽ 92
522· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 53 P. Tzadua Fetha Nagast .... ገጽ 39
523· British Library MSS. Orient 793 .... ገጽ 43
524· P. DE Lagarde. Reliquiae ... Graec. .... ገጽ 92
525· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 20 P. Tzadu, Fetha Nagast .... ገጽ 120
526· B. L. Mss. Orient .... ገጽ 43
527· P. DE Lagarde, Reliquiae Graaec .... ገጽ 91
528· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 53 P.Tzadua. Fetha Nagast .... ገጽ 40
529· British Library Mss. Orient 793 .... ገጽ 43
530· P.De Lagarade Reliquiae Graec .... ገጽ 91
531· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13 P. Tzadua Fetha Nagast .... ገጽ 85
532· British Library Mss. Orient 793 .... ገጽ 43
533· P.De. Lagarde. Reliquiae Graec .... ገጽ 92

በመጨረሻ የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ አብን እል አሳል እነዚህ 30 ቀኖናት — ሥርዐተ ጽዮን በመለካውያን ዘንድ እንደተመለከተው[534] በግብጽ ቤተ ክርስቲያን በምን ርእስ ወይም ጽሑፍና ቁጥር እንደሚገኙ ምንም ዓይነት—ምልክት አልሰጠም—አላመለከተም ።

ይህ እንደአለ ሆኖ ምንም ቢሆን በፍትሐ ነገሥቱ ዝግጅት ወቅት ለአልታወቁ ምክንያቶች ተጠቀሙባቸውም አልተጠቀሙባቸው እንደተ ጠበቀ ሆኖ በራሱ በቤተ ክርስቲያን—ግብጥ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን እነዚህን ቀኖናት ከግምት ውስጥ አላስገባም—በአእምሮ ውስጥ አልነበ ሩም ለማለት ያስቸግራል ።

ሆኖም ግን ከእነዚህ ቀኖናት አንድም እንኳን ቀኖና በፍትሐ ነገሥት ተጠቅሶ አናገኝም ።

ስለዚህም ከእነዚህ 30 ቀኖናት የትኞቹ ቀኖናት የፍትሐ ነገሥቱ ምንጮች መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚቻል አልሆነም ።

534· ከዚሁ ገጽ 113–136

ገጽ

3. ረስጠአ— ቀለሚንጦስ ቀዳማዊ

በመጀመሪያ "ረስጠአ" በሁሉም ቀኖናውያን መድበላት/መድበላ ቀኖናት "ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት" ወይም "ቀኖናት ሐዋርያውያት " ሐዋርያውያት ቀኖናት" በሚል ርእስ የታወቁ በግሪክ ቋንቋ 85ና በላቲን ቋንቋ ትርጉማቸው 84[535] ቀኖናት ማለት መሆኑን በቅድሚያ መገንዘብ ይቻላል ።

የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ አብን እል አሳል የተመረኮዘባቸው እነዚህ ቀኖናት ሲሆኑ ምንጭነታቸው ራሳቸው ሐዋርያት ስለመሆናቸው ያለው ልምድ ቀደም ባሉት ዘመናት ለብዙ ጊዜ በምሥራቅ—በምዕራብም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍትና የቀኖናተ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ምርምርና ጥናት ርእስ ሆኖ ቆይቷል ።

ሁ በምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ባለው ልምድ መሠረት እነዚህ 85 ቀኖናት የሐዋርያት ትምህርትንና ሥርዐትን ይዘው ሆኖም በራሳቸው በሐዋርያት በቀጥታ ተጽፈው ሳይሆኑ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው ከዚያም ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን አስፍረው የተቀረጹ ዕውቅ ቀኖናት ናቸው ።

ስለዚሁ በ681 በትሩሎ የተሰበሰበው አምስተኛው—ስድስተኛው ዐቢይ ሲኖዶስ[536] በሁለተኛው ቀኖናው እነዚህን 85 ቀኖናት በሐዋርያት ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ግን በሐዋርያት ስም እየተነገሩ የመጡ እውቅ የአብያተ ክርስቲያናት ቀኖናት መሆናቸውን አረጋግጦ አጸደቀ ።

5ኛ – 6ኛው ዐቢይ ሲኖዶስ እነዚህን ቀኖናት ባጸደቀበት በዚሁ ሁለተኛው ቀኖናው በእነዚህ 85 ቀኖናት በ85ኛው ቀኖና የቅዱሳት መጻሕፍት ተከታይ ሁነው የሚገኙትን "ትእዛዘት ዘሐዋርያት" ወይም "ትእዛዛት ሐዋርያውያት" በመባል የሚታወቁትን ትእዛዛተ ቤተ ክርስቲያን የሐራጥቃዎች (ሐራጥቃ ኤረቲክስ ፡ መናፍቅ የሚለው ግሪክ ቃል /ትምህርት ተጨምሮባቸው በመገኘታቸው ውድቅ አደረጋቸው ጣላቸው ።

535· 49ኛው ቀኖና እና 50ኛው ቀኖና አንድ ቀኖና ሁነው ተጠርዘዋል ።

536· ይህን ሲኖዶስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አታውቀውም አትቀበለውም ፤ ምክንያቱም ከአንድ ባሕርይና ሁለት ባሕርይ እምነት ልዩነት በኋላ የተጠራ ሲኖዶስ በመሆኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አልተካፈለችበትምና ነው ።

ይህም ሁኔታ እንደ "ትእዛዛት ሐዋርያውያት" የ85 ቀኖናት ርኝጠኛነትን ከጥርጣሬ ላይ ጣለ ምክንያቱም ሁለቱም በሐዋርያት በሲኖዶስ ሥርዐት እንደተጻፉ ይቆጠሩ ነበርና ። ሆኖም ሲኖዶሱ ቤተክርስቲያንን እጅግ ያሳስብ ለነበረው ችግር ቀኖናቱን በማጽደቅና ትእዛዛቱን በመጣል መፍትሔ ሰጠ ።

ሉ በምዕራብ በሌላ በኩል አሁንም የእነዚህ ቀኖናት ከሐዋርያት መምጣታቸው ጉዳይ ለብዙ ዘመናት የተራራቀ አመለካከትን ይዞ ቆይቷል ።

በመጀመሪያ የሮማ ሊቀ ጳጳሳት ጌላሲዮስ ቀዳማዊ /492 — 496/ ቀኖናት ሐዋርያውያት በሐዋርያት ስም የተላለፉ እንጂ ከሐዋርያት ያልመጡ ወይም በሐዋርያት ያልተጻፉ Liber Qui Appeatur canonum apostolorum Apocrypha) የሐዋርያት ቀኖናት መሆናቸውን በአዋጅ "De Libris Non Reciendis) አመለከተ ።[537] በተቃራኒው የሊቀ ጳጳሳቱ አዋጅ ይዘት ማለትም የቀኖናቱን ሁኔታ የሚመለከተው ክፍል በርግጥ በዚሁ ሊቀ ጳጳሳት ስለ መታወጁ ያጠራጥራል ምክንያቱም ይህ ሁኔታ በቆዩ ብዙ የእጅ ጽሑፎች አይገኝምና ነው ።

በምዕራብ የመጀመሪያዎቹ 50 ቀኖናት ብቻ ነበሩ የሚታወቁት እነዚህም በ Codex Canonum Ecclesiasticorum Dionysii Exiguii /500/ ተመዝግበው (Qui Dicuntur Apostolorum) "በአምስተኛው ስድስተኛው ሲኖዶስ ቅዱሳንና ስቡሐን ሐዋርያት" ስም በሚል ርእስ ተለይተው የሚታወቁ ሲሆን [538] 35 ቀኖናት ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር አብረው የማይሄዱ ወይም የሚቃረኑ ሆነው በመገኘታቸው ተትተዋል ለምሳሌ ካህኑን በሽረትና ምዕመናኑን በውግዘት በመዛት የቅዳሜን ጾም የሚከለክለው 66ኛው ቀኖና[539] ምክንያቱም እንደሚታወ

537· De libris non reciendis በ ሊቀ ጳጳሳት ጌላሲዮስ በDecretum Gratiani P.L. T. LIX ዐምድ 178 Mansi T.8 ዐምድ 150 152 Preuschen. Analecta. Kurzere Texte zur Geschichte der älten kirche und des kanones. Freiburg. 1893 ገጽ 154 የግርጌ ማስታወሻ 36 Hefel. Concilen Geschichte...T.I. ገጽ 719። ፈረንሳይኛ ትርጉም Leclerq. Histoire des conciles 1869 T.I. ገጽ 644. F. Nau canons des apôtres paris E.D.T.T. II - 2 ገጽ 1606·
Bickell. Geschichte der kirchenrechts ገጽ 74

538· ቀኖና 2

539· አሁድ ቀንን ወይም ከአንድ ቀን በስተቀር ቅዳሜን ሲጾም የተገኘ ካህን ይሻር ፣ ምዕመን ከሆነ ይወገዝ ፣"

ቀው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቅደሜ ይጾማልና ።

ስለዚህ ይህ ቀናና እንደ Ingratus Romanis Auribus ሆኖ ይቆጠራል ።

ቆይቶ ሊቀ ጳጳሳት ኦርሚዳስ (Hormidas) /514 — 523/ የጌላሲዮስን አዋጅ (De libris non reciendis) እንደገና በአወጀበት ጊዜ ማለትም ቆይቶ ተጨማሪ ምንዓልባት 35 ቀኖናት ተሰርዘዋል ።[541]

ስለዚህ የሐዋርያት ቀኖናት ሐዋርያዊ ምንጭነት ትውፊት ከላይ እንደተመለከተው (Centuriatores (ዘ) magdburg[542] በተባሉና በTurrianuና ተከታዮችም መካከል ወደ ከፍተኛ ኑፋቄ ደርሶ ግጭት እስከተከተለበት 15 — 16ኛው ምዕት ዓመት ድረስ የክርክር ርእስን ይዞ ቆይቶ ነበር ። ማለትም ይህን ትውፊት የፊተኞቹ በመጠራጠር የኋለኞቹ በመደገፍ ሲሆን በመጨረሻ ግን የኋለኞቹ ትምህርት ሊጸና ችሏል ።

ስለዚህ ዛሬ በምሥራቅም ሆነ በምዕራብ በተለየ ከካቶሊክ (ቤተ ክርስቲያን) ቀኖናዊ ሕግ የማይለይ ክፍልን የያዙትን 50 ቀኖናት አስመልክቶ እነዚህ ቀኖናት በጽሑፍ በሐዋርያት እንዳልተቀረጹ ነገር ግን ከሐዋርያት ልምድ በአጠቃላይ ከጥንት ቤተ ክረስቲያን ትምህርት ልምድ እንደመጡ ያለወን ንድፈ ሐሳብ ተቀባይነትን አግኝቷል ።

፫·1 ሐዋርያውያት ቀኖናት የተጻፉበት ዘመንና ቦታ

በመጀመሪያ እነዚህ ቀኖናት በራሳቸው በሐዋርያት ተጻፉ ማለት የተጻፉበት ዘመንም 1ኛው ምዕተ ዓመት /ዘመነ ሐዋርያተ ማለት ይሆናል ግን ይህ አስተሳሰብ በታሪክም ሆነ በተግበር ድጋፍ አይኖረውም ።

የቀኖናት ሐዋርያውያት ዘመነ ሥርጭት በሁለት መልኮች ሊመረምር ይችላል ።

540· Pet.us de marca ᎤᏟ concordia et imperii paris 1704 Bibl. III. cAp. 2. የግርጌ ማስታወሻ 3። Funk, Die Apostolischen konstitutionen ገጽ 74·

541. F.Nau. canons des apötres D.C.T.I.II አምድ 1606። Moiteuil. Histoire de droit Byzantin. Paris 1848 T.I ገጽ 193 Bickell, Geschichte uer ...irchenrechts ገጽ 75 Pitra juris ecclesiastici graecoromani ... T. ገጽ XLI.

542. ዕልቅና – መሪነት ለዘመናተ የተከፈለችውን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከ16ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የሚጽፉ ጸሐፊት "Centuriatores" ተብለው ይጠራሉ ። P. Polmann Felecius illyricus, histoire de L' église. R.H.E.T. 37 ገጽ 27 – ..
G.G cross. The oxford. Dictionary. Of the christian church. London 1961 ገጽ 73

1/ Terminus a quo
2/ Terminus ad quem
Terminus a quo

የቀኖናት ሐዋርያውያት ሥርጭት ማለትም በተቃረበ መልክ ብቻ ይሆናል እነዚህ ቀኖናት የተጻፉበትን ዘመን ለማየት የሚሞከረው ምክንያት ስለዚህ ሁኔታ የታሪክ ጸሐፍትና መምህራን ሕጋውያን ቀኖናት አስተሳሰብ ንድፈ ሐሳቦች በጣም ተራርቀው ስለሚገኙ ነውና ። የእነዚህ ቀኖናት ችግሮች ጸሐፊዎች ወይም ተመራማሪዎች ሁሉም እነዚህ ቀኖናት ሐዋርያውያት የሐዋርያት አለመሆናቸውን ቢስማሙም ነገር ግን መቼ እንደተጻፈ አይስሙም ምክንያቱም እነዚህ ቀኖናት የተጻፈበት ዘመን ከ1ኛው ምዕተ ዓመትና ከሁለተኛውም ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ እስከ 5ኛው ምዕተ ዓመት 4ኛው ዐቢይ ሲኖዶስ ይደርሳልና[543]

በራስ አስተሳሰብ ላይ የተመረኮዘ/የተያያዘ ንድፈ ሀሳብ የሐዋርያት ቀኖናት የተጻፉበት ዘመን/ወይም እንደምንመለከተው ሰነዳዊነት/ሁለተኛው ምዕተ ዓመት መሆን ይኖርበታል ምክንያቱም በስም እንኳን ሳይሆን የነዚህ ቀኖናት ሐዋርያውያት ብዙዎች ድንጋጌዎች ይዘት በ3ኛው ምዕተ ዓመት ሥራ ጽሑፍ ዲድስቅልያ ዘሐዋርያት ውስጥ ይገኛል[544] 2ኛም· ቀኖናት ሐዋርያውያት የተጻፉበት ዘመን 3ኛው ምዕተ ዓመት እንደሆነ ሊቆጠር ይችላል ምክንያቱም በተለየ በ3ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በቀጥታ በሐዋርያት ስም ቀኖናትን ወይም በኢ ቀጥታ የቤተክርስቲያን ቀኖናት ፣ ቀኖናተ ቤተ ክርስቲያንን ወዘተ· መጥቀስ ወይም ማንሳት ዘወትር አጋጣሚ ነበር ለምሳሌ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አለክሳንድሮስ (325) ቀኖና ሐዋርያትን (12 ፣ 13 ፣ 14፣) ጠቅሷል—ተጠቅሟል[545] ትልቁ አትናቴዎስ ቀኖናተ ሐዋርያትን (29·30) ጠቅሷል[546] አውሳብዮስም ቀኖናተ ሐዋርያትን (13)

543. Beveregius: Synodicon sive pandectae canonum 55. Apostolorum et Conciliorum ab Ecclesia Graeca Receepotorum Oxford 1672. Achelis. Apostolischen Kirchenordnung. R.E.T T. ገጽ 739 Hefel - Leclerq, Histoire T. I ገጽ 613—615።

544 ከዚሁ ገጽ 218–308

545· Θεοδωρήτους Εκκλησιαστική Ιστορία A: ሕትመት PARMEITER P.G.T·25 ዐምድ 284

546· Επιστολή Εγκύκλιος P.G.T. 25 ዐምድ 25:
Απολογητικός κατ΄Αρεσνών P.G.T. 25 ዐምድ 284

አመልክቷል[547] ትልቁ ባስልዮስ ቀኖናት ሐዋርያውያትን (17፣ 25) ተጠቅሟል ።[548] በዚሁ መልክም በዚህ ጊዜ ክልል ውስጥ እነዚህ ቀኖናት በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ዐበይትና ንዑሳን ሲኖዶሳት ተጠቅሰዋል ለምሳሌ ከኒቅያ ሲኖዶስ (325) ቀኖናት 14 ፣ 15 ፣[549]

ነገር ግን በተቃራኒው ይህ ዘመን እነዚህ ቀኖናት ሐዋርያውያት በብዛት ከላይ በተጠቀሱት ሲኖዶሳት እና ቀኖናት ላይ ተመሥርተው የተቀረጹ መሆናቸውን በመደገፍ የተቀረጹበት ዘመን በ5ኛው ወይም በ6ኛው ምዕተ ዓመት መሆኑ ይደገፋል ።

በ2ኛው ምዕተ ዓመተ መጨረሻና በ3ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜያት ተጽፈው በመጨረሻ በአንድ አቀነባባሪ ሰው ተሰባስበው በአንድ ሰነድነት ሊዋሐዱና አንድ ወጥ ሰነድ ሲሆኑ የመጀመሪያውን ክፍል ቀኖናት ሐዋርያውያት ይይዛሉ ። ስለዚህ የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ሲኖዶሳት ፣ የቤተክርስቲያን አባቶች ፣ ጸሐፍት ሐዋርያውያት ቀኖናትን ወይም "ጥንታውያት ቀኖናትን ወይም ቤተክርስቲያናዊ ሥርዐትን በሚጠቀሱበት ጊዜ በአንድ በኩል እነዚህን ዛሬ የሚታወቁትን ሐዋርያውያት ቀኖናትን በሌላ በኩል በቅዱሳት መጽሐፍት የታቀፉትን ትእዛዛት ማለታቸው ነበር በሌላ አነጋገር በቤተክርስቲያን ተግባራዊ ሕይወት የተገኙትንና በቃል ሲያያዝ የተላለፉትን ቀኖናት የላይኞቸቹ ቀኖናትና ጸሐፍት ጥቅሶች የተመለከቷቸው የአባቶች ሥራዎችን ጨምረው ነበር የሚጠቅሱት ።

በተቃራኒው Sebastien Drey የሌላው ትምህርት ቤት አስተሳሰብ ተወካይ ስለ ጥንቱ Codex Ecclesiae Primitivae) የነበረውን ንድፈ ሐሳብ በመጠራጠር ቀኖናት ሐዋርያውያት በሁለት ሂደቶች እንደተቀረጹ አመለከተ[550]

1· ዲዮናስዮስ ንዑስ በ500 የተረጐማቸው 50 ቀኖናት በ5ኛው ምዕተ ዓመት የተቀረጹ ሲሆኑ የቀሩት ሌሎች 35 ቀኖናት ቆይተው በ6ኛው ምዕተ ዓመት ተቀርጸው ሁለቱም በአንድ ታቅፈው አሁን

547· De vitae constantni ገጽ 61—62 ሕትመት Hickel, Geschichte der kirchenrec· ገጽ 109 P.G.T 20 ዐምድ 1135—1137

548· Επιστολή πρός Αμφιλόχιον καί 3.12 (Αρχαίος Κανών υπηρεσίας) P.G.T. 32 ዐምድ 672 - 681

549· ቀኖና 15 = ሐዋርያውያት ቀኖናት 21፣ 22፣ 23፣ 24 ቀኖና 2 = ሐዋርያውያት ቀኖናት 80 ቀኖና 5 = ሐዋርያውያ ቀኖናት 12 ፣ 13 ፣ 32 ፣ ቀኖና 6 = ቀኖናሐዋርያውያት ቀኖና 34 ።

550· S. Drey, Neue Untersuchungen "Über Die-Konstitutionen Und Kanonen Der Apostel. Tübingen 1832 ገጽ 403

ያላቸውን ትርጽ ይዘዋል ይላል ፡፡

S. DREY የጥንት ቤተ ክርስቲያን "Codex Canonum primitivae" የሚባለውን ሰነድ እንደማታውቅና ለዚህም እንደ አልተጠቀመችበት ቀኖናት ሐዋርያውያት የሚለው ጥቅስም በምንም ዓይነት ሁኔታ አንድ ዓይነት መድበለ ቀኖናት ሐዋርያውያት ማለት እንደአልነበረ ነገር ግን በትዱሳት መጻሕፍት ከሚገኙ ትእዛዛት ሐዋርያውያት ወይም ከጥንት ቤተ ክርስቲያናዊ ልምድ (ዘመነ ሐዋርያት ልምድ) ጋር ግንኙነት እንደነበረው ይደገፋል ፡፡[551]

ከዚህም የተነሳ የነዚህ ቀኖናት ሐዋርያውያት አብዛኞቹ ከፍሎች ከሚከተሉት ቀኖናት ተወስደዋል ፡፡

ከዲድስቅልያ ዘሐዋርያት (3ኛው ምዕተ ዓመት)[552]

ከኒዎቂሳርያ (አዲሷ ቂሳርያ/315)[553]

ከኒቅያ /325/[554]

ከአንጾኪያ /341/ [555]

ከላኦዶቅያ /372/ [556]

ከቁስጥንጥንያ /381/[557]

ከቁስጥንጥንያ /394/[558]

ከኬልቄዶን /451/[559]

ከመስሎ ኢግናጢዮስ ወደ ፊሊጵስዩስ መልእክት 5ኛ ምዕተ ዓመት)[560]

ከትእዛዛት ሐዋርያውያት (5ኛው ምዕተ ዓመት) [561]

ከታላቁ ባስልዮስ ቀኖናት[562]

551- H. Leclerq: Cannons Apostoliques D.A.C.L.T. 112 1917 ዐምድ

552- ቀኖና 41 42

553- ቀኖና 19

554- ቀኖና 20 23 ፡ 79

555- ቀኖና 7 15 ፡ 27 ፡ 32 ፡ 40 ፡ 75

556- ቀኖና 44 ፡ 70 71

557- ቀኖና 74

558- ቀኖና 28

559- ቀኖና 26 ፡ 66 ፡ 72 ፡ 80 ፡ 82

560- ቀኖና 69-70

561- ቀኖና 1-2-6-7-19-25-32-46-48-50-52-59-63-65-78

562- ቀኖና 24-

እነዚህ ቀኖናት በ5ኛው ወይም በ6ኛው ምዕተ ዓመት እንደተጻፉ የሚደግፈውን የDrey ንድፈሐሳብ ለምሳሌ F.funk እና J.W.Bickell ከአንድ አንድ መሻሻያዎች ጋር ተቀበሉት ፡፡ F.Funk. የጥንት ቤተ ክርስቲያን ትጠቀምባቸው የነበሩ በተለየ ቀኖናት ሐዋርያውያትን ጨምሮ የያዘ Codex Canonum Ecclesiae Primitivae የሚባል ሰነድ እንደነበረ የሚያስተምረውን የBeveregiusንደፈ ሐሳብ ድጋፍ እንደ ሌላው አድርጎ በመቁጠር ማለው እንደዚሁም ከ4ኛው ምዕተ ዓመት በፊት እነዚህ ቀኖናት ነበሩ የሚለውንም አስተባሰብ ነቀፈ[563] P.J.W. Bickell አመለካከትም ተመሳሳይ ነበር ፡፡

Bickell እነዚህ ቀኖናት ሐዋርያውያት በሁለት ሂደቶች እንደተፈጠሩ አድርጎ የሚቀበለውን ትምህርትን ውድቅ አደረገ[564] ስለዚህም እነዚህ ቀኖናት ሁለት የተለያዩ ሥራዎች ሳይሆኑ አንድወጥ ሥራዎ ብቻ መሆናቸውን ደገፈ ፤ ስለዚህም 50 ቀኖናት የአንድ ጸሐፊ እና 35 የሌላ ጸሐፊ ሳይሆኑ 85 ቀኖናት ባአንድነት

የአንድ ጸሐፊ ዝግጅቶች መሆናቸውን ደገፈ[565] ይህንም F.funk የደገፈው አመለካከት ነው ፡፡ [566]

ሆኖም የBeveregius ግንዛቤ አነሰም በዛ ወደ እውነተኛው የእነዚህ ቀኖናት ታሪካዊ ቁም ነገር የተቃረበ ይመስላል ፤ ምክንያቱም በመጀመሪያው እነዚህ በምርምር ላይ የሚገኙ ቀኖናት የሐዋርያት ሥራዎች መሆን አይችሉም ከዚህም በመነሳት የዘመነ ሐዋርያት ሥራዎች መሆን አይችሉም ፡፡ ናቸው የሚያሰኘው በሐዋርያት ስም መጠራታቸው ብቻ ነው ምክንያቱም "ሐዋርያ" "ሐዋርያት" የሚለው ቃል ወይም "ሐዋርያዊ" "ሐዋርያውያን" የሚለው ትጽል በጥንት ቤተ ክርስቲያን ለሐዋርያ ወይም ለሐዋርያት ብቻ የሚሰጥ አልነበረም ነገር ግን ለቤተ ክርስቲየን አባቶች ማለትም በ13ኛው መጨረሻና በ14ኛው መጀመሪያ ምዕተ ዓመት የነበረ ንስጥርሳዊ ሶርያዊ ሱርሰጣዊ ጸሐፊ በጥንት ቤተክርስቲያን ኤጲስ ቆጶሳት "ሐዋርያት" ተብለው ይጠሩ እንደነበር እንደ አመለከተው ለኤጲስ ቆጶሳት ይሰጥ ነበር[567]

563- F.Funk: Die Apostolischen koostitutionen ገጽ 180

564- J.W Bickell Geschichte Der Kirchenrechts ገጽ 75

565- J.W. Bickell Geschichte der Kirchenrechts. ገጽ 82

566. Funk. Apostolischen koostitutionen ገጽ 108

567- A. Maio, Scriptorum ገጽ 6-8

ነገር ግን ዘቀኖናት ቤተ ክርስቲያን Codex Caponum Ecclesiae Primitivae ማለትም ቀኖናት ሐዋርያውያት አንድ ክፍልን እንደያዙ የሚቆጠረው ሰነድ እውነት እንደአለው የሚደግፍ ሆኖ አልተገኘም ምክንያቱም እስከምናውቀው ድረስ በአንድ በኩል ይህን የመሰለ በቤተ ክርስቲያን ሕግ ምንጮች አልተጠቀሱም በሌላም በኩል በራሳቸው ቀኖናት ሐዋርያውያት እንደእነዚህ ሁነው ሊረዱ የማይችሉ ሁነው አልቻሉም ።

ቀኖናቱ ስለተጻፉበት ዘመን ከአሉት ንድፈ ሐሳባውያን ሁኔታዎች አልፎ ራሳቸው የቀኖናቱ አንድ አንድ ድንጋጌዎች ቀኖናቱ የተጻፉበት ዘመን አለመሆኑን ያሳያሉ ምክንያቱም ቀኖናቱ በዘመነ ሐዋርያት ከነበረው የቤተ ክርስቲያን ልምድ ጋር የማይሄዱና ያልታወቁ ድንጋጌዎችን ይዘዋል ለምሳሌ በሉ ሦስቱ አሠረ ክህነት (ኤጲስ ቆጶስና ቅስናና ዲቁና) ትእዛዛት[568] ስለ ንዑሳን መዕርጋተ ክህነት ንፍቀ ዲቁና አናጉኒስጢስነትና መዘምርነት[569] ።

ስለ አርብዐ ጾም[570] ፋሲካን ከአይሁድ ፋሲካ ጋር አብሮ ስለ አለማክበር [571] ስለ ዐርብና ረቡዕ ጾም[572] ስለ አውራጃዎች ሲኖዶሳት ጥሪ[573] ስለ መናፍቃን --ሐራጥቃዎች) ጥምቀት [574]

568· ቀኖና 7·25·44·45·51·53·61·68·69·70

569· ቀኖና 43·69 የአናጉንስጢስ ሲመተ ማዕርግ በሁለተኛ ምዕተ ዓመት መጨረሻ ተገልጧል ።
ጠርጥልያኖስ Praescript cap 41 ፡ አውሳብዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 4·3 የንፍቀ ዲያቆን ሲመተ ማዕርግ የተከሰተው በ3ኛው ምዕተ ዓመት ነው አውሳብዮስ ቤተክርስቲያን ታሪክ 4·3 የመዘምር ማዕርግን በሚመለከት ትእዛዛተ ሐዋርያት 3 ።

570· ቀኖና 69 በ2ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ የነበረው የፑግዱኖስ ኤጲስ ቆጶስ ኢሬኔዎስ የፋሲካ ጾምን ጊዜ የሚወስን ቀኖናዊ ትእዛዝ እንደነበረ ያውቅ እንደአልነበረና ስለዚህም ልዩነት እንደነበረ ያመለክታል ። የኢሬኔዎስ መልዕክት ለሮሜ ኤጲስ ቆጶስ ቢክቶር አውሳብዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 5·24 በ3ኛው ምዕተ ዓመት የነበረ ዲዮናስዮስ (ዲዮኒስዮስ) የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት/ፓትርያርክ የፋሲካ ጾም ጊዜ ከ6 ቀን አይበልጥ እንደነበረ ይነጋራል ። የሚዮናስዮስ መልዕክት ለፔንጻፖሊስ ኤጲስ ቆጶስ ባሲሊዲስ አውሳብዮስ የቤተክርስቲያን ታሪክ 7—26

571· ቀኖና 7·70 ምክንያቱም የትንሽ እስያ አብያተ ክርስቲያናት በ2ኛው ምዕተ ዓመት የፋሲካን በዓል በኒሳን ወር (ሚያዝያ) 1 ቀን ከአይሁድ ጋር ያከብሩ ነበር ። የኢሬኒዎስ መልዕክት ለሮሜ ኤጲስ ቆጶስ ቢክቶር አውሳብዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 5·24

572· ቀኖና 69

573· ቀኖና 37

574· ቀኖና 46

ነገር ግንም ከ3ኛው ምዕተ ዓመት በኋላም ሥራ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም በተደጋገሚ እንደተወሳው በሲኖዶሳትም ሆነ በቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሱት ሐዋርያውያት ቀኖናት ጥቅስ ሌላ ሊሆን አይችልም ከሐዋርያውያት ቀኖናት በስተቀር ።

ስለዚህ ሐዋርያውያት ቀኖናት የተጻፉበት ዘመን በአንድ በኩል በ2ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው ክፍለ ዘመን መካከል እንደሆነ በሌላም በኩል ወደፊት እንደሚታየው በ400 ዓመት አካባቢ እንደሆኖ ይደገፋል ። ምክንያቱም በመጨረሻ እነዚህ ቀኖናት "ትእዛዛት" ሐዋርያውያት" የሚባሉት ትእዛዛተ ሐዋርያት የ47ኛው ምዕራፍ ብቻ አባሪ ሁነው ይገኛሉ። የህን የመጨረሻውን ምዕራፍ ብቻ አይደለም ይዘው የሚገኙት ነገር ግን በቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር መዝገብ እነዚህን ትእዛዛት ይዘው ይገኛሉ[575] ይህም ማለት ከቀኖናት ሐዋርያውያት የጽሕፈት ዘመን ጋር የተያያዘ ነው ። ይህም ጊዜ በ400 ዓመት አካባቢ ሲሆን ሲታሰብም ምንም ቢሆን ከዚያም በኋላ ነው ሊሆን የሚችለው ። "ሐዋርያውያት ትእዛዛት" Constituiōnes Apostolicae ወይም ትእዛዛት ሐዋርያውያት Constitutiones Apostolorum የቤተ ክርስቲያን ሕይወት በሚደነግጓቸው የአብያተ ክርስቲያናት (በሲኖዶሳትና አባቶች) ቀኖናት መካከል አለመያዛቸው ወይም አለመመደባቸው ቢኖርም ለቤተ ክርስቲያን ሕግጋት ምንጮች ከፍተኛ ግምት ያለውን ክፍል ይዘው ይገኛሉ ።

በታሪክ ሐዋርያውያት ቀኖናት ዛሬ በሚገኙበት መልካቸው አንድ ወጥ ሰነድን አልያዙም ነበር ምክንያቱም እነዚህ ቀኖናት ምን አልባት በጥንት ጊዜ ሦስት የተለያዩ መድበላተ ቀኖናት ሁነው ግን የተጠሰነ ስምን ሳይዙ ይገኙ ነበር ።

ሆኖም ያሰባሰባቸው ማን እንደሆነ ባይታወቅም በአንድበኩል አፖሊናርዮስ Apolinarius እንደነበር ወይም አርዮሳዊው ሰውር ኢግናጢዮስ አሰባሰቦ የአሁኑን ቅርጽ ለማስያዝ በአንድ ሰነድ አቀናጅቷቸዋል ይባላል ።

1· ከእነዚህ መድበላተ ቀኖናት የመጀመሪያው መድበለ ቀኖናት

575· ቀኖና 85 "ወእሉ ቀሌሚንጦስ ለእናንተ ኤጲስ ቆጶሳት በ8 መጻሕፍት የተቀናጁ ትእዛዛት"
Καί αι διαταγαί υμίν τοίς επισκόποις δι΄εμού κλημέντος εν οκτώ βιβλίοις προσεφωνημέναι

ትምህርተ ሐዋርያት/ዲድስቅልያ ዘሐዋርያውያት[576] የተባለውን ቀኖና ዊ ሰነድ ምንጭ አድርገው የተዘጋጀት የመጀመሪያዎቹ ስድስት መጻሕፍ ትን ይይዛል ። ልዩ ልዩ ቅንጅቶችና ቅንብሮች ተደርገውባቸው እያንዳ ንዱ መጽሐፍ በምዕራፎች እንዲከፈል ተደርጓል ።

ስለዚህ 1/ የመጀመሪያው መጽሐፍ 10 ምዕራፎችን ሁለተኛው 63፣ ሦስተኛው 20 አራተኛው 14 ፣ አምስተኛው 20 እና ስድስተኛው 30 ምዕራፎችን ይዘው ይገኛሉ ።

2/ ሁለተኛው መድበለ ቀኖናት 49 ምዕራፎች ያለውን ሰባተኛውን መጽሐፍ ሲይዝ ከእነዚህ 49 ምዕራፎች 32/1·32/ ምዕራፎች ምን አልባት በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ ላይ በሶርያ ወይም በእስክንድርያ ከተጻፈ "ትምህርተ 12 ሐዋርያት ለአሕዛብ" ዲድስቅልያ ዘ ፲ ወ ፪ ሐዋርያት" ላይ እንደተመሠረቱ ይደገፋል[577]

3) ሦስተኛው መድበለ ቀኖናት 46 ምዕራፎችን ይዞ የሚገኘውን ስምንተኛውን መጽሐፍ ይዞ ሲገኝ ከዚህ ጋር 47ኛውን ምዕራፍ ይዘው 85 ሐዋርያት ቀኖናት አባሪዎች ሁነው ይገኛሉ ።

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች (1·2) አንድ ጊዜ "ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ" ሌላ ጊዜ "ግብጻዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ"[578] በሚል ርእስ የሚታወቀውን ስለ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን የአቡሊዲስ ሥራ ምንጭ ያደርጋሉ ።

የሚከተሉት 25/3·37/ ምዕራፎች ቅዳሴ ቀለሚንጦስ የምትባል አንጾኪያዊ ቅዳሴን ፣ ጸሎትን ዘወትር ወይም የቀላሚንጦስ ትእዛዝ?[579] የመጨረሻዎቹ 19 ምዕራፎች /28·46/ ልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲየናውያን ቀኖናትን እና እንደ ተቀጽላ ሆኖ የሚቆጠረው 47ኛ ምዕራፍ 8! ሐዋርያውያት ቀኖናተን ይይዛሉ ።

ከዚህ ላይ ሐዋርያውያት ትእዛዛት የሐዋርያት ሥራዎች እንደ አይደሉና ስለዚህም የዘመነ ሐዋርያት ሥራዎች እንደአልሆኑ ሁሉ ስለ ሐዋርያውያት ቀኖናት የተሰነዘረው አመለካከት ከዚህም ላይ ይሰራል ።

576· ከዚሁ ገጽ 219–23ሃ

577· ከዚሁ ገጽ 213–214,139

578· ከዚሁ ገጽ 219–239,181–192

579· J.T.S. 1915. ገጽ 323

ቢሆንም ቅሉ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ጥንታውያን የቤተ ክረስቲያን ሥራዎች ቢሆኑም በወስጣቸው ከተያዙት ምሥጢራት የተነሳ ለሁሉም እንዳይደርሱ ስለ ተደረጉ በስፋት ሊታወቁ አልቻሉም ነበረ ...[580]

ስለዚህ የሐዋርያውያት ትእዛዛት ዘመነ ጽሕፈት (500) እስከ አሁን በተደረጉ ምርምሮች መሠረት በታሪክ ጸሐፍትና ቀኖናተ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተለያየ ጊዜ ሆኖ ተገኝቷል ። "ትእዛዛት ሐዋርያውያት 47ኛውንም ምዕራፍ በያዙት 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት መዝገብ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ከተመዘገቡት መጻሕፍት ጋር ተመዝገበው ይገኛሉ። ነገር ግን 5ኛው—6ኛው ዐቢይ ሲኖዶስ በሁለተኛው የማጽደቂ ያ ቀኖና በውስጣቸው ስሕተትና ባዕድ ትምህርት አለባቸው በማለት እነዚህን "ትእዛዛተ ሐዋርያውያት" አላጸደቀም ምክንያቱም ቀኖናቱ 581

580· ".... ἅς οὐ χρή δημο- σιεύειν ἐπί πάντων διά τά ἐν αὐταῖς μυστικά" (
ሐዋርያውያት ቀኖናት 85 ። እነዚሁ ትእዛዛት Apocrypha Arabica Kitaabal Mägli ወይም The Book of the Rolles' One of the Books of Clement ከምሥጢርነት የተነሳ ለምዕመናን እንዲደበቁ ከታዘዙበት ከቀለሚንጦስ መጻሕፍት አንዱ ጋር ይመሳሰላሉ
P.O.T. 10 ገጽ 1 — 58
A. Harnack, die lehr der zwölf Apostel ገጽ 241·
F Funk, Die Apostolischen konstitutionen ገጽ 70 — 96 116—118 161 — 64 311 — 314

581· ἐπειδή δ'ἐν τούτοις κανόσιν ἐκτέλεται δέχεσθαι ἡμᾶς τάς τῶν αὐτῶν ἁγίων ἀποστόλων διά Κλήμεντος διατάξεις, αἷς τισι πάλαι ὑπό τῶν ἑτεροδόξων ἐπιλύμα τῆς Ἐκκλησίας νόθα τινά καί ξένα τῆς εὐσεβείας παρενετέθησαν, τό εὐπρεπές κάλλος τῶν θείων δογμάτων ἡμῖν ἀμαυρώσαντα, τήν τῶν τοιούτων διατάξεων προσφόρως ἀποβολήν πεποιήμεθα πρός τήν χριστιανικωτάτου ποιμνίου οἰκοδομήν καί ἀσφάλειαν, οὐδαμῶς ἐγκαίνοντες τάς αἱρετικάς ψευδολογίας νοήματα, καί τῇ γνησίᾳ τῶν ἀποστόλων καί ὁλοκλήρῳ διδαχῇ ...συνείροντες
A. Αλιβιζάτου: Οἱ Ιεροί Κανόνες ገጽ 75 ገጽ
Επιφανίου κατ'αιρέσεων P.G.T. 41 ዐም 836

ለምሳሌ በእነዚህ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ገብተው ስለተገኙት ባዕድ/ስሕተት ትምህርቶች ንዑስ ክርስቲያን ከመጠቀሙ በፊት መመስከር ያለበት በሰባተኛው መጽሐፍ 41ኛ ቀኖና የሰፈረው ጸሎተ ሃይማኖት ተመልክቷል። [582] ቢሆንም በዚህ የመጀመሪያው የኒቅያ ዐቢይ ሲኖዶስ በጉባኤ በሲኖዶሱ ላይ በተገኙ አባቶች በጸደቀ ጸሎተ ሃይማኖት "ዘዕሩይ ምሳለ" የሚለው ኃይለ ቃል አይገኝም[583] በተቃራኒው "እስመ አልቦ ማሕለቅት ለመንግሥቱ" ተይዞ ይገኛል ።

የኒቅያ የመጀመሪያው ዐቢይ ሲኖዶስ "ጸሎተ ሃይማኖት" በሁለት ግልጥ መሠረት ነገሮች ግድፈትና ውስከት ተሻሽሎ መጥቷል ። በዚህ በተጠቀሰው በትእዛዛቱ ሰባተኛው መጽሐፍ (ምዕራፍ) በጸሎተ ሃይማኖት ላይ የሚታየውን መሻሻል ያደረገው በ341 በአንጾኪያ የተሰበሰበው አውሳቢያኖሳውያን ተብለው የሚጠሩ ክፍሎች ሲኖዶስ እንደነበረ ይደገፋል[584] "የሐዋርያውያት ትእዛዛት" ጸሐፊ ከታወቁ አውሳቢያኖሳውያን አንዱ እና ጊዜውም ከ341 በኋላ እንደሆኖ ይቆጠራል ።

"ሐዋርያውያት ትእዛዛት" ለመጀመሪያ ጊዜ በግሪክ ቋንቋ ተጽፈዋል ። በ1863 በላቲን ቋንቋ (ሮማይስጥ) ተተርጉመው በ1578 በFr. Turrianus ታተሙ በዚያም በP.G[585] እና mansi ታቅፈዋል[586]

የተሟላ ሕትመት እንደሆነ ተቀባይነትን ያገኘው በF.funk የተደረገው ሕትመት ሲሆን በF. Funk ታትሞ የሚገኘውን ሰነድ ከዚህ ሕትመት ተወስዶ ነው[587]

ስለ ሐዋርያውያት ትእዛዛት በርከት ያሉ ጥናቶች መደረጋቸው ቢታወቅም ከዚህ ማመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አልታየም ሆኖም የበለጠ ለመረዳት ለሚፈልግ ሰው የQuasten ጥናትን መመልከት እንዲችል

582· ዛሬ በሕፃናት ጥምቀት ጊዜ "ጸሎተ ሃይማኖትን" Σύμβολον τής πίοτεως የክርስትና አባት ይደግማል ።

583· ዘዕሩርይ ምስለ" Ομουοὺσιον የሚለው ኃይለ ቃል የኒቂያ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ዐምድና ድድ ነበር ።

ሶቅራጥስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ A. 18.

584· Γ. Δέρβου: Χριστιανική Γραμματολογία T.B. ገጽ 710-766.

P.G.T.I ዐምድ 5.. — 1156

585· MANSI. T. I ዐምድ 256 — 296

586· F. funk didascalia et constitutiones apostolorum-padernborn 1905.

586. F. Funk didascalia et constitutiones Apostolorum padernborn 1905 Quasten, Patrology , T.II

ይጠቅማል[589]

3.3.2. ሐዋርያውያት ቀኖናት የተጻፉበት ዘመን መቆሚያ—መዳረሻ ጊዜ ፤

ሐዋርያውያት ቀኖናት የተጻፉበት ዘመን መቆሚያን Terminus ad Quem አስመልክቶ ያለው ችግር እነዚህ ቀኖናት የተጻፉበትን ዘመን መነሻን Terminus a quo በሚመለከት ያለውን ችግር አይመስልም ምክንያቱም ይህ Terminus ad quem ወታወቁ የጊዜ ምልክቶች አሉትኛ ነው ።[588]

አንደኛ 500 ዓ·ም ዲዮናስዮስ ዘይንዐስ ከ85 ቀኖናት የመጀመሪያዎቹን 50 ቀኖናት ከግሪክ ቋንቋ ወደ ላቲን—ሮማይስጥ ቋንቋ የተረጎመበት ዘመን ነው [589] ሁለተኛ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት –ፓትርያርክ—ሳዊሮስ በ520 ዓ·ም በመልእክቱ "በቀለሚንጦስ ለአሕዛብ የተላኩ ትእዛዛት" በሚል ርእስ 21–23 ሐዋርያውያት ቀኖናትን ያወሳል። የኒቅያአንደኛ ዐቢይ ሲኖዶስ ቀኖና አንድ እና ቀኖና ዘጠኝ በእነዚህ ቀኖናት ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ይደግፋል[590]

ሦስተኛ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት /ፓትርያርክ /565–577/ ዮሐንስ ማዕምር በመድበለ ቀኖናቱ/ብሔረ ሕግ ወቀኖና– Nomocanon: የጌታ ቅዱሳን አርድእትና ሐዋርያት በቀለሚንጦስ አማካይነት 85 ቀኖናትን ሠሩ በሚል ርእስ 85 ቀኖናትን አስፍረዋል ።[591] እነዚህ ቀኖናት በሐዋርያት ተዘጋጅተው በቀለሚንጦስ አማካይነት እንደተላኩ ይደገፋል[592]

589· ከዚሁ ገጽ 154–156

590. E.W. Brooks: The Sixth Book Of The Selected Letters Of Severius Patriarch Of Antioche In syriac Version Of Athanasius Of Nisibis 1902 T. II ገጽ 463—464። የእንግሊዝኛ ትርጉም 1904 T II ክፍል 11 ገጽ 409—412 F. Nau, Canons Des Apötres, D.T.C. II ዐምድ 1606።

591·የዮሐንስ ማእምር ብሔረ ሕግወቀኖና ሕትመት Nomocanon/1671 voelli et Justelli. Bibliotheca Juris Canonici T.II.ገጽ 501

592. Bickell. Die Geschichte Der Kirchenrechts..ገጽ 76 Funk, Die Apostolischen konstitutionen. ገጽ 192

እነዚህ ከዲዮናስዮስ ዘይንዐስ እና ከአንጾኪያ ሲቀጻጻሳት—ፓትር ያርክ ኅዊሮስ ጋር በአንድ ወቅት በዮሐንስ ማእምር ብሔረ ሕግወቀኖና Nomo Canon የተያዙት 85 ቀኖናት መሆናቸው ታውቆ ጸደቁ ። ስለዚህም እነዚህ ቀኖናት በሐዋርያት የተሰጡ ስለመሆናቸው በቢዛንቲን የቆየው ልምድ ፡

Τό δέ έσεσθαι πιστεύομεν είπερ η τών Ιερών Κανόνων παρατ., τησις φυλαττοίτο, ήν οΐ τέ δικαίως υμνούμενοι καί προσκυνηταί καί αυτοπάται του Θείου Λόγου παραδέδωκεν Απόστολοι καί 'Αγιοι Πατέρες εφύλαξαν τέ καί υφηλήσαντο // 593

ከብዙ ጸሐፍትና መተርጉማን ተቀባይነትን አግኝተዋል ።
ስለዚህ ሐዋርያውያት ቀኖናት ከ500 ዓ.ም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት በስፋት ለመታወቅ እንደመቻላቸው መጠን ይህ ጊዜ /500ዓ.ም/ እነዚህ ቀኖናት የተጻፉበተ ዘመን ሊያልፈው ፡የማይቻልበተ ዘመ, terminus ad quem/ሆኖ ይቆጠራል [594]
ሌላው የቀኖናቱ ችግር ርእስ የቁጥራቸው መጠን ነው ምክንያቱም በልዩ ልዩ የእጅ ጽሑፎች የእነዚህ ቀኖናት ቁጥር አንድ ጊዜ 50 ወይም 76 ሌላ ጊዜ 81,83 ወይም 84 የታወቀውም 85 እየሆነ መገኘቱ ይታወቃልና ። በመጨረሻ በከልቄዶናዊት ቤተ ክርስቲያን በ500 ዓ.ም አካባቢ በዮሐንስ መተርጎም የተጠቀሰው 85 ቀኖናቱ ቁጥር እና በ5–6ኛው የትሩሎሲኖዶስ 2ኛ ቀኖና የጸደቀው ይህ አሐዝ ሲጸና [595]
በኢ.ኬልቄዶናውያት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በዐረብኛ ተናጋሪ ዎች መለካውያን ዘንድ በፍትሐ ነገሥቱ መቅድም የተጠቀሰው 82 ወይም 83 ቀኖናት ጸንቷል [596]

በተመሳሳይ ሁኔታ በምዕራብ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በዲዮናስዮስ ዘይንዐስ የተረጎሙት 50 ቀኖናት[597] እና 84 ቀኖናት [598] ይገኛሉ ።

593. Voelli e Iustelli. Bibliothecae Juris canonici I II ገጽ 604
594. Fulton John, Indes canonuin-Greek text an english translation and complet digest of the entire canon law. M.Y 1892 ገጽ 52።
595. Ράλλη-Ποτλής Σύνταγμα Τ.Α. ገጽ 5-335, Τ.Β. ገጽ 1-113.
596. Α. Αλιβιζάτου: Οί Ιεροί Κανόνες ገጽ 75
597. Mansi T. I 30-48
598. Mansi. T.I 40-66

ሆኖም በምሥራቅና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ይፋ መድበላተ ቀኖናት መካከል የ84[599] እና 85 200 ቀኖናት ይዞታዎች መካከል የታየው ልዩነት በይዘት ሳይሆን የቁጥር መሆኑ ግልጥ ነው ። ስለዚህም የተለየ ምርምር ማድረጉ አይታይበትም ነገር ግን በቁጥራቸው የተከሰተው ልዩነት ከ47—85 ይጀምራል[601]

ነገር ግን በማንሲ (Mansi) ሕትመት ይህ ልዩነት የቁጥር ልዩነት ነው ይህም በ12ኛው ቀኖናና በ13ኛው ቀኖና መካከል ማለትም ሁለቱ ቀኖናት አንድን ቀኖና 12ኛ ቀኖናን ይዘው በመገኘታቸው መሆኑ ይታወቃል ።[602]

በታቃራኒው መስመር በኢ.ኬልቄዶናውያት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ከትርጉም ወደ ትርጉም የቀኖናቱ ቁጥሮች ብቻ ሳይሆኑ የይዘታቸው ልዩነት ከፍተኛ ነው ።

ስለ..ህ ልዩ ልዩ በተለይ የምሥራቅ ቋንቋዎች ትርጉማቸውን አስመልክቶ የሚዘረዘሩት ቀኖናት ግድፈት ፡ ተጨማሪ ሐተታ ፡ ጭምቀት ወይም ከፍፍል በከፍተኛ ደረጃ ይታይባቸዋል ።[603]

3.3. ሐዋርያውያት ቀኖናት የተጻፉበት ቦታ፡

ሐዋርያውያት ቀኖናት የተጻፉበ Αποστόλων ለመወሰን ለማግኘት ቀላል አይደለም ምክንያቱም እ..ዩ ገጽ 1-74. ..አንድ/ ብ..ውሰን ጊዜ እንደ አለመጻፋቸው ሁሉ በአንድ ῶν Κανόν ቦታም አልተጻፉም ፡ ስለዚህም ማለት የሚቻለው ምን ዓልባት በቃል ሲያያዝ በመጣ የሐዋርያት ትምህርት ላይ በመመሥረት በልዩ ልዩ ስፍራዎችና ጊዜያት እየተቀረጹ– እየተነደፉ መጥተው በመጨረሻ በአንድ አቀነባባሪ ሰው ወደ አንድ ወጥ ሰነድነት ሊዋሐዱ ችለዋል ነው ። ወደፊት እንደምንመለከተው በሶርያ በ400 ዓ.ም[604] በሶርያ ሜቄዶንያ ቀመረ ዘመን "Octobrios" ጥቅምት

599. Mansi. T.I 30-48
600. Ράλλη-Ποτλής Σύνταγμα Τ.Β. ገጽ 1-112.
601. P. Pitra. Juris Ecclesiasticorum Graecoromanum.
602. Mansi T.I. ዐምድ 30 – 48
603. በተለያዩ የእጅ ጽሑፎች ስለሚገኙ ሌሎች የቁጥሮች ልዩነቶች
604. ከዚሁ ገጽ 158

የሚለው የወር ስም "Upereberetaios" [605] ሁኖ ከሚገኝበት 37ኛ ቀኖና መሠረት መደምደሚያው ወደ መሆን ሊደረስበት ይችላል ።[606]

3.4. የሐዋርያውያት ቀኖናት ጸሐፊ ፤

በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሲያያዝ በመጣው ልምድ–ትውፊት መሠረት ተቀባይነትን አግኝቶና ፀንቶ ከቆየው አሰተሳሰብ ወይም ልምድ አንፃር ሐዋርያውያት ቀኖናት አሁን በሚገኙበት ቅርጻቸው የጻፋቸው— ያዘጋጃቸው ወይም ያቀነባበራቸው ሰው ማን እንደነበር ባይታወቅም ቅሉ አንድ ሰው /ግለሰብ/ እንደነበር ነው መረዳት የሚቻለው ። ይህም ስም የለሽ /ስም አልባ ጸሐፊ እነዚህ ሐዋርያውያት ቀኖናት አባሪዎች ሁነው የሚገኙባቸው "ሐዋርያውያት ትእዛዛት"ን ያሰበሰበው ሰው እንደነበረ ይታመናል ። ይህም ሰው ዝነኛው አርዮሳዊ Apolinarius አ ፖሊናርዮስ መስመ ኢግናጢዮስ አፖሊናርዮስ(pseudoigntius, apolinarius) ስድስት አዋልድ መልዕክቶችን የጻፈውና ስባት እውነተኞች መልዕክቶችን ያዘጋጀ እንደነበረ[607] ይታሰባል ። ይህም ሰው እነዚህን ሐዋርያውያት ቀኖናት ከአቀነባበረ በኋላ በሌሎችም ቀኖናት እንደተደረገው ሁሉ

605· በዓመቱ በሁለተኛው ወር የኤጲስ ቆጶሳት ሲኖዶስ ይደረግ

"δεύτερον τού έτ ረፊቅ አብያት γίνεσθω τών Επι-
σκόπων καί ανακριέτωσαν άλλη ሐ ነገሥ ..α τής ευσεβαίς
καί τάς εμπίπτουσας Εκκλησιαστικ λογίας, διλυέ-
τωσαν άπαξ μέν τής τετάρτης εβδομάδος τής Πεντικοστής
δευτέρα δέ υπερβερέτσιος δωδεκάτη." Οκτώβριος = Υπερβερέταιος

606· Beveregius, Studicum De Canonibus APostolici: Cotelerius, Pateres Apost. 1724 T.I. ገጽ432·Beveregius: Codex Canonum T-II Appendice ገጽ 1
Funk. Die Apostolischen Constitutionen ገጽ 191·
Bardy:Canons Apostoliques D.D.C.T.II ገጽ 1288. Nau. Canons des Apôtres D.T.C.T. 22 ገጽ 1605

607. Funk :Didascalia Apostolorum : TIIገጽ 604
Funk: Die Apostolischen Konstitutionen ገጽ 204
Bardenhewer, Les Pe'res Del' e'glise ፈረንሳይኛ ትርጉም 1898 T.I ገጽ 52
M. Ligthtfoot. The Apostolic Fathers, London 1885 ገጽ 273
Ροδοπούλου: Η αναφορά τής Λειτουργίσς τού κλήμεντος 1959 ገጽ 25.

ከሐዋርያት በቀለሚንጦስ ለምዕመናን እንዲተላኩ አድርጎ እንዲቆጠሩ አድርጓል ማለትም ስለ ሥርዐተ ጽዮን–30 ቀኖናተ ሐዋርያት የታተመ ስለ 85 ቀኖናትም ይሠራል ።

3.5 ሕትመት

የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ግሪክ ሰነድ በመጀመሪያ ጊዜ በሕትመት በ1531 በ Haloander ታተመ[608] ። ከዚያም ለሌሎች ሕትመቶች በሚከተሉት ጸሐፍትና ተመራማሪዎች ተከናውነዋል በ1672 G. Beveregius[609] በ1759 በMansi[610] በ1806... Αγαπίου Ιερομονάχου-Νικοδήμου Μονοχού: [611] በ1652 Ράλλη - Ποτλή [612] በDe Lagarde[613] በ1864 በ1864 በP.pitra[614] ፤ በ1865 በJ. Migne[615] ፤ በ1989 በHefel[616] በ1896 በF. Laauchte[617] ፤ በ1906 በ Funk.[618] Α. Αλιβιζάτου [619], በ1955 Αποστολική Διακονία [620]

---

608 Νεαρών τού Ιουστινιανού Βασιλέως Βιβλίον NUEMBERG.

609. Synodicon sive Pandectae Canonum SS, Apostolorum et Consiliorum Ab Ecclesia Graeca Receptorum Oxford 1759 T I ገጽ 1—57

610· Sanctorum Conciliorum Nova et Amplissima Collectio Florentiae 1759 አዲስ ሕትመት 1960 T.I. ዐምድ 29—48

611· Πήδαλιον ήτοι άπαντες οί Ιεροί καί Βείοι Κανόνες τών τέ Αγίων καί Πανεφήμων Αποστόλων, Αγίων Οικουμενικών Συνόδων, Λειψια 1806 ገጽ 1-74.

612· Σύντογμα Θείων καί Ιερών Κανόνων, ΑΘΗΝΑΙ 1962 Τ.11 ገጽ 1-112

613·Reliquiae: Graec. 1856 ገጽ 1—45

614· Juris Ecclesiastici Graecorum Historia et Monumenta. Roma 1864 T.I. ገጽ 1545

615. Theodori Balsamani, Zonarae, Aristeni, In Canones SS Apostolorum et Conciliorum Commentaria: P.G.T. CXXIV ዐምድ 35—217

616. Histoire des Conciles (ፈረንሳይኛ ትርጉም) Paris 1869 T.I Appendice ዐምድ 1216—

617· Die Kanones Der Wichtigsten Ältkirchlichen Concilien Nebsi Den apostolischen Kanones, Leipzig 1896.

618. Didascalia — Padernborn 1906 ገጽ 664

619· Οί Ιεροί Κανόνες, ΑΘΗΝΑΙ: 1969 ገጽ 137-155

620· Βιβλιοθήκη Ελλήνων Πατέρων καί Εκκλησιαστικών Συγγραφέων, ΑΘΗΝΑΙ: Τ.II 1955, ገጽ 172-180

3.6 ጥናቶች

ሐዋርያውያት ቀኖናትን አስመልክቶ የተደረጉ ጥናቶች እጅግ በርካታ ናቸው ። ሆኖም ከዚህ ላይ እያንዳንዱን ጥናት መዘርዘሩ በጣም አስፈላጊም አይደለም ምክንያቱም ጽሑፉ የተነሳበትን ዓላማ አጥር ሊዘል ይችላልና ሆኖም ግን ለመመልከት ፍላጐት ላለው ሰው (P) Quasten ጥናትና ከዚያም የተሰባሰቡትን ሌሎች ጥናቶች መመልከት ይቻላል[621]

3.7 የ85 ቀኖናት የጥንት ትርጉም—ትርጓሜዎች

እንደሚታወቀው 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀደም ብሎ በሚከተሉት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል ።

1· በላቲን — ሮማይስጥ
2· በሶርያኛ — ሱርስጥ
  ሀ) በንስጥሮሳውያን
  ለ) በያዕቆባውያን
3· በግብጥ
4· በዐረብኛ
  ሀ) በመለካውያን
  ለ) በንስጥሮሳውያን
  ሐ) በያፅቆባውያን
5· በግእዝ

3.7.1 የ85 ቀኖናት የላቲን—ሮማይስጥ ትርጉም

በላሎን ከተማ ድልማትያ ኤጲስ ቆጶስ እስጢፋኖስ ጥያቄ መሠረት[622] ዲዮናስዮስ (ዲዮኒስዮስ) ዘይንዕስ በ500 ዓ/ም የመጀመሪያዎችን 50 ቀኖናት ከግሪክ ቋንቋ ወደ ላቲን ቋንቋ - - ሮማይስጥ ተረጐመ ። በአጠቃላይ በዲዮናስዮስ ዘይንዕስ የተደረገው የእነዚህ ቀኖናት ትርጉም

621· Quasten: Patrology. ገጽ 23

622. Epist. AD. Stephanus Episcopum ሕትመት Voelli — Justeli Bibliotheca Juris Canonici T.I ገጽ 201. Assemani: Juris Orient. T.I ገጽ 107 Bardy: Canons Apostoliques: D.D.C. T. II[2] ገጽ 1290

በሁለት ደረጃ ተከናውኗል ማለትም በብዙ የእጅ ጽሑፎች ተመሥርቶ በዲዮናስዮስ ዘይንዕስ የመጀመሪያ ትርጉም 26 እና 27 ቀኖናት ተጣምረው 26ኛውን ቀኖና እንዲይዙ ሁኖ 49 ቀኖናትን ይይዛል ።

ይህ ትርጉም ለመጀመሪያ ጊዜ በC.H. Turner በ1899 መታተሙ ታውቋል[623]
በልዩ ልዩ ቋንቋዎች[624] የእጅ ጽሑፎች የሚገኘው ሁለተኛው ትርጉም 49 ቀኖናትን ሳይሆን 50 ቀኖናትን ይዞ የሚገኝ ነው[625]

ስለዚህ በምዕራብ 50 ቀኖናት ብቻ Codex Canonum Ecclesiasticorum Dionysii Exiguii የተያዙ ናቸው እነሱም Qui Dicuntur Apostolorum የሚል ገጽታ ተሰጥቶአቸዋል [626]

ስለዚህም ዲዮናስዮስ በእሱ የተተረጐሙትን ቀኖናት በሚከተለው ዓይነት በመቅረጽ በሐዋርያት ትውፊትም — ትምህርት ላይ አልተመሠረቱም ከማለት ይልቅ ሐዋርያዋያት ናቸው የሚለውን ይቀበላል ።" Incipient Regulae Ecclesiasticae Sanctorum Apostolorum, Prolatae Per Clementem, Ecclesiae Romanae Pontificem. Qae Ex Graecis Exemplaribus in Ordinentae Primo Ponuntur Quibus, Quamplurimi Qui Dem Consensum Non Praebuere Facilem et Tamen Postea Quaedam Constituta Pontificicum Expsis Canonibus Asumpta Esse Videntur"[627] በታቃራኒው ግን በብዙ ጸሐፍት አመለካከት ድጋፍ ባይኖረውም ከሐዋርያውያት ትእዛዛት ጋር ቀደም ብለው እነዚህ ቀኖናት ተተርጉመው እንደ ነበር ይደገፋል[628] ።

623 C.H. Turner: Ecclesiae Occidentalis Monumenta Juris Antiquissima: Oxford. 1899 T.I. ገጽ 1- 32

624. F Maassen, Geschichte Der Quellen Und Der Literatur Des Canonischen Rechts in Abendenland Graz 1870 ገጽ 348—440

625. Mansi T ገጽ 49—66

626· ከዚሁ ገጽ 138–148

627. C..T. Turner: Ecclesiae Occicdentalis... T.I. ገጽ 1

228. A. Spagnolo and Turner: A Fragment of Latin Version of the Apostolic Constitutions. J.S.T. 1912 T. XIII ገጽ 39 C. Turner: Ecclesiae Occidentalis... 1913 TI II ገጽ 329—333 Turner: Primitive Edition of the Apostolic Constitutions and Canons J.T.S.T.XV ገጽ 55 Bardy, Canons Apostoliques D.D.C. T II ገጽ 1280።

ከዚህም የተነሳ በብዛት ተቀባይነት ያገኘው ትምህርት የ85 ቀኖናት የመጀመሪያው ላቲናዊ ትርጉም የዲዮኒስ ዮስ ትርጉም እንደነበር ነው ።

ስለዚህ የዲዮናስ ዮስ ዘይንዕስ ትርጉም በ1· Marlin በ1524 ታተመ[629] ። ከዚያም እንደተመለከተው ሂሳዊ ሕትመት በC.H. Turner ተካሄደ[630]

P. F. Mansi ሕትመት በአንድ በኩል በዲዮኒስዮስ እንደተረጐመ የመጀመሪያዎቹን 50 ቀኖናት[631] በሌለ በኩል ከላቲን ትርጉም ጋር 84 ቀኖናትን በግሪክ ቅጃቸው ይዞ ይገኛል[632]

3·7·2 የ85 ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም

የ85 ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም በተራ ምን አልባት በ7ኛው ምዕተ ዓመት በርግጥም የዚህ ትርጉም የእጅ ጽሑፍ ጊዜ ሆኖ የሚታሰበው ሆኖ የሚገኘው ጥንታዊ ሁለተኛ ትርጉም ነው[633]

ስለዚህ ይህ ጥንታዊ ትርጉም በንስጥሮሳውያን ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በያዕቆባውያን ቤተክርስቲያን በአገልግሎት ላይ ይገኛል[634]

3·7·2·1 የያዕቆባውያን ሐዋርያውያት ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም

በያዕቆባዊት ቤተክርስቲያን አገልግሎት ላይ የሚገኙት ሐዋርያውያት ቀኖናት በመጀመሪያ በ85 ቀኖናት ፈንታ 82 ቀኖናትን ይዘው

629. Codex Canouum Ecclesiasticorum Dionysii Exiguii Paris 1524 እንደገናም Corpus Juris Ecclesiastici በብዙ ቦታዎች ታትሟል F. Nau. Canons Apostoliques D.T.C.T. 1I ገጽ 124
630. Codex Canonum Ecclesiaticorum Dionysii Exiguii, 524
631· ከላይ ገጽ 41,154-156
632. Mansi T.I ዐምድ 49—66
633. Mansi T.I. ዐምድ 29—48
634. Wright Catalogues of Syriac Mss. London. 1876. Add. 14526 Fol. 9. የ7ኛው ምዕተ ዓመት M. Lightfoot. St. Clement of Rome T.I. ገጽ 373-374 የግርጌ ማስታወሻ በሁለት አብያተ ክርቲያናት መስነውያት ያዕቆባውያተ በአገልግሎት ላይ የሚገኙት ሱርስጥ ትርጉሞች "Syriaca et Syriaca Altera" በሚሉ ርእሶች በFunk በተመለከተው መልኩቸው ። Lecclerq: Canons Apostoliques D.D.C.L. ዓምድ 1920 የግርጌ ማስታወሻ 16 ተመልከት ።

ይገኛሉ ምክንያቱም ሁለት ወይም የበለጡት የግሪኩ ቋንቋ ቀኖናት ወደ አንድ ወይም ወደ በለጡ ቀኖናት በመሰባሰብ በ82 ቀኖናት ሊወሰኑ ችለዋል። ይህም እንደሚታወቀው ሁለት ቀኖናት ማለትም 12 እና 13 ግሪክ ቀኖናት በሱርስጥ ትርጉም አንድ ቀኖናን (12ኛውን ቀኖና) 49 እና 50 ግሪክ ቀኖናት በሱርስጥም ትርጉም 49ኛውን ቀኖና ሲይዙ በሌላም በኩል የሱርስጥ ትርጉም ግሪካውያት ቀኖናትን ተራ አይከተልም። የተወሰኑ ቀኖናት ተራቸውን በመለወጥ ስለዚህም 47ኛው ሱርስጥ ትርጉም ቀኖና ከ49ኛው ግሪክ ቀኖና ጋር ተዛውሮ ሲገኝ 65ኛው ቀኖና ከ62ው ቀኖና በፊት ይገኛል ፤ ከ50ኛው ቀኖና ጋር ከተዋሐደው 49ኛው ሱርስጥ ትርጉም ቀኖና መጨረሻ ላይ ጥምቀትን አስመልክቶ ሰፋ ያለ ድንጋጌ ተጨምሮበታል[635] ነገር ግን በ46ኛውና 47ኛው ቀኖናትም ጭማሪዎች ተመልክተዋል ግን አንድ ግሪክ ቀኖና (48ኛው ቀኖና) በሱርስጥ ትርጉም አይገኝም[636]

ጭማሪዎች ትእዛዛት የተደረጉባቸው እነዚህ ቀኖናት በሰነዶች ሕዳጋት ኮከብ ዓይነት (ጩረቃ) ምልክት ተደርጐባቸዋል ለምሳሌ Syriaca et Syriaca Altera በሚል ርእስ funk ባመለከታቸውና በP. DE Lagarde ታትመው በBibliotheque Nationale de Paris በሚገኘው የእጅ ጽሑፍ የሚገኙ ናቸው[637] ይህ የሐዋርያውያት ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም በስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘያዕቆባውያን[638] ከላቲን ትርጉም ጋር በ1856 በP.De! Lagarde ታትመዋል[639] የተከሰቱትን ልዩነቶች በሚመለከት በቀለሚንጦስ እጅ ለአሕዛብ የተላኩ ትእዛዛተ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያናውያት ቀኖናት" በሚል ርእስ በእሱው 1856 ታትመዋል[640]።

ሆኖም በሱርስጥ ትርጉሙና በግሪኩ እናት ሰነድ መካከል የተመለከቱት ልዩነቶች ሁሉ እንደተጠበቁ ሁነው ሱርስጡ ሰነድ በትክክል

635. P. De Lagarde Reliquiae...Syriac ገጽ 62
636. P. De Lagarde Reliquiae...Graec ገጽ XXIX—XXX
637 P. De Lagarde, Reliquiae...Syriac ገጽ 62
638. F. Nau, la Version Syriaque De l'Octateuque, Bardenhewer. Geschichte Der Ältkirchen Literatur. Freiburg.
639. P. De Lagrade: Reliquiae...Syriac ገጽ 44—61
640. P. De Lagarde: Reliquiae...Graec ገጽ XXXCIII—XXXIII

ከግሪኩ እናት ሰነድ የተተረጐመ መሆኑ ይደገፋል[641]

3·7·2·2· የንስጥሮሳውያን ሐዋርያውያት ቀኖናት ሱርሰጥ ትርጉም ፡

በንስጥሮሳውያን ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት ላይ የሚገኘው የሐዋርያውያት ቀኖናት ሱርሰጥ ትርጉም በንስጥሮሳዊ Ebedjesus (1318) መድበለ ቀኖናት ይገኛል…ከተወሰኑ አንድ አንድ ለውጦች በስተቀር እነዚህ ቀኖናት ከተጠቀሱት ያዕቆባዊት ቤተክርስቲያን ቀኖናት ጋር ልዩነት የላቸውም[642] 47ኛው ፡ 50ኛው ፡ 62ኛው ፡ 65ኛው ቀኖናት ቦታ አለወጡም በተቃራኒው ግን 44ኛው ቀኖና 43ኛውን ቀኖና ይቀድማል ፡፡

ብቁጥር የንስጥሮሳዊት ቤተክርስቲያን ቀኖናት 83 ሲሆኑ የያዕቆባዊያት ቤተክርስቲያን ቀኖናት 82 ናቸው ምክንያቱም በያዕቆባዊት ቤተ ክርስቲያን 12ኛ እና 13ኛ ቀኖናት 12ኛውን ቀኖና ፤ 49ኛው እና 50ኛው ቀኖናት 49ኛውን ቀኖና እንደያዙ ሁነው ሲገኙ[643] በተቃራናዊ 48ኛ ቀኖና በንስጥሮሳዊተ ቤተ ክርስቲያን አይገኙድልም ፡፡ በ49ኛው ቀኖና መጨረሻው ግን ተጨማሪ ድንጋጌዎች ይታያሉ[644] ፡፡ ይህ የቀኖናቱ ሱርሰጥ ትርጉም ሰነድ ከላይ እንደተመለከተው Ebedjesus ብሔረ ሕግ ወቀኖና (መድብለ ቀኖናት)[1] በተያያዘ መልኩ ከላቲን ትርጉም ጋር በሚከተለው ርእስ" "Synodus Secunda Canones Apostolorum... per Sanctum Clementi discip- ulum apostolorum...[645]

3·7·3·የሐዋርያውያት ቀኖናት ግብጥ ትርጉም

ሐዋርያውያት ቀኖናት በሁለት ግብጣውያን ቋንቋዎች ተባይቅና ሳዲቅ፡ ሚምፊቲቅ ትርጉሞች ተመልሰው መጥተዋል ፡፡

የተባይቁ የቀኖናቱ ትርጉም በ1848 Tattam በተባለ ሰው " The Apostolical Constitutions ወይም Canones of the Apostles in Coptic በሚል ርእስ ታትመው ሲገኙ ይህም ቶባይቅ ራሱ ከተመለሰበት

641. P. De Lagarde Reliquiae...Graec ገጽ XXIX—XXX
642- ከዚሁ ገጽ 55
643- ከዚሁ ገጽ 156-157
644- Bardy: Canons Apostoliques D.D.C.T. II
645. A Maio: Scriptorum...T.X. ገጽ 8—17 175—184

ትርጉም ሚምፊቲቅ ትርጉም ይቀድማል[646]

የእነዚህ ቀኖናት ሰነዶች አዲስ ሕትመት መኖር ወይም አለመኖር መረጃ አልተገኘም ፡፡

3.7.4 የሐዋርያውያት ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም

የሐዋርያት ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም 83 ፤ 82 እና 81 ቁጥሮችን ይዘውና ልዩ ልዩ አርእስት ተሰጥቷቸው ሲያያዙ መጥተዋል[647] ፡፡ የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብነ እል አሳል መለካውያንና ንስጥሮሳውያን ቀኖናት ሐዋርያውያትን ወደ ዐረብኛ ቋንቋ ለመተርጐም ጥረት ማድረጋቸውን ይገልጣል ፡፡ ነገር ግን የቀኖናቱ ቁጥሮች በመለካውያን ዘንድ በያዕቆባውያንም እንደ አሉት ሁሉ 83 ሲሆኑ በንስጥሮሳውያን ዘንድ "መጽሐፈ ኩሉሙ ክርስቲያን" ተብሎ በሚታወቀው መድበለ ቀኖናት ዘወልደ ጠይይብ ንስጥሮሳዊ እንደተመለከተው 82 ናቸው[648] ይህኑ መጽሐፈ ኩሉሙ ክርስቲያን በዐረብኛ ቋንቋ "መጽሐፈ ክርስቲያናዊ ሥነ ጥበብ[649] በመባል ሲታወቅ ከIbant— Tajjib (1849) ብሔረ ሕግ ወቀኖና Nomocanon ጋር ይመሳሰላል[650]

ወልደ ጠይብ ወይም Ahu-l Farag Ibn al–Tavvib እንጸኪያዊ ንስጥሮሳዊ ሊቀ ጳጳሳተ—ፓትርያርክ ጸሐፊ ፡ መነኩስና ሊቀ ካህናት የነበረ ሰው ሲሆን ፈላስፋና ሐኪምም ነበር ፡፡ ስለዚህም ምሥጢራተ መለኮትንና የትርጓሜና የሕገ ቤተክርስቲያን ሥራዎችን የጻፈና የአርስጣጣልንና የጋሊኖስን ፍልስፍና ትርጓሜ የመረመረ ሰው ሲሆን በተለየ በጣም የታወቀበት ሥራው ሕገ ክርስትና — Fiqu An Nastraniaa " Das Recht Der Christenheit" Des Nestorianischen Presbyteres Abu– Hoenerbach

646. Lightfoot: St. Clement of Rome ገጽ 342
647. Riedel, Die Kirchenrechtsquellen... ገጽ 157
648. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
649. Guidi, Il Fetha Nagast... ገጽ 11 የግርጌ ማስታወሻ 3
650. Guidi: Il Fetha Nagast... ገጽ 11 የግርጌ ማስታወሻን 3
651. Guidi: Zdmg. T. ገጽ 388—391
Ruhens Duval: La Litterarure Syriaque, PARIS. 1899 ገጽ 177 E. sachau — G. Bruns: Syrisch-Römisches Rechtsbuch, Aus Dem Fünftem Jahrhundert, Herausgegben...Leipizg 1880. Riedel. Die Kirchenrechtsquellen ገጽ 148—152

ch S. Spies 1946 ታትሞ ሊሰራጭ ችሏል[652]

የቀኖናቱ አርእስቶችና ቁጥሮች ከእጅ ጽሑፎች ወደ እጅ ጽሑፎች ይለያያሉ ለምሳሌ በ Bibliotheque Nationale de Paris በሚገኙ ቁጥር 252 የእጅ ጽሑፎች በተለያዩ ርእሶች ሁለት ሰነዶች ይገኛሉ ።

ከእነዚህም የመጀመሪያው "ቀኖናተ ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን" ወይም "አርድእት ያዘዟቸውና ቀለሚንጦስ የጻፋቸው አባስታላሳት" (አብጠሊሳት) በሚል ርእስ የሚገኝ ሲሆን የቀኖናቱ ቁጥር 82 ሲደርስ[653] በአንጻሩ በመለካውያን ዘንድ ቲትላሳት (ተጥላሳት) በሚል ርእስ ተያይዘው የመጡት ቀኖናት ቁጥር 81 ሁኖ ይገኛል[654] በተቃራኒው በቁጥር 252 አሁንም የሚገኘው የእጅ ጽሑፍ ርእስ ቲትላሳት (ተጥላሳት) ከላይ ለተመለከተቱት 30 ሐዋርያውያት ቀኖናት ተበጥቶ ይታያል [655] በሌላ በኩል "ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያውያት ዘበእደ ቀለሚንጦስ በሚል ርእስ የተቀረጹና በእጅ ጽሑፍ ሕዳግ የተከፈሉ ከሱርስጥ ትርጉም ቀኖናት ጋር ሲመሳሰሉ እነዚህም በ49ኛው ቀኖና ጭማሪ ዝርዝሮችን ይዘው ይገኛሉ[656]

የእነዚህን ቀኖናት አርእስት Vansleb በ1671 ወደ ፈረንሳይኛ ተርጉማቸዋል [657]።

3.7.5 የሐዋርያውያት ቀኖናት ግእዝ ትርጉም

"በሐዋርያት ተጽፈው በቀለሚንጦስ የተላኩ ቀኖናት" በሚል ርእስ የተቀረጹ ግን የተለያየ ይዘትና ክፍፍል ያላቸው ቤተ ክርስቲያናውያት ቀኖናት ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉመው ይገኛሉ ። በጥቅል "ሲኖዶስ ዘቅዱሳን አበዊነ ሐዋርያት፡ ወዘተ· "ተብለው ይጠራሉ ። በአለፈው ክፍል ስለቀኖናተ ሐዋርያት ዘጽርሐ ጽዮን ተነግሮዋል[658] "ረስጠአ" በሚል ርእስ የሚመረመሩትን ቀኖናት አስመልክቶ ከ85 ቀኖናት ላይ የተቀነባበሩ አራት ዓይነት ቀኖናት በግእዝ ትርጉም ሲገኙ ቁጥሮቻቸው የአንዱ

652. C.S.C.O. Paris 1956. ገጽ 161—162 1958 ገጽ 167—168
653. Ms Arabe de Paris No 252. ገጽ 12—37
654. Mss. Melchetes Arabes de Paris No. 235. 4ኛ 236 ፡ 7ኛ ከዚሁ ገጽ 116—140
655· ከዚሁ ገጽ 126–150
656. MS. Arabe de Paris No. 250. ገጽ 562 567
657. Vansleb: Histoire de L'eglise ገጽ 25 ሀረብኛ "ቲትላሳት" ግእዝ "ተጥላሳት"
658· ከዚሁ ገጽ 113–136

56 ሲሆን የሦስቱ 81 ፡ 82 እና 83 ሆነው ይገኛሉ[659]

እነዚህ ቀኖናት እንደሌሎች ልዩ ልዩ ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናት ከዚህ ላይ ባይመረምሩም በተለያዩ ቅደም ተከተል "በሲኖዶሱ" ተደዘዋል[660] ። ምክንያቱም ከእጅ ጽሑፎች ወደ እጅ ጽሑፎች የተለያየ የቀኖናቱን አርእስት አሰጣጥና ተራ አቀማመጥ አግኝቶና ማነጻጠሩ በአጭሩ በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ አልተሞከረም ቢሆንም በባቲካን ቤተ መጻሕፍት Codex —Borgio Etiopico ቁጥር 1 በመጠቀም ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ መሰመር አስችሏል ።

1· በ"ሲኖዶስ" በተቀመጡበት መልካቸው ከ81 ቀኖናት መካከል በተራ ቅደም ተከተል አቀማመጥ የመጀመሪያዎቹ ቀኖናት "ቀለሚንጦስ ያስተላለፈው የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶስ" በሚል ርእስ የተቀመጡት ሲሆኑ እነዚህም ቀኖናት "አብጠሊሳት" ይባላሉ[661] ስለዚህ እያንዳንዱ ቀኖና "አብጠሊስ 1ኛ" "አብጠሊስ 2ኛ "አብጠሊስ 3ኛ" ወዘተ በሚል ርእስ ይለያያሉ ።

2· በሁለተኛው ተራ ቅደም ተከተል ተመዝግበው የሚገኙት 81 ቀኖናት "በቀለሚንጦስ የተሰራጩ የቅዱሳን ሐዋርያውያት ቀኖናት ሲኖዶስ" በሚል ርእስ ሲለዩ እነዚህም በበኩላቸው "በጥሊሳት" ተብለው ይጠራሉ[662] ነገር ግን የዚህ ቅደም ተከተል ተራ ቀኖናት "ቀኖናት" በመባል ይታወቃሉ ምክንያቱም እያአንዳንዱ ቀኖና "ቀኖና 1ኛ" "ቀኖና 2ኛ" "ቀኖና 3ኛ" ወዘተ የሚል ርእስን እየያዙ ስለሚገኙ ነው ።

3· በሦስተኛው ተራ ተደዘው የሚገኙት ቀኖናት ከቀለሚንጦስ ጋር በሐዋርያት የተደነገገ ሲኖዶስ" የሚል ርእስ[663] ሲኖራቸው እነዚህም ቀኖናት "ትእዛዛት" ይባላሉ ። ምክንያቱም እየአንዳንዱ ቀኖና "ትእዛዝ 1ኛ ፡ ትእዛዝ 2ኛ ፡ ትእዛዝ 3ኛ" ወዘተ በሚል ርእስ ስለሚለዩ ይሆናል ።

659· ከዚሁ ገጽ 210
660· ሀ· 81 ተራ 3 MS. Borgio Ethopico ገጽ 63 64
ለ· 81 ተራ 4 Borgio Etiopico ገጽ 84 94
ሐ· 81 ተራ 7 Borgio Etiopico ገጽ 50 56
661· Borgio Etiopico ገጽ 63
662· Borgio Etiopico ገጽ 84
663· Borgio Etiopico ገጽ 103

ከእነዚህ የመጨረሻዎች ቀኖናት "ትእዛዝ" ጋር ተጣምረው (ተያይዘው "ስለክርስቶስ በጴጥሮስ የቀለሚንጦስ ሲኖዶስ" በሚል ርእስ የተቀረጹ) የተወሰኑ ቀኖናት ይገኛሉ ። ስለዚህ አሁን በመመርመር ላይ የሚገኙት ቀኖናት ሁሉም 81 ቁጥርን እየያዙ ቢገኙም እንደ ሚከተለው በልዩ ልዩ አርእስት ይከሰታሉ ።

ሀ· ከእነዚህ ቀኖናት መካከል የመጀመሪያውን ተራ ይዘው የሚገኙት ቀኖናት "አብጠሊስ" (አብስጠሊስ) ወይም "አብጠሊሳት" "አባስታላሳት" አባስጣላሳት (Abastalasat) የሚለው ኀይለ ቃል በዚሁ ዓይነት መልክ በዐረብኛው ትርጉም ይገኛል[664] በሌላም በኩል አብጠሊስ ሲበዛ አብጠሊሳት የሚሉት ኀይላተ ቃላት ከሌለ ግሪክ ቃል "አብጠሊስ" አፓስቶሎስ ትርጉም ሐዋርያ ፡ አብጠሊሳት አፓስቶሊ ትርጉም ሐዋርያት የተወሰዱ ቃላት መሆናቸው ይደገፋል ። ከሌሎች በተለየ ከሮማይስጥና ጽርእ በግእዝ ቋንቋ የተወሰዱ ቃላት የቅርጽ ለውጦችና የፊደሎች ዝውውሮች እንደ አጋጠማቸው መመልከቱ አስፈላጊ ይመስላል ። ስለዚህ አንድ አንድ ምሳሌዎችን መመልከት ይቻላል ።

ልሳነ ጽርእ	ትርጉም	ግእዝ
ኤፓክቲ	ተውሳከ ተርፍ	አበቅቴ
ኢብሎጊዮስ	ብሩክ	አውሎጊዮን፣
አግዮስ ኪርዮስ	ቅዱስ እግዚእ	አግዮስ ኪርዮስ
አግዮን ፕኒብማ	ቅዱስ መንፈስ	አግዮን ማንጦን
አግዮን ፕኒብማቶስ	የቅዱስ መንፈስ	አግዮን ፓንዋማንጦን
አሊቲኖስ(ን)	እውነተኛ በውነት	አላቲኖስ
ኤፓጎሜኒ	ተውሳከ ትርፍ	ጳጉሜን
ፕሳልትርዮን	መዝሙር	ፕሳልቴ
ፕሳልቲስ	መዘምር	አብሲሊጲስ
ፕሊንቲዮስ	አበቅቴ ዐሐይ	ፕንቅዮን
ሲንታንያ	ሲጦን	ሲጦን
ፔንቲኮስቲ	በዓለ 50	ጰንጠቆስጢ
አፖካሊፕሲስ	ራዕይ	አቡቀለምሲስ
ፕራክሲስ	ግብረ ሐዋርያት	አብረክሲስ
ኮሬ ኢጲስቆጶስ	የአውራጃ ኢጲስቆጶስ	አቢስኮቦስ
ወዘተ		
ቃል ሲዛወር ለምሳሌ		
ቴኦሎጎስ	ነባቤ መለኮት	ታዎሎጎስ

664· I.Guidi Il Fatha Nagast ገጽ 15 የግርጌ ማስታወሻ ፤ W. Riedel, Die Kirchenrechtsquellen... ገጽ 299

በሁለተኛ ተራ የተቀመጡት ቀኖናት "ቀኖና" ወይም "ቀኖናት"[665]

ሐ· ሦስተኛውን የቅደም ተከተል ቦታ ይዘው ያሉት ቀኖናት "ትእዛዝ" ወይም ትእዛዛት[666] ።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ሐዋርያውያት ቀኖናት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ መተርጐማቸው ይታማናል ። ሆኖም ግን የቀኖናቱ ትርጓሜ ትርጉም በተለያዩ ሰዎች ማለትም እንደ ቀኖናቱ ቁጥር ልክ — ብዛት "አብጠሊሳት" "ቀኖናት" እና "ትእዛዛት" ማለትም ሦስቱም ዓይነት ቀኖናት በሦስት መተርጐማን መመለሳቸው ሲታመንበት ነገር ግን በርግጥም በተለያዩ ጊዜያት መመለሳቸውን መገንዘብ ይቻላል ። ምክንያቱም ዐረብኛው ሰነድ አንድ ጊዜ "ከአብጠሊሳት ሌላ ጊዜ ከትእዛዛት ጋር ይገጣጠማል ። ለምሳሌ የትእዛዛት (ቀኖናት) ድንጋጌ በዐርብኛው ሰነድ አባስታላሳትም ሆነ በግእዙ ቀኖና አብጠሊሳት አይገኝም ። የመጨረሻዎቹ 79—81 ቀኖናት በግእዝ አብጠሊሳትም ሆነ በዐረብኛ አባስታላሳት አይመለሱም ።

በJ. Ludolphus የ81 ከኖናት (አብጠሊሳት) አርእስትንና ከ11 13 ያሉትን ቀኖናት በሙሉ ወደ ላቲ ፡ ቋንቋ በ1661 ተርጉሟል[667] በሌላ በኩል የእነዚህ ቀኖናት ሦስት ትርጉሞች በአንድ P Abbadie ቁጥር 65·ዐ·4·11 የእጅ ጽሑፍ ተዩዘው ይገኛሉ[668]

ሆኖው 81 ሐዋርያውያት ቀኖናት እና የተመለከቱት ሦስት ቅርጻቸው እስከማውቀው እስከ አሁን ገና አልታተሙም ለማንኛውም አንባቢ በተለየ ለሚመራመር ሰው በስፋት ሊታወቁና ሊደረስባቸው አልታቻለም ስለዚህ እስከ ዛሬ አልታተሙም በቅርቡ ታትመው ለአንባቢያን እጅ እንደሚበቁ ተስፋ ይደረጋል ።

ይህም እነዚህ 81 ቀኖናት ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛው ቀኖና ዝርዝር ወይም በኢትዮትጵያ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ዘሰመንቱ መጻሕፍት ዘበእደ ቀለሚንጦስ[669] ተይዘው ከሚገኙት ተመሳሳይ ቀኖናት

665· ከዚሁ ገጽ 211

666· ከዚሁ ገጽ 213

667· Ludolphus: Commentarius... ገጽ 30—333

668. Catalogus Raisonè Des Mss. Ethiopiennes Apartenannt a'Antoine d'Abbadie Paris 1859 ገጽ 76—77። F. Nau: Canons Des Apôtres D.T. C T II ዐምድ 1611። Funk: Apostolischen Constitutionen ገጽ 215—216

669 Kaί αι διαταγαί υμίν τοίς επισκόποις δι 'εμού κλημέντος εν οκτώ βιβλίοις προσεφωνημέναι

ላይ እንደ ተመሠረተ የሰማል ።

እነዚህን ትእዛዛት እንደሚታወቀው አምስተኛ ስድስተኛ የትሩሎ ዐቢይ ሲኖዶስ አላጸደቃቸውም ቢሆንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ሲኖዶስ አትቀበለውም ።

ስለዚህ ለኢትዮጵያ ቤቷ ክርስቲያን እነዚህ ትእዛዛት በሲኖዶሱ ውሳኔ ተሠርዘዋል ብሎ ለመቀበል አይቻልም ቢሆንም ሐቁ ከላይ እንደተመለከተው በውስጣቸው በሰፈሩት ምሥጢራት ምክንያት በስፋት ሊሰራጩ አለመቻላቸው ነው[670] ይህ የችግሩ ንድፈ ሐሳባዊ ክፍሉ ነው ምክንያቱም ስምንት መጻሕፍት ሁነው የተጠቀሱት ቀኖናት የሐዋርያውያት ቀኖናት ሰነድን አይዙም ። በተቃራኒ ግን ከእነዚህ ትእዛዛት ሐዋርያት 8 መጻሕፍት — ሱርስጥ ስምንት ብሔረ ቀኖናት የተወለደ ሲሆን [671] ከዚህም ዐረቢ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት[672] እና ግብጥ ሰበዓቱ ብሔረቀኖት[673] ተወልደዋል ።

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነትን ከአገኙት 27 መጻሕፍት በተጨማሪ በጥቅል ሲኖዶስ ዘቅዱሳን አበዊን ሐዋርያት ወይም በእጭሩ ሲኖዶስ በሚል ርእስ 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ይገኛሉ ።

በዚህ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ወይም ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ የተቀነባበሩ ዘበእደ "ቀለሚንጠስ" በሚል አድራሻ የሚታወቁት ሁሉም ቀኖናት ታቅፈዋል ለምሳሌ 'ዲድስቅል ያ ራሱ አለመያዙ ቢታይም ግን እንደሚታወቀው የስድስት ትእዛዛት ሐዋርያውያት መጻሕፍት ምንጭነት መያዙ ይታያል ።

"በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን በይፋ የተወሰደ አቋም ባለመኖሩ ስለ እነዚህ ትእዛዛት ሐዋርያውያት ያሉት አስተሳሰቦች እንደ ተጋጩ ሆነው ነው የሚታዩት ።

3·8 የረስጠአ—የሐዋርያውያት ቀኖናት ይዘት

81 ሐዋርያውያት ቀኖናት እንደመጡባቸው 85 ቀኖናተ ሐዋርያት ስለ

670· ከዚሁ ገጽ 147

671· ከዚሁ ገጽ 206

672· ከዚሁ ገጽ 270

673· ከዚሁ ገጽ 209

ቤተ ክርስቲያን መልካም አስተዳደር ሥርዐት የሚናገሩ ቀኖናት ናቸው ። ምክንያቱም የቀኖናቱ አብዛኛው ክፍል በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ውጭ የምዕመናን አባላትንም አቋም ይመለከታል ማለትም እነዚህ ቀኖናት የቤተ ክርስቲያን ሕግ ሥርዐትን ይይዛሉ ····

ሌላ የእነዚህ ቀኖናት ግልጥ መታወቂያ በየቀኖናቱ ትእዛዝ የተመለከቱት አብዛኞቹ ርእሶች ጉዳዮች በራሳቸው ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው የተያዙ ሳይሆኑ ነገር ግን የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን አባላት ከእነዚህ ቀኖናት ጋር በተያያዘ ሥርዐት እንዴት እንደሚራመዱ የሚያመለክቱ ናቸው ለምሳሌ ስለ ፋሲካ የሚናገረው ቀኖና ፋሲካ እንዴት እንደሚከበር ሳይሆን ከአይሁዶች ጋር መከበር እንደማይገባ ነው የሚናገረው [674] ስለ ጾመ 40 የሚናገረው ቀኖና ራሱን እንደ ጾም አድርጎ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አባላት ባለመፈጸሙ ከክህነት መሻር ወይም በማውገዝ ቅጣት ዛፉ የግዴታ ጾም መሆኑን ይናገራል [675]

ስለዚህ እነዚህ ቀኖናት እንደ ሌሎች ሁሉም ቀኖናት ሁለተኛ ደረጃ ቀኖናተ ሕግ አስፈጻሚ ቀኖናተ ሕግ ተብለው የሚታወቁት ባሕርየ ቀኖናተ ሕግን ተከትለዋል ወይም በሌሎች ቀኖናተ ሕግ ተቀድመዋል ማለትን ያመለክታሉ ። እነዚህ ቀኖናተ ሕግ አሉታውያን ወይም አዎንታውያን ቀኖናተ ሕግ ሊሆኑ ይችላሉ ለምሳሌ ፋሲካን ከአይሁድ ጋር አብሮ ማክበርን መከልከል የፋሲካ በዓል መከበርን የሚደነግግ ሕግ አለ ማለት ነው ይህም ፋሲካን ለማክበር ጾመ 40ን የሚያዝ ሕግ ቀድም ተደንግጓል ማለት ነው ።

በተቃራኒው የአንድ አንድ ቀኖናት ድንጋጌዎች ጉዳዮችን በራሳቸው የሚወስኑ መጀመሪያ ደረጃ ቀኖናተ ሕግ–መሠረታውያን ቀኖናተ ሕግ ባሕርይን ይዘው የሚገኙ ሁነው ሊገኙ ይችላሉ ለምሳሌ በሁለት ኤጲስቀጶሳት ካልሆነ በስተቀር የኤጲስቆጶሳት ሹመት አለመፈቀድ [676] ስለዚህ መሠረታዊ ቀኖና ሕግ ተጥሏል ነው የሚባለው ። የእነዚህ ቀኖናት ይዘት በፍትሐ ነገሥት የተጠቀሱትን ትእዛዛት ከሚመስሏቸው የግሪኩ ቋንቋ 85 ቀኖናት ድንጋጌዎች ጋር በማነጻጸር ይመረምራል ።

674· 81= ቀኖና 7፡85 = ቀኖና 7

675· 81= ቀኖና 64·65፡85 = ቀኖና 69·70

676· 81= ቀኖና 1 2·4·5 80 ··········

በመሠረቱ የሐዋርያውያት ቀኖናት ይዘት በሦስት ክፍሎች ተከፍሎ መታየት ይችላል

1· ክፍል አንድ ፡ ስለ አሠረ ክህነት
2· ክፍል ሁለት ፡ ስለ ካህናትም ሆነ ምዕመናን ግዴታዎች
3· ክፍል ሦስት፡ ስለ ቅዱስ ቁርባን

1· ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አሠረ ክህነት [677] መመዘኛዎች አለታውያን [678] ስለ ተግባራት ጠባይና ሥነምግባር [679] ስለ ግዴታዎች (መወሰን ወይም መከልከል) [680] ስለ ድቀት [681]
2· ስለ ምዕመናን ተግባራትና ሥነምግባር [683] እና ግዴታዎች መወሰን ወይም መከልከል [684]
3· ስለ ቤተ ክርስቲያንና ምሥጢራተ ቁርባን ስለ ሥጋ ወደሙ [685] ስለ ጵርሰፎራ [686] ስለ ጥምቀት [687] ስለ ካህናት ጋብቻ [688] ስለ ፋሲካ [689] ስለ ዓርብና ረቡዕ ፡ ስለ 40 ጾም [690] ስለ መጻሕፍተ ሐሰት [691] ስለ ቀኖናውያት መጻሕፍት [692]

677· ቀኖና 1·2 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·2፡ 6·1, 7·2, 3·81
678· ቀኖና 36·61·78·81·84· = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 5·16, 2,7.2
679· ቀኖና 17,18,34,38·4041·83·84 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·3 6·4· 8·3
680· ቀኖና 6·7 10·11·12·14·15·16·19·20·22·23·25·26·27·28·29·31·32·33·35·39·42·44·45·46·47·51·57·58·59·62·63·64·65·66·67·69·72·73·83·84· = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·3
681· ቀኖና 28 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6·3·6·5,7·5
682· ቀኖና 33 44·56· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6·3,7·4
683· ቀኖና 43· 4857·63·65·66·72·84· = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11·1.5·11
684· ቀኖና ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11·2·3
685· ቀኖና 8,9 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 12
686· ቀኖና 3·4 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13
687· ቀኖና 49·50 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5
688· ቀኖና 5·16,17,18,25 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ
689· ቀኖና 7 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15
690· ቀኖና 49 70 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2·2
691· ቀኖና 85 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2·1
692· ቀኖና 74·75 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5

4. ረስጠብ — ቀለሚንጦስ ዳግም

ቀኖናት ሐዋርያውያተ ዘፍትሐ ነገሥት የሚታወቁበት - የሚጠቀሱበት ምኅፃረ ቃል “ረስጠብ” ቀለሚንጦስ ዳግም ሲሆን በግብጽና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት አጅግ የታወቁትን 127 ቀኖናት የመጀመሪያውን ክፍል 71 ቀኖናትን ወይም ባሳዲቅ ትርጉም 78 ቀኖናትን ይዞ የሚገኘው ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ወደፊት እንደምንመለከተው ረስጠጅ (ቀለሚንጦስ ግልስ) በሚል ምኅፃረ ቃል የሚጠቀሱትን 56 ሐዋርያውት ቀኖናትን ወይም በሳዲቅ ትርጉም 79 ቀኖናትን ይዞ የሚገኘው ክፍል ነው ።

127 ቀኖናት በመቅደማቸው የሚከተለውን ዐረብተ ነገር በቅድሚያ በማስፈር በሲኖዶስ የመጀመሪያውን ስፍራ ይይዛሉ ።

“ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለማጠናከርና በሁሉም ሁኔታዎች የሚነሱ ችግሮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በቀላሉና በፍጥነት ለመፍታት የሚያስችል ምእላደ ቀኖናት ሐዋርያውያት ከመኖር አስፈላጊነት ዓላማ የተነሳ በእግዚአብሔር ረዳትነትና በኦርቶዶክስ እምነት የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶስን ዝግጅት እናስቀድማለን” [693]

ስለዚህ በሲኖዶስ ከተያዙት ቀኖናት መካከል 71 ቀኖናት በቅድሚያ ሰፍረው ይገኛሉ ሆኖም በተለያዩ አርእስት ተቀርጸው - ተገኝተው ይታያል ስለዚህ ቀኖናተ ቤተ ክርስቲያንን ለማጉልበት በሐዋርያት የታወጀ “ሲኖዶስ” “ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት” [694] ወይም “ስለ ቤተክርስቲያን አደረጃጀት በቀለሚንጦስ የተዘጋጁ 71 ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት” [695] የሚሉ የተለያዩ ርእሶችን ይዘው ሲገኙ 56 ቀኖናት ደግሞ የሲኖዶስ ሁለተኛው ክፍል “በቀለሚንጦስ እጅ በሐዋርያት የተሰጠ ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን” “ወይም ውሱናት በሐዋርያት ጽሑፋት በቀለሚንጦስ 56 ቀኖናት ዘቤተ ክርስቲያን” ወይም በአጭሩ የመጀመሪያዎቹ 71 ቀኖናት “ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት” canones ecclesiastici [696] ሁለተናዎቹ “ቀኖናት ሐዋርያውያት” canones Apostolici ተብለው ይጠራሉ

693. Ms. Borgio Etiopico ገጽ 5 ሲኖዶስ ገጽ 1–40
694. Ms. Borgio Etiopico ገጽ 5 ሲኖዶስ ገጽ 41 48
695. Ms. Borgio Ethopilo ገጽ 7 ሲኖዶስ ገጽ 49
696. Ms. Arabe de Paris No 251 ገጽ 66

በመሠረቱ የሐዋርያውያት ቀኖናት ይዘት በሦስት ክፍሎች ተከፍሎ መታየት ይችላል

1· ክፍል አንድ ፡ ስለ አሠረ ክህነት
2· ክፍል ሁለት ፡ ስለ ካህናትም ሆነ ምዕመናን ግዴታዎች
3· ክፍል ሦስት፡ ስለ ቅዱስ ቁርባን

1· ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አሠረ ክህነት [677] መመዘኛዎች አሉታውያን [678] ስለ ተግባራት ጠባይና ሥነምግባር [679] ስለ ግዴታዎች (መወሰን ወይም መከልከል) [680] ስለ ድቀት [681]
2· ስለ ምዕመናን ተግባራትና ሥነምግባር [683] እና ግዴታዎች መወሰን ወይም መከልከል [684]
3· ስለ ቤተ ክርስቲያንና ምሥጢራተ ቁርባን ስለ ሥጋ ወደሙ [685] ስለ ጵርሰፎራ [686] ስለ ጥምቀት [687] ስለ ካህናት ጋብቻ [688] ስለ ፋሲካ [689] ስለ ዓርብና ረቡዕ ፡ ስለ 40 ጾም [690] ስለ መጻሕፍተ ሐሰት [691] ስለ ቀኖናውየት መጻሕፍት [692]

677· ቀኖና 1·2 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·2፡ 6·1, 7·2, 3·81
678· ቀኖና 36·61·78·81·84· = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 5·16, 2,7,2
679· ቀኖና 17,18,34,38·4041·83·84 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·3 6·4· 8·3
680· ቀኖና 6·7 10·11·12·14·15·16·19·20·22·23·25·26·27·28·29·31·32·33·35·39·42·44·45·46·47·51·57·58·59·62·63·64·65·66·67·69·72·73·83·84· = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·3
681· ቀኖና 28 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6·3·6·5,7·5
682· ቀኖና 33 44·56· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6·3,7·4
683· ቀኖና 43· 4857·63·65·66·72·84· = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11·1,5·11
684· ቀኖና ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11·2·3
685· ቀኖና 8,9 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 12
686· ቀኖና 3·4 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13
687· ቀኖና 49·50 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5
688· ቀኖና 5·16,17,18,25 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ
689· ቀኖና 7 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15
690· ቀኖና 49 70 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2·2
691· ቀኖና 85 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2፡1
692· ቀኖና 74·75 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5

4. ረስጠብ — ቀለሚንጦስ ዳግም

ቀኖናት ሐዋርያውያተ በፍትሐ ነገሥት የሚታወቁበት፦ የሚጠቀሱበት ምኅፃረ ቃል "ረስጠብ" ቀለሚንጦስ ዳግም ሲሆን በግብጽና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ለጅግ የታወቁትን 127 ቀኖናት የመጀመሪያውን ክፍል 71 ቀኖናትን ወይም ባሳዲቅ ትርጉም 78 ቀኖናትን ይዞ የሚገኘው ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ወደፊት እንደምንመለከተው ረስጠጅ (ቀለሚንጦስ ሣልስ) በሚል ምኅፃረ ቃል የሚጠቀሱትን 56 ሐዋርያውት ቀኖናትን ወይም በሳዲቅ ትርጉም 79 ቀኖናትን ይዞ የሚገኘው ክፍል ነው ።

127 ቀኖናት በመቅደማቸው የሚከተለውን ዐረፍተ ነገር በቅድሚያ በማስፈር በሲኖዶስ የመጀመሪያውን ስፍራ ይይዛሉ ።

"ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለማጠናከርና በሁሉም ሁኔታዎች የሚነሱ ችግሮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በቀላሉና በፍጥነት ለመፍታት የሚያስችል ምእላደ ቀኖናት ሐዋርያውያት ከመኖር አስፈላጊነት ዓላማ የተነሳ በእግዚአብሔር ረዳትነትና በኦርቶዶክስ እምነት የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶስን ዝግጅት እናስቀድማለን" [693]

ስለዚህ በሲኖዶስ ከተያዙት ቀኖናት መካከል 71 ቀኖናት በቅድሚያ ሰፍረው ይገኛሉ ሆኖም በተለያዩ አርእስት ተቀርጸው – ተገኝተው ይታያል ስለዚህ ቀኖናተ ቤተ ክርስቲያንን ለማጉልበት በሐዋርያት የታወጀ "ሲኖዶስ" "ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት" [694] ወይም "ስለ ቤተክርስቲያን አደረጃጀት በቀለሚንጦስ የተዘጋጁ 71 ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት" [695] የሚሉ የተለያዩ ርእሶችን ይዘው ሲገኙ 56 ቀኖናት ደግሞ የሲኖዶስ ሁለተኛው ክፍል "በቀለሚንጦስ እጅ በሐዋርያት የተሰጠ ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲየን" "ወይም ውሱናት በሐዋርያት ጽሑፋት በቀለሚንጦስ 56 ቀኖናት ዘቤተ ክርስቲያን" ወይም በአጭሩ የመጀመሪያዎቹ 71 ቀኖናት "ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት" canones ecclesiastici [696] ሁለተናዎቹ "ቀኖናት ሐዋርያውያት" canones Apostolici ተብለው ይጠራሉ

693. Ms. Borgio Etiopico ገጽ 5 ሲኖዶስ ገጽ 1–40
694. Ms. Borgio Etiopico ገጽ 5 ሲኖዶስ ገጽ 41–48
695. Ms. Borgio Ethopilo ገጽ 7 ሲኖዶስ ገጽ 49
696. Ms. Arabe de Paris No 251 ገጽ 66

በየአጋጣሚዎች ከላይ እንደተባለው እነዚህ ቀኖናት የሐዋርያት ሥራዎች አይደሉም ወይም ከአንድ ስም የለሽ አዘጋጅ አልመጡም ነገር ግን ቀኖናዊና ሥነ ቅዳሴያዊ ይዘት ከአለባቸው ልዩ ልዩ ሥራዎች ተወስዶ የተቀነባባረ ሥራ ውጤቶች ናቸው የሚለው አመለካከት ጉልቶ ይታያል። ስለዚህ ቀኖናቱ የሚመጡባቸው ምንጮችን በመከተል በሦስቱ ክፍሎች ይከፈላሉ ።

1· የ71 ቀኖናት የመጀመሪያው ክፍል 20 ቀኖናትን = 1 – 20 ወይም 23 (1 23) የያዘው ክፍል ሲሆን እነዚህ ቀኖናት ከቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት Apostolische kirchenordnung or canones apostolorum ecclesiastiastici የመጡ በመሆናቸው ይደገፋሉ [697]

2· ሁለተኛው ክፍል 26 ቀኖናትን 21–47 ወይም 32 = 31–63 ቀኖናትን ሲይዝ ይህም 32 ቀኖናት ያሉትን ግብጣዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ Aegyptische Kirchenordnung orConstitutiones ecclessiae aegyptiaca ይይዛል [698]

3· ሶስተኛው ክፍል 23 = 48–71 ወይም 16 = 63–78 ቀኖናት የያዘው ከሐዋርያውት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች የመጣ– የተወሰደ ክፍል ነው ። ብዙ ጊዜ የሁለቱ ክፍሎች ቀኖናት ድንጋጌዎችን ይደጋግማል ።

ስለዚህም እነዚህ ቀኖናት የመጡባቸው ምንጮች አንድ በአንድ መመርመራቸው አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል ።

4.1. ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት

ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቀዱሳን ሐዋርያተ [699] በ20 ወይም 30 ቀኖናት ተሰባስበው የተቀረጹ ነገር ግን በጥንት የቤተ ክርስቲያን ሕግ [700] ከፍተኛ ትርጉም ያለውን በተለይ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በሱርስጥ ወይም በዐረብኛ ቀለሚንጦሳዊ ብሔረ ቀኖናት ወይም በግብጣዊ ብሔረ ቀኖናት የተያዘውን ሥራ ይይዛሉ [701]

697· ከዚሁ ገጽ 168–181

698· ከዚሁ ገጽ 181–196

699· Funk, Doctrina Duodecim Apostolorum T.liv-lv

700· A. Χριστοφιλοπούλους Ελληνικόν Εκκλησιαστικόν Δίκαιον ገጽ 89

701· ከዚሁ ገጽ 106–210

4.1.1 ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት የተጻፉበት ቦታና ዘመን

ሀ· ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት የተጻፉበት ቦታ ግብፅ [702] ወይም ሶርያ [703] እንደነበረ ይጠቀሳል ። ቢሆንም እውነቱ እነዚህ ቀኖናት የተጻፉበት ቦታ ምንም ቢሆን መካከለኛው ምሥራቅ ነው። ምክንያቱም ሁሉም ማለት ይቻላል ስም አልባዎች ሰነዶች ወይም መስማተ ሐዋርያውያን ሥራዎች ማለትም የሐዋርያት ሳይሆን በለውር – በስም ለቅዱሳን ሐዋርያት በታወቁ ምክንያቶች የተሰጡ ሥራዎች የተጻፉበት አካባቢ ነው [704] ማለትም ትምህርት ዘ 12 ሐዋርያት [705] "ዲድስቅልያ ዘሐዋርያት ፡ "ሐዋርያውያት ትእዛዛት" [706] "85 ሐዋርያውያት ቀኖናት" [707] ፡ ወዘተ· (100–400)

ለ· ቀኖናት ቤተክርስቲያውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት የተጻፉበት ዘመንን የሚመለከቱ የሐሳብ ልዩነቶች ይታያሉ ማለት እነዚህ የተጻፉበት ዘመን በ2ኛውና 4ኛው ምዕተ ዓመታት መካከል ይወድቃል ይህም ምክንያቱም ከታች እንደተመለከተው እነዚህ ቀኖናት በአንድ በኩል በከፊል ከትምህርተ 12 ሐዋርያት 2ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ (160) ሥራ [708] ከባርናባስ መልዕክት ይህም የዚሁ ጊዜ ሥራ [709] ተመርኩዘው እንደተቀረጹ በሌላ በኩል ደግሞ የ4ኛው ምዕተ ዓመት ሥራ ከሆኑት

ሐዋርያውት ትእዛዛት 7ኛው መጽሐፍ ጋር ይመሳሰላሉ ነገር ግን

702 O.Bardenhewer; Geschichte der Ältkirchlichen literatur T.1 ገጽ 782
A.Krawutzky: Uber das Ältkirchlichen unterrechtsbuch, die zwei wege oder die entscheidung des petrus T.Q. T.LXIV 1882 359-44 Quasten: Patrology T.1I. ገጽ 119

703 P.-P.Périer,127 canons des apotres P.O.T. 86 ገጽ 554 M.Achelis: die apostolischen Kirchenordnung., Realenzyclopädie I ገጽ 739

704· ከዚሁ ገጽ 149–152

705· ስለ ትምህርተ 12 ሐዋርያት ከዚሁ ገጽ 113–136

706· ስለ ዲድስቅልያ ከዚሁ ገጽ 219–239

707· ስለ ሐዋርያውያት ቀኖናት ከዚሁ ገጽ 137–166

708· ስለ 85 ቀኖናት ሐዋርያውያት F.Nua: canons des apôtres D.T.C.T. 112 ገጽ 1614

709· ከዚሁ ገጽ 177

የተለያዩ ጊዜያት በመታሰባቸው ትክክለኛ ጊዜን ማመልከት አልተቻለም Bardenhewer እነዚህ ቀኖናት የተጻፉበት ዘመን 3ኛውን ዘመን ወይም 4ኛውን ምዕተ ዓመት ያስቀምጣል [710] A.Harnack የእነዚህ ቀኖናተ የጽሕፈት ዘመን 300–350 መሆኑን ይገምታል [711] Funk ይህ ጊዜ በሦስተኛው ምዕተ ዓመት ውስጥ እንደሆነ ይናገራል [712] እንደ Achelis እነዚህ ቀኖናት በትምህርተ 12 ሐዋርያት እና በቀኖናት ሐዋርያውያት መካከል ማለት 140–160 መካከል ተጽፈዋል ። [713]

ስለዚህም ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት የተጻፉበት ዘመን በ3ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ሊሆን ይችላል ወደፊት እንደምናመለክተው ከላይ በምንጭነት የተመለከቱት ሥራዎች ትምህርተ 12 ሐዋርያት፡ ውልዕክተ በርናባስ ፣ የቤተ ክህነት ሁኔታና የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ሲታዩ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የ2ኛው ምዕተ ዓመት ሥራዎች ሲሆኑ የተከተሉት ሁለቱ የ2ኛውና የ3ኛው ምዕተ ዓመት ሥራዎች ነበሩ

4.1.2. ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት የተጻፉበት ቋንቋ

ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት በመጀመሪያ የተጻፉበት ቋንቋ ግሪክ ቋንቋ – ልሳነ ጽርእ ነው ምክንያቱም የእነዚህ ቀኖናት መነሻ ሰነድ በሙሉ ወይም በከፊል በዚህ ቋንቋ አሁንም ይገኛል።

ሙሉ ሰነዱ – ቀኖናት በሙሉ ቅርጻቸው "ድንጋጌዎች ዘበእደ ቀለሚንጦስ ወቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት" የሚል ርእስን ይዞ በቪዬና በሚገኝ አንድ የ14ኛው ምዕተ ዓመት የእጅ ጽሑፍ ተጠብቆ ተገኝቷል[714]

710. O.Bardenhewer. Geschichte Der Ältchristlichen Literatur, T.1 ገጽ 82, Bardnhewer Patrologie, T.II ገጽ .141. Batifol: Anciennes Litteratures Chrétiennes, la Litterature Greque, 1817 ገጽ 74,

711. A.Harnack Geschichte Der Ältkirchlichen Literatur, Die Ueberlieferung T.U. 1886 T.II ገጽ 214–219፣ T.I 1893 ገጽ 463, T.II FASC. 1904, ገጽ 485, Die Chronologie, ገጽ 532·

712. H.Funk, Kirchengeschichte Abhandlungen und Untersuchungen 1899 T.II ገጽ 236–251፣ Funk, Doctrina Duodecim Apostolorum ገጽ · Liv-lv, Funk. Didaskalia ... T.II ገጽ .XLII-XLIV

713. Achelis: Apostolischen Kirchenordnung R.E. ገጽ 733

ይህም የእጅ ጽሑፍ–ሰነድ በመጀመሪያው J.Bickel, Apostolischen Kirchenordnung በሚል ርእስ በ1863 አሳትሞ ሲገኝ[715] ከዚያም በኋላ በተነሱ ጸሐፍት በጥቅም ላይ ሊውል ችሏል [716]

በቪዬና የተገኘው የእጅ ጽሑፍ – ሰነድ እንደገና በ1854 በየDe Lagarde መታተሙ ሲታወቅ [717] አሁንም በዚሁ ጸሐፊ "ድንጋጌዎች ዘበእደ ቀለሚንጦስና ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት" ከግብጥ ትርጉም ጋር ሊታተሙ ችለዋል [718]

በሌላ በኩል ርእሱና የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች የማይገኙበትን የቀኖናቱ የመጀመሪያውን ክፍል (ቀኖናት 4–14) የያዘ አንድ የ14ኛ ምዕተ ዓመት የእጅ ጽሑፍ "ምኅፃረ ምልዓተ ትምህርት ዘሐዋርያት" በሚል ርእሰ በኦቶቢያን ቤተ መጻሕፍት – Codex Ottobianus ይገኛል። [719]· በCodex Ottobianus የሚገኘው የእጅ ጽሑፍ በተገኘበት ርእሱ በካርዲናል Pitra በ1864 የታተመ ሲሆን [720] ይህም Codex Ottobianus 14-14 ቀኖናት ይዞ የሚገኘው ሰነድ የተገኙበትን ብዙ ለውጦችን ጨምሮ በመስኮብ ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ መጻሕፍት በሚገኝ የ10ኛው ምዕተ ዓመት የእጅ ጽሑፍ መገኘቱ ተረጋግጧል [721] ።
ይህንም የእጅ ጽሑፍ "እምነ ትእዛዛት ዘቅዱሳን ሐዋርያት" ከሚፈ ቅርጽ ጋር በGebhardt, Harnack እና Zohn 1886 ታትሞ ተሰራጭቷል [722] ከዚያም በአንድ ወይም በሌላ ቅርጽ–መልክ የእነዚህ ቀኖናት ሕትመቶች በልዩ ልዩ የታሪክ ጸሐፍትና የቀኖና ሊቃውንት ተከታትለ

714. Codex vindonensis Hist. Graec. Olim 45 N.7.

715. J.W.Bickell. Geschichte des Kirchenrechts, T.I ገጽ .107 - 132.

716. Nau. Les Canons des Apôtres. D.T.C.T.II ዐምድ . 1613

717. P. De Lagarde, Reliquiae .... Graec /4 - 79.

718. P. De Lagarde, Analecta Anteneceaena. Bunnen 1854 T.II .451-468.

719. Διδαχή τῶν Ἀποστόλων Codex Ottobianus No 408. Rendel Haris, the Teaching of the Apostles. London, 1887. .21.

720. Pitra, Juris Ecclesiastici Graecorum Historia et Manumenta. Rome. 1864.T.I . 77 -86

721. Codex Mosquensis, Bibl. St. Synodi - Codex Graec. N. 124.

722. Gebhardt. Harnack and Zohn. Patrum. Apostolorum Opera 2ኛ ሕትመት 18 FASC. T.I ክፍል II ገጽ XXIX -XXXI.

ዋል 1886 Hilgenefeld [723] 1883 ፊላታወስ[724] ቀኖናቱ የመጨረሻ ቅርጻቸውን ሊይዙ ይችሉ ዘንድ "Die lehr der zwnolf" apostel" በሚል ርእስ በ1884 Harnack [725] Funk: canones apostolorum eccesiastici በሚል ርእስ በመጨረሻም TH.scherman በ1903 በትምህርተ 12 ሐዋርያት ላይ እንደተመሠረተና በብዙ የእጅ ጽሑፎች ርም መስኮብ ፓሪስ እና በመጀመሪያ የPitra ቀጥሎም Apostolischen kirchenordnung በሚል ርእስ የHarnack ትርጉሞች የተገኘውን የቀኖናቱ የመጀመሪያው ክፍል 1–12 (ግሪክ 3 14) አሳተመ [727]

4.1.3. ትርጉሞች

4.1.3.1 የቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ላቲን – ሮማይስጥ ትርጉም

ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ቀደም ብለው በ5ኛውና በ6ኛው ምዕተ ዓመት መካከል ከግሪክ ቋንቋ (ልሳነ ጽርእ) ወደ ላቲን ሮማይስጥ መተርጐማቸው ታውቋል [728] ቢሆንም የዚህ ላቲን ትርጉም ሙሉ ሰነዱ አልተገኘም ። ስለዚህ 13–20 (ግሪክ 18–30) ቀኖናት Palimpest ms. በተገኘው የ6ኛው ምዕተ ዓመት የእጅ ጽሑፍ ሰነድ በ1900 በHauler ሊታተሙ ችለዋል [729] Hauler ይህ የእጅ ጽሑፍ

723. Hilgenfeld. Novum Testamentum Extra Canonum. Receptum Fasc. V. Lipsiae 1886² ገጽ 96-106.

724. Φιλοθέου, Διδαχή τών 12 αποστόλων, Κνω/πολιν 1883 ገጽ οβ: - ογ: Hilengenfeld ሕትመት ድጋሚ

725. A.Harnack, Die Lehr Der Zwölf Apostel. : T.U.T.II 1886. FASC. I ገጽ 255 – 237.

726. Funk, Doctrina Duodecim Apostolorum. Canones Apostolorum Ecclesiastici ac Reliquiae duabusiis TÜbingen 1887 ገጽ I-III, LIII-LVIII 50-73.

727. TH. Schermann, Eine Elfapostelmoral Oder Die X-Rezension Der "Abeiden Wege" 1903, Münich: VieröFfentlichungen Aus Dem Kirchen Historishen Seminar. Fasc, 2. N. 2 Die Allgemeine Kirchenordnung, Frühchristliche Liturgien und Kirchliche Überlieferung. T.I.S. G.K.A. 1914 ገጽ 12-34

728. F.Nau: les canons de apötres D.T.C.T II ገጽ 1613

729. E. Hauler: didascalia apostolorum fragmemta veronensia latina accedent canonum qui decuntur apostolorum et aegyptiorum reliquiae. Leipzig. fasc.I ገጽ 91-101

የአንድ የጥንት የእጅ ጽሑፍ ግልባጩ እንደነበር ለዚህም የእነዚህ ቀኖናት ተርጓሚ ከኢሮኒሞስ የተደረገውን የቅዱሳት መጽሐፍት ትርጉም ይጠቅሳልና [730]

ስለዚህም በዚህ ሰው የተገለጸው መደምደሚያ "Quare Codex Graecus, Ex quo Archetypus Latinus Fluxit Certe Exeunte Vel potius Medio Quarto Saeculo Antiquior Putandus Est"[711]

4.1.3.2 የቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ሱርስጥ ትርጉም

የሱርስጥ ቀላሚንጦሳዊ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት አንድን ክፍል የያዙትን ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ሱርስጥ ትርጉም [732] ምን ጊዜም ቢሆን ከእናቱ ግሪክ ቋንቋ እንደ ተደረገ ይታመናል ።

ስለዚህ የእነዚህ ቀኖናት ተርጓሚ በ687 ዓ·ም ያዕቆብ ትሑት የተባለው ሰው እንደነበርም ይታወቃል ምክንያቱም በግሪኮች ዘመን አቆጣጠር 998 ዓመት (687) በያዕቆብ ትሑት የተመለሰው የቀለሚንጦስ 2ኛው መጽሐፍ መጨረሻ 3ኛ መጽሐፈ ቀለሚንጦስ "ትምህርተ 12 ሐዋርያት–Malfonouta በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሰላምታ ይደርሳቸው" በሚል ርእስ በሮሚ በሚገኝ አንድ የእጅ ጽሑፍ ሊተላለፍ ችሏልና [733] የሱርስጥ ትርጉም ሰነድ ሙሉ ቃል ሲያያዝ መጥቷል ለምሳሌ Rahmani, doctrina duodecim apostolorum በሚል ርእስ[714] ባመለከተውና በሮሜና possoul በሚገኘው የእጅ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል ይህ የእጅ ጽሑፍ የዚህ የሱርጥስ ትርጉም 3–14 ቀኖናትን ሳሳተመው Delagarde እንዳልታወቀ ይገመታል[735] Baumastark እነዚህን ቀኖናት ከጀርመንኛ ትርጉም ጋር እንደአሳተመ ይታወቃል[736]

730. F. Nau, canons des Apötres D.T.C. tII' ገጽ 1613

731. E- Hauler didascalia Apostolorum.T.VIII- ገጽ 92T101

732. ስለ ሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ከዚሁ ገጽ

733. Rahamani testamentum domini notri Jesu christi 1899 ገጽ XIV

734. Rahmani: Testamentum ... ገጽ X.

7:5. P.de Lagarde: Reliquiae ... Graec. ገጽ 19–23.

736. A: Baumstark, Στρωμάτιον Αρχαιολογικόν Internationale Kongress Für Christliche Archaeologie ... rome 1906 ገጽ 15-31

4.1.3.3. የቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቀዱሳት ሐዋርያትግብጥ — ቅብጥ ትርጉም

ቀኖናት ቤተ ክርስቲናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት በሁለት ግብጣውያን ቋንቋዎች ሳዲቅና መምፌቲቅ ትርጉም ተላልፈው መጥተዋል ። ሰዲቅ ግብጥ ትርጉም ከእናቱ ግሪክ የተደረገ መሆኑ ሲደገፍ መምፊቲቅ ትርጉም ግንደ ከግሪክ ቋንቋ ሰነድ ሳይሆን በዚህ ከሳዲቅ ትርጉም መሆኑ ይደገፋል [737] የእነዚህ ቀኖናት ሳዲቅ ትርጉም ሰነድ በእንግሊዘኛ ትርጉም ተተርጉሞ 1848 በ H. Tattam ሊታተም ሲችል [738] ቆይቶም በ1877]Ph. schaff እንደገና ታተሞ ተሰራጭቷል። [739]

4.1.3.4 የቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ዐረብኛ ትርጉም

ተያይዞ የመጣው የቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ዐረብኛ ትርጉም የተደረገው ከእናቱ ግሪክ ቋንቋ ሳይሆን ከሳዲቅ - ግብፕ ትርጉም መሆኑ ይታሰባል [740] የእነዚህ ቀኖናት ግብጥ ፥ ዐረብኛና ግእ፤ ትርጉም ሰነድ በ G.Horner በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ 1848 እንደ፥ ተመ መረዳት ተችሏል [741]

1.4.3.5. የቀኖናት ቤተ ክርስቲያነውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ግእዝ ትርጉም

የቀኖናት ቤተ ክርበቲያኑውያት ዘቀዱሳን ሐዋርያት ግእዝ ትርጉም ከግብጥ—ቅብጥ ሳይሆን ከዐረብኛው ትርጉም ሰነድ እንደሆነ ይታሰባል[742]

737. Lightfoot St. Element of Rome, Appendice ገጽ 466-478 P.De.Lagarde: Aegyptiaca ... ገጽ 239-248, De la Garde Reliquiae ... Grec ገጽ X.
738. H Tattam: the Apostolical Constitlutions or Canons of The Apostles in Coptic London 1848,
739. Ph. Schaff: The Oldest Church - Called The Teaching of The Twelf Apostles N.Y. 1877 ገጽ 249-257.
740. Lecercq: C.A.L. T.II .19.
741. G Horner: the statutes of the Apostles or Canons Ecclesiastici Edited With Translation And Correction From the Ethiopic and Arabic London 1904
742. I. Guidi: Il Canone Biblico Della Chiesa Copta. : Revue Biblique 1203 ገጽ 173.

ነገር ግን በአንድ ወቅት ከግብጥ—ቅብጥ ለመተርጐሙ የተገለጠ አመለካከት ነበር [743] ምክንያቱም የእነዚህ ቀኖናት ግእዝ ትርጉም ሰነድ ይዘት ከቅብጥ ትርጉም ሰነድ የበለጠ ምልዓትን ሲያሳይ ከዐረብኛው ትርጉም ሰነድ ግን ያነሰ ስፋትን ያመለክታልና ፡ የእነዚህ ቀኖናት ግእዝ ትርጉም ከላቲን(ሮማይስጥ)ትርጉም ጋር 1691 በLudolphus የታተመ ሲሆን[744] ቆይቶ ከእንግሊዝ ትርጉም ጋር በHorner ታትሟል[745]

4 2 የቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ምንጮችና ይዘት

ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት የተቀነባበሩባቸው ምንጮችን ዘሚመለከት የተለያዩ አመለካከቶች በመደጋገፍ ወይም በመለያየት ቀርበዋል ።

በመጀመሪያ በ1882 Krawutzcky እነዚህን ቀኖናት በጥልቀት በመመርመር የእነዚህ ቀኖናት ምንጮች "ሁለት መንገዶች"[746] በሚል ርእስ በጥንት ቤተ ክርስቲያን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አንድ ዓይነት መ፤ ጽሑፍ እንደነበር ገልጧል ። በዚህም መልክ በ1883 ይህ ሰነድ ተገኝቶ ባሌጺስ ቆጶስ ፊላታወስ ዘከርቢዮን የታተመው ትምህርተ 12 ሐዋርያት ማለት ነው[747] ነገር ግን ይህ ሁለት መንገዶች ሰነድ እየአንዳንዱ ሐዋርያት "አለ" የሚላቸውን ቃላት አልያዘም ። ስለዚህም ጸሐፊው ሁለት መንገዶች ሰነድን አቀነባብሮ ቃላቱን (አረፍተ ነገሮችን ለሐዋርያት አከፋፍሎ ማለትም እየአንዳንዱ ቀኖና "እገሌ ሐዋርያ አለ" በሚል አገላለጥ እንዲጀምር አድርጎ በመቅረጽ ከእነዚህ ሁለት መንገዶች ሌላ ጸሐፊው አብዛኛውን ጊዜ ሥነ ምግባራትንና ሕግን የሚመለከቱና በጥንት ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎቶች ላይ የነበሩ ግን በሐዋርያት

743. P.De Lagarde: Reliquiae ... Grace ገጽ X-XV. Lightfoot, St. Clement Of Rome Appendice ገጽ 469, Funk, Apost. Konstitutionen ገጽ 247.
744. Job. Ludulphus; Commentarius ... T.I. . 214-328.
745. Horner; Statutes 1904.
746. Hammer:Les péres Apostoliques,Paris 1907 ገጽ XXI Δέρβου, Εκκλησιαστική Γραμματολογία Τ Β. ገጽ 359 445
747 Krawutzcky. Über Das Unterrechtsbuch Die Zwei Wege T.O.T XIV ገጽ 1882 359 45

ስም[748] ወደ አንድ ስነድነት የተጠቃለሉ የተወሰኑ ቀኖናውያን ድንጋጌዎች በሐሳቡ ውስጥ ነበሩ ማለትም ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ። በሌላ በኩል Hilgenfeld የቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት የእስክርድርያው ቀለሚንጦስ ቅዱስ መጽሐፍ ሲል መጠቀሱን መነሻ ማስረጃ በማድረግ በ2ኛው ምዕተ ዓመት መጻፋቸውን ከሚደግፈው Duae viae vel judicium petri ጋር ስለመመሳሰላቸው ያስተምራል[749] ማለትም እነዚህን ሁለት መንገዶች የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናዊ ክፍል አድርጎ ይቆጥራቸዋል ። በቀለሚንጦስ ዘእስክንድርያ የተጠቀሰው መጽሐፍ የቅዱሳት መጻሐፍትን ክፍል ይይዛል እንደዚህም እንደመሆኑ መጠን ንዑሳነ ክርስቲያንን ማስተማርያ የሚጠቀሙበት ትምህርት ሁለት መንገዶች" በሚል ስያሜ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር ።

ስለዚህም እንደ Higenfeld ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ሌሎች ሳይሆኑ የRufinus duae Viae vel Judicium Petri ናቸው[750] P.de lagarde duae Viae ስለ ተጻፈበት ዘመን ሲስማማ ነገር ግን እነዚህ Duae Viae ከትምህርተ 12 ሐዋርያት ጋር መመሳሰልን አልተቀበለም ሆኖም ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያትን ማለትም ከላቲን ትርጉም ጋር ያሳተማቸውን እነዚህን ቀኖናት Duae vel Judicium Petri መሆናቸውን ይረዳል [751] ይህም አስተሳሰብ ከM.G vial Krüger ድጋፍን አግኝቷል [752] D.Bardenhewer ለነዚህም ቀኖናት የተሰጠው ርእስ ቆይቶ ጭማሪ መሆኑን ያሳያል በእውነቱ ግን Rufinus የተናገረላቸው ሁለት መንገዶች መሆናቸው ነው[753] ስለዚህ እነዚህ ቀኖናት አንድ ጊዜ ከትምህርተ 12 ሐዋርያት ሌላ ጊዜ ከDuae Viae ጋር ይምታታሉ ። መልዕክተ በርናባስንና ሁለት መንገዶችን አይወክሉም ። ግን ጸንተው የሚገኙት አስተሳሰቦች እነዚህ ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናው

748· Δέρβου, Εκκλησιαστική Γραμματολογία Τ.Β: ገጽ 650

749· A Hilgenfeld: Novum Testamentum. Extra canonem receptum 1866. FASC. T. IV. ገጽ 96 106 ወይም 1884 ገጽ 110 – 121

750· Rufinus: Commentarius In Symbolum Apostolorum C. 38. P.L. XXI

751· P.Delagarde: Analecta Antinecaena ሕትመት Bunnsen 1854 ገጽ 451 460

752· M.G - Krüger. Ältchristlichen literatur, Leipzig. 1895 ገጽ 224

753· D Bardenhewer: Les Peres Le Église ፈረንሳይኛ ትርጉም ገጽ 43 44

ያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ከላይ የተመለከቱትን ሰነዶች አይወክሉም ማለት ነው ። ሆኖም ግን ጸሐፊው ግብጻዊ ወይም ሶርያዊ እነዚህን ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ለማዘጋጀት እነዚህ የተጠቀሱትን ሥራዎችና ሌሎችንም ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያናት ምንጮች መጠቀም ችሏል [754] በተቃራኒው Harnak የቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት አቀናጅ እነዚህን ቀኖናት ሲያቀናጅ ከሚከተሉት አምስት[755] ምንጮች ላይ ተመርኩዞ እንደሆነ ይስማዋል[756]

1· መልዕክተ በርናባስ (መልዕክት መስመ በርናባስ)
2· ትምህርተ 12 ሐዋርየት (2ኛው ክፍለ ዘመን)
3· መዝገበ አስማተ ሐዋርያት
4· የቤተ ክህነት ሁኔታ
5· የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ

ስለዚህ ሁለቱ የመጀመሪያዎቹ መልዕክተ በርናባስ እና ትምህርተ 12 ሐዋርያት የቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት የመጀመሪያውን ክፍል (4–14) ሲይዙ 3ኛው መዝገበ አስማተ ሐዋርያት "ሐዋርያ አለ" የሚለውን ሐረግ—አንቀጽ ሲይይዝ አራተኛው የቤተ ክህነት ሁኔታ (የ3ኛው ዕምተ ዓመት ሥራ) ስለ ኤጲስ ቆጶስ[757] ስለ ካህናት [758] ስለ አናጉንስጢስ[759] ስለ ዲያቆናት [760] ስለ መበለታት[761] ምርጫ የሚያሳይ ሲሆን ለቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ሁለተኛው ክፍል (16–22) ምንጭ ሆኖ ያገለገለው ሰነድ ነው ። አምስተኛው የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ (የ2ኛው ክፍለ ዘመን ሥራ) ስለ ዲያናቆናት[762] እና

754· ከዚሁ ገጽ 137 148

755· Leclerq: canons apostoliques D.C.L.T. ዐምድ

756. A-Harnack:Die lehr der zwölf apostel T.U.TI.1-2 1884-1886. ገጽ 109 Harnak.The sources of the apostolic canones...ገጽ1 Harnack:Quellen der sog apostolischen kirchenordnung T.V.T. 2.5. 1886

757· ቀኖና 15 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5

758· ቀኖና 24 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6

759· ቀኖና 17 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8

760· ቀኖና 18 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 7

761· ቀኖና 19 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10

762· ቀኖና 22 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8

የቤተክርስቲያን አገለግሎቶች ፡ ስለ ቅዱሳት ምሥጢራት [765] የሚወሰን ምዕመናን[763] ተግበራት ዝርዝር የሚመለከተውና[764] ስለ ዲያቆናውያተ ፡ ውን ሰበተኛውን ክፍል (22–29) ይይዛል[766]

በሌላ በኩል Duchesne[767] Bardenhewer[768] Funk[769] Achelis[770] ሁለቱን ብቻ መልዕክተ በርናባስንና ትምህርተ ሐዋርያትን የመጀመሪያው 4–14 ቀኖናት እንደመነጩባቸው ሲቀበሉ በተቃራኒው A.Harnack ሁለት ሥነ ጽሑፎች ተብለው የተጠሩትን የቤተ ክህንትን ሁኔታዎችና የቤተ ክርስቲያንን ሁኔታዎች ለቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ምንጮች አደርጎ አልተቀበለውም ሆኖም አእምሮ ሊቀበለው የሚችለው እነዚህ ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት የመጀመሪያውን ክፍል (4–14) ቀኖናት በሚመለከት የተመረኮዙት ከትምህርተ 12 ሐዋርያት እንጂ ከመልዕክተ በርናባስ እንደአልሆነ በአንድ በኩል በሌላ በኩል ለትምህርተ ንዑሳን ክርስቲያን በዚሁ መልኩ የበለጠ ይጠቀሙባቸው የነበሩ በተወሰኑ ቀኖናውያን ድንጋጌዎች ላይ ተመሥርተው የተቀነባበሩ መሆናቸው ነው አስተሳሰቡ ።

በተለየ Funk የነዚህ ቀኖናት ጸሐፊ 16–30 ቀኖናትን በቤተ ክርስቲያን ይገኙ ከነበሩ ጥንታውያን ምንጮች እንደተበደረ ይደገፋል[771]

የቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ይዘት በሚመለከት የሚከተሉት ሁኔታዎች ይታያሉ ።

ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውት ዘቅዱሳን ሐዋርያት በአራት ክፍሎች

763· ቀኖና 23 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11
764· ቀኖና 24-28 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9
765· ቀኖና 25-26 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8
766.A. Harnack T.U 1886 T II ገጽ 214–219 Geschichte Ältchristlichen literatur, T.I. 1893 ገጽ 463 I.II 1904. ገጽ 485 (300 350)
767· DUCHESNE, Buletin CRITIQUE, 1886 T. VII ገጽ 367
768· O. Bardenhewer Patrogie T.II ገጽ 141
769· H. Funk: zur Apostellehr und Apostolischen kirchenordnung T.69 1887 ገጽ 276-306. 355-374. Funk: Die Apostolischen Kirchenordnung: Kirchengeschichte Abhandlung Und Untersuchungen T.II Padernborn 1899 ገጽ 236 261
770· Achelis, Apostolische Kirchenordnung R.E T.I ገጽ 730–734
771· Doctrina duodecim T. LIV–LV ገጽ 42 22

ይከፈላሉ ።

1· እነዚህ የመጀመሪያው ክፍል ሁለት ቀኖናትን 1–2 (በግሪክ እናቱ ሦስት 1 3) ይዞ የሚገኝ ሲሆን ከ12 ሐዋርያት የእያንዳንዱ ሐዋርያ ነም የሰፈረበትና ወንጌልን ለመስበክ ዓለምን ከመከፈላቸውና እጣ ወደ ወጣባቸው ቦታዎች ከመስመራቸው በፊት ሲኖዶስን አድርገው በክርስቶስ ትእዛዝ የሥነ ምግባር ቀኖናትን እንደ ደነገጉ የሚያመለክተውን መቅድም ይዟል[772] 12 ቀኖናትን (3 14) በግሪክ እናቱ ግን 11 ቀኖናትን (4 14) የያዘው የእነዚህ ቀኖናት ሁለተኛው ክፍል ሰነድ ሁለት መንገዶችን የሕይወት መንገድንና የሞት መንገድን ያወሳል ማለትም ሐዋርያት ክርስቲያኖች ሊከተሏቸው ስለሚገባቸው የሥነ ምግባራት ትእዛዛት ይናገራሉ ። 4 ቀኖናትን(15–19) በግሪኩ 8 ቀኖናትን (15–22) የያዘው የቀኖናቱ ሦስተኛው ክፍል ስለ ቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት በተለየ Harnack እንደተመለከተው ስለ ቤተ ክህነት ሁኔታዎች የሚናገሩ ድንጋጌዎችን ሲይዝ[773] በዚህም ሐዋርያት ስለ ኤጲስ ቆጶሳት[774] ቀሳውስት[775] አናጉኒስጢሳት [776] ዲያቆናት[777] ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ተልዕኮ የሚኖራቸው መበለቶች[778]

3 ቀኖናትን (20 22) በግሪክ እናቱ 7 ቀኖናትን (22 28) የያዘው የቀኖናቱ አራተኛው ክፍል ስለ ዲያቆናት[779] ስለ ምዕመናን ተግባራት[780] ስለ ሥጋ ወደሙ አፈጻጸም ሥርዐት[781] ስለ ሴቶች አገልግሎት በተለየ ችግረኞችን በመርዳት … [782] ።

አምስተኛው የቀኖናቱ ክፍል እንደ ግሪኩ እናት ሰነድ ልዩ ልዩ ትእዛዛትን የያዘ መደምደሚያን ይይዛል [783]

772· ቀኖና 1
773· ገጽ ከዚሁ ገጽ 110
774· ቀኖና 15 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·9 ግሪኩ ሰነድ 16
775· ቀኖና 16 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6 ግሪኩ ሰነድ 17 18
776· ቀኖና 17 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8 ግሪኩ ሰነድ 19
777· ቀኖና 18 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 7 ግሪኩ ሰነድ 20
778· ቀኖና 19 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8 ግሪኩ ሰነድ 21
779· ቀኖና 20 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 7 ግሪኩ ሰነድ 22
780· ቀኖና 21 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11 ግሪኩ ሰነድ 23
781· ቀኖና 22 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13·14 ግሪኩ ሰነድ 25
782· ቀኖና 23 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8 ግሪኩ ሰነድ 24—28
783· ቀኖና 24 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8 ግሪኩ ሰነድ 29 — 30

ከላይ እንደተባለው ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት እየአንዳንዱ ቀኖና በሚከተለው ዐረፍተ ነገር እንዲጀምር ተደርጎ ለ 12 ሐዋርያት ተከፍለዋል "እገሌ ሐዋርያ አለ" ብዙ ጊዜ "ልጄ ሆይ" ለምሳሌ ዮሐንስ ሁለት መንገዶች ናቸው አንዱ የሕይወትና አንዱ የሞት ··· አለ[784] ጴጥሮስ አለ ··· አትግደል[785]

"ፊልጶስ አለ ልጄ ጉጉ አትሁን"[786] ይህ ዓይነቱ አነጋገር በጥንታው ያን ሲኖዶሳትም ይገኛል ። መናፍቃንን ስለማጥመቅ በቅጵርያኖስ ዘመን በካርኪዶና[255] በተጠራው ሲኖዶስ ቅጵርያኖስ አለ ኤጲስ ቆጶሳት[787] ዩቪያኖስ የመናፍቃን ጥምቀት ያልተቀደሰና ሕገወጥ መሆኑን በመመከር እንደጻፈልኝ ሰሙ[787] ኬኪሎስ ዘቲስጳሊስ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ አንድ ጥምቀትን አውቃለሁ ከቤተክረስቲያን ውጭ ምንም አይኖርም አለ[788]

በቅርጣግና (ቀጠግ) ካርታየኒስ ሲኖዶስ እየአንዳንዱ ተካፋይ ኤጲስቆጶስ እገሌ ኤጴስ ቆጶስ ይህን አለ ብሎ የሚጀመር ቀኖናን ያሰፍራል ለምሳሌ አውሬሊዮስ "በእኛ ዘንድ ያለው ይህ ነው አለ"[789] ይህን የመሰለው ቅርፅ በግብጽና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት አዋልድ መጽሐፍትም ሲያያዝ መጥቷል ።

ምስጢረ ሰማይ ወምድር የሚባለው መጽሐፍ የሚጠቀሰው ሲሆን ይህ በግእዝ ቋንቋ የሚገኘው መጽሐፍ ከፈረንሳይኛ ትርጉም ጋር በJ. Perruchon ታትሞ ይገኛል[790] ። ሐዋርያት ዓለምን በእጣ በተከፋፈሉት ጊዜ ጴጥሮስ የማያምን ሰው አይድንም አለ··· [791] በመጨረሻ ሐዋርያት ዮሐንስን በማስቀደም በመነሳት በተራ ይናገራሉ[792] በዚህም መሠረት

784· ቀኖና 3 (ግሪኩ ሰነድ ቀኖና 4)
785· ቀኖና 5 (ግሪኩ ሰነድ ቀኖና 6)
786· ቀኖና 7 (ግሪኩ ሰነድ ቀኖና 8)
787· ቀኖና 2
788· ቀኖና 2
789· ቀኖና 1
790· J. Perruchon, libere des mystêres du ciel et de la terre. texte ethiopicn public et traduit. P.O.T.I ገ።8 86 88
791. E.Revillout,les apocryphes coptes;les evangiles des doule apôtres et de saint barthllemy publiė et traduit . P.O.T.II. ገጽ 133; 138. 154. F.Nau; canons des apôtres D.T.C.T. II ገጽ 614
792· ቀኖናት 2 — 3 (ግሪኩ ሰነድ 3 — 4)

ጴጥሮስ አንድ ጊዜ ጴጥሮስ[793] ሌላ ጊዜ ኬፋ[794] እየተባለ በሁለት ስሞች ተጠቅሷል ። ሆኖም ይዘቱ ክፍፍል እኩል አይደለም ምክንያቱም "አለ"ን በሚከተሉት ዝርዝሮች እንመለከተዋል ። ዮሐንስ አምስት ጊዜ[795] ማቴዎስ ሁለት ጊዜ[796] ጴጥሮስ አምስት ጊዜ[797] እንድርያስ ሦስት ጊዜ[798] ፊልጶስ ሦስት ጊዜ[799]

ስምኦን አንድ ጊዜ[800] ፡ ያዕቆብ አራት ጊዜ[801] ፡ ናትናኤል አንድ ጊዜ[802] ቶማስ አንድ ጊዜ[803] ኬፋ ሦስት ጊዜ[804] ፡ በርተሎሜዎስ አንድ ጊዜ[805]፤ያዕቆብ ዘይሁዳ አንድ ጊዜ[806] ። በግሪኩ ሰነድ መሠረትነት ላይ ከላይ የተመለከተው አስተያየት ሲታወስ ምክንያቱም በግእዝ ትርጉሙ የሚታየው ልዩነት ተደጋፊነት አለው ። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት የግሪኩ—እናቱ ሰነድ የያዛቸው 30 ቀኖናት በግእዝ ትርጉማቸው ወደ 22 ቀኖናት ተሰብስበዋልና ነው ። በዐረብኛ ደግሞ የበለጠ ወደ 20 ቀኖናት ተጨፍልቀዋል ።

4·2 ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ

ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ – Aegyptische kirchen-Ordnung or constitutiones ecclesiae aegyptiaca በመባል የሚታወቀው ሕገ ቤተክርስቲያን 32 ቀኖናትን ይዞ የተቀረጸ ሲሆን የ71 ቀኖናት (ረስጠብ) ሁለተኛው ክፍል ማለትም ከ21–47 ወይም በሳዲቅ ትርጉም 31–62 ያሉትን 27 ቀኖናት የያዘውን ሁለተኛውን ክፍል ይዞ የሚገኘው

793· ቀኖና 5 (ግሪኩ ሰነድ ቀኖና 6 ፣ 15 ፡ 16 ፡ 30)
794· ቀኖና 13 (ግሪኩ ሰነድ ቀኖና 13 21)
795· ቀኖና 3 ፣ 4 ፣ 17 ፣ 18 ፣ 25
796· ቀኖና 5 ፡ 20
797· ቀኖና 6 ፣ 15 ፡ 16 ፣ 25 ፣ 30
798· ቀኖና 7 ፣ 12 ፣ 24
799· ቀኖና 8 ፡ 23 ፡ 29
800· ቀኖና
801· ቀኖና 10 ፣ 19 ፣ 27 ፡ 28
802· ቀኖና 11
803· ቀኖና 12
804· ቀኖና 13 ፣ 21 ፣ 25
805· ቀኖና 14
806· ቀኖና 11

ክፍል ነው ። ይህም ሰነድ ለጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊ ሕግና ሥርዐተ ቅዳሴ ከፍተኛ ግምት ያለው ምንጭ ሆኖ ኑሯል[807] ግብፃዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ በመጀመሪያ ከአቡሊዲስ ሥራዎች በተለየ ከ3ኛው ምዕተ ዓመት አቡሊዲስ ሐውልት–መንበር ላይ ተቀርጾ ከሚገኘው "ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ" ተብሎ ከሚታወቀው አንድ ሥራው እንደተቀነባበረ ይገመታል ።

"ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ" በራሱ በአቡሊዲስ በ215–220 መካከል በጳጳስ ካሌስቶስ ሥር ከምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ተገልላ በእሱ መሪነት ሥር ለምትገኘው ቤተክርስቲያን ስለነበረ ዓላማ እንደተጻፈ ይታመናል ።

4·2·1 የግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ የተጻፈበት ቦታና ዘመን

ከላይ እንደተባለው ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ከ"ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ" ጋር ይመሳሰላል — አንድ ሆኖ ይታያል ። ስለዚህም ግብጻዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ በሌላ አነጋገር "ሐዋርያዊ ትውፊት" የተጻፈበት ዘመን በሮሜ በ215–220 መካከል እንደሆነ ይታመናል ። በዚህ ሁኔታ በጸሐፍትና ተመርማሪዎች መካከል ማለት ጸሐፊው አቡሊዲስ ፡ ዘመኑ 215—220 እና ቦታው ሮሜ ስለመሆኑ ልዩነት አልተፈጠረም ማለት ይቻላል ነገር ግን በተቃራኒው ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ የሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስን ሌላ ስያሜን አይዝም ። ስለዚህም ግብጻዊ ቤተክርስቲያን ትእዛዝ ራሱ በ215—220 በሮም በአቡሊዲስ የተጻፈው ሐዋርያዊ ትውፊት አይደለም ነገር ግን ግብጻዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ ከሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ ላይ ተመሥርቶ እንደገና የተቀነባበረ ማለትም በአንድ ቃል ግብጻዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ አዲስ ከተፈጠሩት – ከተከሰቱት ቀኖናውያን ኑምልኮታውያንና ሥነ ቅዳሴያዊያን ሁኔታዎች ጋር

ዘመጣጣም የዳበረና የተቀነባበረ የሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስን አዲስ ቅርጽ ይዞ የሚገኝ የቤተክርስቲያን ሕይወት እድገት ውጤት ነው ። Schawrtz "ሐዋርያዊ ትውፊት" የሚል ርእስን ይዞ በተገኘው

807. Pöchl, Geschichte Kirchenrechts Zweite erweiterte aufläge: wien TII ገጽ

ሐውልት እንደ ተገለጠው በቤተክርስቲያናውያት ቀኖናት–ልምዶች የተመለከተው ግን የጠፋው የአቡሊዲስ ሥራ በግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ታቅፎ የተገኘ ለመሆኑ ያለውን አስተያየት አስፍሯል[808]

ስለዚህ ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ሰፋ ባለበት መልኩ–ቅርጹ ጸሐፊው አዘጋጁ የሐዋርያዊ ትውፊት ሰነድን እንደገና ዘማቀነባበር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ነገር ግን እየአደረ የተፈጠሩ ሁኔታዎችን ወይም ስለ ሥርዐተ አምልኮት–ሥርዐተ ቅዳሴ አዲስ የተፈጠሩ ሁኔታዎችን ለመሸፈን ከዳበሩት ጥንታውያን ምንጮች በይበልጥም ከሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ወይም ድንጋጌዎች ዘበእደ አቡሊዲስ ከሚባል ጽሑፍ ላይ ተመሥርቶ እንደነበር ይታያል[809]

ከዚህም በመነሳት ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ የተጻፈበት ዘመን 5ኛው ምዕተ ዓመት እንደሆነ ይገመታል[810] ግን የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ጸሐፊ – አቀነባባሪ የ6ኛው ምዕተ ዓመት ሥራዎች ከሆኑ ቀኖናተ አቡሊዲስ ላይ እንደተመረኮዘ የሚደገፉ ሌሎች ንድፈ ሐሳቦች አሉ ። ስለዚህም ቅብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ የተጻፈበት ዘመን 6ኛው ምዕተ ዓመት ይሆናል ይላሉ ። በተቃራኒው ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ከቀኖናት ዘአቡሊዲስ ላይ ተመሥርቶው የተዘጋጀ ሳይሆን ነገር ቀኖናተ ዘአቡሊዲስ ከትእዛዙ ላይ ተመሥርተው እንደተዘጋጀ ይደገፋል[811]

ስለዚህ የግባጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ የተጻፈበት ዘመን ማቆሚያ–መድረሻ Terminus a quo ቀኖናት ዘአቡሊዲስ እንደተጻፈ

Schwartz:Ueber der pseudoapostolischen Kirchenordnung.strasbourg 1910

809. Επιτομή τού Βιβλίου Η΄ τών Αποστολικών Διαταγών Β.Ε.Π.Τ.Β.ገጽ 181

810. Achelis: de ältesten quellen des orientalischen kirchenrechts I. Buch. die canons Hippolyti. U.T.TI.T.4.6 ገጽ 38 137 Achelis: Hippolytus im kirchenrechts Z.K.G. 15/1895 ገጽ 1 43 Achelis: Hippolytstudien. T.U. T.I.T4. 1897.

811. Funk.die apostolischen konstitutionen ገጽ 261:Funk.Die symbolstücke in deraegyptishen kirchenordnung und canons Hippolyts T.Q. 1899 ገጽ 161 187

በት የሚታሰበውን 500 የማያልፍ መሆኑ ሊታመን ይችላል በተቃራኒው ይህ ትእዛዝ የተጻፈበት ዘመን Termainus ad quem አምስተኛው ምዕተ ዓመት እንደሆነ ይቆጠራል[812] መነሻሽለዚህም ከዚህ በኋላ የሚታሰበው ዘመን ተተባይነት አይኖረውም[813] E.Hauler የሚያወሳው የዚህ ትእዛዝ ላቲን ሮማይስጥ ትርጉም የ4ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ እንደሆነ ከአለው ሁኔታ ይደግፋል[814] ሆኖም የትእዛዙ ላቲን ትርጉም በVerona ካቴድራል ቤተመጻሕፍት የ5ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ክፍለ ጊዜ ሆኖ የሚቆጠር Palimniston የእጅ ጽሑፍ ይገኛል[815]

የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ጸሐፊ ስም አልባ ነው ። ስለዚህም ሳይታወቅ ይኖራል ። ሆኖም የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ጸሐፊ የሐዋርያውያት ትእዛዛት የ8ኛው መጽሐፍ ጸሐፊ ነው የሚባል ግምት አለ ከዚህም በመነሳት የተጻፈበት በታም ግብጽ ተደርጎ ይወሰዳል[816]

ምክንያቱም በምሥራቅ ሰፍኖ በሚገኘው ቤተክርስቲያን ልምድና ሥርዓት የተቀነባበረው ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ብቻ ሳይሆን ራሱ በሮሜ በመሠረታዊ ቅርጹ የተዘጋጀው ሐዋርያዊ ትውፊትም ቢሆን በምሥራቅ በተለይ በግብጽና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴያዊ ሕይወት ያሳደረውን ያህል ከፍተኛ ተፅዕኖ በምዕራብ ቤተክርስ ቲያን አላሳደረም ምክንያቱም ወደፊትም እንደምንመለከተው ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ እናት ሰነዱ ጠፍቶ ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ በመጣበት ትርጉሙ በግብጥ ፡ ዐረብኛና ግእዝ ቋንቋዎች ተይዞ ሊገኝ ችሏል።

812. Funk: die Apostolischen Konstitutionen ገጽ 279 280 Batiffol: Revue critique 1901 T.X. ገጽ 254

813. Funk: des testament unseres heren und vervandten. Schriften, Mayence 1901. funk: Didascalia. I.T.II ገጽ 97 119

814· ከዚሁ ገጽ 185–186

815· ከዚሁ ገጽ 185–186

816· ከዚሁ ገጽ 183

4·2·2 ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ የተጻፈበት ቋንቋ

እንደሚታወቀው ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ በግሪክ ቋንቋ ነው የተጻፈው[817] ነገር ግን የዚህ ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ ወደ ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ሲቀነባበር በዚህ ግሪክ ቋንቋ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጥያቄ ይነሳል ። መልሱ ነው ማለትም ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ በመጀመሪያ በግሪክ ቋንቋ ነው የተቀረጸው ነገር ግን ይህ እናት ሰነድ ጠፍቶ በሌሎች ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ትርጉም ሊገኝ ችሏል ።

4·2·3 ትርጉሞች

4·2·3·1 ላቲን–ሮማይስጥ ትርጉም

የግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ አንድ አንድ የተቋረጡ ክፍሎች በVerona ካቴድራል ቤተ መጻሕፍት በሚገኝ አንድ የ4ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ Palimniston የእጅ ጽሑፍ ላቲን ትርጉም ይገኛል ።

ይህ የተመለከተው ላቲን ትርጉም ከግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ እንጂ በእናቱ እንደነበረው ከሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ የመጣ – የተደረገ አይደለም ምክንያቱም የዚህ የላቲን ትርጉም ነጠብጣቦች (Fragments) ከሚመስሏቸው የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግብጥ ትርጉም (ሳዲቅ ትርጉም) ቀኖናት እንደ E.Hauler ሕትመት[818] 31–33 34·36·48 60 እና 62 ቀኖናት ወይም በFunk በታተመ መልካቸው[819] XVI 15ᴮ–27ᵃ XVIII-XXI XXXII 15ᴮ–36ᵃ ቀኖናት ይገኛሉና ቢሆንም የቀኖናቱ ላቲን መልስ ትርጉም ከሥነ ጽሑፍ አንጻር ከግሪኩ እናት ሰነድ ቅርጽና

817. J. Quasten, patrology. T II ገጽ 109

818. Hauler- didascalia T.I.ገጽ 101-121 Wilmart texte latin de paradosis de saint Hippolyte. R.F.R. 9.1916 ገጽ 62–71 ። Wilmart: unréglenen ecclesiestique de. IIe siècle la tradition apostolique de saint Hyppolyte: Revue Francais 96.1918 ገጽ 81 126፤ Nau canons des apôtres D.T.C.T.II ገጽ 1615፡ Botte. L,authenticite' de la Tradition de st Hippolyte R.T.A.M. 1611949 ገጽ 177...

819. F.Funk. Die Apostolischen Konstitutionen ገጽ 29–34 Achelis Die Ältesten ገጽ 1–23

ይዘት ጋር ተነጻጽሮ ሲታይ በትክክል የተደረገ ትርጉም ሆኖ ተገምቷል ስለዚህም ወደ መጀመሪያው ቅርጹና ይዘቱ እንዲመለስ ጥረት ተደርጓል ማልት ነው[820]

4.2.3.2 የግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግብጥ ትርጉም

4·2·3·2·1 የግብጻዊ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ ሳዲቅ ትርጉም

ይህ ትርጉም ምን ዓልባት አንድም የአባቶች ሥራዎች (ሥነ ጽሑፎችና ትምህርቶች) ፡ የሲኖዶሳት ቀኖናትና ውሳኔዎች ትርጉሞች ወይም እነዚህን ሥራዎች ፡ ጽሑፎች ፡ ቀኖናትና ውሳኔዎች እንደገና ማቀነባበር ፡ ማዘጋጀትና አዲስ ወጥ ሥራዎችን መጻፍ ሁል ጊዜ ግን እነዚህ ሥራዎችን ፡ ጽሑፎችንና ቀኖናትን ለሐዋርያት ወይም ለጥንት አባቶችና ጸሐፍት በመስጠት በተከሰተበትና

ከፍተኛ እንቅስቃሴዎች በታዩበት ዘመን ቀደም ብሎ በ500 አካባቢ ከግሪክ እናት ሰነድ ተደርጓል[821]

ስለጥንቱ ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ (ሳዲቅ) ትርጉም ያለው አመለካከት እንደማስረጃ ሆኖ የሚቀርበው ይህ ግብጥ ትርጉም —ሳዲቅ ትርጉም ብዙ ግሪክ ቃላትን ይዞ ግን የቅብጥ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጽን ይዘው ወይም ወደ ቅብጥ ቋንቋ ቅርጽ ተለውጠው የሚገኙ ቃላትን ይዞ መገኘቱ ነው ። ይህም በP. De lagarde ሕትመት መሠረትነት steinford ባመለከተው ሁኔታ በቀላሉ ሊለዩ ይችላሉ[822]

የቅብጥ –ሳዲቅ የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ትርጉም ሰነድ የእጅ ጽሑፍ በዓመተ ሰማዕታት (ዲዮቅልጥያኖስ) 722 = 1006 ዓ·ም·) ተጽፎ በቅርቡ ተደርሶበት በብሪቲሽ ሙዚዬም ይገኛል[823] ይህ የእጅ ጽሑፍ በሁለት ክፍሎች (መጻሕፍት) 71 እና 78 ቀኖናት ተከፍሎ የሚገኝ ሲሆን በTattam ከታተሙት መጻሕፍት I—VI ቀኖናት ጋር ይነጻጸራል[824]

---

820. J.Quasten: patrology T.II ገጽ 181
821· ከዚሁ ገጽ 151
822. Quasten,Patrology, T.II ገጽ 181
823. Leclerq, Canons Apostoliques, D.A.C.L. T.II ገጽ 12 32 T II 19-32
824· ከዚሁ ገጽ 174-175

የ1320 እጅ ጽሑፍ የ440 የእጅ ጽሑፍንም ከግምት በማስገባት በ1883 በP. de Lagarde. ታትሞ የተሰራጨ ሲሆን በዚህ P. De Lagarde ከተደገመው ሕትመት ላይ. በsteinford[825] ከተደረገ ጀርመንኛ ትርጉም ጋር በAchelis ሊታተም ችሏል[826]

ይህ ሳዲቅ ትርጉም ሰነድ እንደዚሁም በካይሮ ፓትርያርክ ቤተ መጻሕፍት ከተገኘ አንድ አዲስ የእጅ ጽሑፍ በU.Bouriant ታትሟል

4·2·3·2·2 የግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግብጥ—ሚምፊቲቅ ትርጉም

ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ከሳዲቅ ትርጉም ወደ ሌላም ግብጥ ቋንቋ ሚምፊቲቅ ወይም ቦካይቲቅ ተመልሶ ይገኛል ነገር ግን በሁለት የግብጥ ቋንቋዎች ሳዲቅና ሚምፊቲቅ ትርጉሞች መካከል በሳዲቅ ትርጉም ሰነድ ገብተው ከሚገኙ ሕጸጾች የተነ[illegible]ደሆነ የሚቀጠሩ ልዩነቶች ይመለከታሉ ምክንያቱም አሁን ያለው ሳዲቁ ትርጉም ሰነድ እናቱ ትርጉም ሰነድ ሳይሆን ነገር ግን በ8ኛው ወይም በ9ኛው ምዕተ ዓመት ከተተረጎሙበት ሰነድ የተገለበጠ እንደሙሁ[illegible]ን የመጀመሪያ—ትርጉም (ቦካይቲቅ ትርጉም) አይገኝም[828] ቢሆንም በልዩ ልዩ የእጅ ጽሑፎች እንደሚገኝ ይታወቃል[829] የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ሚምፊቲቅ ትርጉም በTattam በተደረገው የግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ሕትመት ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ሚምፊቲቅ ወይም ቦካይቲቅ ትርጉም ከእንግሊዘኛው ትርጉም ጋር ሁለተኛውን መጽሐፍ

---

825. De Lagarde Aggyptiaca ገጽ 239-291፡ 309-338
826· Achelis, Die Ältestem T.U. VI ገጽ 226 ገጽ 39 136
827. K.Bouriant, Les Canons Apostoiorum De Clement De Rome Traduction En Dialecte Copte Thebain, D'apres un Manuscript De la Bibliotheque Du Patriarche Jacobite Du Caire. Le Recueil De Travaux Relatifs a La Philosophie et arc heologie Chretiennes Egyptinnes et Assyriennes T.V. ገጽ 199-216፡ VI, ገጽ 97-115።
828. Duchesne: Origines du culte chretiene. paris 1898[2]appendice IV ገጽ 504-521
829. ሕትመት Till-J.Leipoldt: uei koptische texte der kirchenor dnung hippolytes, Berlin 1954

ሲይዝ Constitutiones Apostolici Aegyptiaci የመጀመሪያውን መጽሐፈ ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት Canones Apostolici Aegyptiaci ይይዛል [831] ። ሦስተኛው መጽሐፍ ከሐዋርያውያት ትእዛዛት 8 መጻሕፍት 8ኛውን መጽሐፍ ሲይዝ አራተኛው ፣ አምስተኛውና ስድስተኛው መጻሕፍት ከእነዚህ ሐዋርያውያት መጻሕፍት ከሰባተኛው መጽሐፍ የሚከተሉትን ምዕራፎች ይይዛሉ ። ስምንተኛው መጽሐፍ ሐዋርያውያት ቀኖናትን ይይዛል [832] ።

Tattem የተጠቀመበት የእጅ ጽሑፍ እንደ ዓመተ ሰማዕታት ዲዮቅልጥያኖስ 1048/1320 ዓ·ም የተጻፈና በበርሊን የተገኘ አንድ የእጅ ጽሑፍ ነው [833] ቢሆንም የግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ማምፊቲክ ትርጉም ሰነድን ሲያሳትም የዚህኑ ትእዛዝ ሰዲቅ ትርጉምን እንደተመለከተ ለመገንዘብ ተችሏል ።

4·2·3·3 የግብጻዊ ቤተክርስቲያን ትእዛዝ ዐረብኛ ትርጉም

የግብጣዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ ዐረብኛ ትርጉም ሰነድ ከሳዲቅ ትርጉም ሰነድ እንደመጣ ቢታወቅም ይህ የትእዛዙ ዐረብኛ ትርጉም ሰነድ እንደሚምፊቲቅ ትርጉም ከመጀመሪያው እናቱ ሳኪዲቅ ትርጉም ሰነድ ሳይሆን ከቆየ ግልባጩ በመሆኑ መሠረታዊ ልዩነትን ያሳያል [834] የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዛት ዐረብኛ ትርጉም በ10ኛው ምዕት ዓመት አካባቢ እንጂ ከዚያ በፊት ግን እንዳልተደረገ ይታመናል [835] ዛሬ ያለው የቢህ ትእዛዝ ዐረብኛ ትርጉም ሰነድ የ13ኛው ምዕት ዓመት የእጅ ጽሑፍ ነው [836]

---

830. Tattam: the apostolical constitutions or canons of the apostles in coptic London 1848 bibl. III-IV ገጽ 147 178፣ 92 171

831· ከላይ ገጽ 167–181

832. Leclerq: canons apostoliques. D.C.L.T.II ገጽ 1932

833. Ms. orient no. 519

834. Leclerq: canons apostoliques. D.A.C.L.T.II ገጽ 1932።

835. J. Quasten: patrology. T-II ገጽ 182 DIX: the treatise on the apostolic tradition of bippolytus. Rome 1916 ገጽ XLIX.

836. G.stam: Episcopacy on the apostolic tradition. basel. 1926 ገጽ 12

4·2·3·4 የግብጻዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግእዝ ትርጉም

የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግእዝ ትርጉም ሰነድ ከግብጥ ወይም ከዐረብኛ ትርጉም ሰነድ የመጣ መሆኑ ይጠረጠራል ። ምክንያቱም የዚህ ትእዛዝ ትርጉም ከሁለቱም መጣባቸው ከሚባልባቸው ትርጉሞች (ግብጥና ዐረብኛ ሰነዶች) ስፈ ርቀትን ያሳያል ። ችግሩ ከላይ እንደተባለው በዚህ ብቻ አይወሰንም ፡ የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግእዝ ትርጉም በዚህ ብቻ ሳይሆን በደንቡ መሠረት በሁሉም ማለት ይቻላል ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናትና ሥራዎች በትርጉማ ሂደት ጉዞ አራተኛውን ደረጃ ይይዛል ለምሳሌ ይህን ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝን እንጠቀማለን ።

ከላይ እንደተባለው ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ በመጀመሪያ በግሪክ ቋንቋ እንደተጻፈ ከዚህም ይህ ከግሪክ ቋንቋ እናት ሰነድ ወደ ግብጥ ቋንቋ ከዚህም ግብጥ ቋንቋ ወደ ዐረብኛ ከዚህም ዐረብኛ ቋንቋ ወደ ግእዝ ተመልሷል ማለት ነው ።

ስለዚህም አንድ ሰነድ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ከዚያም ሌላ ቋንቋ ወደ ሦስተኛ ቋንቋ ከዚያም የበለጠ ወደ አራተኛ ቋንቋ ሲመለስ ሲተረጎም በግድ የመጠን ቅርጽ ለውጥ (መጨመር ፡ መቀነስ) ፡ የዕንስ ሐሳብ ለውጥ) ትርጉም ፡ ማንዛቢ) ፡ የቅደም ተከተል መሸጋሸግ) የፊቱ ወደ ኋላ የኋላው ወደፊት) ሲከተቱበት በአንድ በኩል እነዚህን በየጊዜው ከሚፈጠሩት ሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም ወይም ምን አልባት የተረሱትን ፍሬ ነገሮች ለማስተካከል ወይም ለማረም ሲባል የተወሰኑ ጭማሪዎችን ለማስገባት ወይም ሥርዋጾችን ለመጨመር የሦስተኛ እጅ ጣልቃ ገብነትን ሊያስወግድ እንደማይችል ርግጠኛ ሐቅ ነው ።

ከዚህም በመነሳት የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግእዝ ትርጉም ሰነድ በመጀመሪያ በዐረብኛ ትርጉሙ ሰነድ የማይገኙ ምዕራፎችን ይይዛል ፡ ይህም ልዩ ልዩ ምክንያቶች ይኖሩበታል ወይም የግእዙ ሰነድ ተርጓሚ እንደተለመደው ያልነበሩ ነገሮችን ጨምሯል ወይም እነዚህ ፍሬ ነገሮችን ከያዘ አንድ ዐረብኛ ትርጉም ሰነድ መልሷል ።

ስለዚህ የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግእዝ ትርጉም ዛሬ ከሚገኘው ዐረብኛ ትርጉም እንደአልተመለሰ ነገር ግን በጣም ከቆየ

በበኩሉ እንደዚሁም በጣም ከቆየ አንድ ሌላ ግብጥ–ሳዲቅ ትርጉም ከመጣ–ከተመለሰ እንደሆነ ይቆጠራል [837]። ስለዚህ እነዚህ ትእዛዛት በቦታዎች ቤተክርስቲያናውያን ልምዶችና ባህሎች ጋር እንዳይጋጩ ከማድረግ ዓላማ በመነሳት ቆይተው ከግብጥና ዐረብኛ ትርጉሞች ሰነዶች እንደተቀነሱ ይደገፋል ። ነገር ግን አንድአንድ (የተወሰኑ) ትእዛዛት በቤተክርስቲያን ልምዶችና ባህሎች ጋር መጋጨታቸው አልተጠቀሰም ሐቁ ግን እነዚህ ምዕራፎች በትእዛዙ የግእዙ ትርጉም እንደተጨመሩ ማሰቡ ነው [838]

ስለዚህም ይህ የትእዛዙ ግእዝ ሰነድ ዝርዝር ቀኖናውያት ትእዛዛትን ፡ ስለ እሥረ ክህነትና ጸሎተ ቡራኬ እንዲሁም ሙሉ ቅዳሴን [839] ይዞ እንደመገኘቱ መጠን ከእነዚህ ሁለት ትርጉሞች ሰነዶች መሠረታዊ ልዩነት አለው ። በሌላም በኩል የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግእዝ ትርጉም ብቻ በላቲን ትርጉም የሚገኙትን የሥርዐተ ክህነትና የጸሎተ ቡራኬዎች ሰነድን ይዞ መገኘቱ ልዩ ያደርገዋል [840]። የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግእዝ ትርጉም በመጀመሪያ በጸሐፍት ሊታወቅ የቻለው አንድ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ተብሎ በተገኘ ሰነድ ነው ። Ludolphus ይህን የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ግእዝ ትርጉም ከላቲን ትርጉም ጋር በ1691 ያሳተመው ሰው ሲሆን [841] ይህም ሰነድ ተሻሽሎ ከጀርመንኛ ትርጉም ጋር በAcheilis ታትሟል [842] በመጨረሻ ይህም ሰነድ በDuensing ታትሞ ሲገኝ [843] በፈረንሳይኛ ከሂስ ጋር

837 ሁኖም ይህ አንድም ከአንዱ ወደ ሌላው ግብጥ ወይም ዐረብኛ ትርጉም እንጂ ከሌላ ለምሳሌ ከሱርስጥ ትርጉም ሰነድ እንደ አልመጣ መገንዘብ ይቻላል ።

838./ Quasten: Patrology T.II. ገጽ 182

839 Stam:Episcopacy. on apostolic tradition ገጽ 11

840. J. Quasten: Patrology T.11 ገጽ 182

841. Ludolphus በመጀመሪያ የ127 ቀኖናትን አርእስት ተርጉሞ ቀጥሎም የእነዚህን 127 ቀኖናት የመጀመሪያ ክፍል ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት መጀመሪያዎች ቀኖናት (23 ቀኖናት) ሙሉ ቃላትና የሁለተኛውን ክፍል ግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ የመጀመሪያዎች ሁለት ቀኖናትን የሰለተኛው ቀኖና የመጀመሪያ ሐረግ (እንደ ግብጥ ትርጉም 21 22.እና 23) ተርጉሟል ። Commentarius...I–11 ገጽ 314 328

842. Achelis: die canones Hippolyte ገጽ 39 47, 61-64

843. H. Duensing, der Aethiopische texte der Kirchenordnung G.W.G.phol.Hist.K.I.3.32 Götingen

በW.D. Maxwell በ1945 ታትሟል [844] በመጨረሻ የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ግእዝ ትርጉም የተከናወነው ምንም ቢሆን ከ15ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያዎች በፊት መሆን ይኖርበታል ምክንያቱም መድረሻውን ዘመን Terminus adoquem ሊያሳይ የሚችለው በብሪት ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ የ1440 ዓ.ም አንድ የእጅ ጽሑፍ ነው [845]።

4·2·3·5 የግብጻዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ምንጮችና ይዘት

ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ እንደተወለደበት "ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ" የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛውን መጽሐፍ በምንጭነት አይዝም ። በተቃራኒው አሁን በአለበት መልኩ እሱ ... ልቅ በሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ [846] እና በዚህ የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ Epitome ማለትም ከእነዚህ ሰነዶችና ከይዘቱ መገንዘብ እንደሚቻለው ምን ዓልባትም በጥንት ቤተክርስቲያን በአገልግሎት ላይ በነበሩ ቀኖናውያት አምልኮታውያትና ሥርዓተ ቅዳሴያውያት ትእዛዛት ላይ እንደተመሠረተ ይታመናል [847]።

ነገር ግን ጸሐፊው የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ጸሐፊ መሰሎ ኢግናጢዮስ Pseudoignatius ሊሆን ይገመታል

844 B Botte: Le texte de la tradition apostolique: bech. TH. ANC MED T 22. 1955 ገጽ 162. stam: episcopacy... ገጽ 11

845· ዝዚሁ ገጽ 182 184

846. የንጽጽር ሰሌዳውን ዘዚሁ ገጽ ተመልከት

847 የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ-Epitome የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ቢጋርን እንደሚይዝ ወይም የሐዋርያውያት ትእዛዛት የ8ኛው መጽሐፍ ምንጭ እንደሆን ... ግን "ቅዳሴ አንጾኪያ" የሚባለውን ክፍል የያዙትን 5–15 ምዕራፎች እና የዘመትር ጸሎትንና ሥርዐተ ቅዳሴን የያዙትን 35–41 ምዕራፎች ይዘዋል ይተዋል። Wordsworth. the Ministry of grace. London 1901 ገጽ 33

በተቃራኒው ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ በራሱ በሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ እንደተወለደና የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛውን መጽሐፍ Epitome እንደሚይዝ ነገር ግን ምንም ቢሆን ከሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ በኋላ እንደተፈጠረው እንደተዘጋጀ ይቆጠራል ። Quastern: Patrology: T.III ገጽ 182

Connolly the so called egyptian church order and drived documents. 916 ገጽ

Dix the Treatise... ገጽ LXXIV

የግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ይዞት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል ከነዚህም የመጀመሪያው ክፍል 31 41 (ሳዲቅ ትርጉም) ቀኖናትን የያዘው ክፍል ሲሆን በሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ወይም Epitome የያዘውን ከቤተክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ጋር የተዛመዱትን እና የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና ምዕመናን አቋምን ከሚመለከቱት ትእዛዛት ጋርም የተያያዙን ትእዛዛት ይይዛል [848] ሁለተኛ ክፍል 42 62 (ሳዲቅ ትርጉም) ቀኖናትን ያቀፈ ሲሆን በተቃራኒው አስቀድሞ ከነበሩ ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናት ጋር የሚመሳሰሉ ትእዛዛትን አይዝም ። ከዚህም የተነሳ የግብጣዊ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ ሁለተኛው ክፍል ምንጮች ከላይ እንደተባለው ምንዓልባት በጥንት ቤተክርስቲያን የነበሩ ልዩ ልዩ ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናት እንደሆኑ ይደገፋል ።

ስለዚህ ሐዋርያዊ ትውፊት በአበሊዲስ በሚል ርእስ እንደተፈጠረ በሚቆጠረው ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝና በእሱም ላይ ተመሥርተው ተዘጋጅተዋል ከሚገኙት ሌሎች ሥራዎች መካከል ንጽጽር ማድረግን ለማስቻል ስለቀኖናት በአበሊዲስ በምንናገርበት ክፍል ሁሉም ትእዛዛትን እናመለክታለን [849]

4·3·ሦስተኛው ክፍል ቀኖናት 48—71 (63—78)

·የረስጠብ የመጨረሻው ክፍል 24 ቀኖናትን ማለትም ከ48 71 (ወይም 16 በሳዲቅ ትርጉም 63 78) የያዘ ክፍል ነው ነገር ግን እነዚህ ቀኖናት የረስጠብ የአለፉት ሁለት ክፍሎችን፡ ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያትን[850] እና ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊትእዛዝን[85] በያዙት ቀኖናት እንደ ተመለከተው አንድ ዓይነት መለያ ይዘው አይታዩም ወይም በአንድ የተወሰነ ርእስ አይታወቁም ።

በእነዚህ ቀኖናትም ላይ የተደረጉ ጥናቶች አሁንም ከአለፉት

848 ሐዋርያውያት ቀኖናት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖናት 1 15 Funk: Didascalia T.II ገጽ XI-XIX

849· ከላይ ገጽ 162

850· ከዚሁ ገጽ 168–181

851· ከዚሁ ገጽ 181 192

ሁለት–ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያትና ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ጋር ሲነጻጸሩ በጣም አነስተኞዎች ናቸው ። እንዲያውም የተሻለ የሉም ማለት ይቻላል ።

በአጠቃላይ የእነዚህ ቀኖናት ማለትም የሦስተኛው ክፍል ከአንደኛውና ከሁለተኛው ክፍል ቀኖናት ጋር ያላቸው ግንኙነቶች–ዝምድናዎች የተቃረቡ ናቸው – የተያያዙ ናቸው ምክንያቱም የመጨረሻዎቹ ከሁለተኛው ክፍል (ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ) ቀኖናትና ስለዚህም በተዘዋዋሪ ከሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ተወልደዋልና ስለዚህም እነዚህን ቀኖናት ያሰባሰበው ሰው የቤተ ክርስቲያንን ሥነ ቅዳሴና ሥነ ምግባር…የሚመለከቱ ትእዛዛትን በማሳጠር ወይም በመጨመር ወይም በመተው ፍሬ ነገሩን በልዩ ልዩ ቀኖናት (ቅደም ተከተል–ተራ እንደ አቀነባበረ ይገመታል [852] ማለትም የሁለተኛው ክፍል ቀኖናት (ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ) ምንዓልባት ቆይተው ከተፈጠሩት የቤተክርስቲያን ሁኔታዎች ጋር በመጣጣም እንደገና የተዘጋጁ ናቸው ማለት ይቻላል ።

4·3·1 የረስጠብ ሦስተኛው ክፍል የተጻፈበት ዘመንና ቦታ

የረስጠብ ሦስተኛው ክፍል ቀኖናት ምንም ቢሆን በግብጽ ወይም በሶርያ ተዘጋጅተዋል ። በይበልጥ ከተመሠረቱባቸው የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍም ሆነ ከግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ ቆይቶ የተዘጋጁ ሥራዎች ናቸው ።

4·3·2 የረስጠብ ሦስተኛው ክፍል የተጻፈበት እናት ቋንቋ

የረስጠብ ሦስተኛው ክፍል የተጻፈበት እናት ቋንቋ ግሪክ ቋንቋ ነው። ግን በግብጥ ቋንቋዎች (ሳሂትና ሚምፊቲቅ) ፥ ዐረብኛና ግእዝ ትርጉም ይገኛል። ግብጥ–ሳሂት ትርጉም በመጀመሪያ በ1883 ታትሞ ሲሰራጭ [853] ቆይቶ በጀርመንኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በLeipoldt በ1904

852· Périer: Las 27 Canons des Apôtres P.O.8/1912

853. P. de Lagarde: Egyptiaca ገጽ 239

ታትሟል [854] ።

2· ሌላው ግብጥ – መምሬቲቅ ትርጉም ከእንግሊዝኛ ትርጉም ጋር በ1888 በTattam የታተመ ሲሆን [855] በTattam የታተመው የሚምሬቲቅ ትርጉም ቀኖናት ከሳዲቁ ትርጉም እንደመጣ እንደ P.De Lagarde አመለካከት ይታመናል [856] ቢሆንም የሚምሬቲቅ ትርጉም ቀኖናት በቀለሚንጦስ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ከተያዙት ቀኖናት አይለዩም ግን ከሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ክፍሎች (ከነዚህ የመጀመሪያው ክፍል የቀለሚንጦስ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 7ኛውን መጽሐፍ የሚይዘው ነው) በተደረጉባቸው ለውጦች ይለያሉ) [857] ማለትም Constitutiones sev statua plurimorum Apostolorum[858]

4·3·3 የረስጠብ ሥስተኛው ክፍል ዐረብኛ ትርጉም

የዚህ ክፍል ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም ምን ዓልባት ከሳዲቅ ትርጉም የመጣ መሆኑ ሲታመን ሁለት ዓይነቶች የቀኖናት ሰነዶችን ይይዛል ።

አንድ በBibliotheque Nationale de Paris የሚገኝ የእጅ ጽሑፍ [859] ሁለት የቀኖናትን ትርጉሞች

1· በሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ምዕራፍ XXXII ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት ሳይኖረው ከሳዲቅ ትርጉም ጋር ጐን ለጐን የሚሄዱ 48–71 ቀኖናትን [860]

2· በዐረብኛው ቋንቋ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት 7ኛውን መጽሐፍ የሚመሠረቱት ሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ምዕራፍ XXXII መጀመሪያ ክፍል ላይ ከሚታይ ጣልቃ ገብነት ጨማሪ ጋር ከቀለሚንጦስ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት 4–7 ያሉትን መጽሐፍት ይይዛል ። ይህም አንዱ ከሱርስጥ የተመለሰና ሌላው ከግብጥ የተተረጐመ ሆኖ ይታያል ምክንያቱም ሁለቱም ከመጡባቸው ሰነዶች ጋር ይጣጣማሉና ።

4·3·4 የረስጠብ 3ኛው ክፍል ግእዝ ትርጉም

የረስጠብ ሦስተኛው ክፍል ወደ ግእዝ መተርጐሙ ሲታወቅ የዚህ ትርጉም ቀኖናት አርእስት ከላቲን ትርጉም ጋር በLudolphus ታትመዋል [861] ።

4·3·5 የረስጠብ 3ኛው ክፍል ምንጮችና ይዘት

ከላይ እንደተመለከተው እነዚህ ቀኖናት ከግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ የተወሰዱ ወይም እንደገና የተቀነባበሩ እንደመሆናቸው መጠን በሙሉ ወይም በከፊል ከሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ላይ ማለትም በሚከተሉት ቀኖናት ላይ ይደገፋሉ 1·2·3–5·11–17·23–28·30·34·46 (ቀለሚንጦስ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 6ኛው መጽሐፍ 27–28·30–31·32 መጨረሻና መጀመሪያ ሐረግ ፣ 33–34 42–46)

ከእነዚህ ቀኖናት በአንዱና በግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ መካከል ንጽጽር በDe Lagard ተደርጓል [862]

ስለዚህ እነዚህ ቀኖናት ከቀለሚንጦስ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት (ሱርስጥ ዐረብኛና ግብጥ ትርጉሞች) 4ኛውን [863] 5ኛውን [864] 6ኛውን [865] እና 7ኛውን መጻሕፍት [866] ይይዛሉ

በእነዚህ ቀኖናት ስለ ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ እንደተነገረው የቤተክርስቲያንን አገልጋዮች ተዋረድ–ማዕርገ ክህነት ተዋረድና ሥነ ሥርዓት እንደዚሁም ሥርዓተ ቅዳሴን የሚመለከቱ ጉዳዮችን

854. K.Leipoldt: Saïdische Auszüge As Dem Buch Der Apostolischen Konstitutionen Der Dritte Teitle Der Canones Ecclesiatici T.U. 1904 T. XXVI Fasc 16 ገጽ 1–57
855. Tattam, Apostolical Constitutions or Canons of the Apostles Bibl. III-VI. ገጽ 92 171·
856. P.Dc. Lagarde: Reliquiae... Gracc ገጽ 15· NAU.
857. P. De. Lagarde: Reliquiae...Graec ገጽ XV NAU. Canons des Apôtres D.C.T. T 11-12 ገጽ 1615-Leclerq: Canons Apotoliques D.A.C.L. T 11-2 ገጽ 1936
858· ስለ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 6ኛው መጽሐፍ ከዚሁ ገጽ 207
869. Ms. Arabe de Paris No 252
860. Ms. Arabe de Paris No 86

861. Ludolphus: Commentarius... ገጽ 305 310
862. P.Dc Lagarde: Reliquiac...Gracc ገጽ XIII-XVI
863· የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖናት 1–2
864· የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖናት 3–5 ፣ 16–26
865· የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖናት 27–28 ፡ 30–35፡ የ32 መጨረሻ ሐረግ 33–34 ፡ 41–46 የ32 መነሻ ሐረግ
866· ሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖናት 29 ፣ 6–19

የሚወስኑ ትእዛዛት ታቅፈዋል [867]

ስለዚህ 71 (ወይም 78) ቀኖናት ከተጠቀሱት ሦስት ምንጮች ላይ ይፈለጋሉ ። ከእዚህም የተነሳ ከልዩ ልዩ ቤተሰቦች ተመሳሳዮች ምንጮች የመጡ ስለሆኑ መድብለ ቀኖናት ዓይነት ሁነው ይገኛሉ ።

71 ቀኖናት ከቀለሚንጦስ ዐረብኛ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 2 7 (7) መጽሐፍትን ይይዛሉ ። ይህ የ71 ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም Tattam የተጠቀመበት ግብጥ–ሳዲቅ ትርጉም ሰነድ ሆኖ እንደተገኘ ይቆጠራል [868]

ነገር ግን እናቱ ሳዲቁ ሰነድ በዓመተ ሰማዕታት – ዲዮቅልጢያኖስ 722 ዓመተ ሰማዕታት 1000 ዓ·ም ተጽፎ በብሪቲሽ ሙዚየም የሚገኝም የእጅ ጽሑፍ መሆኑ ይታመናል ። የዚህ የእጅ ጽሑፍ ይዘት በሁለት መጻሕፍት ይከፈላል

የመጀመሪያው መጽሐፍ 71 ቀኖናትን ሲይዝ ሁለተኛው መጽሐፍ 7ዘ 78) ቀኖናትን ይይዛል ። እነዚህም በTattam ከተተሙት 1 6 መጻሕፍት ጋር ይነጻጸራሉ [869] ። P.Delagard በብሪቲሽ ሙዚዬም በቁጥር 1320 (MS.Orient) የሚገኘውን ሰነድ ያለ ትርጉም ያሳተመ ሲሆን [870] በቁጥር 440 የሚገኘውን የእጅ ጽሑፍም ከመመልከት አልቦዘነም ። ሌላው የሳዲቅ ትርጉም ሰነድ እንደዚሁ በካይሮ ፓትሪያርክ ቤተ መጻሕፍት ከተገኘ የእጅ ጽሑፍ በK.Bouriant ሊታተም ችሏል [871]

867· ከዚሁ ገጽ 191–192

868. Leclerq: Canons Apostoliques D.A.T.L. T.II ገጽ 1932

869. Tattam: Apostolical Constitutions ገጽ 209-238

870. P.De Lagarde: Aegyptiaca... ገጽ 239-238

871. K. Bouriant: les Canons Apostolorum De Clèment de Rome T.II ገጽ 190

5· ረስጠጅ—ቀለሚንጦስ ማልስ

ለፍትሐ ነገሥት እንደ ሐዋርያውያት ቀኖናት 3ኛ መጽሐፍ ሆኖና ረስጠብ [872] ተብሎ የተመለከተው ክፍል 56 ቀኖናትን የያዘው ቀኖናዊ መጽሐፍ ነው ።

ከላይ እንደተባለው 56 ቀኖናት ከ71 ቀኖናት ጋር በአንድነት የግብጥና ግእዝ ትርጉም 127 የታወቁ ቀኖናትን ይይዛሉ [873]

የእነዚህ ቆኖናት ቁጥር በዐረብኛና ግእዝ ትርጉሞች 56 (ወይም 71) ሲደርስ በግብጥ ግን 71 ይደርሳል [874] ስለ ቀኖናት አጠቃላይ ሁኔታ የተጻፈበት ዘመን ፣ ቦታ ፣ ጸሐፊው ወዘተ··· ከላይ ከተመለከትናቸው ሁለት መስማተ ሐዋርያውያት ቀኖናት (ረሰጠአ እና ረሰጠብ) በምንም ዓይነት አይለዩም [875] ምክንያቱም እንደእነዚያ 81 ቀኖናት እነዚህም ቀኖናት የግሪኩን እናቱን ቋንቋ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት እንደገና መቀነባበርን — አዲስ ቅርጽን ይዘው ይታያሉ – ስለዚህም እንደገና ቁጥሮችን በማስተካከል በአጠቃላይ ብዙ ቀኖናትን ወደ አንድ ቀኖና በማሰባሰብ ማለትም ከ85 ቀኖናት 2–4 ቀኖናት የ56 ቀኖናት ሁለተኛውን ቀኖና ይይዛሉ 12–13 ቀኖናት 10ኛውን ቀኖና ፣ 17–19 ቀኖናት 12ኛውን ቀኖና 21–24 ቀኖናት 15ኛውን ቀኖና 42–44 ቀኖናት 23ኛውን ቀኖና 54–57 ቀኖናት 38ኛውን ቀኖና ፣ 62–71 ቀኖናት 49ኛውን ቀኖና ፣ 71–73 ቀኖናት 50ኛውን ቀኖና 75–79 ቀኖናት 52ኛውን ቀኖና ፣ 80–82 ቀኖናት 53ኛውን ቀኖና ፣ 83–84 ቀኖናት 54ኛውን ቀኖና ይዘው ወይም ከእነሱ የተወሰዱ ቀኖናትን በመቀነስ – በማስቀረት ማለትም ከ85 ቀኖናት 45·47–50 (43·44·55·45–49 ቀኖናት) በ56ኛው ቀኖናት አይገኙም ። ከዚህም የተነሳ በ85 ቀኖናት ሐዋርያውያት ግሪክ እናት ሰነድ 85ኛው ቀኖና የሚጠቀሰው የቀለሚንጦስ 8ኛው መጽሐፍ (የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛው መጽሐፍ ከ56 ቀኖናት 55ኛው ቀኖና ተቀንሶ ሊገኝ በሌላ በኩል ራእየ ዮሐንስ ተይዞ ስለሚገኝ ነው

872· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2 Guidi: il canone biblico della chiesa copta: Revue biblique 1901, ገጽ 102-164

873· ከዚሁ ገጽ 197

874· ከዚሁ ገጽ 198–199

875· ከዚሁ ገጽ 199 200

6· 127 ቀኖናት ሐዋርያውያት

እስከ አሁን ከተመለከቱ ሁለት ክፍሎች(ረስጠአ እና ረስጠብ) 127 ቀኖናት ወይም በግዝፀ 149 ቀኖናት ሊወለዱ ችለዋል ።

እንደ ፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብን እል አሳል እነዚህ 127 ቀኖናት ከእነሱ በፊት ከተመረመሩት 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ጋር በመግቢት ላይ ይገኛሉ ።

የመጀመሪያው የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብን እል አሳል ከላይ እንደተባለው ከግሪክ ቋንቋ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ የተተረጐሙ ሐዋርያውያት ቀኖናት እንደአሉና ቀጥሎም መለካውያንና ንስጥሮሳውያን እነዚህን ቀኖናት በአንድ ላይ እንደሚጠብቁአቸው የቀኖናቱም ቁጥር በመለከውያንና በያዕቆባውያን ዘንድ 83 እና በንስጥሮሳውያን ዘንድ 82 መሆናቸውን ሲያመለክት [876] ግብጣውያን ግን የመጀመሪያውን 71 ቀኖናትን እና ሁለተኛውን 56 ቀኖናትን በማስያዝ በሁለት መጻሕፍት እንደ አሳትሟቸው ይታወቃል ነገር ግን እየአንድአንዱ መጽሐፈ ቀኖናት ቁጥር አንዱ በሌላው በመጨመር ወይም በመቀነስ ይለያያል ። እነሆ የአንድ መጽሐፍ ወደ ሁለት (ሀ እና ለ) መከፈል ቀጥሎም ሦስት መጽሐፍት ሆኖ መጠቀስ ሳያስገርም አይቀርም ። የፍትሐ ነገሥቱ ሰነድ ከዚህም ላይ ሆነ በሌላውም ቦታ – ክፍል ብዙ ጊዜ ደጋግመን እንደ አወሳነው አይገባም ሆኖም ሊረዳ የሚችለው ከአጠቃላይ ይዘቱ አንጻር ነው Ad sensum ።

በመጀመሪያው በመለካውያን 83 እና በንስጥሮሳውያን 82 ቀኖናትን ይዘው ከግሪክ ቋንቋ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ ስለ ተተረጐሙ ቀኖናት አንድ ወጥ ሰነድ እና ግብጣውያን ቁጥራቸው 127 ወደ ሆኑ ሁለት ሰነዶች እንደከፈሏቸው ይነገራል ።

እስከዚህ የሁኔታው ታሪክ ሂደት ሥርዐትን የተከተለ ይመስላል ነገር ግን ቀጥሎ የመጀመሪያው ረስጠአ ፡ ሁለተኛ ረስጠብና ፡ ሦስተኛው ረስጠጅ እንደሚባሉ ያመለክታል ። ስለዚህ አንዱ ሰነድ ረስጠአ በሁለት ተከፍሎ በሁለተኛም ደረጃ ከላይ እንደተባለው አንድ ጊዜ (ረስጠአ) ተብሎ ለ81 ቀኖናት ሌላ ጊዜ ለ71 ቀኖናት (1–20 የመጀመሪያው ክፍል) ተሰጥቶ ሲጠቀስ ረስጠጅ እንዴት ተፈጠረ? የሚል ጥያቄ ይነሳል [877]

876· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል ሁለት

877· ከዚሁ ገጽ 197

ነገር ግን ቀለሚንጦስ ቀዳማዊና ቀለሚንጦስ ዳግም (ረስጠአና ረስጠብ) የቀለሚንጦስ ቀዳማዊ ንዑስ ክፍልን አይዙም ። ስለዚህ ይህ የቀኖናት ወደ ሦስት ክፍፍል ከመገልበጥ ስሕተት ወይንም ከራሱ ከጸሐፊው ጥንቃቄ ጉድለት ሊሆን ይችላል የሚል ግንዛቤ አለ ። ቢሆንም 127 ቀኖናት ረስጠብ 71 ቀኖናትና ረስጠጅ 56 ቀኖናት ($71 + 56 = 127$) ተደምረው መሆኑ ይታያል ።

የ79 ቀኖናት ግብጥ ትርጉም ቀኖናት ከእንግሊዝኛ ትርጉም ጋር በTattam የታተሙ ሲሆን [878] ከፈረንሳይኛ ትርጉም ጋር በP.de. Lagarde ታትመዋል [879] ። 127 ዐረብኛ ትርጉም ቀኖናት ከፈረንሳይኛ ትርጉምና ሂስ ጋር በPérie የታተሙ ሲሆን [880] የግእዝ ትርጉም ሰነድ ከላቲን ትርጉም ጋር በpell ታትመዋል [881] G.Horner ደግሞ ግብጡንም ሆነ ዐረብኛውንና ግእዙን ሰነዶች ከእንግሊዝኛ ትርጉም ጋር አሳትሟል [882] ። የ127 ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም አርእስት ወደ ፈረንሳይኛ ቋንቋ በVansleb[883] እና ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ በRiedel ተተርጉመዋል። የግእዙ ትርጉም አርእስት በLudolphus ተተርጉመዋል [884] የግእዝ ትርጉም ሰነድ ደግሞ ወደ ላቲን በLudolphus ተመልሷል[885]

6· 127 ቀኖናት ግእዝ ትርጉም

የ127 ቀኖናት ግእዝ ትርጉም በአንድ አንድ ሁኔታዎች እንደሚደግፈው ከግብጥ–ሳዲቅ ትርጉም ሰነድ ሳይሆን ከዐረብኛ ትርጉሙ እንደሆነ ነው [886] ምክንያቱም የግእዙ ትርጉም ሰነድ በመጠኑ የተለየ ሆኖ

878. Tattam: the Apostolical constitutions...1848

879. P. De Lagade: Acgyptiaca... 209-281: Reliquiac... gracc.9. Funk...dic apostolischen konstitutionen. ገጽ 243–245

880. Jean Périer et Augustin:les 127 canons des apôtres. P.O.T.፥ 8 ገጽ 551–7፡0

881. W. Pell: canons apostolorum aethiopici Leipzig 1975.Funk:dic apostolischen konstitutionen ገጽ 263

882. G. Horner: the statutes of the apostles...1984.

883. J. Vansleb: Histoire dè èglise d 'Alexandrie 1677.

884. Riedel: Kirchenrechtsquellen ገጽ 120·

885. J. Ludolphus: commentarius ...ገጽ 303–314

886. Ludolphus : Historia Aethiopici. Frankfurt. 1681 T. III. C.IV

Ludolphus. Commentarius ገጽ 300–329

ይገኛልና ነገር ግን ከዚህም ከራሱ ዐረብኛ ትርጉም ጋር ባለው ግንኙነት የእነዚህ ቀኖናት ግእዝ ትርጉም ከግብጡ ጋር ሲነጻጸር በመጠኑም ነው ቢባልም በጣም የራቀ ነው ለምሳሌ የግእዙ ትርጉም 40ኛው ቀኖና ከሴራጲዎኖስ ኤጲስ ቆጶስ ቅዳሴ ጋር ግንኙነቶች ያላቸው ልዩ ልዩ ትእዛዛትን ይይዛል ። ስለ ሢመተ ኤጲስ ቆጶስ የሚናገረው 23ኛው ቀኖና ፣ ስለ ሢመተ ቀሳውስት የሚደነገገው 24ኛው ቀኖና ፣ ስለ ሢመተ ዲያቆናት የሚገልጠው 25ኛው ቀኖና ሥነ ሥርዓተ ጥምቀትን የሚያሳየው 35ኛው ቀኖና እና ሌሎችም ቀኖናት ዘዐረብኛው ትርጉም ሰነድ የሉም ። ነገር ግን በተቃራኒው እነዚህ ቀኖናት በሐዋርያውያት ትእዛዛት ይገኛሉ ። የሥርዐተ ቅዳሴ ይዘት ያላቸው ሌሎች ትእዛዛትም አንድም ከሐዋርያውያት ትእዛዛት አንድ ሰነድ ተዛማጅ ትእዛዛት – ቀኖናት ወይም በጥንት ጊዜ ከነበሩ ሌሎች የተወሰኑ ቀኖናት ተወስደው መሆን ይኖርባቸዋል ። እነዚህና ሌሎች ቀኖናት በግእዝ ትርጉም ሰነድ ተይዘዋል ። እነዚህ ሥነ ቅዳሴያውያት ትእዛዛት ስለ ሕሙማን ስለ መንገደኞች ፣ ስለ ዝናማት ፣ ስለ ፍሬ ምድር ፣ ስለ አየር ፣ ስለ ማያተ አፍላግ ፣

ስለ ወንዞች ፣ ስለ አቅርቦተ መስዋዕት ፣ ስለነገሥት ፣ ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ፣ ወዘተ· ስለ ጸሎተ ነግሕ ፣ ስለ ቅዱስ ምስጋና ፣ ስለ ንዑሳን ክርስቲያን የሚጸለይ ጸሎትን የያዙ ትእዛዛት ናቸው ። የዐረብኛና ግእዝ ትርጉም ቀኖናት የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ክፍል–አካል ሆነው ይጠራሉ ስለዚህም Ludolphus እንዲህ ሲል ይጽፋል ።

“Illos (127 Canons Coptes-Arabes) Habessini in octo partes dividunt et evangelistarum apostolorumque scriptis canonicis tanquam Novellas quasdam adjungunt quasi ejusdem sint plane auctoritatis et absolutissimae christianorum landectae” Achelis እንደሚናገረው [887] የ84 ቀኖናት ጸሐፊ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቀጥሎ የቀለሚንጦስ 8 መጽሐፍትን አስቀምጦ መገኘቱ ሲረጋገጥ የሐዲስ ኪዳንን ክፍል ይዘዋል ማለት አይቻልም ነገር ግን ሱርስጥም ሆነ ዐረብ ቀለሚንጦሳዊ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ከሐዲስ ኪዳን መጽሕፍት የሚቀጥለውን ተራ ቁጥር ይዘው ይገኛሉ[888]

887. Achelis: Rcalcnzyclopädic:.. ገጽ 239

888. Ruvens duval, Anciennes chrétiennes litteratures. II Litterature syriaque ue ገጽ 20–91

7· የሐዋርያውያት ቀኖናት ረስጠአ ፡ ረስጠብ ፡ ረስጠጅ እና 85 ቀኖናት ግንኙነት

በአንድ በኩል በረስጠአ ፡ ረስጠብና ረስጠጅ በራሳቸው መካከል በሌላም በኩል በእነዚህ ቀኖናትና በ85 ግሪክ አናት ቀኖናት መካከል ያሉት ግንኙነቶች ሰፊ ምርምርና ሐተታ የሚያስፈልጋቸው መሆናቸው ባይካድም ቦታ ለመቆጠብ በጣም ወደ ዝርዝር አንገባም ሆኖም በመጀመሪያ በረስጠአ በረስጠብና ረስጠጅ መካከል በሁለተኛው ደረጃ በእነዚህ ቀኖናትና ያለጥርጥርም እነዚህ ቀኖናት በተቀነባበሩባቸው 85 አናት ግሪክ ቀኖናት መካከል ንጽጽር ለማድረግ ቢሞከር በሁለቱም በኩል ከፍተኛ ዓይነትና መጠን ያላቸው ልዩነቶችን ፡ ጭማሪዎችን ፡ ቅነሳዎችን ፡ ግድፈቶችን ፡ መጣመርን ፡ የቦታ ዝውውሮችን ፡ ወዘተ· መመልከት ይቻላል[889]

እነዚህን መሰል ግንኙነቶችና ልዩነቶች ብንመረምር በመጀመሪያዎች ረስጠአና ረስጠጅና ተብለው በሚታወቁት ሁለት ቀኖናት መካከል ያሉት ልዩነቶች በእነዚህ ሁለት ቀኖናትና ረስጠብ በሚባሉት ቀኖናት በአንድ በኩልና በሌላም በኩል በ85 ቀኖናት መካከል ካሉት ልዩነቶች ጋር ተመሳሳይ አይደሉም ይህም ምክንያቱም በፊተኞች ሁለት ቀኖናት (ረስጠአና ረስጠጅ) መካከል ያሉት ልዩነቶች ከተወሰኑ መሸጋሸግ = አንድ አንድ ለውጦችና የቀኖናቱ ርእስ ቅርጽ በስተቀር በጣም ጐልተው የሚታዩ አይደሉም ።

በተቃራኒው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀኖናት ረስጠአና ረስጠጅ እና በሦስተኛዎች ቀኖናት ረስጠብ መካከል የሚታዩት ልዩነቶች በጣም ግልጥ ናቸው ምክንያቱም በአንድ በኩል በመጨረሻዎቹ ቀኖናት “ትእዛዛት” በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀኖናትና በ85ቱ ግሪክ አናት ቀኖናት ፈጽሞ የማይታወቁ ትእዛዛት ይታያሉ ለምሳሌ ስለ ጾላት ፡ ስለ ንዋየ ቅድሳት ፡ የሚናገሩት ትእዛዛት በሌላ በኩል የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀኖናት ረስጠአና ረስጠጅ ሰፍቶ መገኘት ለምሳሌ ከመጀመሪያዎች ቀኖናት ረስጠአና ረስጠጅ የመጀመሪያው ቀኖና በሚከተለው መልክ እንደገና ተቀርጿል

899· ከዚሁ ገጽ 120

ሲመተ ሊቀ ጳጳሳት ያለ ኤጲስቆጶሳትም ኤጲስቆጶስም የሆነ መጥሮጶሊስ መኖር እንዲፈጸም አይፈቀድም በዚያ ቦታም ለተገኙትም ሆነ ላልተገኘው ሕዝብ በኃላፊዎቻቸው አማካይነት መልዕክቶችን ያስተላልፋል

ኤጲስ ቆጶስ በክርስቲያኖች ቅዳሜ (እሁድ) ቀን በሦስት ካልተቻለ በሁለት ኤጲስ ቆጳሳት ይሰየማል…" በሌላ መልክ ይኸው የ85 ቀኖናት ቀኖና አንድ ኤጲስ ቆጶስ በሁለት ወይም በሶስት ኤጲስቆጶስ ይሾማል።[890]

እነሆ የቤተ ክርስቲያን ሊቃናት ማዕርጋት ሦስት ተዋረድ ኤጲስ ቆጶስ ፤ መጥሮጶሊስና ሊቀጳጳሳት (ኤጲስቆጶስና መጥሮጶሊስና ሊቀ ጵጵስና) ምክንያቱም ይህን ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ቀኖናውያን ማዕርጋት—ተዋረድ ማለትም ይህ ቀኖና በተጻፈበት— በተደነገገበት ዘመን የቤተክርስቲያን አስተዳደር ሦስት ማዕርጋት በዚህ መልካቸው አይታወቅም ነበር[891] ሲመተ ኤጲስቆጶስ እሁድ ቀን እንዲፈጸም የሚለው ትእዛዝ ከእናት ቀኖናው ጋር ሲነጻጸር አዲስ ትእዛዝ ነው ። እነዚህ ሁሉ ተጨማሪ ገጽታዎች—ክስተቶች ከጊዜ ሂደት ተዕዕኖ የተነሳ ከቤተክርስቲያን ሕይወት የመዳበር ሁኔታዎችና እንቅስቃሴዎች ግፊት በመመንጨት ቆይተው የተፈጠሩ ሁኔታዎች ናቸው ነገር ግን በተለየ የቀኖናቱ ተርጓሚዎች ቀኖናቱን ወደ ግእዝ በሚተረጉሙበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪካውያን ልምዶች ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ ድንጋጌ ዎችን – ትእዛዛትን ለመጨመር ጥንቃቄ ወስደዋል ለምሳሌ ስለ ጽላተ ኪዳን የተጨመረው ትእዛዝ ግልጥ ምስክር ነው[892]

በመጨረሻው እነዚህ ሁሉ እንደተጠበቁ ሁነው በእነዚህ "ሐዋርያውያት" ተብለው በሚታወቁ ቀኖናት መካከል ያሉት ግንኙነቶች በጊዜ ሂደት በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ከተፈጠሩ ችግሮች ጋር እንዲጣጣሙ ቆይተው የተጨመሩ ትእዛዛት ያሉም ቢሆን ሁሉም (ቀኖናት) ከአንድ ምንጭ መምጣታቸውን በግልጥ ያሳያሉ ። ስለዚህም ረስጠእ እና

890· ቀኖና 78 A. Αλιβιζάτου: Οἱ Ιεροί Κανόνες ገጽ 197

891· 85 ቀኖናት ስለተጻፉበት ዘመን ከዚሁ ገጽ 128

892. Ντιμπεκούλου Ζέουντε, Αἱ σχέσεις εκκλησίας καί πολιτείας έν Αιθιοπίο κατά τό σύνταγμα του 1955

Dibekulu Zewde : The Relations between state and Church in Ethiopia According to the Constitution of 1955 1977 ገጽ 109

ረስጠጅ በሚል ቅርጽ– ምኅጻረ.ቃላት ቀኖናት የ81 ፣ የ56 ግእዝ ቀኖናት እና የ85 ግሪክ እናት ቀኖናት ቁጥሮች Vansleb በአስቀመጠው መልክ ከዐረብኛው ትርጉም ቀኖናት ጋርም በማስተያየት በሚከተለው ሰንጠረዥ ይታያሉ[893]

81[894]	81[895]	56[896]	85[897]	84[898]	81	81	56	85	84
1	1	1	1	1	29	27	21	30	30
2	2	2	2	2	30	29	22	31	31
3	3	2	3	3	31	30	23	32	32
4	4	2	4	4	32	31	24	33	33
5	–	3	5	5	33	32	25	34	34
6	7	4	6	6	34	33	26	35	35
7	7	5	7	7	34	34	27	36	36
8	7	6	8	8	35	35	28	37	37
9	8	7	9	9	36	36	29	38	38
10	9	8	10	10	37	37	30	39	39
11	–	9	11	11	38	38-39	31	40	40
12	10	10	12-13	12-13	39	-	32	41	41
13	11	11	14	14	40	40	33	42-43	42-43
14	12	12	15	15	41	41-42	34	44-45	44-45
15	13	12	16	16	42	-	-	46	46
16	14	13	17	17	43	44	-	47	47
17	15	13	18	18	44	45	-	48	48
18	16	13	19	19	45	46	35	49	49
19	17	14	20	20	46	47	36	50	-
20	18	15	21	21	47	48	37	51	50
21	19	15	22	22	48	49	38	52	51
22	20	15	23	23	49	50	38	53	52
23	21	15	24	24	50	51	38	54	53
24	22	16	25	25	51	52	38	55	54
25	23	17	26	26	52	-	39	56	55
26	24	18	27	27	53	53	40	57	56
27	25	19	28	28	54	54	41	58	57
28	26	20	29	29	55	55	42	59	58
					56	–	–	60	59

893· Vansleb Histoire de l èglise .... ገጽ 251

894· አብጥሊሳት

895· አብጥሊሳት

896· ግጽው

897· ግሪክ ቀኖናት

898· ላቲን ትርጉም ቀኖናት

57	-	43	62	61
58	57	44	63	62
59	58	45	64	63
60	51	46	65	64
61	60	47	66	65
62	61	47	67	66
63	-	48	68	67
64	62	49	69	68
65	63	59	70	69
66	64	50	71	70
67	65	50	72	71
68	66	50	73	72
69	67	51	74	73
70	68	52	75	74
71	69	52	76	75
72	70	52	77	76
73	79	52	78	77
74	72	52	79	78
75	73	53	80	79
76	74	53	81	80
77	75	53	82	81
78	76	54	83	82
79	77	54	84	83
80-81	78	55	85	84
	79	56		
	80			
	81			

ሆኖም በሌላ በኩል በፍትሐ ነገሥቱ እየተጠቀሱ በሚገኙበት መልካቸው በብዛት የመመታታት ሁኔታዎች በግልጥ ይታያሉ ማለትም ረስጠእ በሚል ርእስ የሚነገርላቸው "ሐዋርያውያት ቀኖናት" ከ85ቱ ሐዋርያውያት ቀኖናት መምጣታቸው ቢረጋገጥም አለመገናኘትም ይታይባቸዋል ። ምክንያቱም የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብነ እል እሳል "ረስጠእ" በሚል ምኅጻረ ቃል የሚጠቅሳቸው ሐዋርያውያት ቀኖናት የሚከተለው ችግር አለባቸው ረስጠእ በሚል ምኅጻረቃል ከ85 ግሪክ ቀኖናት ጋር በማዛመድ ለተመረመሩት ቀኖናት ቀኖናውያን ጥቅሶች ሁነው ይገኛሉ በዚያም ማለትም የቀኖናት መጨመር መቀነስ መለዋወጥ ወይም መዘዋወር እንደተጠበቀ ሆኖ በረስጠእ ስም የተጠቀሱ ቀኖናት ከ85 ግሪክ ቀኖት

ጋር ይገናኛሉ ለምሳሌ በዓመት ሁለት ጊዜ የሲኖዶስ መጠራት[899] ስለ መጻሕፍተ ሐሰት[900] ስለ ተከሰሰ ኤጲስቆጶስ ጥሪ[901] በኤጲስቆጶስ ላይ ስለሚመሰክሩ ምስክሮች[902] በኤጲስ ቆጶስ የቤተክርስቲያን አስተዳደር[903] ከወሰን ዕላፊ አሥረ ክህነት መስጠት[904] በጉቦ ሲመተ ኤጲስ ቆጶስ[905] ስለ ቅዱሳት መጽሐፍት ዝርዝር[906]

ሌላ ጊዜ ረስጠእ ሁነው የተጠቀሱ ጥቅሶች ግን የረስጠብ ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ሁነው ይገኛሉ ማለትም ከነዚሁ ርስጠእ ተብለው ከተጠቀሱ ቀኖናት ከ85 ቀኖናት ጋር ሳይሆን ከትእዛዛት ዘበእደ ቀለሚንጦስና ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ጋር ነው ግንኙነቶች ያላቸው ለምሳሌ ለኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ቢያንስ በ12 ሰዎች ስለዚህም የአቅራቢያ ቤተክርስቲያን ኤጲስ ቆጶሳት መጠራት[907]

በችግር ወቅት ኤጲስቆጶስ በአንድ ኤጲስቆጶስ መሾም[908] ስለ ኮከብ ቆጣሪዎች[909] ወዘተ ። በአጠቃላይ ይህ የተፈጠረ መማታት በ81 ቀኖናት (ረስጠእ) ፣በረስጠብ የመጀመሪያው ክፍል ትእዛዛት ዘበእደ ቀለሚንጦስ እና ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ሲያጥሩ ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት– Conones ecclesiastici መካከል ብቻ ይወሰናል ።

899- ረስጠእ 36 ረስጠጅ 27 (28) ትእዛዛ 35 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 = 85 ቀኖናት ቀኖና 37
900- ረስጠእ 54 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2·1 = 85 ቀኖናት ቀኖና 60
901- ረስጠእ 69 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·3 = 85 ቀኖናት ቀኖና 74
902- ረስጠእ 70 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 85 ቀኖናት ቀኖና 75
903- ረስጠእ 37 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 85 ቀኖና ቀኖናት ቀኖና 38
904- ረስጠእ (ትእዛዝ) 33 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 34 = 85 ቀኖናት ቀኖና 35
905- ረስጠእ 5·9·15 28 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 = 85 ቀኖናት ቀኖና 29
906- ረስጠእ 81 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2·1 = 85 ቀኖናት ቀኖና 85
907- ረስጠብ 15 ፍትሐ ነገስት አንቀጽ 15·1 = 13
908- ረስጠብ 58 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·2 = 63
909- ረስጠብ 9 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11·11 29·28 33

8· ቀለሚንጦስ ሰመንቱብሔረ ቀኖናት

ቀለሚንጦሳዊ ብሒረ ቀኖናት በሱርስጥ ፡ ግብጥና ዐረብኛ ትርጉም በአንድ ተመሳሳይ መልክ ሳይሆን ነገር ግን ከይዘቱና ሥርዐተ አቀማመጥ ልዩነት ጋር ሲኖር ችሏል ።

8·1 ቀለሚንጦስ ሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት

ቀለሚንጦሳዊ ሱርስጥ ሰመንቱ ብሒረ ቀኖናት በኤዴሳ በ687 እንደተዘጋጀ ይገመታል[910] ምክንያቱም ከላይ እንደታተተው ይህን ስምንቱ ብሔረ ቀኖናትን የያዙት ሰነዶች ከ6ኛው ምዕተ ዓመት ቀድመው የነበሩ ሥራዎች ናቸው ለምሳሌ የመጀመሪያዎችን ሁለት መጻሕፍት የያዘው ኪዳን ዘእግዚእ፡ በ520 የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት–ፓትርያርክ በነበረው ሳዊሮስ ይጠቀሳል[911] ይህ ሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት P.De Legarde ከእሱ በመነሳት ግሪኩን እናቱ ሰነድ ያስተካከለው[912] እና በ1956 ያሳተመው[913] ሲሆን በዚሁ በየ·De Lagarde ሕትመት መሠረትነት ቀለሚንጦሳዊ ሰመንቱ ብሒረ ቀኖናት የሚከተሉትን ሥራዎች ይይዛል ።

1· ኪዳን ዘእግዚእ 1[914]
2· ኪዳን ዘእግዚእ 2[914]
3· ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት[915]
4· ስለ ሲመትና ሀብተ ክህነት ትእዛዛትና ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት[916]
5·ስለ አሥረ ክህነት ትእዛዛት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ዘበእደ አቡሊዲስ[917]

910. F. Nau; Canons des Apôtres :D.T.C.T:II² ገጽ 1617., A. Baumstark, Ueber den Octateuchus-Clement, seine Geschichte und seine handschriftliche ueberlieferung. :Römische Quartalschrift. T.XIV. 1906. 1-45. ገጽ 291 300
911። W.Brooks: The sixth book of the select letters T.B.ገጽ 243
912· P.De legared: Recliquiae...syriac...1856 ገጽ 1-61
913. P. De lagatde: Reliquiae...Graec ገጽ 80 89·74 77· 90 15 89 95· 20 25
914· ስለ ኪዳን ዘእግዚእ ከዚሁ ገጽ 240 246
915· የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖና 1 2 (ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ) ከዚሁ ገጽ 181 196
916· የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖና 3 5 ፡ 16 26
917· የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖና 27–28 ፡ 30 31 ፡ የ32 መጨረሻ ሐረግ 33 34 የ32 የመጀመሪያ ሐረግ

6· ስለ ክህነትና ምዕመናን ትእዛዛት ዘሐዋርያት Statuta plurimorum Apostolorum[918]
7· ስለ ቅዱስ ምሥጢረ ቁርባንና ምስጢረ እምልኮት ትእዛዛት ዘቅዱሳን ሐዋርያት[919]
8· 85 ቀኖናት ሐዋርያውያት[920]

8·2 ቀለሚንጦስ ዐረብኛ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት

በ Riedel ሐተታ መሠረት[921] የቀለሚንጦስ ዐረብኛ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት የሚከተሉትን ቀኖናት ይይዛል ።

1· ኪዳን ዘእግዚእነ 1–2[922]
2· ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት[923]
3· ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ[924]
4· ስለ ስጦታና ሀብተ ክህነት ትእዛዛትና ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት[925]
5· ስለ አሥረ ክህነት ትእዛዛት ሐዋርያውያት ዘበእደ ቀለሚንጦስ (ጸሎቶች ሳይጨምሩ) የቀኖና 11 መጨረሻው ክፍልና የቀኖና 12 የመጀመሪያ መስመሮች (እኔ የዮሐንስ ዘብዴዎስ ወንድም ያዕቆብ አለ የሚለው ሐረግ ሲቀር (እና ቀጥሎም ከቀኖናት 13–15 እና 17–26 አንድ አንድ ይዘቶች ጭምር[926]
6· ስለ ካህናትና ምዕመናን ትእዛዛት ወይም– Statuta plurimorum apostolorum [927]

918· የሐዋርያውያት ትእዛዛት 8ኛ መጽሐፍ ቀኖና 29፡ 6 29
919· ከዚሁ ገጽ
220· Pitra: Juris Ecclesiastici Graecorum. T.I.
921. Riedel: Die kirchenrechtsquell ገጽ 156 157 Ms. Arabe de paris No 252
922·1–2 መጻሕፍተ ኪዳን ዘእግዚእ የሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት የመጀመሪያዎችን ሁለት መጻሕፍት ይይዛሉ ።
923· 2ኛው መጽሐፍ የሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 2ኛው መጽሐፍም ነው ነገር ግን በሱርስጥና ዐረብኛ ሰመንቱ ብሔራተ ቀኖናት መካከል ልዩነቶችና ሌሎች ዝርዝሮች ነገሮች እንደአሉ Rahmani ያመለክታል ። Testamentom ገጽ X-XI
924· ይህ 3ኛው መጽሐፍ ከሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ጋር አንድ ነው
925· ይህ 4ኛው መጽሐፍ በሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት የተያዘው ነው
926· ይህም 5ኛው መጽሐፍ ከሚታየው ልዩነቶች ጋር በሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት የሚገኘው 5ኛው መጽሐፍ ነው ሆኖም ሥርዐተ ጸሎት እና ቀኖናት 16–26 ይጐድላሉ ።
927· 6ኛው መጽሐፍ ሰምንቱ ብሔረ ቀኖናት ከሱርስጥ ሰነድ ጋር አንድ ነው የቀኖና 32 የመጀመሪያው ሐረግ ሲቀር በስተቀር

7· የቀኖና 32 መጀመሪያ ሐረግ ብቻ [928]

8· 81 ቀኖናት[929] Bibliotheque National de Paris በሚገኝ የእጅ ጽሑፍ የተያዘው ዐረብኛ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት[1930] በሕዳጉ ሌሎች የቀኖናት ትእዛዛትን ይዞ ሲገኝ[931] 2ኛው መጽሐፍ በ28 ቀኖናት ተከፍሎ ይታያል ። 3ኛው መጽሐፍ ድርብ ክፍፍልን ሀ· 22–47 ቀኖናትንና ለ· 31–68 ቀኖናትን ይዞ ይገኛል[1932] ። 5ኛው መጽሐፍ በ12 ቀኖናት ሲከፈል 7ኛው መጽሐፍ ድርብ ቁጥርን ይዘው ይታያሉ (ቁጥሮችን ይደግማሉ) ።

በሌላ በኩል የዐረብኛ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 7ኛው መጽሐፍ ይዘት Canones qui statuta Fuerunt distincte ab unoquoque per Ebediesus በሚል ርእስ በሚገኘው (P) EBediesus መድበለ ቀኖናት ይገኛል[933] እንደገናም ስለ ምሥጢረ እምልኮት በሰምኦን ቀነናዊ የተላኩ ቀኖናት[934] ወይም ቀዳማውያት ትእዛዛተ ሐዋርያት[935] በሚል ርእስ በቀለሚንጦስ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ይገኛል ። እንደ Funk [936] በ Ebediesus የተሰበሰበና በMaio የታተመ[937] ሱርስጥ ሰነድ በግእዝ ትርጉምም እያንዳንዱ 25 ቀኖናትን በያዙ ሁለት ሰነዶች ሊተላለፍ ችሏል[938] በመጨረሻ የሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 5ኛውና 6ኛው መጽሐፍት ከምሥጢረ እምልኮት ትእዛዛተ ሐዋርያት ጋር አንድ ዓይነት ናቸው[939] በሌላ በኩል በልዩ ልዩ ዐረብኛ የእጅ ጽሑፎች ምልዓተ ምሥጢራት በሚል ርእስ ሰነድ አንድ ዓይነት ሥራ ይገኛል ለምሳሌ

928· የ7ኛው መጽሐፍ ይዘት ፍሬ ነገር የሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 7ኛው መጽሐፍ ይዘት ነው ።

929· 81 ቀኖናት ከሱርስጥ ሰምንቱ ብሔረ ቀኖናት 81 ቀኖናት ጋር አንድ ነው ።

930· No. 252 P. De Lagarde: Reliquiae ...Graec ... ገጽ X1

931· ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ቀኖና 1

932· ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ በዐረብኛና በግብጥ ትርጉም ባለበት መልኩ

933. A. maio: Scriptorum.... T.X. ገጽ 17 22

934. MS. arabe De Paris No. 243 FOL 205-220

935. MS. ARABE DE PARIS No. 252 ገጽ 38–52

936. Funk: Die Apostolischen Konstitutionen 245–246

937. A.maio: Scriptorum.... ገጽ 17–22

938· ሆኖም በእለዉ ሲኖዶስ 25 ቀኖናት አልተያዙም ።

939· J.Pitra: Juris Ecclesiastici Graccorum T.1

በBibliotheque de paris የሚገኘው እና Rahmani የገለበጠው[940] የእጅ ጽሑፍ Saint clement ordona de cacher du vulgaire በሚል ርእስ[941] 8 መጻሕፍትን ይይዛል ። ቅርጸ ርእሱ ለቅዱስ ኤፍሬም የተሰጠ ዐረብኛ ሰነድ ከጀርመንኛ ትርጉም ጋር[942] ሱርስጥ ሰነዱም በ Carl Bezold[993] ቆይቶም ይኸው ዐረብኛ ሰነድ ከእንግሊዝኛ ትርጉም ጋር በM.D.Gibson ታትሟል[944] በአጠቃላይ እንደሌሎች ሐዋርያውያት ቀኖናት ተመሳሳይ ሥርጭትም የሌለው ይህ ሰነድ ..... በውስጣቸው ካሉት ምስጢራት ምክንያት የተነሳ ለሁሉም እንዳይሰራጩ—ለሕዝብ እንዳይሰራጩ ከታዘዙት 8 መጽሐፍተ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ጋር ይመሳሰላል ።
በግእዝ ትርጉም የሚገኝ ወይም ምን ዓልባት በግእዝ ተዘጋጅቶ የመጣ ተአምረ ኢየሱስም የሚባል አዋልድ መጽሐፍ ጴጥሮስ ከኢየሱስ የሰማቸውን ሁሉ ለቀለሚንጦስ እስተላልፎለት በ8 መጽሐፍት እንደቀዳቸው አድርጐ ይናገራል[946]

ነገር ግን በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት መጨረሻ ቀኖና (85) የተጠቀሱ 8 መጻሕፍት በአሁኑ ጊዜ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ዘሰመንቱ መጻሕፍት ተብለው የሚታወቁት መጻሕፍት እንጂ ከላይ የተጠቀሱት 8 መጻሕፍት (ዐረብኛ አዋልድ) እንደአልሆኑ ታውቋል ።

8·3 ግብጥ ሰብዐቱ ብሔረ ቀኖናት

እንደ P.De Lagared ሐተታ ግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ከዐረብኛ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ሰባቱን መጻሕፍት (2–8) ይይዛል [947] ማለትም በግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት የዐረብኛው ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት የያዘው የመጀመሪያው መጽሐፍ ኪዳን ዘእግዚእ አይገኝም ።

940. MS.Arabe De Paris CAT. 70-76 ገጽ 18–19·

941. A-Harnack: Die Üeberlieierung ገጽ 779–786

942· የግርጌ ማስታወሻ

943· Carl Bezol, Die Schatzhoehle: Leipzig. 1883

944. Carl Bezol, Die Schatzhoehle: Leipzia. 1883

945. G.Gibson: Arabica Apocrypha: Studio Syriaca. London 1801 ገጽ VIII

946. Sylbain Grebaut: les Miracles de Jèsus-Texte ethiopien puouee et traduit. P.O. T. XII ገጽ 550–552

947. P.De Lagarde: Reliquiae... Graec. ገጽ X1

እንደ F.Funk ግን የግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት 7ኛው መጽሐፍ በዐረብኛው ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 81 ሐዋርያውያት ቀኖናት ፈንታ 56 ሐዋርያውያት ቀኖናትን ይዞ ይገኛል[948]

ዘሌላ ዘኩልበንጽጽር መልክ ለመመልከት ሲሞከር በአጭሩ በሱርስጥ ፣ ዐረብኛና ግብጥ ብሔራተ ቀኖናት መካከል የጐላ ልዩነት አይታይም ስለዚህ

1/ በሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ሁለት ኪዳናት ዘእግዚእ ሰፍረው ሲታዩ በዐረብ ሰሙንቱ ብሔረ ቀኖናት አንድ ኪዳን ብቻ ሲያዝ በግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት አንዱ ወይም ሁለቱም ኪዳናት ተዘለ ዋል።

2/ በዐረብ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናትና በግብጥ ሰባቱ ብሔረ ቀኖናት የተያዘው ግብጣዊ ቤተክርስቲያናዊ ትእዛዝ በሱርስጥ ሰመንተ ብሔረ ቀኖና አይገኝም

3/ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 83 ቀኖናት ፣ በዐረብ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት 81 ቀኖናት እና በግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት 56 ቀኖናት ሁነው ሰፍረዋል ። የግእዝ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናትን—ሲኖዶስን ስንመለከት ሁለት ኪዳናትን ከመያዙ ጋር ቁጥሮችን አንድ በአንድ በማነጻጸር ባይሆንም በይዘት ከተጠቀሱት ሰመንቱ ብሔራተ ቀኖናት የመራራቅ መንፈስ እምብዛም ሊታይበት አይችልም ሆኖም ግን ዝርዝር ምርምርን ይጠይቃል ።

8·4 የግእዝ ሰመንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ—ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ

ቀደም ብሎ እንደተመለከተው በየትኛውም ቤተክርስቲያን ከልል የጋራ ተቀባይነትን አግኝተው በአገልግሎት ላይ ከሚገኙት 27 መጻሕፍተ ሐዲስ ኪዳን በተጨማሪ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን "ሲኖዶስ ዘአበው ሐዋርያት ቅዱሳን" ወይም ከአጭሩ "ሲኖዶስ" በሚል ርእስ በሚታወቀው የቤተርስቲያን መድበለ ቀኖናት ሰመንት ብሐረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ መገኘቱ ይታወቃል ።

948. Funk. Die apostolischen konstitutionen ገጽ 263

ሁኖም ግን በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን "ሲኖዶስ" ተብሎ የሚጠራ መድበለ ቀኖናት — ሥርዓታተ ጸሎትና ቅዳሴ መኖሩ ቢታወቅም በውስጡ ቀኖናትና ሌሎች ትእዛዛት የትኞቹ መሆናቸውን በትክክልና በግልጥ ለይቶ ማስቀመጡ አዳገች ይሆናሉ ምክንያቱም ቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛው መድባለ ቀኖናት ይህ ነው ብሎ ወስኖ በቤተክርስቲያን ያስተላለፈው ዓይነትና መጠኑ የተረጋገጠ ሲኖዶስ መኖሩ ያጠራጥራል ።

ስለዚህ ከአንድ ሲኖዶስ ወደ ሌላ ሲኖዶስ የእጅ ጽሑፎች ልዩነት ሊታይ ይችላል በአጋጣሚም እስከ አሁን ለሕትመት የበቃ ሲኖዶስ የለም።

እንግዲህ 'ሲኖዶስ' ምን ይመስላል? ምን ይዟል? ወዘተ· ብሎ ለማሳየት ራሱን የቻለ ጥናት የሚጠይቅ ስለሆነ ወደዚያ አንገባም ። ለዚህ ጽሑፍ መንደርደሪያ ይሆን ዘንድ ግን ለጊዜው በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር የሚገኝ አንድ የእጅ ጽሑፍ ሲኖዶስን ለመመልከትና ለመጠቀም ተሞክሯል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መደበኛው መድበለ ቀኖናት ነው? ለሚለው ጥያቄ ወደፊት ለማጥናት ጥረት መደረግ እንደአለበት የተጠበቀ ሁኖ ።

ይህ ሲኖዶስ የሚከተሉትን ቀኖናትና ፡ የጸሎትና ቅዳሴ ሥርዓታት ይዞ ይገኛል ።

1·ልዩ ልዩ ቀኖናት ሐዋርያውያት

1·1 72 ቀኖናት ዘአበው ሐዋርያት

እነዚህ ቀኖናት "ሲኖዶስ ዘአበው ሐዋርያት··· በሚል ርእስ ተነስተው ቁጥራቸው 72 ሲሆን የመጀመሪያው ቀኖና(ቀኖና ትእዛዝ 1) "ይበሉ ዮሐንስ··· " ብሎ በመጀመሪያ የሐዋርያትን ስሞች ይዘረዝራል ። የመጨረሻው ቀኖና—ትእዛዝ (ቀኖና ትእዛዝ 72) ስለ ሥርዐተ ክህነት···ይናገራል ።

እነዚህ ቀኖናት በፍትሐ ነገሥት ብዙ ጊዜ ረስጠብ ተብለው የሚጠቀሱት ቀኖናት ናቸው

1·2· 56(57)ቀኖናት ዘቤተክርስቲያን

"ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ዘወሀብዋ ሐዋርያት ቅዱሳን···በእደ ቀለሚንጦስ···" ብለው የሚነሱት ቀኖናት 57 ወይም 56 ቀኖናት ሲሆኑ

የመጀመሪያው ቀኖና—ትእዛዝ (ቀኖና — ትእዛዝ 1) ለአንድ ኤጲስ ቆጶስ ሥርዐተ ሲሞት ለንት ኤጲስ ቆጶሳት መገኘት እንደሚኖርባቸውና የመጨረሻው ቀኖና—ትእዛዝ 56 ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን ጨምሮ ይናገራል ።

መደበኛ ቀኖናት 56 ሲሆኑ 57ኛው ጭማሪ ነው በሌላ በኩል በፍትሐ ነገሥት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር በሚናገርበት ጊዜ ረስጠጅ ሳይሆን[949] ረስጠብ ተብሎ ሲጠቀስ 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ግን አልተመለከቱም ።

1·3 ሲኖዶስ ዘቀለሚንጦስ ዘጸሐፈ ጴጥሮስ ረድእ ርእሰ ሐዋርያት

ይህ ሲኖዶስ በቀኖና ተከፋፍሎ የተቀነባበረ ሲኖዶስ—ምዕላደ ቀኖናት አይደለም ። በፍትሐ ነገሥትም አልተመለከተም[950]

1·4·30 ቀኖናተ ሐዋርያት

"ሲኖዶስ መጽሐፈ ዜናሆሙ ለሐዋርያት…ሲኖዶስ ዘጸሐፈ ቀለሚንጦስ በእንተ ሐዋርያት…"በሚል ዝርዝር ርእስ የሚነሳ ሲኖዶስ—ምእላደ ቀኖናት (30 ቀኖናት) ከመግቢያ ሰፊ ዝርዝር ጀምሮ ከሥርዐተ ጽዮን ጋር ይመሳሰላል[951]

ቀኖናት—ሥርዐተ ጽዮን በፍትሐ ነገሥት ዓይን ተብለው ከሚመለከቱ በስተቀር በሰነዱ ውስጥ በአንድም ቦታ ላይ አልተጠቀሱም።

1·5·82 ቀኖናት—አብጥሊሳት ዘሐዋርያት

"ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ዘዜነዋ ቀለሚንጦስ በእንተ ጴጥሮስ…ወይእቲ ትሰመይ አብጥሊስ" እነዚህ አብጥሊሳት ተብለው የተሰጡት 82 ቀኖናት የመጀመሪያው ቀኖና—አብጥሊስ (ቀኖና—አብጥሊስ 1) አንድ ኢጲስ ቆጶስ ሊቀባ ስንት ኢጶስ ቆጶሳት መገኘት እንደሚገባ ሲደነገግ የመጨረሻው ቀኖና—አብጥሊስ (ቀኖና—አብጥሊስ 82) ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር ይናገራል ። ይህም እንደ 56 ቀኖናት 56ኛ ቀኖና 8

949 ሲኖዶስ ገጽ 1—48
950 ሲኖዶስ ገጽ 48—54
951 ሲኖዶስ ገጽ 54—58

መጻሕፍት ቀለሚንጦስን ይደምራል ግን በፍትሐ ነገሥት እነዚህ ቀኖናት አሁንም አብዛኛውን ጊዜ ረስጠአ ተብለው ሲጠቀሱ 8 ቀኖናትን ይዘው እንደሚገኙ በተጠቀሰው ቀኖና 82(ረስጠአ 82) አልተመለከቱም[952]

1·6 ቀኖናተ ስምአን ቀነናዊ·

"ሲኖዶስ ዘአበው ሐዋርያት ቅዱሳን…ሥርዐተ ክህነት ዘስምአን ቀነናዊ" በሚል ርእስ የሚነሳ ክፍልም ሲኖር በፍትሐ ነገሥት አልተጠቀሰም[953]

1·7 80 ቀኖናት—ሥርዐተ ሐዋርያት

"ሲኖዶስ ሥርዐተ ሐዋርያት ምስለ ቀለሚንጦስ…" ሲኖዶስ ሥርዐተሐዋርያት ተብለው ከተያዙ 80 ቀኖናተ ሐዋርያት ቀኖና 1 ስለ አንድ ሲመተ ኤጲስቆጶስ ስንት ኢጶስቆጶሳት መገኘት እንደሚኖርባቸው ሲደነገግ የመጨረሻው ቀኖና (ቀኖና 80) ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ያመለክታል ። ሆኖም ግን 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን አይጨምሩም[954] ከቁጥሮች ልዩነት በስተቀር ከ56 ቀኖናት እና 82 ቀኖናት (1·2 እና 1·5) ጋር አንድ መሆናቸው ቢታይም ዝርዝርም ባለመሆናቸው ምን አልባት የመጀመሪያዎች 85 ግሪክ ቀኖናት ግልባጩ ይሆናሉ የሚል አስተሳሰብ አለ ።

1·8 80(81)ቀኖናት—አብጥሊሳት ዘሐዋርያት

"ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን ዘሀገረ ቀለሚንጦስ ወይእቱ ትስማይ አብጥሊስ" በሚል መነሻ የሚጀምሩት ቀኖናት 80 (81) ቀኖናት አብጠሊሳት ሲኖራቸው አሁንም የመጀመሪያው ቀኖና—አብጥሊስ (ቀኖና—አብጥሊስ 80) ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ይናገራል…8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስም ተጨምረው ተመልክተዋል።እነዚህም ቀኖናት በስያሜ ከ82 ቀኖናት አብጥሊሳት ጋር ሲመሳሰሉ በይዘት ከ56 ፡ 82 ፡ 80 ቀኖናት ጋር አንድ ናቸው[955] እስከአሁን በቁጥሮች 1.1, 1.2, 1.3, 1.4,

951 ሲኖዶስ ገጽ 58- 70
952 ሲኖዶስ ገጽ 76 81
953 ሲኖዶስ ገጽ 81 86
954 ሲኖዶስ ገጽ 86--98
955 ሲኖዶስ ገጽ 86 98

1.5, 1.6, 1.7 እና 1.8 ከተዘረዘሩት ቀኖናት 1·3 እና 1·6 በስተቀር የቀሩት 30/82 80/81 እና 80 በአንድነት 56 እና 72 ቀኖናት የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ የተጠቀመባቸው ቀኖናት ሲሆኑ አሁንም ከ30 ቀኖናት በስተቀር በሌሎች ቀኖናት አልፎ አልፎ ግን ብዙ ጊዜ "ሀሎ በፍትሐ ነገሥት ቀኖና" እያለ በፍትሐ ነገሥት የተጠቀሱትን አንድ አንድ ቀኖናት 56 (57) 82 80 (81) እና 80 ይዘቶች ከማስፋትና ከማጥበብ በስተቀር አንድ ዓይነት ቀኖናት ናቸው ማለትም ከ85 ግሪክ እናት ቀኖናት በመነሻነት ግልባጮች ናቸው ።

2· ሲኖዶሳውያት ቀኖናት

2·1 መልዕክተ ጴጥሮስ

በዚህ ክፍል በመጀመሪያ መልዕክተ ጴጥሮስ የሚል ርእስ ሲመለከት ከርእሱ አልፎ የተዘረዘረ ነገር የለም[956]

2·2 24 ቀኖናት ዘእንቆራ[957]

2·3 14 ቀኖናት ዘአኩሳርያ–ዘአፍራቅያ–ቅርጣግና[958]

2·4 20 ቀኖናት ዘኒቅያ[959]

2·5 83 ቀኖናት ዘኒቅያ[160]

2·6 ሕንጻ መነኮሳት ዘ 318 አበው[961]

2·7 25 (19) ቀኖናት ዘግንግራ[962]

2·8 25 ቀኖናት ዘአንጾኪያ[963]

2·9 59 ቀኖናት ዘላኦዶቅያ[964]

2·10 21 ቀኖናት ዘሰርድቅያ (ሲርድቅያ)[965]

---

956 ሲኖዶስ ገጽ 99 ቢሆንም መቅድሙ ብቻ ተመስክቶ ይዘቱ በሰነዱ አልተጠቀሰም

956 ሲኖዶስ ገጽ 99

957. ሲኖዶስ ገጽ 99 104

958. ሲኖዶስ ገጽ 105 107

959. ሲኖዶስ ገጽ 110 115

960. ሲኖዶስ ገጽ 116 136

961. ሲኖዶስ ገጽ 137 140

962. ሲኖዶስ ገጽ 108 109

963. ሲኖዶስ ገጽ 140 142

964. ሲኖዶስ ገጽ 142 154

965. ሲኖዶስ ገጽ 154 158

2·11 14 ቀኖናት ዘቁስጥንጥንያ[966]

2·12 11 ቀኖናት ዘኤፌሶን[967]

2·13 11 ቀኖናት ዘኤፌሶን[968]

2·14 29 ቀኖናት (አምስተኛው ጉባኤ ቦታው ያልተገለጠ)[969]

2·15 23 ቀኖናት (ስድስተኛው ጉባኤ ቦታው ያልታወቀ)[970]

3· ከሲኖዶሳውያት ቀኖናት ቀጥለው የሚገኙት ልዩ ልዩ ስያሜዎችን የያዙ መጽሕፍት

3·1 ትርጓሜ 10 ቃላት ዘዮሐንስ አፈወርቅ

ከትልቅ ሰድ ንባብ በኋላ[971]

ልዩ ልዩ ትእዛዛት ይከተላሉ[972]

3·2·1 ግጸዌ ትምህርት ሕግ ወሥርዐት ወተግሣጽ[973]

3·2·2 ግጸዌ ትምህርት ከመይትፈለጡ[974]

3·2·3 ግጸዌ ወትምህርት አብሱጠሊስ ቀኖና በእንተ ፍርሃተ እግዚአብሔር[975]

3·2·4 ግጽው ወተግሣጽ ፣ አብስጠሊስ ቀኖና[976]

3·2·5 ግጽው ሥርዐተ ትምህርት ጥበብ ፣ ተግሣጽ ፣ አብስጠሊስ[977]

3·2·6 ቀኖናት በእንተ ንስሐ[978]

3·3·7 ቀኖናት ያልተሰጣቸው ቀኖናት[979]

---

966. ሲኖዶስ ገጽ አልተዘረዘሩም

967. ሲኖዶስ ገጽ አልተዘረዘሩም

968. ሲኖዶስ ገጽ አልተዘረዘሩም

969. ሲኖዶስ ገጽ አልተመለከቱም

970. ሲኖዶስ ገጽ አልተመለከቱም

971. ሲኖዶስ ገጽ 158—164

972. ሲኖዶስ ገጽ 164—166

973. ሲኖዶስ ገጽ 166 168

974. ሲኖዶስ ገጽ 130—175

975. ሲኖዶስ ገጽ 175—109

976. ሲኖዶስ ገጽ 109—190

977. ሲኖዶስ ገጽ 191—208

978. ሲኖዶስ ገጽ 209—212

979· ሲኖዶስ ገጽ 212—238

4· መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ

በመጨረሻ የሚገኙት ስምንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ—ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ ሲሆኑ በመጀመሪያ ይቤ ቀለሚንጦስ" ብሎ ጀምሮ የተለዩ ርእሶችንም ሆነ ቀኖናትን ሳያመለክት ።

በስድ ንባብ ይዘቱን ያትታል ቢሆንም

4·1 ይቤ ቀለሚንጦስ

4·2 ቀዳሚ ምሥጢራት ዘከሠተ ጴጥሮስ[980]

4·3 ንቀድም ወንጽሕፍ ኃይለ ወተአምረ[981]

4·4 ዘነግሮ ጴጥሮስ ለቀለሚንጦስ[982]

4·5[983]

4·6 ሥርዐት ዘቅድስት ቤተክርስቲያን[984]

4·7 ቀለሚንጦስ ሣልስ ነገረ ዘበንስሐ[985]

6·8 በትር ዘዘበጦ ለሰይጣን[986]

እንግዲህ እነዚህ ስምንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ተብለው የተመለኩቱት መጻሕፍት በአንድ በኩል በጣም ዝርዝር ከመሆናቸው ጋር ሥነ ሥርዐትን ይዘው የተቀረጹ አይደሉም ። በሌላም በኩል እነዚህ መጻሕፍት ናቸው ወይ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቁጥር ወደ 81 መጽሐፍት ያሰደረሱት? ይህን ማረጋገጥ የዚህ ጽሑፍ ዓላማና ግብ አይደለም በሌላ በኩል ፍትሐ ነገሥት ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው 81 መጻሕፍት በማለት ቢነሳም መጻሕፍቱን ሲዘረዝር 72 መጽሕፍትን ነው ቆጥሮ የሚያቆመው ።

ስለዚህ የፍትሐ ነገሥት መትርጉማን ይህን 72 ቁጥር ወደ 81 ለማድረስ ሁለት ኪዳናትን ፣ አንድ ዲድስቅልያንና ስድስት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን ማለትም (2+1+6 =9) ዘጠኝ መጽሐፍትን ከ72 መጻሕፍት ላይ በመደመር 81 መጻሕፍትን ያሳያሉ ።

980. ሲኖዶስ ገጽ 238—253
981. ሲኖዶስ ገጽ 254—284
982. ሲኖዶስ ገጽ 285—308
983. ሲኖዶስ ገጽ አልተመለከተም
984. ሲኖዶስ ገጽ 309—313
985. ሲኖዶስ ገጽ 313—324
986. ሲኖዶስ ገጽ 325—339

ነገር ግን በአንድ በኩል መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ አሁን ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ፰ መጻሕፍት ሲሆኑ በሌላ በኩል እንደ ፍትሐ ነገሥት መትርጉማን ስድስት ናቸው ። አሁንም እነዚህ የቀለሚንጦስ መጻሕፍት ስመንት ሲባሉ እነማን ናቸው? ስድስትስ ሲባሉ የትኞቹ ናቸው?

እነዚህን መጻሕፍት ለይቶ ማሳየቱ ከጥናትም አልፎ በግልጥም በቤተ ክርስቲያን በኩል ቢገለጥ ይመረጣል ።

እንግዲህ ስመንቱም ሆኑ ስድስት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ በአጭሩ ከላይ በተመለከተ ቅጻቸው ከሱርስጥ ወይም ዐረብኛ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ወይም ከግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ ጋር የሚዘመዱ አይደሉም ።

ቢሆንም በሲኖዶስ የተያዙ ቀኖናት ሐዋርያውያትን

— ረስጠአ
— ረስጠብ
— ረስጠጅ
— ሁለቱ ኪዳናትን

አስመልክቶ ነው ሲኖዶስ ከሱርስጥና ዐረብኛ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ወይም ከግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ ጋር የሚቃረበው ።

እንግዲህ ከአሐዝ አንጻርም ሆነ ከይዘት አንጻር ስመንቱ ወይም ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ

1· ስመንቱ ሱርስጥ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ
2· ስመንቱ ዐረብ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ
3· ሰብዓቱ ግብጥ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ

በመባል የሚታወቁትን መድበላተ ቀኖናት በንጽጽር መልክ ማየት ይቻላል ።

5· ኪዳናት ዘእግዚእነ ወመድኃኒነ

ሁለት ኪዳናት በሲኖዶስ የመጨረሻ ክፍል ሰፍረው ይገኛሉ ።

5·1 አንደኛው ኪዳን ዘእግዚእ ዝርዝር መግቢያ ሐታታ ሲኖረው 55 ቀኖናትን ይዞ ይገኛል ።

5·2 ኪዳን ዘእግዚእ በቀኖና ተቀነባብሮ ሳይሆን በስድ ንባብ ተቀርጾ የሚገኝ መጽሐፍ ነው እነዚህም

ከመጽሐፈ ኪዳን ልዩ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል ።

9· ዲድስቅልያ ዘሐዋርያት = ድስቅ

ዲድስቅልያ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ወይም በሌላ አጠራር ምልዕት ዲድስቅልያ ዘ12 ሐዋርያት ወእርድእት[987] ቀኖናዊና ሥርዐተ ቅዳሲያዊ ይዘትና ቅርጽ ከአሏቸው የጥንት ቤተክርስቲያናውያን ሥራ ምች አንዱ ነው ። ዲድስቅልያ — ዲዳስካልያ Didascalia Διδασκαλία τών Αποστόλων የሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉም ትምህርት ማለት ነው[988] ዲድስቅልያ በፍትሐ ነገሥት የሚጠቀሰው "ድስቅ" በሚል ምኅፃረ ቃል ነው[989]

9·1 ዲድስቅልያ የተጻፈበት ዘመንና ጸሐፊ

ዲድስቅልያ ስለ ተጻፈበት ዘመንና ጸሐፊ ሲያያዝ የመጣው ልምድ አፈታሪክ ከላይ ስለ ሐዋርያውያት ቀኖናትና ስለ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ተደጋግሞ የታወሳ ነው[990] ። የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብነ እል እሳል ዲድስቅልያ 12ቱ ሐዋርያት ከሐዋርያው ጳውሎስና ኤጲስቆጶሱ ያዕቆብ ጋር በኢየሩሳሌም ተሰብስበው እንደጻፉት ይቀበላል[991] ። በዚህ መሠረተ ሐሳብ መሠረት ዲድስቅልያ በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ሲኖዶስ 49—50 ዓ/ም ተጽፏል ነው[992]

ነገር ግን ዛሬ ያለው ግንዛቤ ዲድስቅልያ የሐዋርያት ሥራ እንደአልሆነና ስለዚህም በዘመነ ሐዋርያትም እንደአልተጻፈ ነገር ግን ሙያው ሐኪም ፥ ትውልዱ አይሁዳዊ የሆነና መጠነኛ የሥነ መለኮት ትምህርት እና በአስተዳደር ሥራ ብቁ ልምድ ያለው የኋላ ስም አልባ ጸሐፊ ሥራ እንደሆነ ነው ። ይህ ጸሐፊ በመጀመሪያ የኤጲስ ቆጶስን ሥራ

987. P.D. Lagarde. Didascalia Apostolorum, Leipzig, 1854.

988. ፍትሐ ነገሥሥት መቅድም ክፍል 2

989· ፍትሐ ነገሥትት መቅድም ክፍል 2

990. Funk: La date de la Didascalie Des Apôtres. R.H.E. 1901 T. II ገጽ 198። Kircbengeschichte Abhandlungen Und Untersuchungen. Aderborn 1907. T.3. ገጽ 275—284. P.Galtier: La Date de La Didacalie Des Apôtres. R.H.E. 1947. T.42 ገጽ 55-351. J. Stam: Eposcopacy on the appostolic tradition. BASEL. 1936 ገጽ 6. Plöchl. W. Geschichte der Kirchenrechts Zweiter Aufläge ገጽ 108 ገጽ 696—703 ።

991· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

992· ሱርስጥ ዲድስቅልያ ምዕራፍ 25 ተመልከት

ከሕክምና ሙያ ጋር ያነጣጥራል ፣ በኤጲስቆጶስ ትምህርት የተቀረጸውን የክርስቲያኖች ጠባይ ሕመምተኞች በሐኪሞች ከሚደረግላቸው ልዩ ልዩ ቀዶ ጥገናዎች ጋር ያመሳስላል ። ይህን ዲድስቅልያ ለመጻፍ የበለጠ ብሉይ ኪዳንን ወይም ሐዲስ ኪዳንን ነው የተጠቀመ [993] ። ነገር ግን እንዚህ ንድፈ ሐሳቦች ስለ ጸሐፊው ማንነት በተለያየ በሙያ ሐኪም [994] በትውልድ አይሁዳዊ ስለመሆኑ በራሳቸው ማረጋገጫዎች ሊሆኑ አይችሉም ምክንያቱም በኤጲስ ቆጶስና ሐኪም መካከል ንጥጥር ለማድረግ ከዚያም ይህ የኤጲስ ቆጶሱና የሐኪሙ ንጽጽር ማለትም በኢጲስ ቆጶሱ የታነጸው የክርስቲያኖች ሞራላዊና መንፈሳዊ እድገት ለሕመምተኞች በሐኪም ቀዶ ጥገና ከሚደረገው ፈውስ ጋር ለማነጣጠር የግድ አንድ ሰው ሐኪም መሆን አይኖርበትም ። ማንም በቂ ማኅበራዊ ትምህርትና ልምድ ያለው ሰው ይህን ንጽጽር ማድረግ አያዳግተውም ። በሰፋት ብሉይ ኪዳንንም ሆነ ሐዲስ ኪዳንን መጠቀምን በሚመለከት የጸሐፊው አይሁዳዊ ትውልድነትን አያረጋግጥም ። ምክንያቱም ከሁለት ተኩል ምዕተ ዓመታት ልምድ በኋላ ማንኛውም ክርስቲያን ብሉይ ኪዳንንም ሆነ ሐዲስ ኪዳንን ለመጠቀም የሚያዳግተው አይሆንምና ነው። ነገር ግን በአንጻሩም ከሚመረመረው ፍሬ ነገር አንጻር ክብደቱን በአንዱ ወይም በሌላው ሌላ ይመጣል ፣ የበለጠ በብሉይ ኪዳን ወይም በሐዲስ ኪዳን ሊጠበብ ይችላል ። ከዚያም ሥነ መለኮታዊያን ፍሬ ነገሮችን ባለመመር መሩ መጠነኛ ሥነ መለኮታዊ ምሁር ነበር በማለት ስለተሰጠው ጠባይ እውነትነት ሊኖረው አይችልም ምክንያቱም ጸሐፊው ሥነ መለኮታዊ ይዘት ያለው ጽሑፍ ለመጻፍ ሳይሆን የሕፃናት አስተዳደግ ፣ የትምህርትና፣ ሥነ ምግባር መመሪያን ለመጻፍ ስለነበር ነው ዓላማው[995] ።

ስለዚህ ዲድስቅልያ ምንጓልባት በሶርያ በ3ኛው ምዕተ ዓመት

993. 9. Stam: Episcopcy on the Apostolic tradition ገጽ 6· Quasten: Patrology T. II ገጽ 47 Achelis—Fleming: Die Syrische Didascalic T. U.T. XXV ገጽ 338 Marcel Viard; LA Didascalie Des Apôtres - Introduction, Critique, Esquisse Historique 1990 ገጽ 35።

994. Achelis — Fleming: Dic Syrische Didascale T.U.T. XXV ገጽ 84 (CAN. XXI—XXVI).

995. ምዕራፍ ቀኖናት 2—3

መጀመሪያ አጋማሽ እንደተጻፈ ይታመናል[996] ። በሌላም በኩል ዲድስቅልያ የተጻፈበት ቦታ ፍልስጥኤም በተለይ ኢየሩሳሌም ነው ይባላል። ለዚህም ምክንያት የሚቀርበው ድጋፍ ጸሐፊው የሙሴን ሕግ በማክበርና የአይሁድ ልምድን በመጠበቅ የጸኑ በይሁዳ የሚገኙ ክርስቲያናት በአእምሮው ነበሩ የሚል ነው ።

ይህ አስተሳሰብ በመሠረቱ አእምሮ የሚቀበለው ነው ሲባል ይችላል። ምክንያቱም በቅርጽ መድበለ ትምህርታት — ተግሣጸት ነውና [997] ።

በመንፈስ — በመሠረተ ሃይማኖት የእህትነት ግህበር አንድነት ብሎ ለሚጠራት ማኅበረ ክርስቲያን ከመላው ክርስቲያን ማኅበረሰብ የተላኩ ቤተ ክርስቲያናውያት ትእዛዛትን የያዘ ሥራ ነው[998] ። ዲድስቅልያ በመጀመሪያ ትእዛዘ "ሐዋርያት" ወይም ትእዛዛተ ሐዋርያት በሚል ርእስ በኤጲፋንዮስ ተወስቷል (348—403) [999] ። በሌላ በኩል የሐዋርያት ትእዛዛት የመጀመሪያዎቹ ስድስት መጻሕፍት ጸሐፊ እነዚህን መጻሕፍት ለማዘጋጀት ዲድስቅልያን በምንጭነት ተጠቅሟል[1000]።ቀጥሎም ዲድስቅልያ በOpus Imperfectum in Matthem ጸሐፊ ስውር አፈወርቅ[1001] Pseudochrysostomos 6ኛው ምዕተ ዓመት (መጽሐፈ ቀኖናት "ወይም" ቀኖናተ ሐዋርያት

996. M. Viard, La Didascalie Des Apôtres . ገጽ 37። funk: Ladate de la Didascalie. T.U.E.T.III ገጽ 798። Achelis—Fleming La clate syrische Didascalie. T.U.T.XXX ገጽ 329። Connolly: The Use of Didache in The Didascalia. J.T.S 24/1924 ገጽ 151።

997. ምዕራፍ (ቀኖና) 1—7· 17·1·10 ፡ 4

998. Stam: Episcoapcy on the Apostolic Tradition ገጽ 66

999. Epiphanius: Adversus Haereses. LXX. T.10. P.G.T. 42 ዐምድ 358 LXXV.6 P.G.T. 42 አምድ 512 LXXX.7— P.G.T. 42 ዐምድ 765። ED Dindorf T. II ገጽ 410 T. III. ገጽ 546. 360. 255—258; Funk; Didascalia...T. II ገጽ 8 11

1000. ከዚሁ ገጽ 160

1001. የአፈወርቅ ንግግር 1· XLIII—XLIV. P.G.T. LVI ዐምድ 618፡ 626 ፡ 707 ፡ 778፡ 858 935።

በሚል ርእስ ተወስኗል[1002] ። በመጨረሻም በያዕቆባውያን መዝገበ ቀኖናት ተመዝግቧል[1002]። ቀጥሎም በFunk ከዲድስቅልያ ጋር በተያያዘ የተወሱት Une Verso Epistulae Athanas II እና One Syriac MS of British Museum ከመጠቀስ ሊታው አይችሉም[1004] ። ዲድስቅልያ የተጻፈበትን ዘመን በሚመለከት የጸሐፊዎች አመለካከቶች ይለያያሉ — ይቃረናሉ ።

በመጀመሪያ ዲድስቅልያ የተጻፈበት ዘመን 3ኛው ምዕተ ዓመት ማለትም ከመጀመሪያው አጋማሽ ጀምሮ እስከ መጋባደጃው ባለው ጊዜ እንደሆነ ተቀምጧል ። እንደማስረጃውም የተወሰደው ከብዙ ነገሮች መካከል በዲድስቅልያ የ3ኛው ምዕተ ዓመት የቤተ ክርስቲያን ማዕርግና ሥርዓት ፡ የኤጲስ ቆጶስ[1005] የቄስና የዲያቆን[1006] የዲያቆናዊት [1007] የንፍቀ ዲያቆን[1008] የአናጉንስጢስ[1009] ማዕርግና ደረጃ ሲመለከት የዝቅተኞቹ አገልጋዮች Clerici Minores ማለትም የኋላ ዘመናት ማዕርጋት አልተመለከቱም ።

9·2 የዲድስቅልያ ምንጮች

ዲድስቅልያ እንደተባለው በሐዋርያት እንደ አለመዘጋጀቱና ስለዚህም የኋላ ዘመንና ጸሐፊ ሥራ ሆኖ እንደ መቆጠሩ መጠን ከነበሩ ሥራዎች ላይ የተመረኮዘ ወይም ቢያንስ የተመሰጠ ሥራ መሆኑ ይታያል በየመጀመሪያ ዲድስቅልያ ከሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ ላይ ተመሥርቶ እንደ ተጻፈ[1010] ወይም እንደመነሻ "ትምህርተ ሐዋርያትን" ይዞ

1002. G. bar Hebreaus: Nomocanon Ecclesiae Antiochenae Syrum (Latin Interprete A. Assemano B.O.T.I 1— 268 T. 3. VII — XXXVII
ED. A. Maio: Scriptorum: ...T.X. ገጽ 50, 240 (Syriac) G. Bar Hebreaus: Ethicon II. 3,10,5,6, ed. P. Bedjam 1898, 171—193 (26. 87.97.280).
1003. Funk Didascalia II ገጽ 12—14
1004. ምዕራፍ 5(5—11)
1005· ምዕራፍ 12
1006· ምዕራፍ 12 16
1007· ምዕራፍ 16
1008· ምዕራፍ 9
1009· ምዕራፍ 9
1010. Stam: Episcopcy, on the apostolical tradition ገጽ 6· J Quasten. Patrology T.II ገጽ

እንደተቀረጸ ወይም ራቡ ትምህርተ 12 ሐዋርያት የተደረጉትን ለውጦችና ጣልቃ ገብነቶች ይዞ ወደ ዲድስቅልያ እንደተለወጠ[1011] ነገር ግን ሆኖም ዲድስቅልያ በቀድሙ ግንኛዎችም ሥራዎች ተመሥርቶ — ተመርኩዞ እንዳልተጻፈ ያለው ተቃራኒ ሐሳብ አልቀረም ምክንያቱም በትምርተ 12 ሐዋርያት እና በዲድስቅልያ መካከል ያሉት ልዩነቶች በጣም ሰፊ እንደመሆናቸው መጠን በትምህርተ 12 ሐዋርያትና ሱርስጥ ዲድስቅልያ መካከል የቆዩ ሌሎች ግን ያልተላለፉ ሥራዎች እንደ ነበሩ ይታሰባል[1012]።

ይህም ሆኖ ግን የዲድስቅልያ ዘሐዋርያት ዋና ምንጭነት ማለትም አንድ አምስተኛውን የያዘው ቅዱስ መጽሐፍ ነው ። ይህም እንደተጠበቀው የዲድስቅልያ ጸሐፊ ቤተክርስቲያናውያን — ቀኖናውያንና ሥነ ቅዳሲያውያን ሥራዎችን ፡ ትምህርተ ሐዋርያትን፡ መልዕክታት ኢግናጢዮስን ፡ የተወሰኑ አዋልድ ሥራዎችንና በርግጥም ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስን ፡ ሐዋርያውያት ትእዛዝትን በምንጭነት በአገለገሉበት መልኩ ተጠቅሟል[1013] ።

፱·3 ዲድስቅልያ የተጻፈበት ቋንቋና የተመለሰባቸው ቋንቋዎች

ዲድስቅልያ ዘሐዋርያት እንደተባለው በመጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ ግሪክ መሆኑ ሲታመንበት ግን እናት ሰነዱ ጠፍቶ በልዩ ልዩ

1011. H. holzcy: dic abhängkeit der syriche didascalic von didache; compte rendu du IV. congress seientifique internationale des catholiques sciences religiuses. Freiburg 1897 ገጽ 249—278 Connolly. The use of didache in the didascalia T. 25/1924 J.T.S. ገጽ 151—153።
1012. F. Nau; La didascalie Syriaque paris 1902. ገጽ 4-5. 164-165.
1013. A Harnack; Geschichte der altchristilichen literatur bis Eusebius. Leipzig 1893. T.I. ገጽ 315-518: 1894. T. II ገጽ 488-501 J.V Bartlet: Fragments of didascalia in Greek; J.T.S. 18/1917: I.V. Bartlet: church lifg and church orders during the first centuries with special reference to the eastern church ordrs. london 1943. F. Burkitt The didascalia J.T.S. 30/1930 ገጽ 258 Achelis — Flemming die syrische didascalie T.U.T. XXV ገጽ 320—300. viard: la didascalie des apôtres ገጽ 21-22. Leclerq: didascalie. D.A.C.L.T. IV ገጽ 809.

ቋንቋዎች ተርጉሞና ሐዋርያውያት ትእዛዛት የመጀመሪያዎች ስድስት መጻሕፍት እንደመነጩበት ምንጭ ሁና ሊገኝ ችሏል ።

9·4 የዲድስቅልያ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ትርጉሞች

9·4·1 የዲድስቅልያ ላቲን–ሮማይስጥ ትርጉም

የዲድስቅልያ የሁለት አምስተኛውን ነጠብጣቦች እንደያዙ የሚገመቱት ክፍሎች (1—6 እና 8) በVerona በሚገኝ ምን ዓልባት የ5ኛው ምዕተ ዓመት Codex Veronensis lat. LV. 53 አንድ ላቲን የእጅ ጽሑፍ (palimpsest m.) ይገኛል [1014] ።

ይህ ላቲን ትርጉም በ4ኛው ምዕተ ዓመት እንደተካሄደ ይገመታል[1015] እነዚህ የተጠቀሱት የላቲን ትርጉም ክፍሎች በ M. Hauler ታትመው ሊገኙ ሲችሉ[1016] ከእነዚህም የተወሰኑትን ደግሞ በሌላ ሕትመት አጋጣሚ ይኸው ሰው ሊጠቀምባቸው ችሏል[1017]

ከግሪኩ ቋንቋ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ጋር ጐን ለጐን በFunk የተደረገው የዲዮስቅልያ ሕትመት ከፍተኛ ግምት ያለው ሕትመት ነው[1018]

የዲድስቅልያ ላቲን ትርጉም ከግሪክ እናት ሰነድ እንደተደረገ ይታያል ። ይህን ዲድስቅልያ ወደ ላቲን የተረጐመው ሰው በ408 ምዕተ ዓመት ቅዱስ ጳውሊኖስ ዘአባይ እንደሆነ ይገመታል ። ይህም ትርጉም የተከናወነው ከRufinus ከመጣ አንድ ሰነድ[1019] ሲሆን በዚህም ጊዜ

1014· እነዚህ በላቲን ትርጉም ተገኝተዋል የሚባሉት የዲድስቅልያ ነጠብጣቦች የሚከተሉት የሐዋርያውያት ትእዛዛት ምዕራፎች 1· 1–2, 5–7 , 8–11, 2·6–12, 14–15, 18–20 (የተወሰኑ ዐረብና ግብጥ ተናናት 13—20 ግሪክ ተናናት 10—30) የተመረኰዙባቸው ክፍሎች ናቸው ።

1015. F. Nan: La didascalie...ገጽ 733

1016. E. Hauler: Didascalia...ገጽ 185

1017. E. Hauler, eine latinische palimpsest uebersetzuog der didascala apostolorum, (les comptes rends de lacademie de scicnce de vilenne) T. CXXXIV.T.3. 1896 Sitzungsberichte de l'academie de vienne) P. Corsson: Zur Latinische didascalia apostolorum. Z.N.W. 1906 T.1. ገጽ 332—343.

1018. Funk; Didacalia...T II

1019. F.Nau: Didascalie D.C.T.T.IV ገጽ 716

ማለትም ይህን ላቲን ትርጉም ለማከናወን የተቻለው ጳውሊኖስ ሩፊኖስ በአደረገለት ርዳታና ድጋፍ መሠረት እንደሆነ ይታመናል[1020] በሌላ በኩል ይህ ትርጉም ከግሪክኛው ሰነድ ወደ ላቲን ለመመለስ ጥንቃቄ ወይም ትኩረት ያልሰጠበት ትርጉም ማለት ስሕተት የተሞላበት ሥራ ሆኖ ይቆጠራል ለምሳሌ ብዙ ግሪክ ቃላት በዚህ ላቲን ትርጉም ተጣመው (ተገልብጠው ይገኛሉና ለምሳሌ ፓሮኪ —ፓሮኪያ ፣ አርፋኖስ አርፋኒታስ፣ ፓራሊፓሚኖን ፓራሊፓሚንዩም ወዘተ·[1021] ። ይህም ሁኔታዎች በእሉበት መልካቸው ትክክለኛዎችንና ተስማሚዎችን ምትክ ቃላት ለማግኘት ያለ መቻል በአንድ በኩል ባሌላ በኩል ይህ አለመቻል እነዚህን ምትክ ቃላት ባለማግኘት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ራሱ ትርጉሙ ትክክለኛ ትርጉም አለመሆኑም ነው ምክንያቱም በዚሁ ላቲት ትርጉም በግሪኩ እናት ሰነድ በሐዋርያውያት ትእዛዛትና በሱርስጥ ትርጉም በተገኘበት መልኩ ከፍተኛ ልዩነት ይታያል[1022]።

ይህም ሆኖ ግን የዲድስቅልያ ላቲን ትርጉም ነጠብጣቦች ዲድስቅልያ ቀደም ብሎ በምዕራብም ስለመኖሩ ታሪካዊ ምስክርነትን ይዟል ።

9·4·2· የዲድስቅልያ ሱርስጥ ትርጉም

ዲድስቅልያ ከላይ እንደተመለከተው ከተወሰኑ ነጠብጣቦች በስተቀር ግሪክ እናቱ ሰነድ ጠፍቶ በሙሉ መልኩ ማለትም ይዘቱ በሱርስጥ ተርጉሙ ነው በመጀመሪያ ሊገኝ የቻለው ።

የዲድስቅልያ ሱርስጥ ትርጉሙ ሰነድ Didascalia apostolorum syriac በሚል ርእስ በፓሪስ በሚገኝ የ9ኛው ወይም የ10ኛው ምዕተ ዓመት የእጅ ጽሑፍ (codex sangermanensis-parisiensis oricnt 38 [1023] በP. De lagarde በ1854 ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ

1020. F. Nau: En Acts du XIVE Congress internationale des oricntalistes paris. 1906. T.1. ገጽ 35—38 Leclerq: didascalie...D.Ac.L.T.IV ገጽ 806

1021. M. Viard: La didascalie des apotres ገጽ 14።

1022. F. Nau: diascalie...D.T.C.T. 4 ገጽ 735.
በዚህ ላይ ልዩነቶችን ለማሳየት—ለማረጋጥ የዲድስቅልያ ግሪክ ሱርስጥና ላቲን ሰነዶች የመጀመሪያዎች ሐረጐች ጐን ለጐን ተቀርጸው ተነጻጽረዋል ።

1023. P. De lagarde: Didascalia apostolorum, syriac. 1854 MS. De. paris. Bibliotheque nationale de paris no. 62.

ሲገኝ[1024] በሌላም በኩል በአንድ Scarfe በሚባል ሰሚናር በJ. Rendel Harris የተገኘ ሌላ ሜሶጶጣሚያዊ የእጅ ጽሑፍ Codex mesopotamicus ወይም (codex harrisianus) በ M.P. Gibson የታተመ ሲሆን [1025] በዚህም አጋጣሚ P. P.M. Gibson codex sangermanensis የተወሰነው ፍሬ ነገሮችን ይዞ በሚገኘው ፣ codex mesopotamicus codex cantabrigiensis እና codex mussei borgiani መካከል ያሉትን ዋና ዋና መነጣጥሎችን ዘርዝራ አቀነባብራለች [1026] ከእነዚህ በስተቀር ሱርስጥ ዲድስቅልያ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንግሊዝኛ በረቧ ፣ በ connolly [1027] እና ፈረንሳይኛ በF. Nau [1028] ጀርመንኛ በ Achclis-fleming ተተርጕሞ ፣ ታትሟል[1029] ሱርስጥ ዲድስቅልያ ከሐዋርያውያት ትእዛዛት 1—6 መጻሕፍት ከአንድ አንድ ልዩነቶችና ተራ ቅደም ተከተል ለውጥ በስተቀር ተመሳሳይ ይዘት እንደ አለው ይታያል በሌላም በኩል በP. De Lagarde ሕትመት ያልታየው መቅድም በGibson ይገኛል ።

ሱርስጥ ዲድስቅልያ አንድም በሙሉ ወይም አንድ አንድ ነጠብጣብ ክፍሎች በልዩ ልዩ አብያተ መጻሕፍት በሚገኙ የእጅ ጽሑፎች ይገኛሉ[1030] እንደተባለው በሚከተለው መልክ የሐዋርያውያት ትእዛዛት የመጀመሪያዎች መጽሕፍት የፈለቁበት ሱርስጥ ዲድስቅልያ በ26 (27) ምዕራፎች ይከፈላል ።

ሱርስጥ ዲድስቅልያ	ሐዋርያውያት ትእዛዛት
1	1·1 [1031]
2	I 2 [1032]
3	I 8 [1033]
4	II 1 [1034]
5	II 6 [1035]
6	II 12 [1036]
7	II 18 [1037]
8	II24 [1038]
9	II 25 [1039]
10	II 27 [1040]
11	II 43 [1041]
12	II 57 [1042]
13	II 59 [1043]
14	III 1 [1044]
15	III 5 [1045]
16	III 15 [1046]
17	IV 1 [1047]
18	IV 5 [1048]
19	V III 15 [1049]

1024. M.P. Gibson; The didascalia apostolorum in syriac horae semiticae No. I. 1903.

1026 M.P. Gibson: the didascalia apostolorum in English translation. Horae semiticae no II, London 1903. J. Quasten. patrology. T. II ገጽ 151።

1027. R.H. connolly; Didascalia apostolorum. The syriac Version translated and accompanied by the verona latin fragments. Oxford 1929.

1028. F. Nau; La didascalie C'est-a dire l'enseignement catholique des douze apôtres et saint disciples de notre sauveur en canoniste contemporain 1901—1902.

እነዚህም ሁለት ቅዳሴዎች በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዐተ ቅዳሴ ከፍተኛውን ቦታ ይዘው የሚገኙት ቅዳሴዎች እንደመሆናቸው

1299. D-HaNeberG. Canones Hippollyti Arabic Codibus Romaanis Cum Versione Latina Annotationibus et Prolegomenis Monachi 1870.
1300 H.Achelis. Åltesten Quellen des Orientalischen Kirchenrechts. I Buch die Canons Hipolyte T.U. 1891. T.U.H. Vieharer. Canones Hippolyti...Christian worship...
1301. Riedel: Die Kirchenrechtsquellen... ገጽ 193 230
1302. Vansleb. Histoire Del'eglise ገጽ 193 230
1303. P.O.T. XXXI
1304. W.Till-J. Leipoldt. der Koptische text der Kirchenordnung Hippolyti. Berlin 1954, Dix. the treatise... ገጽ LXXVI-LXXXI.
1305. መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝና በአማርኛ በአሕተመቶ እቴጌ መነን እንተ ይእቲ ወለተ ጊዮርጊስ፣ አዲስ አበባ 1942 ቁጥር 1 170 ገጽ 44 62 ።
1306. G. Dix: the Treatise... ገጽ XVI...
1306. መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝና በአማርኛ ቁጥር 1—84 ገጽ 63 69

መጠን በአንድ በኩል በሌላም በኩል ለምዕመናን ብዙ ድካምን የማያስከትሉ አሰልች ባለመሆናቸው የዘወትር ቅዳሴዎች ሁነው ያገለግላሉ ።

1·2 የቀኖናተ አቡሊዲስ ይዘት

የ38 ቀኖናቱ አቡሊዲስ ይዘትን በሚመለከት በተለይ ከግብጣዊ ቤተክርስቲናዊ ትእዛዝ ይዘት ከአጠቃላይ ደግሞ ከሐዋርያውያት ትእዛዛት የ8ኛውን መጽሐፍ Epitome ጨምሮ የተለየ አይደለም[1308] ነገር ግን ከሐዋርያውያት ቀኖናት ከሚባሉት ረስጠአ ረስጠብ ረስጠጅ እና ዲድስቅልያ ዘሐዋርያት በአንድ በኩል በሌላ በኩል ከ106 ቀኖናተ ባስልዮስ ወደፊት ከሚመረመሩት ቀኖናት ጋር ያላቸው ግንኙነቶች በጣም የተቃረቡ ናቸው ።

ስለዚህ በእነዚህ ቀኖናተ አቡሊዲስና ከላይ በተመለከቱት ቀኖናት ሀ/ ሥርዐተ ቅዳሴያዊ ለ) ቀኖናዊ እና ሐ) ሥነ ምግባራዊይ ይዘት ያላቸው ትእዛዛት ታቅፈዋል ።

1·2·1 የቀኖናተ አቡሊዲስ የሥርዐተ ቅዳሴው ክፍል

— ለአምልኮት በተወሰነ ቦታ (መካነ መሥዋዕት) ከአምልኮት ሥርዐት በስተቀር ለሌላ ሥራ ? ደማይፈቀድ

— ከካህን በስተቀር ማንም ሰው ወደ መንበረ ቅድስት —ቅድስተ ቅዱሳት መግባትና ሥጋ ወደሙን መቀበል እንደማይችል[1309]

— ስለ አልባሳተ ቅዳሴ ነጭ እንጂ ዝንጉርጉር አለመሆን የንጽሕና ምስል[1310]

— ስለ ጊዜያተ ጸሎት (በቀን ሰባት ጊዜ)[1311]

— የመጀመሪያውን የምድር ፍሬ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስለመውሰድ

1307. A. Αλιβιζάτου, Οἱ Ἱεροὶ Κανόνες ገጽ 26. Κεχάλι Αλέμου: Η Χριστολογία τῶν Αἰθιοπικῶν ἀναφορῶν ἐν σχέσει πρὸς τὸ Δόγμα τῆς Χαλκηδόνος, ΘΕΣ/ΝΙΚΗ 1977
1308. Hanssens: La Liturgie d'Hippolyte P.O.A. 115/1949. Funk: Die Liturgie Der Åthiopischen Kirchenordnung. Der. tur. Quartalschrift 1998 1898 ገጽ 513.
1309. ቀኖና 29· 19 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 1·12 ቀኖና ባስልዮስ 25 92·72 ፡ ረስጠብ 7 ቀኖና 19 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 1
1310. ቀኖና 37 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 12 በስ· 96
1311. ቀኖና 27·26 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14 በስ 18 ፡ ዶቅ 37 12 ረስጠአ 40· 68 47 ፡

ማቅረብ[1312]

— ስለ ሥጋና ወደሙ መቀበል[1313]

— በጠረጴዛ ላይ ስለ መጸለይ (በምግብ ወቅት)[1314]

1·2·2· የቀኖናቱ ቀኖናዊ ክፍሉ የያዛቸው ትእዛዛት

ለምሳሌ ስለ ኤጰስ ቆጶስ ምርጫና ቅባት ፣ ችሎታዎች መመዘኛዎችና ተግባራት[1315] ስለ ቀሲስ[1316] እና ስለ ንፍቅ ዲያቆን[1317] ስለ መዘምር [1318] ስለ ድንግል [1319] ስለ ሥርዐተ ጥምቀት [1320] ስለ ካህናት ከአንድ ቤተክርስቲያን ወደ ሌላ ክርስቲያን እንዴት ማዛወር—ሥርዐተ ዝውውር[1321]

1·2·3· በእነዚህ ቀኖናት የተመዘገቡት ሥነ ምግባርና ሥነ ሥርዐት ትእዛዛት[1322]

በእግዚአብሔር ፊት የሰው (መነኰስ) ፍጹምነት[1323]

ስለ ርስ በርስ መፋቀር[1324]

ወዘተ

ረስጠጅ 5

1312· ቀኖና 35·3 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 18·14 በስ 18·8

1313· ቀኖና 28 14·2 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13 ረስጠብ 43· ማቴ 5·23—24 1ኛ ቆሮንትስ 11· ·27

1314· ቀኖና 21 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14— በስ 28 ረስጠብ 47· መዝሙር 56 1— 10 ማቴ 14·19···

1315· 2 ·3 24·37·31 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ አግባብነት ያለው ትእዛዝ አልያዘም

1316· ቀኖና 4·9 21 31 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ

1317· ቀኖና 5·10 31·35 ፍትሐ ነገሥት ንቀጽ

1318· ቀኖና 6· 34 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8·3 ረስጠአ 59 ዶቅ 11

1319· ቀኖና 9·32 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10·8 ድስቅ 14· በስ·43

1320· ቀኖና 7· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8·2—ረስጠብ 27· በስ 48

1321· ቀኖና 7 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8·2—ረስጠአ 27 በስ 48

1322· ቀኖና 7 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8·2—ረስጠአ 27 በስ 48

1323· ቀኖና 7 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8·2 ረስጠአ 27 በስ 48

1324· ቀኖና 9·38 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 3·11 ረስጠአ 43

1325· ቀኖና 8 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6 8 ረስጠአ 43

1326· ቀኖና 38 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10·6

1327· ቀኖና 22 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9·4 — ማቴ 10·12 13

2· ቀኖናት ባስልዮስ፡ በስ — ባስልዮስ[1328]

በቁማርያ ዘቀጳዶቅያ ሊቀ ጳጳሳት ትልቁ ባስልዮስ ስም ዘራሱ በትልቁ ባስልዮስ ከተጻፉ 8 መልዕክቶችና ስለ መንፈስ ቅዱስ ከአቀነባበረው ሥራ የተሳቡና ቁጥራቸው 92 የሚደርስ ቀኖናት ይገኛሉ።

ስለዚህም 86 ቀኖናት ለአምፊሎኪዮስ ዘኢኮንዮ ከተጻፉ ሦስት መልዕክቶች[1329] 87ኛው ቀኖና ለዲዮዶሮስ ዘታርሱ ከተጻፈ መልዕክት[1330] 88ኛው ቀኖና ለካህን ጎርጎርዮስ ከተጻፈ መልዕክት [1311] 89ኛውና 90ኛው ቀኖናት በሥሩ ወደሚገኙ ኮሬ ኤጲስ ቆጶሳት[1332] ከተላኩ መልዕክቶች ፡ የመጨረሻዎች ሁለቱ 91ኛውና 92ኛው ቀኖናት[1333] [1332] ስለመንፈስ ቅዱስ ከጻፈው ሥነ ጽሑፍ[1334] የተወሰዱ ናቸው ።

እነዚህ ቀኖናት በ5ኛው 6ኛው የትሩሎ ዐቢይ ጉባኤ መጽ ?ቃቸው ይታወሳል[1335] ። ከእነዚህም ቀኖናት ጐን በግብጽና በኢትየ ጵያ አብያተ ክርስቲያናት በቁሳርያ ኤጲስ ቆጶስ ታላቁ ባስልዮስ ስም 106 ቀኖናት ይገኛሉ ።

ስለዚህ በፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ እብነ እል አሳል አገላለጥ መሠረት እነዚህ ቀኖናት ስለ ምንኩስና ሕይወትና ጋብቻና ስለመሳሰሉትም ጉዳዮች የሚመለከቱ ቀኖናት ሲሆኑ እነሱም በግብጻውያንና መላከውያን ዘንድ እንደሚገኙ ሲታወቅ የቆኖናቱ ቁጥር 106 ነው ። በስፋት በጥቅም ላይ የሚገኙም ቀኖናት ናቸው ።

ቀኖናተ ባስልዮስ በፍትሐ ነገሥቱ "በስ" ባስልዮስ በሚል ምኅፃረ ቃል ይጠቀሳሉ ። እንደዚሁም ስለ ምንኩስና ከተናገራቸው ኀድላት ተወስደው በአንቀጸ መነኮሳት (አንቀጽ 10) ተይዘው የሚገኙት ቀኖናት ሲኖሩ እነዚህም በፍትሐ ነገሥቱ አሁንም "በስ" ባስልዮስ ተብለው ይጠቀሳሉ[1335]። 106 ቀኖናተ ባስልዮስ ራቀም ቀረበ ምን ጊዜም ቢሆን የኋላ ጊዜ ሥራዎች ናቸው ።

1328· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1329· A. Α...ρι.ζατου; Οἱ Ἱεροὶ Κανόνες ገጽ 354 388

1330· A. Αλιβιζάτου: Οἱ Ἱεροὶ Κανόνες ገጽ 385 389

1331· A. Αλιβιζάτου; Οἱ Ἱεροὶ Κανόνες ገጽ 389 390

1332· A. Αλιβιζάτου; Οἱ Ἱεροὶ Κανόνες ገጽ 390 391

1333· A. Αλιβιζάτου; Οἱ Ἱεροὶ Κανόνες ገጽ 391 392

1334· Bardy; Regle de Saint Basil D.D.C. 1937 T. II ገጽ 137

1335· A. Χριστοφιλοπούλου; Ελληνικόν Εκκλησιαστικόν Δίκαιον ገጽ 354 388

ሆኖም የራሱ የባስልዮስ ሥራዎች እንደ አልሆኑ ቢደገፍም በከፍተኛ መጠን ከተጠቀሱት 92 ቀኖናተ ባስልዮስ ላይ ተመሥርተው የተቀረጹ መሆናቸው ይታያል[1336]

ነገር ግን ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አትናቴዎስ 107 ቀኖናት እና ከ38 ቀኖናተ አቡሊዲስ ጋር ቀጥታ ግንኙነት እንደአላቸው ይታያል ።[1337]

ስለ 38 ቀኖናተ አቡሊዲስ የተነገረው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግን በሁሉም ማለት ይቻላል ቀኖናውያን መድበላት በትልቁ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አትናቴዎስ ስም የቤተክርስቲያንን ሰላምና ሥርዓት የሚመለከቱ ሦስት ቀኖናውያን መልዕክቶች ይገኛሉ[1338]

በሌላ በኩል በግብጽና ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መድበለተ ቀኖናት በትልቁ አትናቴዎስ ስም 107 ቀኖናት ተይዘው ይገኛሉ[1339] ለንጉሠ ነገሥት ዩስጢኒያኖስ በቊስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ስም የተላኩ 35 ቀኖናትም መኖራቸው ይታወሳል[1340] እነዚህም ቀኖናት ኤጲ ስቆጶስ ለመሆን በቅድሚያ ምንኩስናዊ አስኬማ መቀበል ወይም አሥረ ክህነት መያዝ ግዴታ መሆኑን የሚደነግጉ ሲሆን ግን በፍትሐ ነገሥት ስለ አትናቴዎስ ስምም ሆነ ቀኖናት ምንም አልተወሳም ።

ሆኖም በትልቁ አትናቴዎስ ስም የሚታወቁት ቀኖናት ከእንግሊዝኛ ትርጉም ጋር በW. Riedel ታትመው ተሰራጭተዋል[1341]

1336 ለምሳሌ	106 ቀኖናት	92	ቀኖናት
	11		50
	20		8
	7		49
	34		60
	43		10,29
	22		4,48

1337. A. Αλιβιζάτου; Οἱ Ἱεροί Κανόνες ገጽ 344 - 352
1338. Renaudotius. Historia Patriarchum Alexandrinorum Jacobitarum ab Marcousque Ad finem Saeculi XIII Paris 1713 ገጽ 97
1339. Vansleb, Histoire de l' églis ገጽ 283—285
1340. The Canons of Athanasius of Alexandria, London 1904.
1341. ሲኖዶስ Borgio Etiopico ገጽ -

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ በትልቁ ባስልዮስ ስም 17 ቀኖናት ብቻ ተይዘዋል ።

የፍተሐ ነገሥት ጸሐፊ እብነ እል አሳል ስለ መነኮሳት የሚናገረውን ክፍል አንቀጸ መነኮሳትን ለማቀነባበር ትእዛዛትን የምንክሱና ሕይወት የሚመራባቸው[1342] 55 መመሪያዎች[1343] እና 313 ነጥቦች [1344] በመባል ከሚታወቁት የትልቁ ባስልዮስ ቀኖናውያት ትእዛዛት ወስዶ ነው የተጠቀመው ።

106 ቀኖናተ ባስልዮስ እስከ አሁን በዝርዝር ጥናት አልተካሄደባቸውም ስለዚህ ብዙ ምንጮች ማግኘት ያዳግታል ። ሆኖም ስለ እነዚህ ቀኖናት ከጀርመንኛ P. Riedel ሕትመት በቂ መረጃዎች ማግኘት ይቻላል[1345] የቀኖናቱ አርእስት በ Vanleb በፈረንሳይኛ ቋንቋ ተተርጉመዋል[1346]። p 106 ቀኖናተ ባስልዮስ ይዘት ሁሉንም ማለት ይቻላል የቤተክርስቲያን ሕይወት ገጽታዎችን ይሸፍናል ። ስለዚህ በአጭሩ በRiedel አገላለጥ መሠረት ቀኖናቱ 1—2 ስለ እምነት[1347] 3—27 ተግሣጽ 28—37[1348] ስለ መሐይምንና ምዕመናን 38—95[1349] ስለ ካህናት 23—25[1350] ስለ ሥርሀተ ቅዳሴ አርእስት 26—10[1351] የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ እብነ እል አሳል ፍትሐ ነገሥቱን ለምቅረጽ በሁሉም ማለት ይቻላል ሕገ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሕግንክ በተለይም ከሥጋዊ ሕግ ማለትም የቤተሰብና የውርስ ሕግን ፡ የሥነ ምግባር ሕግን በሚመለከት

1342. K. Μουρατιδου; Μοναχική υπακουή έν αρχαία Εκκλησία, AΘHNAI: 1956 69
K. Μουρατίδου; Χριστιανική Ποιναντική έν τοίς ασκη-τικοίς του Μ. Βασιλείου, AΘHNAI: 1952 ገጽ 50 Murphex. Saint Basel and Monsticism; washington 1930. c. Morisno N. St. Basil and His Rule A Study in early Monasticism Oxford 1912
1343. P.G.T. 31 ዐምድ 889—1012
1344. P.G.T. 31. ዐምድ 1053—1306
1345. Riedel. Kirchenrechtsquellen ገጽ 230— 380
1346. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 43·5 ቁኖና 2
1347. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቀኖና 9 አንቀጽ 24·5 ቀኖና 11
1348. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቀኖና 9 አንቀጽ 24·5 ቀኖና 11 አንቀጽ 25 ቀኖናት
1349. አንቀጽ 48·3 ቀኖና 23 25 22 14· 11 አንቀጽ 47 ቀኖና 27 አንቀጽ 9·5 ቀኖና 5· 21 22
1350. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 20 ቀኖና 33 አንቀጽ 22 ቀኖና 31 አንቀጽ 44·12 ቀኖና 29 አንቀጽ 95 ቀኖና 29

በስፋት ቀኖናተ ባስልዮስን ተጠቅሟል [1352] ስለ ምንኩስና ሕይወት የሚናገሯቸው ቀኖናት ክፍል አግባብነት ባለው አንቀጽ ብቻ ተወስ ኗ ል[1353]

ስለዚህ 106 ቀኖናት ለፍትሐ ነገሥት ምንጭነት እንደ ሐዋርያው ያት ቀኖናት (ረስጠእ ፡ ረስጠብ ፡ ረስጠጅ ፡ ዲድስቅልያ እና ቀኖናተ አቡሊዲስ ከፍተኛ ድርሻ ኑሯአቸው ይገኛሉ[1354] ።

3· ቀኖናተ ዲዮኒስዮስ፡ደ — ዲዮናስዮስ[1355]

ቀኖናተ ዲዮናስዩስ—ዲዮኒስዮስ በሚባልበት ጊዜ በግብጽ ቤተክርስቲያን ልዩ ልዩ ቀኖናውያን መድበላት ለምሳሌ በካዘን ጴጥሮስ ሳፍሮ የሚገኝ የአርዮስ ፋጉስ ዳኛ ዲዮናስዮስ ሥራ "ቃለ እምነት" ማለት ጸሎተ ሃይማኖት መሆኑ ይታመናል[1356].

በርግጥ እንደሚታወቀው በዲዮስዮስ አርዮስፋጎስ — አርዮስፓጊቲስ ጽሑፎች ሥነ መለኮታውያን ቤተክርስቲያናውያን ሥራዎች Corpus Dionysiacum ተያይዘው መጥተዋል ።

1· ስለ ሰማያውያን ማዕርጋት De Caelesti Hierarchia[1357]

2. ስለ ቤተክርስቲያን ማዕርጋት — De Ecclesiastica Hierarchia[1758]

1351· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5·1 ቀኖና 52 ቀኖና 45·38 ቀኖና አንቀጽ 6 ቀኖና 83፤ 2 ቀኖና 51 ቀኖና 53 ።

አንቀጽ 7·2 ቀኖና 56 ቀኖና 58·63 64 66 72· 73 78·84·87 81·92 59·90 91 አንቀጽ 8·2 ቀኖና 55 አንቀጽ 9·1 ቀኖና 49·50 55·47 አንቀጽ 17·1 ቀኖና 86 አንቀጽ 22· ቀኖና 85·2 55·52·43·47·71 77·79·8081· 83 59·90·91 አንቀጽ 14 ቀኖና 77 አንቀጽ 17 ቀኖና 86 አንቀጽ 22 ቀኖና 88 አንቀጽ 43·9 ቀኖና 22·19 ቀኖና 32 አንቀጽ 22·11 ቀኖና 40 አንቀጽ 23 ቀኖና 52 አንቀጽ 24·1 ቀኖና 43

1352 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 12· ቀኖና 96·97·99 አንቀጽ 13 ቀኖና 99·98·10 ፍትሐ ነገሥቱ አንቀጽ 23 ቀኖና 52 አንቀጽ 24·1 ቀኖና 43·5 ቀኖና 32 30·33 አንቀጽ 42 11 ቀኖና 40· አንቀጽ 43·9 ቀኖና 92·12 ቀኖና 82

1353· አንቀጽ 10

1354· 106 ቀኖናተ ባስልዮስ በSans Al-riasah abul baracat ibn ktbr : encyclopedia ምዕራፍ 5 ስፍኖ ይገኛል ። A Riedel. Die Kirchenrechtsquellen ገጽ 130

1355· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1356. Riedel, Die Kirchenrechtsquellen...

1357. P.G. T.3 ዐምድ 119 370

1358. P.G. T.3 ዐምድ 369—584

3. ስለ መለኮታውያን ስሞች —De Divinus Nomitibus[1359]

4· ስለ ምሥጢራዊ ሥነ መለኮት Mystica Theologia[1360]

5. ለልዩ ልዩ ሰዎች ስለተላለፉ 11 መልዕክቶች 1361 —

6· ስለ ሥርዐተ ቅዳሴ (ስለ አንድ ቅዳሴ) Liturgia Sancti Dionysii[1362]

7. እና ሌሎች አንድ አንድ ጽሑፎች[1363]

እነዚህ ሥራዎች አንድ ጊዜ Pseudodionysia እንደ ሆነ የሚጠሩ ሥራዎች የግብረ ሐዋርያት ዲዮናስዮስ አርዮስፋጎሳዊ[1364] እና የአቴንዘ የመጀመሪያው ኤጲስ ቆጶስ ሥራዎች እንደ አልሆኑ ጥብቀ ሂሣዊ ቁጥጥር ተደርጎባቸዋል [1365] ነገር ግን የ5ኛው ምዕተ ዓመት እንደሆኑ የሚቆጠሩ ሥራዎች ለዲዮናስዮስ አርዮስፋጎሳዊ Pseudoareosphagus ተሰጥተው ይገኛሉ [1366] እንደሚታወቀው ዘ ፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ አብነ አል አሳል አእምሮ ውስጥ የነበረው ማለት ይቻላል ሥራ ቃለ እምነት የዲዮናስዮስ አርዮስፋጎሳዊ ሥራዎች ሁነው በተመለከቱት ሥራዎች Corpus Dionysia ዝርዝር ውስጥ እንኳን አልታቀፈም ነበር ።

በሌላ በኩል እነዚህ ቀኖናት የእስክንድርያው ሊቀጳጳሳት ዲዮናስዮስ[265] 4 ቀኖናት ስለ መሆናቸው መደገፍ ይቻላል ምክንያቱም እንደሚታወቀው እነዚህ ቀኖናት ለፔንዳ ፖሊስ ኤጲስ ቆጶስ ባሲሊዲስ ከተላከ የዲዮናዮስ መልዕክት ከተሰወዱ ቀኖናት ፡ ስለ ፋሲካ[1367] ስለ ጾም[1368] ስለ ጸሎት[1369] ስለ ሥጋ ወድሙ መቀበል[1370] የሚናገሩ ቀኖናት ተመልክተው ይገኛሉ [1371]።

1359. P.G. T.3 ዐምድ 585—996

1360. P.G. T.3 ዐምድ 997—1064

1361. P.G. T.3 ዐምድ 1065—1122

1362. G.T.Z. ዐምድ 1023—1133

1363. P. Godet: Denis, L'aréopagite D.D.C.T.IV ዐምድ 429—438

1364· ግብረ ሐዋርያት 17·34

1365· አውሳብዮስ የቤተክርስቲያን ታሪክ 4·23·4 P.G.T. XX ዐምድ 568

1366· Bardenhewer, Lespères ገጽ 11—22

1367· ቀኖና ሀ

1368· ቀኖና ለ

1369· ቀኖና ሐ

1370· ቀኖና መ

1371· A. Αλιβιζάτου, Οἱ Ἱεροί Κανόνες ገጽ 322 - 327

እንግዲህ ቀኖናተ ዲዮናስዮስ በርግጥ የግብረ ሐዋርያቱ ዲዮናስዮስ ሥራዎች አለመሆናቸውና ግን በስሙ የተላለፉ Pseudodionysia ቢሆኑም ለፍትሐ ነገሥት ምንጩነት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው ። ቀኖናተ ዲዮናስዮስ በፍትሐ ነገሥት ምንጭነታቸው "ደ" በሚል ምኅፃረ ቃል ይጠቀሳሉ [1372] ።

4· ቀኖናተ ጎርጎርዮስ ፡ ግር — ጎርጎርዮስ[1373]

የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ ስለ ቀናናተ ጎርጎርዮስ ሲናገር ስለዚህ ጐርጐርዮስ ማንነት አልተናገረም ነገር ግን በአንድ በኩል ይህ ጐርጐርዮስ ጐርጐርዮስ ዘንሲስ እንደሆነ ይታሰባል ። ምክንያቱም እነዚህ ለፍትሐ ነገሥቱ እንደ ምንጭ የተጠቀሙት ቀኖናት እስከ ተወሰነ ሁኔታ ድረስ ከጐርጐርዮስ ዘንሲስ ሥራዎች ጋር ዝምድና ያላቸው ግን በ4 ቀኖናት ተድልድለው በብዙ የግብጽ ቤተክርስቲያን ቀኖናውያን መድበለት ታቅፈው የሚገኙ ቀኖናት እንደመሆናቸው መጠን የጐርጐርዮስ ዘንሲስ ሁነው ሊቀጠሩ ይችሉ ይሆናሉ[1374] የእነዚህ ቀኖናት ስለ ቤተክርስቲያን መታነጽና ስለቤተክርስቲያን ዕቃዎች (ንዋያተ ቅድሳት) የሚናገረው ክፍል ለሚካኤል ዘድምያጥ ብሔረ ሕግ ወቀኖና አገልግለዋል[1375]

ከጎርጎርዮስ ዘንሲስ ወደሚጠሊጢ ኤጲስ ቆጶስ ዲጶዮስ ከተላከች መልዕክት ተቀርጸውና በሁሉም ቀኖናውያን መድበላት ተይዘው የሚገኙት 8 ቀኖናት[1375] ከላይ ከተጠቀሱት ቀኖናት ዘጎርጎርዮስ ጋር ዝምድና እንደ ሌላቸው ይታያል ።

በፍተ ነገሥቱ ቀኖናት ዘጐርጐርዮስ አንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅሰዋል ። ይህም የተጠቀሰው ቀኖና ይዘት ስለ ጥምቀት የሚናገረው ቀኖና ሲሆ ፣ የሚከተለው ነው ። ለመጠመቅ የሚፈልግ ሰው የመረጠውን ጊዜ አያስተላልፍ ፤ ለነገ አይበል የወላጆችን ወይም የወዳጆችን መምጣት አይጠብቅ በልብስ ምርጫ ምክንያት አያዘግየው ፤ ለጥምቀት የሲቀ

1372· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
1373· ፍትሐ ነገሥት መግቢያ ክፍል Riedel: Kirchenrechtsquellen ገጽ 283 284
1374· ቀኖናዊ መድበል ዘመቃርዮስ ቁጥር 53 Riedel, Kirchenrechtsquellen ገጽ 127
1375· ብሔረ ሕግ ወቀኖናት ዘሚካኤል ዘድምያጥ NO. 4,7,33 Riedel: Kirchenrechtsquellen ገጽ 97

ጳጳሳት ወይም የኤጲስ ቆጳሳት ወይም የቄስ መምጣትን አይጠብቅ ፤ የማጥመቅ ሥልጣን ያለውን እንጂ ምክንያቱም የጥምቀት ሥልጣን በትክክል አንዲት ናትና[1376]።

ከዚህ ላይ ሊመረመር የሚችለው ቁም ነገር (ሐቅ) ሥርዐተ ጥምቀትን የሚፈጽመው ሰው ይህን ተግባር ለመፈጸም ሥልጣንና በሥርዐት አሠረ ክህነት ያለው ሰው መሆኑን ማረጋገጥ ይሆናል[1377]
እነዚህ ቀኖናት በፍትሐ ነገሥት "ግር" — ጐርጐርዮስ በሚል ምኅፃረ ቃል ይጠቀሳሉ[1378]

ከዚህ ቀኖናዊ ጥቅስ ሌላ በፍትሐ ነገሥት ተጠቅሶ የሚገኘው ጐርጐርዮስ ቲዎጎሎስ (ቴአሎጎስ — ነባቤ መለኮት ነው[1379]

ጐርጐርዮስ ቴዎጐሎስ (ቴአሎጐስ — ነባቤ መለኮት[1380] ስለ ጥምቀት በሚናገረው አራተኛ ድርሳኑ አስፍሮት የሚገኘው ሰምና ወርቅ — ምሳሌያዊ ትምህርት በፍትሐ ነገሥት በሚከተለው መልክ ተቀርጾ ይገኛል ።

1· ክፉና ደግ ሕዝብን በሰምዕ ከእነሱም ካህናትን በውስጣቸው የአንድ ንጉሥ ቅርጽ—መልክ በተቀረጸባቸው ሁለት፡ አንድ የወርቅና አንድ የብረት ማኅተሞች መስሎ ሲናገር ማኅተሞች ሰምዕ በታተመባቸው ጊዜ ንጉሣዊ ቅርጽ በወርቅ በታተመበት ማኅተምና በብረት በታተመበት ማኅተም መካከል ልዩነት እንደሌለ ልዩነት ሲኖር የሚችለው የሚታተሙበትን ዘዴ በሚቀበሉትና በማይቀበሉት መካከል እንደሚሆን ኅትመቱን አስመልክቶ ግን የቅርጽ ልዩነት እንደ ሌላ ይገልጣል ።

2· ዳግመኛም ምግባር የጐደለው ካህን እንደ ሰምዕ መብራት

1176· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 3 ቁጥር 29
1377· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
1378· A. Αλιβιζάτους Οἱ Ιεροί Κανόνες Τ.ΙΙ ገ217ጽ 411-421
1379· ቴዎጐሎስ ማለት ኃይለ ቃል ቴአሎጐስ "አ" ወደ "ዎ" ተለውጦ "ጎ" እና "ሎ" ቦታ ተዘዋውረው "ቴአሎጐስ" ቴዎጐሎስ" ወይም "ታዎጐሎስ" ሆኖ ይነበባል ። ኃይለ ቃሉ ሁለት ቃላት ቴኦስ፡ አምላክ መለኮት እና ሎጐስ፡ ነባቢ ተጣምረውበት የተፈጠረ ኃይለ ቃል ሲሆን ትርጉሙም እንደተለመደው ነባቢ መለኮት ማለት ነው ። ጐርጐርዮስ ቴዎጐሎስ ። ዮሐንስ ታዎጐሎስ (ግሪጐርዮስ ቴአሎጐስ ዮሐንስ ቴአሎጐስ) Θεολογία: Θεολόγος
1380· ፍትሐ ነገስት አንቀጽ 3 ቁጥር 29

ለንደሆነና የሚነደው እሳት በክህነት እንደሚመሰል ፡ እሳት ሰሙን እንደሚያቃጥለው ግን ለሕዝብ እንደሚያበራ ከብርሃኑም የተነሳ ጨለማ እንደማያገኛቸው አድርጐ መስሎ ይናገራል ።

3· ሌላም ምሳሌ ይቀጥላል ሁለት አንድ ክፉና አንድ ደግ ሰዎች ሁለቱም ለየራሳቸው ለንጉሡ አቤቱታዎችን — ጥያቄዎችን ያቀርባሉ የሁለቱም አቤቱታዎች ተመሳሳይ — አንድ ናቸው ።

4· አንድ ንጉሥ አንድ ደግና አንድ ክፉ፡ ሁለት መኳንንት (ዳኞች) አሉት ። ደጉ መኰንን ይፈጽምለት ዘንድ ንጉሡን እንዲያማልደው ክፉውን መኰንን ክፉውም መኮንን እንደዚሁ የሱም ጉዳይ መልስ ያገኝለት ዘንድ ደጉን መኮንን አማላጅነት ይልካሉ ።

ነገር ግን ንጉሡ ደግ ሰው ነው ። የሁለቱንም አቤቱታዎች ያውቃል ። ሆኖም ሁለቱ መኳንንት ጉዳዮቻቸው እንደፈጸሙላቸው ደጉ መኮንን በክፉው መኮንን አማካይነት ክፉውም መኮንን በደጉ መኮንን አማካይነት (አማላጅነት) በሚጠይቁበት ጊዜ ንጉሡ በክፉው መኮንን አማላጅነት የቀረበውን የደጉን መኮንን ጉዳይ የአማላጅን ክፉ መኮንን ክፋት (ክፉ ሰውነት) ወደ ግምት ሳያስገባ ሲፈጽምለት በደጉ ሰው አማላጅነት የቀረበውን የክፈውን መኮንን ጉዳይ ግን በራሱ በባለ ጉዳይ መኮንን ምክንያት አልጨረሰለትም ።

ምክንያቱም የአማላጁ መኮንን በጐ ሰውነት የባለቤቱን ክፉ መኮንን ክፉ ጠባይ ሊያስነሳ አይችልም[1381]።

5· ቀኖናተ አፈወርቅ ዮሐንስ ፡ ሐ — ዮሐንስ[1382]

ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ አሠረ ክህነት ከተናገራቸው ቃላት[1383] የተወሰዱ 12 ቀኖናት ይገኛሉ ። እነዚህም በግብጽ ቤተክርስቲያን ተያይዘው መጥተዋል[1384] ። በፍትሐ ነገሥት የተጠቀሰውና ስለ አሠረ

1381· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9 ቁጥር 342 343 P.Tzadua: Fetha Nagast ገጽ 63 64 አንቀጽ 9 ቁጥር 342።

1382· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2 392 Riedel. Kirchenrechtsquellen ገጽ Vansleb Histoire del'eglise d' Alexandrien ገጽ 282

1383· ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ አሠረ ክህነት ቃላት P.G.T 48 ዐምድ 623–692

1384· ብሔረ ሕግ ወቀኖና 8መ ቀርዮስ ቁጥር 5 ፡ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድሜያጥ ቁጥር 6 Riedel. Kirchenrechtsquellen ገጽ 300

ክህነት የሚናገረው 5ኛው ቀኖና ለምሳሌ እንደሚከተለው ይነበባል "ስለ በጐ ፍርሃት ፡ እግዚአብሔርን መፍራት መልካም ነው ። ሰው እግዚአብሔርን ፈሪና አስተዋይ ካልሆነ አለቃ ይሆን ዘንድ አይገባውም…[1385] ። በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ሲኖዶስ የዮሐንስ አፈወርቅ ልዩ ልዩ ቀኖናት (17) ተደርገዋል[1386] በሌሎችም ብዙ ቀኖናውያን መድበላት ተይዘው ይገኛሉ[1387]። ከእነዚህም ከላይ ከተጠቀሱት ቀኖናት ጋር ግንኙነት የሌላቸው ግን ከራቡ የኤፌሶን መልዕክት[1388] የዕብራውያን መልዕክት[1389] እንድም ትርጉምና ከኃጢአተኞች ተግሳጽ[1390] የተወሰዱ ቅዱስ ቁርባንን የሚመለከቱ ቀኖናት ናቸው ።

ስለዚህ በፍትሐ ነገሥት በቀጥታ የተጠቀሰው ቀኖና ዮሐንስ ብቻ ሲሆን ነገር ግን በቀጥታ ባልሆነ መንገድ በፍትሐ ነገሥት የሚጠቀሰው ቀኖና ሁል ጊዜ እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ በሚል ቅርጽ ነው የሚያጋጥመው[1391] ወይም አፈወርቅ ብቻ ። "ቅዱሳን መምሕራንና አፈወርቅ ስለ ሁለት ነገሮች አንዱ በውር ሌላው ግልጽ ይረዳሉ"[1392] ። አፈወርቅም "እግዚአብሔር በዚህ ቃል ከአራት ትእዛዝ ብዙውን አሳለፈ ብሏል"[1393]።

አፈወርቅ በተማጻጹ እንዲህ አለ ለእንግዶችና መንገደኞች የሚያሻቸው ማደሪያ የታወቀ ስለሆነ…[1394] ሆኖም ግን በፍትሐ ነገሥቱ መቅድም እነዚህ ቀኖናት "ሐ" በሚል ምኅጻረ ቃል እንደሚጠቀሱ ቢመለከትም[1395] ዮሐንስ በዚህ ምኅፃረ ፊደል ሳይሆን በስሙ ዮሐንስ ወይም ቅጽሉ አፈወርቅ እየተባለ እንደተጠቀሰ የተመለከተ ሲሆን "ሐ" በሁለት መልኮች ሊታይ ይችላል አንድም የዮሐንስ መካከለኛው – ሁለተኛው ፊደል "ሐ" ወይም ከቅጽሉ አፈወርቅ በግሪክ ቋንቋ

1385· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9 ቁጥር 284።

1386· Mss Borgio Etiopico ቁጥር 9።

1387· A. Αλιβιζάτους Οἱ Ἱεροὶ Κανόνες ገጽ 422 445

1388· ቀኖና ለ

1389· ቀኖና ሐ

1390· ቀኖና ሀ

1391· ለምሳሌ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 43 ቁጥር 1453 አንቀጽ 23 ቁጥር 814።

1392· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ቁጥር 806

1393· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ቁጥር 804

1394· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ቁጥር 819

1395· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

አፈወርቅ ሕርዖስቶሞስ ማለት ስለሆነ የመጀመሪያው ፊደል "ሕ" ሊሆን ይችላል ።

6· ቀኖናት ጢሞቴዎስ ፡ ጢሞ — ጢሞቴዎስ[1396]

በፍትሐ ነገሥት ቀኖናተ ጢሞቴዎስ ተብለው የሚጠቀሱት ቀኖናት በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ በቀረቡ ጥየቄዎች ልክ የተሰጡ 18 መልሶችን ያዘጋጀው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አንደኛ ጢሞቴዎስ (381–385) ቀኖናት ናቸው። እነዚህ ቀኖናት በ5ኛው 6ኛው የትሩሎስ ሲኖዶስ ሁለተኛ ቀኖና የጸደቁ ሲሆኑ በሁሉም ማለት ይቻላል በግሪክ ቋንቋ በሚገኙ ቀኖናውያን መድበላት ይገኛሉ[1397] ። የእነዚህ 18 ጥያቄዎችና 18 መልሶች ቀኖናት ንጽጽር በፍትሐ ነገሥት በተጠቀሙበት መልካቸው እንደሚከለው ሊታይ ይችላል ።

"ጋኔን የያዘው ሰው የማይሰደብ ከሟለውም በኋላምራቁን የማያስለ ግገው ከሆነ በበዓላት ቀን ሥጋና ደሙን ይቀበላል ። ምሥጢሩን የማያቃልል በሌላም በኩል የማይሰድብ ከሆነ በየቀኑ ሳይሆን እሑድ ቀን ብቻ ይቁረብ[1398]። በጢሞቲዎስ ስም በፍትሐ ነገሥት የሚደረገው ጥቅስ በዚህ ትእዛዝ ብቻ ይወሰናል። ይህም ትእዛዝ "ጢሞ" በሚል ምኅፃረ ቃል ይጠቀሳል[1399]።

7· ቀኖናተ አትናቴዎስ

8· ቀኖናተ ኤጲፋንዮስ

በፍትሐ ነገሥት መቅድም የምንጮች ዝርዝር ሳይመለከቱ ነገር ግን በውስጡ—ሰነዱ "በ—እንደተነገረው" በሚል ቅርጽ እየተጠቀሱ የሚገኙ ሌሎች ቀኖናት አበውም ያጋጥማሉ ።

7·1 ቀኖናተ አትናቴዎስ ዘቁስጥንጥንያ

በዚህ መልክም የሚታዩ የመጀመሪያ ቀኖናት ቀኖናተ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘቁስጥንጥንያ ሲሆኑ ከእነዚህም ቀኖናት በፍትሐ ነገሥት

1396· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1397· A. Αλιβιζάτου, Οί Ιεροί Κανόνες ገጽ 401 - 405

1398· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13 ቁጥር 506

1399· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

የሚገኘው ጥቅስ በቀኖናተ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ እንደሚነገረው "ኤጲስ ቆጳስ ሆኖ መሾም የሚችለው ሥልጣን ካህናት ከእላቸው መነኩሳት መካከል ወይም ብቁ ሥራ ሠርቶ ያስየና የተለየ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር ቅዱሳት ቀኖናትን መጠበቁን ያሳመነ መነኮስ መሆን ይገባዋል "1400" የሚለው ቀኖናዊ ትእዛዝ ነው ።

በሌላ በኩል ከዚህ ጋር ሊታወሱ የሚችሉ ሦስት ቀኖናተ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ሲሆኑ እነዚህም ሶስት ቀኖናት ከሚከተሉት መልዕክታት 1) ወደ መነኮስ እሙን ከተላከ መልዕክት 2) ስለ በዓለ ፋሲካ ከተላለፈ መልዕክት እና 3) ለኤጲስ ቆጳስ ሩፊያኖስ ከተሰጠ መልዕክት የተቀነባበሩ ቀኖናት ናቸው[1401]

እነዚህም ሶስት ቀኖናተ አትናቴዎስ ሊቀጳጳሳት ዘእስክንድርያ በመጠኑም ቢሆን በጥንት ቤተክርስቲያን ታሪክ የታወቁ ሲሆኑ ቀኖናተ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘቁስጥንጥንያ ግን ብዙም አይነገርላቸውም ።

8·1 ቀኖናተ ኤጲፋንዮስ

ቀኖናተ አትናቴዎስ የማንኛው አትናቴዎስ ቀኖናት — ቀኖናት ዘአትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘቁስጥንጥንያ መሆናቸው በፍትሐ ነገሥቱ አዘጋጅ እብነ እል አሳል ሲመለከቱ ቀኖናተ ኤጲፋንዮስ የማን ኤጲፋንዮስ ቀኖናት እንደሆኑ አልተመለከቱም ።

በጥንት ቤተክርስቲያን ታሪክ ብዙ ኤጲፋንዮሶች እንደነበሩ ሲታወቅ በቀኖናት ባለቤትነት የታወቀ ኤጲፋንዮስ ግን ብዙም አይወሳም ቢሆንም በፍትሐ ነገሥት በቆኖናተ ኤጲፋንዮስ እንደ አለ የተጠቀሰው ድንጋጌ" በታጨች ድንግል ልጅ የሰሰነ ሰው የቀድሞ እጮናዋ ካልተዋት በስተቀር ሊያጋቡት እንደማይቻል ፡ ባልታጨች ድንግል ልጅ የሰሰነ ደግሞ ማግባት ወይም አለማግባት መቻሉ ወይም መገደዱ በቤተሰቦች ፈቃድ እንደሚሆን ከዚህ በኋላ ድነም ብትሆን ወይም መልከ ደካማ በግድ ይችን ልጅ ማግባት እንደሚኖርበት" የሚያዘው ነው [1402]

1400· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 89። P. Tzadua, Fetha Nagast ገጽ 85

1401· A. Χριστοφιλοπουλου, Ελληνικόν Εκκλησιαστικόν Δίκαιον ገጽ 100

1402· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 878 (ሥርዋጽ እንደ ማብራርያ) P. Tzadua, Fetha Nagast ገጽ 139

ምዕራፍ ዘጠኝ

ቀኖናት ዘሊቃነ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ

በዚህ ክፍል የሚመረመሩት በቀጥታ የፍተሐ ነገሥቱ ምንጮች ሁነው የተመለከቱ የሊቃነ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ቀኖናትና በአጋጣሚ ከምንጮቹ ጋር ከአላቸው መተሳሰር የተነሳ የተወሰኑ አባቶች ሥራዎች ናቸው ። ይህም በቀኖናተ አበው መንደርደሪያ ላይ የተመለከተ እንደመሆኑ መጠን[1403] ወደ በለጠ ዝርዝር መራመድ አላስፈለገም ።

1·ቀኖናተ ክርስቶዱሎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ፡ ክርስጣ—ክርስቶዱሎስ [1404]

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት (ፓትርያክር) ክርስቶዱሎስ ዘውእቱ ገብረ ክርስቶስ Abdelemesih (1047–1077) በግብጽ ቤተክርስቲያን ቀኖናዊ ሕግ እስከ ዛሬ ድረስ ከፍተኛ ኃይልና ተፈጻሚነት ያላቸው 30 ቀኖናት ባለቤት እንደሆነ ይታወቃል[1405]

እነዚህ የሊቀ ጳጳሳት ክርስቶዱሎስ ቀኖናት በተለይ በፍትሐ ነገሥት በተጠቀሱበት መልካቸው ሥርዓተ ቅዳሴውያውን ቀኖናት ናቸው።

በፍትሐ ነገሥቱ ሥርዐተ ቅዳሴን ፣ ቅዱስ ቁርባንን እና ሥርዐተ አጽዋማትን የሚመለከቱ ሦስት ቀኖናት ተጠቅሰዋል ።

1403. Vansleh Histoire de l' 'eglise ገጽ 282።

1404· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1405· Vansleb, Histoire De' è'glise d'Alexandrien. Paris 1677 ገጽ 224 . E Renuadotius Historia Partiarchum Alexandrinorum Jacobitarum... ገጽ 418-449. J.F. Neale. A History of the Holy Eastern Church Partiarchate of Alexandria. London. 1834. T. II 213-222. King: The Rights of Eastern Christendom T II 1949. 348. O Meinardus: A Study of canon Law of Coptic Church.
B.S.A.C. 1961—1962 T XIV ገጽ 10።
O.H. Burmster: The Canons of Christodoulos Patriarch of alexandria Muséon XLX 1932 ገጽ 31-84., sawirus ibn al Makatai.
History of Patriarchs of Egyptian Church Vol. II Part III Cairo 1959 ገጽ 249-255: O.C.A. Patriarchati Orientalis de Prim Milano Riedel Die Kirchenrechtsquellen ገጽ 299 A. Maio Scriptoum T.IV ገጽ 280

ሀ)ስለ ሥርዐተ ቅዳሴ የሚናገረው ቀኖና "ቅዳሴው ሳይጀመር ያልነበረ ካህን ማንኛውም ማዕርግ ይኑረው ቅዱስ ሥጋውንና ደሙን ወይም ሥጋውን በእጁ እንሥቶ መቀበል አይገባውም..." ሲል ይደነግጋል [1406] የቀኖናው ቁጥር አልተመለከተም ።

ለ) ስለ ሥጋ ወደሙ የሚናገረው ቀኖና ከሠርሆተ ሕዝብ አስቀድሞ ሥጋውንና ደሙን በሌላ ኅብስት አያድፈው ፣ ማየ መቁረሩም ከአፉ ምንም ጠብ አይበል" ሲል ያዛል [1407]

ሐ) አጽዋማትን የሚመለከተው ቀኖና እንዲህ ሲል ይደነግጋል ያዛል ። ክርስቲያኖች 40 ቀን ጾምን መጾም ከጥሉላት መከልከል እንደ አለባቸው ሥርሀተ ጋብቻም እንደማይፈቀድ በስሙነ ሕማማት በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሚደረግ ፍጹም አገልግሎት በስተቀር ጥምቀተ ክርስትና፡ ሲመተ ክሀነት ፡ ጸሎት ፍትሐት እንደማይገባ ሆኖም ከዚህ ዓለም ስለሚለዩ ሰዎች በበዓለ ሆሣዕና ግንዘተ ሙታን ፡ መጽሐፈ ሐዋርያት ፡ ወንጌላትና ፀሎተ ፍትሐት መነበብ እንደሚኖርባቸው ።

በጸሎተ ሐሙስ ጸሎተ ተአምኖ ፡ እግዚእ ሕያዋንና ጸሎተ ቡራኬ እንደማይጸለይ ፡ ቅዳሜ ግን እግዚእ ሕያዋን ጸሎተ ፍትሐትና ከመሳሳም በስተቀር ጸሎተ ዕጣን መጸለይ እንደሚቻል ። በዕለተ እሑድ ሥርዓተ ግንዘትን ማድረግ ፡ በፋሲካ ቀን ማልቀስ (ማዘን መተከዝ) እንደምይፈቀድ በአጠቃላይ በጾም ወራት ተድላና ደስታ ማድረግ ፡ ሥርዓተ ጋብቻን ማከናወን ፡ ጥምቀተ ክርስናን መፈጸም ፡ ሲመተ ክሀነትን መስጠት እንደማይቻል ፡ ይህም ሲባል ግን ሞት ለሚ ስጋቸው ሰዎች ጸሎተ ፍትሐት ማድረግና ጥምቀተ ክርስትናን መፈጸ' እንደሚፈቀድ የሚደነግገው ቀኖና ነው[1408]

በእርግጥ ይህ 30ኛ ቀኖና ክርስቶዱሎስ በፍትሐ ነገሥት ተይዞ የሚገኘው በሥርዋጽነት ነው ። ሆኖም ያለፉት 2 ቀኖናት በመሠረታዊ ምንጭነት ነው የሚታዩት ።

ይህ የመጨረሻው ቀኖና ክርስቶዱሎስ በፍትሐ ነገሥት በተያዘበት ሰነድነቱ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ሕግ መሠረታዊ ተጽዕኖ ቢኖረውም እስከምናውቀው ድረስ ቀኖናተ ክርስቶዱሎስ በ

1406. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 12 ቁጥር 496 ቀኖናው ቁጥር አልተማለከተም ።
1407· ቀኖና ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13 ቁጥር 527 ቀኖናት 30 ሲሆኑ 65ኛ ተኖና ከየት መጣ?
1408· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15 ቁጥር 599 P. Tzadua: Fetha Nagast ገጽ 87 ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
1409· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

እዝ ቋንቋ ተተርጉመው አይገኙም ።

ቀኖናተ ክርስቶዱሎስ በፍትሐ ነገሥት "ክርስጣ" በሚል ምኅፃረ ቃል ይጠቀሳሉ[1409] ።

2·ቀኖናተ ገብርኤል 2ኛ ኢብን ቱራይቅ

70ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት (ፓትርያርክ) ገብርኤል ዳግማዊ Abu-l alá said ben Tarik/ibn Turaik (1131-1145) የግብጽ ቤተክርስቲያን የታወቀው ሐጌ ሕግ ነው ።

ሊቀ ጳጳሳት ገብርኤል -Ibn Turaik አዲስ ቀኖናትን ከማዘጋጀቱም ጋር የነበሩትን ቀኖናተ ቤተክርስቲያን አሰባስቦ መድበለ ቀኖናትን አቀነባበረ

የሊቀ ጳጳሳት ገብርኤል 2ኛ ኢብን ቱራይቅ የውርስ ሕግ Epitome Statuatorum De Hereditatibus ለፍትሐ ነገሥቱ የውርስ ሕግ አንቀጽ በእንተ ርስት አንቀጽ 42 ቅንብር ምንጭነት በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሰጥቷል[1410] ። ይህን የፍትሐ ነገሥት ውርስ ሕግ በምንጭነት ያገለገለውን የውርስ ሕግን ለማዘጋጀት ስለ አነሳሱት ምክንያቶች Ratio Leges ራሱ አባ ገብርኤል ሲናገር ስለ ሃላፊ ንብረቶችና ስለ ዓላማውያን ጉዳዮች—ሀብቶች እድል መተላለፍ ጉዳይ የክርስትና ሃይማኖት አባቶች ያስተላለፉት ሕግ ባለመኖሩ የንብረቶች እንዴት መያዝ ፡ መተላለፍ እንደሚኖርበት የሚያመለክቱ ቀኖኖት አያጋጥሙም ነበር ።

ስለቢህ ርስትንና ንብረትን አስመልክቶ ለሚነሱ ችግሮች መፍትሔ ለማግኘት ክርስቲያኖች የግድ ወደ ዓለማዊ—ሥጋዊ ሕግ ወይም ልምድ ከመሄድ ከአለማዳናቸውም በላይ በመካከላቸው የሚጋጩ ውሳኔዎች መስጠታቸው እንደ አልቀረ ግልጥ ነበር ።

ስለዚህ በክርስቲኖች መካከል የሚነሱት ርስትና ንብረት ነክ ጉዳዮች ልዩነቶች ግንኙነቶች በክርስትና ትምህርት ቀኖናውያን ሕጋጋት መሠረት መፍታት ይችሉ ዘንድ በእነዚህም ጉዳዮች ላይ የሚተላለፉት

1410· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 42 ቁጥር 1332 1340 :A.Maio: Scriptororum T.IV ገጽ 280 571

ውሳኔዎች – የፍርድ ቤቶች ውሳኔዎቾ አንድ ወጥነት እንዲኖራቸው ይደረጉ ዘንድ አስፈላጊነቱ ግዴታ ሆነ ። ስለዚህም ሊቀ ጳጳሳት ገብርኤል ከቅዱሳት መጻሕፍት ከቤተክርስቲያናውያት ቀኖናት ፡ ከቀኖናተ ነገሥት ጠስ ፣ መክ ፣ መግና መጅ እና ዲድስቅልያ ላይ በመመርኮዝ የተጠቀሰውን የውርስ ሕግ አዘጋጀ–ቀረጸ

ሊቀ ጳጳሳት ገብርኤል ኢብን ቱራይቅ ለዚህ ለፍትሐ ነገሥት ምንጭነት አገልግሎት ከዋለው የውርስ ሕግ ሌላ የኢጲስ ቆጳሳትንና ቀሳውስትን ሥነ ጠባያት ተግባራት–ትእዛዛት እና ግዝረትን ፡ ጋብቻንና ሥርዐተ ቀብርን ጉዳዮች የሚመለከቱ 32 ቤተክርቲያናውያት ቀኖናትን እንደጻፈ ይታወቃል[1411]

እስኪ ስለ ውርስ ከአባ ገብርኤል የተወሰዱትን ሁለት ትእዛዛት ብንመለከት

"እሱ ሚስት ብትኖረው እሷም ልጆችም ቢኖሯት ከእነሱ እንደ አንዱ ትቆጠር"[1412] ··· እግዚአብሔር ሰውን የምተረዳው ጓደኛ እንፍጠር ለት እነሱም አንድ አካል እንጅ ሁለት አካላት ስለ አይደሉ ከሚስት እንደታዘዘው መጠን ባል ከሚስት ንብረት ግማሹን መውረስ እንደሚ ችል ልጅ ከሌለው ሁሉንም መውረስ እንደሚችል[1413] መረዳት ይቻላል።

3·ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘሀገረ ድምያጥ

በፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ እብነ እል አሳል እንደ መድበለ ቀኖናት የተጠቀሰው[1414] እና ቀደም ብሎ የተወሳው[14 5] ብሔረ ሕግ ወቀኖና

1411. H.O. Burmster: the Law of Inheritance of Gabriel Ibn Turailk Lxx Patriarch of Alexandria: O.C.P.T.I./1935 ገጽ 315 327; Burmster: the Canons of Gabriel LXX patriarch of Alexandria O.C.P.t.i/1935 ገጽ 4 45 Burmster: the Canons of Gabriel Ibn Turaik Muséon.t XLVI/1933 ገጽ 43 54 J.Assemani: De Haereditate P.O.T.I. ገጽ 619 E. Renuadltius Historia Patriarchum Alexandrinorum Jacobitarum.. Paris 1713 ገጽ 500 513. J.Assemani: De Haereditate P.O.T.I.ገጽ 619 E. Renuadotius, Historia II ገጽ 248 E. Buetcher: the History of the Church of Egypt, London 1897. ገጽ 80 Malans.A. History of Copts and Their Churches Trans From the Arabic of Iaq – Ed. Idin el waqrizi ገጽ 93

1412· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2 አንቀጽ 42

1413· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2 አንቀጽ 42

1414· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1415· ከዚሁ ገጽ 58

(መድበለ ቀኖናት) ዘሚካኤል ሊቀ ጳጳሳት ዘሀገረ ድምያጥ ፍትሐ ነገሥት እስከ ተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የግብጽ ቤተክርስቲያን ዋናው መጽሐፈ ሕግ ነበር ይባላል ነገር ግን ይህ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘገብርኤል ኢብን ቱራይቅ[1416] የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብነ እል አሳል በተመሠረተባቸው የፍትሐ ነገሥት ምንጮች ዝርዝር አልተያዘም ምክንያቱም የፍትሐ ነገሥት ምንጮች የተቀነባበሩ ሥራዎችን ወይም መድበላትን አይመለከቱም ነገር ግን የተደነገጉ ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናትና ሥጋውያን ሕግጋት ሰነዶችን ነው የሚመለከተው ።

ፍትሐ ነገሥት የሚይዛቸውን ፍሬ ነገሮች መልክ ለማስያዝም ሆነ ምንጮችን ለማሰባሰብ እነዚህ ብሔራተ ሕግጋት ወቀኖናት–ቀኖናውያን መድበላት በተለይ ዘሚካኤል[1417] ዘድምያጥ ለፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብነእል ኦሳል እንደ መመሪያ ነጥቦች ሁነው ረድተውታል ።

በሌላ በኩል ሚካኤል ዘድያምጥ በግብጽ ቤተክርስቲያን ብዙች ቀኖናውያን መድበላት እየተያዙ የሚገኙት በተለይ ሥርዐተ ቅዳሲያዊ ይዘት[1418] ያላቸው 10 ቀኖናትን እንደጻፈ ይታወቃል ነገር ግን እነዚህም ቀኖናት እንደ ልዩ ልዩ ቀኖናተ ገብርኤል ኢብን ቱራይቅ በፍትሐ ነገሥት ምንጮች ዝርዝር አልተያዙም–አልተወሰዱም ።

4·ቀኖናተ ቄርሎስ 2ኛ

67ኛው የእስክድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ 2ኛ (1078–1092) በ31 ወይም 34 የተከፈሉ ቀኖናትን እንደ አሳተመ ይታወቃል እነዚህም ቀኖናት በግብጽ ቤተክርሲቲያን አብዛኞች ቀኖናውያን መድበላት ተይዘው ሊገኙ ችለዋል[1419]

ሆኖም እነዚህ ቀደኖናት በግብጽ ቤተክርስቲያን ሥርዐተ ቀኖናት የተለየ ከፍተኛ ቦታ ይዘው እንደነበር ቢታወቅም በፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ

1416· ከዚሁ ገጽ 282
1417. A-Maio Scriptorum... T IV ገጽ 280-295
1418. W-Riedel: Die Kirchenrechtsquellen ... ገጽ 299
1419. E.Renaudotius: Historia Patriarchum Alexandrinorum Jacobitarum ገጽ 421—47 Malan. S.A. History of Copts and their Churches ... ... ,92 King, the Rites of Eastern Churches ... ገጽ 348 O.Cp. 1968 ገጽ95 Neale History of the Holy Eastern Church:the Partiarchate of Alexandria t. II 1843 ገጽ 288

እብነ እል አሳል አለመወሳታቸው ጥያቄን ያስከትላሉ ።

5·ቀኖናተ ቄርሎስ 3ኛ ኢብን ላቅላቅ[1420]

75ኛው የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳሳት (1235—1243) ቂርሎስ 3ኛ ኢብን ላቅላቅ ሥርዐተ ቅዳሲያዊ ፡ ሥነ ምግባራዊና ሥነ ሥርዐታዊ ልማዳዊ ይዘት ያላቸው የተወሰኑ ቀኖናትን እንደጻፈ ይታወቃል[1421] ከእነዚህም ቀኖናት በብዙች የግብጽ ቤተክርስቲያን መድባለት ቀኖናውያን ሰፍረው ይገኛሉ[1422]

ቀኖናተ ቄርሎስ ኢብን ላቅላቅ በእብነ እል አሳል በፍትሐ ነገሥት ምንጭነት አልተጠቀሱም ሆኖም ያውም ተከታይ አንቀጽ (52) ሳይሰጣቸው የፍተሐ ነገሥቱ የመሠረሻው ይዘት ሆኖ ተቀምጧል በሌላ አነጋገር ይህ የመሠረሻው ቁጥር አልባ አንቀጽ የአንቀጽ 42 ተቀጽላ ሆኖ ይቆጠራል ምክንያቱም አንቀጽ 42 እና ይህ የመጨረሻው አንቀጽ (52) ስለ ውርስ ጉዳዮች ነው የሚናገሩት ማለት አንቀጽ 42 በእንተ ርስት በሚል ርእስ ሲነሳ ይህ አንቀጽ (52) አንቀጸ ተወርሶ የሚል ርእስን ይዞ ይገኛል ልዩነት ቢኖር በጣም ወደ ዝርዝር ሁኔታዎች ሳንገባ መረዳት የምንችለው የመጨረሻው አንቀጽ እነዚህ ቀኖናት የእስክድርያው ሊቀ

1420· ፍትሐ ነገሥት አባሪ አንቀጽ
1421· G.Graf, Geschichte TIII ገጽ 363 364
Graf, Jahrbuch für liturgie issenschaft ገጽ 119– 134
Renuadotius, Historia Patriarchum Alexandrinorum Jacobitarum ···ገጽ 576—599፡ Neale—A History of the Holy Eastern Church ···ገጽ 304 Vansleb: Histoire del'i glise ገጽ 294— 295። Burmester, The canoms of cyrill III Laqlaq patrlarch Alexandriá 1956. B.S.A C.T XIII – XIV.
Burmster: the Canons of Cyrill III of Alexandria: Museum T.LIX. 1966 ገጽ 245-288 O.C.P 1933 SEP I. Meinsardus: a study of the Canon Law of the Coptic Church R A.C. 1961—1969 ገጽ 60 Κεφέλεβ Ζ. Περί τής ανεξαρτησίας τής Αιθιοπικής Εκκλησίαςገጽ 57ΚΟΣΤΙΝ; Η λατρεία της Κοπτικής Εκκλησίας 1972 ገጽ 55
Kings:the Rites of Eastern Churches ገጽ 351 C.O.I–1968 ገጽ 70
1422· ለምሳሌ ቀኖናዊ መድበል ዘመቃርዮስ ቁጥር 65—67—70 59 ። በዚህ መድበለ ቀኖናት የተያዙት ቀኖናት 10 ቀኖናት ናቸው ። ቀኖናዊ መድበል ዘዮሴፍ ስምአን Assemani ቁጥር 35 ግብጥ–ሱርስጥ መድበለ ቀኖናት ቁጥር 2 Riedel: Die Kirchenrechts Quellen... ገጽ 301 A Maio: Scriptorum ... T IV ገጽ 280 – 281· 238 A Malans. A History of the Copts and Their Churches ... ገጽ 97

ጳጳሳት አባ ቄርሎስ ከኤጲስ ቆጳሳት ፥ ሊቃውንትና መኳንንት ጋር የተስማማባቸው መሆናቸውን ነው[1423]

ነገር ግን ያለው አስተሳሰብ እነዚህ ቀኖናት ወይም ይህ አንቀጽ ፍትሐ ነገሥት ከተቀነባበረ በኋላ ቆይቶ ተዘጋጅቶ እንደተያዘ ነው ። ይህ ባይሆን ኑሮ ተከታታይ አንቀጽን አሁን የሰጠነውን አንቀጽ 52 ይዞ መገኘት ነበረበት ።

፮·ቀኖናተ ቆዝማስ (ኮዝሞስ)

ከእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ ቆዝማስ (ኮዝሞስ) አንድ ዓይነት ቀኖናዊ መድበል እንደ አዘጋጀ መረዳት ሲቻል ይህም ሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ ከኤጲስ ቆጳሳት ፥ ሊቃውንትና መኳንንት ጋር ሆኖና ተስማምቶ ያዘጋጀው የፍትሐ ነገሥቱ አባሪ –ተቀጽላ አንቀጸ ተዋርሶ አብዛኛው ይዘት (ፍሬ ነገር) የመጣበት የታቀደበት ወይም ቀኖናዊ መድበል መሆኑ ታውቋል ይህ የመጨረሻው ክፍል መንደርደሪያ ሀረፍተ ነገር የተጻፈበት ዘመን በመስከረም ወር 17 ቀን 958 ዓመተ ስማዕታት (1241 ዓ·ም) ነው ቀጥሎም ይህ የፍትሐ ነገሥት መጨረሻ ክፍል አንቀጸ ተዋርሶ ከሊቀ ጳጳሳት ቀዝሞስ ውሳኔዎች – መድበለ ቀኖናት ላይ በብዛት ከመመሥረቱ በተጨማሪ ከሦስት ምንጮች ላይ ተመርኩዟል ።

1· ትምህርተ ሊቃናተ ሕግ (የዳኞች ውሳኔዎችና ሕግ ሊቃውንት ሥነ ጽሑፎች)

2· በአምሳላዊ ትርጉም – ሥርዐተ ትርጉም የሚመጡ ቀኖናት ሕግ መርሖች

3· የየአገሮች ልማዶች – ተውፊታውያን ሕጎች [1424]

ይህ የፍትሐ ነገሥት የመጨረሻ ክፍል ከእነዚህ ምንጮች ላይ ተመርኩዞ እንደተዘጋጀ ሲታወቅ በ8 ምዕራፎች ተከፍሎ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች እንደያዘ ተዘርዝሯል ።

1· ለውርስ ስለተተወ ንብረት [1425]

2· ሚስት ከባል ወራሾች ጋር ውርስን መካፈል [1426]

1423· ፍትሐ ነገሥት አባሪ አንቀጽ (አንቀጽ 52)
1424. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 (ተቀጽላ)
1425· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 ቁጥር 1832
1426· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 ቁጥር 1835

3· የወራሾች ቅደም ተከተል (ተራ) [1427]

4· የኤጲስ ቆጳሳትና መነኰሳት ንብረት ውርስ [1428]

5· ነፃ ለወጡና ስለ አልወጡ ባርያዎች ንብረት ውርስ [1429]

6· ያለ ኑዛዜ አለመወረስ [1430]

7· የጸና ኑዛዜ ቢኖርም መውረስ አለመቻል [1431]

8· ስለ አጠራጣሪ ውርስ ጉዳይ ለምሳሌ ወራሽና ተወራሽ አንድ ጊዜ መሞት [1432]

የፍትሐ ነገሥቱ አባሪ – ተቀጽላ የመጨረሻ ክፍል ጸሐፊ እብነ እል አሳል ቆዝማስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት እንደነበር ሲናገር መቼ እንደነበር ግን አያወሳም ምክንያቱም በ1241 በራሱ የተጠቀሰው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት (1235–1241) ቄርሎስ 3ኛ ኢብን ላቅላቅ ነበርና ለዚሁ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሁለት መሠረተ ሀሳቦች በአእምሮ ውስጥ ይዘዋወራሉ ።

ሀ· የተመለከተውን ዘመን [1241] ስሕተት ሊሆን ይችላል ማለትም ቀዝሞስ የሚባል ሊቀ ጳጳሳትም የነበረበት ሌላ ጊዜ ነበርና ምክንያቱም ቀዝሞስ በሚል ስያሜ ሦስት የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት – ፓትርያርኮች ይወሳሉ ከእነዚህም የመጀመሪያው አንዱ ቀዝሞስ ቀዳማዊ 44ኛ ሊቀ ጳጳሳት 722 ዓመተ ስማዕታት (1005 ዓ·ም) ፤ ሁለተኛው ቀዝሞስ ዳግማዊ 58ኛ ሊቀ ጳጳሳት 923 ዓመተ በማዕታት (1216 ዓ.ም) ሌላው ቀዝሞስ ሣልስ 59ኛው ሊቀ ጳጳሳት 935 ዓመተ ሰማዕታት (1218 ዓ·ም) አልፈዋል ።

ለ· ቀዝማስ ሊቀ ጳጳሳት – ፓትርያርክ ሳይሆን በሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ 3ኛ ሥር ከነበሩት ኤጲስ ቆጳሳት አንዱ ነበር የሚለው አመለካከት ሌላው ነው ።

ይህ የመጨረሻው ግንዛቤ በራሱ በአንቀጹ መግቢያ ላይ በተጻፈው ዐረፍተ ነገር ላይ ይመሰረታል ። የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ጌታ አባ

1427. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 ምዕራፍ 3 ቁጥር 1837
1428· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 ምዕራፍ 4 ቁጥር 1853
1429· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 ምዕራፍ 5 ቁጥር 1858
1430· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 ምዕራፍ 6 ቁጥር 1861
1431· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 ምዕራፍ 7 ቁጥር 1865
1432· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52 ምዕራፍ 8 ቁጥር 1866

ቄርሎስ ከኤጲስ ቆጶሳት ከሊቃውንቱና መኳንንቱ ጋር የተስማማበት ነው ይላል ።

ስለዚህ ከሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ወደ ስምምነት ከደረሱት ኤጲስ ቆጶሳት መካከል አንዱ ቀዝሞስ ነበር ማለት ነው ከዚህም በመነጨ ቀዝሞስ የጻፈው ፍሬ ሃሳብ የዚህ ክፍል አብዛኛውን ምንጭ ሊይዝ ችሏል ። ምክንያቱም በሌላ በኩል በኤጲስ ቆጶስ ማዕርግ ሊቀ ጳጳሳት ሊሾፈንበት ይችላል ስለዚህም በዚህ "ከኤጲስ ቆጶሳት ... ጋር የተስማማበት" በሚልበት ጊዜ ሊቃነ ጳጳሳት ማለቱም ሲሆን ስለዚህም ኤጲስ ቆጶሳቱ በሚለው ገጽታ ገብርኤል ኢብን ቱራይቅ ይገኝበታል[1433] ምክንያቱም ይህ አንቀጽ የሊቀ ጳጳሳት ገብርኤል ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘምንጭነት የተያዘበት አንቀጽ 42 አባሪ - ተቀጽላ ሆኖ ይቆጠራልና[1434]

ከላይ እንደተባለው ይህ የመጨረሻ አንቀጽ የመላው ፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ ቅንብር ነው? ከሆነስ በዚህ አንቀጽ የሰፈሩት ፍሬ ሃሳቦች ለምን አግባብነት ባለው አንቀጽ[1435] አልተደዋሐዱም? ወይም የሌላ ጸሐፊ ሥራ ነው? ግን ቆይቶ ከፍትሐ ነገሥት ጋር አባሪ - ተቀጽላ ሆኖ ተያያዘ? የሚሉ ጥያቄዎች በአእምሮ ሊነሱ ይችላል ።

ከዚህም በመነሳት ይህ የፍትሐ ነገሥቱ የመጨረሻው ክፍል (አንቀጽ 52) በፍትሐ ነገሥቱ መጀመሪያ ሕትመት - ሥርጭት ጊዜ ማለትም በእብነ እል አሳል ተዘጋጀም ወይም አልተዘጋጀም ወይም ቆይቶ ከፍትሐ ነገሥቱ ጋር ተያያዘ ከፍትሐ ነገሥቱ የማይነጣጠል ክፍል ሆኗል ወደሚል መደምደሚያ ነው የሚደርሰው ።

1433·P.Tzadua: Fetha Nagast ገጽ 313·

1434· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 42

1435· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 52

ክፍል ሦስት

ፍትሐ ነገሥት ክፍል ሁለት ፡ ሥጋዊ ሕግ

የሥጋዊ ሕግ መሠረታውያን ምንጮች

ምዕራፍ አሥር

ቀኖናተ ነገሥት — የሮማ — ቢዛንቲን ሕጎጋት

እብነ እል አሳል የፍትሐ ነገሥትን ሁለተኛውን - ሥጋዊውን ክፍል ለማቀነባበር ከላይ እንተደባለውና ራሱም እንደጻፈው ለቆስጠንጢኖስ የሮሜ ንጉሠ ነገሥት ለመንግሥቱ ሕጎጋት ይሆኑ ዘንድ በቤተ መንግሥት ተሰብስበው የኒቅያ አንደኛ ሲኖዶስ አባቶች (318 አባቶች) ከደነገጓቸው አራት ቀኖናተ ነገሥት (መጻሕፍተ ሕጎጋት) ምንጮችን እንደሳበ ተመዝግቧል ሆኖም ይህ ዓይነት አተራረክ ከትእዛዘተ ቀኖናት አንጻር ሲታይ ተቀባይነት የሚኖረው ሆኖ ነው የሚታየው ምክንያቱም ቀኖናተ ነገሥት ተብለው የሚታወቁት የፍትሐ ነገሥት - በተለይ ሥጋዊ ክፍል ምንጮች የኒቅያ አንደኛ ሲኖዶስ ሥራዎች - ውሳኔዎች ወይም ድንጋጌዎች አይደሉም[1447] ነገር ግን ቆይቶ የተዘጋጁና ከልዩ ልዩ ምንጮችም የፈለቁ ናቸው ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ በእነዚህ ቀኖናት ላይ ተገቢው ሂሳዊ ጥናት አልተደረገባቸውም ለማለት ባይቻልም ከፍትሐ ነገሥቱ ሰነድ ላይ ይህንም ከእነዚህ ቀኖናተ ነገሥት ጋር በማነጻጸር ግን የተደረጉት ጥናቶች በቂዎች አይደሉም ። ስለዚህም የፍትሐ ነገሥትን ምንጮች በተለየ የሁለተኛውን ክፍል ሥጋዊ ክፍል ወደፊት አንድ በአንድ እንደምንመለከተው በተለያዩ ባለሙያዎች ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል ። ስለዚህም ግልጥ ሥነ ገለጻ የሚከተለው ነው ።

Tandem Nicaeno quoque concilio orienalies adscribunt canones quos vocant imperatorum ... illi vero canones

1436· 1436 —ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 1·2

1447· ቀኖናተ ነገሥትን ስኒቅያ አንደኛ ሲኖዶስ ስለመስጠታቸው ጉዳይ ስለ ሌሎችም የተደረጉት አስተያየቶች ከዚህም ላይ ይሠራል ።

nihlii aliud sunt qunt quam exce⅓rpta ex nomcanonibus graecis, digestis codice Theodosiano et Jurtinianeo, novellis constitutionibus et basilicis, eo ordine disposita, ut corpus quoddam juris constituant, undelites inter christianos possint iudicari. Quamvis porro multas leges complectantur, quae ab illis imperatoribus latae sunt, qui a jacobitis et nestorianis orthodox non existimantur, habent tamen maximam inter omnes ecclesias auctoritatem. Illi autem canones ad Nicaenum concilium relatisunt, quia quasdam constitutiones continent, quae a Constantino Magno editae sunt circa concilii tempora".[1449]

1·ጠስ ፡ ተጥላሳት[1449]

ከቀኖና·ተ ነገሥት የመጀመሪያው መጽሐፍ "አብጣሊስ አብጠሊሳት" ወይም "ተጥላስ ተጥላሳት" [1450] በመባል የሚታወቀው ሲሆን 40 አርእስትን ይዞ የሚገኝ አንድ የሕግ ሰነድ ነው ። ይህም መጽሐፈ ሕግ በፍትሐ ነገሥት በሚጠቀስበት ጊዜ "ጠስ" ተጥላሳት በሚል ምሕፃረ ቃል ይታወቃል[1451] ተጥላስ - ተጥላሳት "ጠስ" በመባል የሚታወቀው የቀኖኖተ ነገሥት አንደኛው መጽሐፍ የቢዛንቲን ንጉሠ ነገሥት ባስልዮስ ዘመቄዶንያ (870 879) 40 አርእስት ይዞ የሚገኘው Procheiros Nomos ትርጉም መሆኑ በመጀመሪያ ሁኤም አማሪ M. Amari ታውቋል [1452] ይህን የአማሪ አስተሳሰብን ቀጥለው ሚሊዮናውያን

1448·Renuadotius Historia pariarchum Alexandrinorum Jacobitarum ab Marco usque ad finem saeculi XIII ገጽ 73

1449· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1450· አብጠሊስ አብጠሊሳት ፡ ተጥላስ ተጥላሳት ስለሚሉት ኃይለ ቃላት ከላይ ገጽ ተመልከት

1451· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1452. M. Amari, Catalogue Des Manuscripts De La Bibliotheque Nationale Par Le Barone De Slane Pt. I (Paris 1883) ገጽ 64 Riedel, die Kirchenrechtsquellen ገጽ 142 – 197

ምሑራን L.A. Nallino [1453] እና G.A. Costanzo [1454] በትክክል ይህ አንደኛ መጽሐፈ ነገሥት — መፍሐፈ ቀኖናተ ነገሥት ተጥላላት የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ባስልዮስ ዘመቄዶንያ Procheiros Nomos ነፃ ዐረብኛ ትርጉም መሆኑን በመደገፍ አጠናክረዋል ።

Procheiros Nomos ጊዜያዊ ሕግ ተብሎ የሚጠራው የሮማ - ቢዛንቲን ሕግ በ870 – 879 መካከል በባስልዮስ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘቁስጥንጥንያ እና አብረውት በነገሡት ልጆቹ ቆስጠንኖስ 8ኛና ሊዮን 6ኛ የታወጀ ሕግ ነው ። ይህ ሕግ ለመታወጅ የነበረው ዓላማ (Lege Ratio) የቀደሙ ሕጐችን ሥርዐተ ሕግ ለማስያዝ (ያለፈባቸውን ሕጐች ለመሠረዝ ፣ ሚኖርባቸውን ለማሻሻል ወዘተ የሚያስችል መንደርደሪያ ቅድመ ዝግጅታዊ ሕግን ማወጅ ነበር ። Repurgatio Veterum Legum ማጠራያዊ ሕግ ነበር ። ይህም ሕግ ቆይቶ ቀኖናተ ነገሥት Leges Imperiales ተብለው ከሚጠሩት ሕገጋት የጀመጀሪያውን ክፍል ይዞ የሚገኘው ነው።

እነዚህም ቀኖናተ ነገሥት Leges Imperatores K. Heibnach Basilicorum Libri LX በሚል ርእስ ሊታተሙ ችለዋል[1455] Procheiros Nomos በመጀመሪያ ከመግቢያና ከላቲን ትርጉም ጋር በE.C. Zachriae Von Ligenthal ታትሞ ሊሠራጭ ሲችል [1456] ቀጥሎም Procheiros Nomos: A Manual of Eastern Roman Law: The Procheiros Nomos Published by the Emperor Basili at Constantinople Between 867 – 879 A.D. በሚል

1453. tC.A. Nallino, Libri Guiridici Byzantini in version Arabe cristiane De Secoli XIt E XIfI R.R.A.L. Serie VI t. i. 1952 ገጽ 101 111 117

1454. G.A. Costazo 1.L'Ecloga Araba Nel Fetha Negest Lac sua Prima Versione In Italiano, Istituto Italiano Di Studi Legislativi Roma 1947

1455. Heimbach: Basilicorum Liberi Lipsiae LX ገጽ 108 አሁንም 1833 1868 ገጽ 108 K.Heimbach Griechenland (Griechisch-Römisches Recht Im Mittelialter Und in Der neuzeit A.E.W..K.T. 86 1868 ገጽ 303–305

1456. Zachariae Von Ligenithal: Procheiros Nomos Imperatorum Basilii Constantini Et Leonis Procheiros Heidelberg 1837 Zechar'iä Geschichte Des-Griechischen Römischen Rechts- Berlin 1893. Costanzo l'ecloga araha Nel Fetha Nagast E. lac Sua Prima Versione in Italiano. I.I.S.L. 1947 ገጽ 73 የግርጌ ማስታወሻ 13

ርእስ በ E.Freshfeld በእንግሊዝኛ [1457] እና እንደዚሁም በፈረንሳይኛ Suplber [1458] ታትመው ሊገኙ ችለዋል ።

ወደ መጨረሻም የZachariae ሕትመት ሰነድ Procheiros Nomos የላቲን ትርጉም ማለትም ግሪከኛው እናት ሰነድ በ1937 በዜፓን እንደገና ታትሞ ሁለተኛ በፎቶ ታይፕ ሕትመት በ1962 ተሰራጭቷል [1459]

ወደ መሠረተ ሐሳቡ ስንመለከትም Procheiros Nomos ከፍትሐ ነገሥት ጋር ከአለው ግንኙነት አንጻር በተጥላሳት ይመሳከራል ።

በፍትሐ ነገሥቱ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ሲመረመሩ—ሲጠኑ ይህ ቀኖና ባስልዮስ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘቁስጥንጥንያ Procheiros Nomos ተጥላሳት በመባል ለሚጠቀሱት ሰነዶች በቀላሉ ምንጭነትን ይዞ ሳይሆን የሚታየው በተቃራኒው ተጠጥላሳት የቀኖናተ ነገሥት

ቀኖናተ ባስልዮስ ቀዳማዊ በርካታ ምዕራፎች ቃል በቃል ግልባጭ ሆኖ ይገኛል ።

ስለዚህ ቀጥለን በፍትሐ ገሥት በተቀመጡበት—በተቀረጹበት መልካቸው በግልጥ ምሳሌነት ሊታዩ እንደሚችሉ የታመነባቸውን የተወሰኑ ተጥላላት ከProcheiros Nomos እናት አርእስቶች ጋር ጐን ለጐን በማስቀመጥ እነሆ ማመልከት ፣ ግንኙነታቸውን ማመሳከርና ማረጋገጥ ይቻላል ።

ርእስ

ሥርዐተ ጋብቻ ፣ የጋብቻ በሥጋ ዘመዶች መካከል — በሕጋዊ ጋብቻ የተዛመዱ ባይሆኑም ክልክል መሆን

ፍትሐ ነገሥስ ጠስ— —ተጥላሳት (አብጠሊስ)

የመጀመሪያው ክፍል ፣ የሥጋ ዘመዶች ጋብቻ ነው ። ከሕግ ጋብቻም ወገን ባይሆኑ እነዚህም (እነ ህም) ሦስት ወገን ናቸው ። ወደ ላይ ያሉ ወላጆች አያቶች ከዚያም በላይ ያሉ ቅድም አያቶች ናቸው ። ወደ ታች ያሉትም ልጆች የልጅ ልጆች፣ የልጅ ልጆች ልጆች ናቸው ። ወደ ጐን ያሉትም የአባቶች ወንድሞች፣ የአባቶች እህቶች ፣ የእናት ወንድሞችና እህቶች ወንድሞችና የወንድሞች ልጆች ዳግመኛም ከአባቶችና ከአያቶች ስለተወለዱ የተያያዙ ዘመዶች እነዚህ ናቸው[1460]።

Procheiros Nomos የሥጋ ዝምድና በሦስት መስመሮች

— ወደ ላይ ወደ ታች ወደ ጐን ይከፈላል ማለትም ወደ ላይ መስመር ወላጆች — አባት እናት ወንድ አያት ሴት አያት ከእነሱም ወደ ላይ የሚቀጠሩ ። ወደ ታች መስመር ተወላጆች ልጅ ወንድ ልጅ ሴት የልጅ ልጅ ወንድ የልጅ ልጅ ሴት የእነርሱም ወደታች የሚቀጥሉ ። ወደ ጎን መስመር ያልወለዱን ወይም ከእኛ ያለ ተወለዱ ወንድም እህት አጎት አክስት ወንድም በልጅ የእህት ልጅ የአጎት ልጅ የአክስት ልጅ እነሱም ወደታች የሚከተሉት [1462]

ከዚህ ላይ መታወስ የሚኖርበት መሠረተ ሐሳብ ጋብቻን የሚከለክሉ የዝምድና ሐረጐች ናቸው ። በሁለት ተከፍለው በፍትሐ ነገሥት በዝርዝር በመመልከታቸው ነው

1· ጋብቻ በግብጻውያንና ንስጥሮሳውያን በክፊል በሶርያውያንም ዘንድ እስከ ሦስት የዝምድና ሐረግ ክልክል ሲሆን 4ኛው እንደሚፈቀድ (ይህም በቀኖናተ ሐዋርያት ባይመለከትም በኒቅያ ጉባኤ ቀኖና ስለሚፈቀድ) የዚህ ድንጋጌ ዓላማም ሩቅ የዝምድን ሐረግ ቁጥራቸው — ብዛታቸው የማይፈቅድላቸው ክርስቲያኖች ዘንድ የጋብቻን ችግር

1457· E.H. Freshfield, A Manual of Eastern Roman Law, Thr Procheiros nomos, cambridge Un. press 1928

1458. Spulber. Paris 1929

1459. Jus graecoromanum T.II. ገጽ 115 288

1460· ጠስ 6 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 842

1461· Procheiros Nomos TIT 7.A, Jus Graecoromanum ገጽ 134

1462· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 842

ለመፍታት ታስቦ ከአራተኛ ትውልድ ጀምሮ መጋባትን መፍቀድ ነው ።

2· ጋብቻ እስከ 6ኛ የዝምድና ሐረግ ድረስ ክልክል ነው ። ይህም በመለካውያን ዘንድ የጸና ሕግ ነው ። (4ኛው አብጠሊስ እንደጻፈው)[1463] ይህ እስከ 7ኛው ዝምድና ሐረግ (ደረጃ) ጋብቻ የሚከለክል ቀኖና በኢትዮጵጰያ ፍትሐብሔር ሕግ ተደንግጓል ። የሥጋ ዝምድና አቆጣጠር የጋራ ከሆነው የዝምድና ደረጃ ጀምሮ ግራና ቀኝ ካለው ትውልድ መስመር እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ነው ። የሥጋ ዝምድና ከሰባተኛው የትውልድ ደረጃ ወዲያ ምንም ውጤት አይሰጥም[1464]

ርእስ
ስለመሸጥና መግዛት

ፍትሐ ነገሥት ጠስ (ተጥላሳት —አብጠሊስ)

ሻጭና ገዢ በገንዘባቸው ሥልጣን ያላቸው ካልሆኑ በቀር መገበያየት እውነተኛ አትሆንም ። በዕውቀት ካልተስማሙ ከመተዳደር ሥር ካልሆኑ ገዥ ለሻጭ ለመስጠት ገዥም ያለ ቅሚያ በመቀበል ካልሆነ በቀር መሸጥ — መግዛት አልተፈጸመም ። የመረጡት ሌላ ሰው ካልተቆጣጠረ ሁለቱ አይስማሙም ። ከእነርሱ አንዱ በጓደኛው ፈቃድ እንዲሆን ከወደደ ቢወድ ይፈጽም ባይወድ ይሻር ከመስማማታቸው በፊት በዋጋ ቢለያዩ ትቀራለች ወይም የገዥ መቀበልና የሻጭ መስጠት — የሚሸጥና የሚገዛ

PROCHEIROS NOMOS

የሽያጭና ግዥ መሠረተ ሐሳብ በዕቃና ዋጋ ልውውጥ ሂደት በተደረሰበት ስምምነት መሠረት ገዥው ዋጋውን ሲከፍል ሻጩ እቃውን ሲያስረክብ ይከናወናል ። ነገር ግን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱ ገዥ ዋጋውን ሲከፍልና ሻጩ ዕቃውን ሲያ

1463· Ecloga Leonis Et Constantini. Tit. 2B'. Procheiros Nomos Tit 39 AB'

1464· የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 551 1 2 ፡ 582

ሁለቱ በፈቃዳቸው ነውና[1465]

ስረክብ የገዢና ሸያጭ ሁኔታ ይፈጸማል[1466]

ይህ ስለ ግዥና ሽያጭ የሚናገረው ጥቅስ በProcheiros Nomosሆነ በፍትሐ ነገሥት የገቢያ ደንብ ትርጉምን—ግንዛቤን ይሰጣል ። በፍትሐ በፍትሐ ነገሥት የተቀረጸው የመገበያየት ደንብ በሰባት ምዕራፎች ተከፍሎ የተዘረዘረ ሲሆን ድንጋጌዎቹ በአብዛኛው ክፍል ከቀኖናተ ነገሥት ሁለተኛው መጽሐፍ "መክ" የተወሰዱ ናቸው·[1467]

ይህ ድንጋጌ በኢትዮጵያ መሠረታዊ ተቀባይነትን እንደ አገኘ ይቆጠራል ምክንያቱም Lex Falcidia-Quart Falcidia የሚባለውን ሥርዐት በመተርጐምም ሳይሆን በገዳም አብሮ መኖር የተወሰኑ ግዴታዎችን ይጠይቃል ። ሀብት—ትኩረት ያለው ሰው ገዳሙ ለሚሰጠው አገልግሎት ውጪ ይረዳ ዘንድ ከዚህ ሀብት—ንብረት የተወሰነ ክፍል መስጠት ይኖርበታል ። ልጆችና ምን አልባት ጥገኞች ካሉት እነሱም አስፈላጊዎች የሆኑትን ነገሮች ሳይነፈጉ (እንዲያው ሳይደረግ) መሆን አለበት ። ሀብት—ንብረት የሌለው ግን ለመሥራትም ወይም ሌላ አገልግሎት ለመስጠት (ለምሳሌ መቀደስ ፣ ማስተማር) የሚችል ሰው ይህንን አገልግሎት ይሰጣል ። ነገር ግን ሁለቱም ነገሮች ያጠሩት ሀብትም ንብረትም የሌለው ወይም ለማገልገል የማይችል ሰው ወደ ፈለገው ገዳም ገብቶ እንዳይኖር ሊከለክል አይችልም ። ምክንያቱም ገዳማቱ ራሳቸው መፈቀርያነ ስብያውያን ድርጅቶች እስከ ሆኑ ድረስ ።

የዚህን ጽሑፍ ዓላማ ከመስመር ላለማስወጣት ሲባል ወደ ሰፌ ዝርዝር ባለመግባት በአጠቃላይ መስመሮች ግን በቀኖናተ ነገሥት Leges Imperatores ወይም Basilica አንደኛ መጽሐፍ — አንደኛ ቀኖናተ ነገሥት Procheiros Nomos ዘባስልዮስ ቀዳማዊ ዘመቄዶንያ እና በጠስ = ተጥላሳት — አብጠሊስ ፣ አብጠሊሳት በሚለው በዚህ ክፍል መካከል ያሉት ግንኙነቶች እነዚህን ይመስላሉ ።

1465· "ጠስ" (አብጠሊስ) 14 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 33 1—7 ቁጥር 1079 "መክ" 26,27. 28.32 40, 41 P. Tzadua: Fetha Nagast ገጽ 40-41

1466· Procheiros Nomos TIT. II

1467. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 33 ቁጥር 1079—1107 (አንቀጹ በሙሉ)

ርእስ

ስለ ኤጲስ ቆጶሳትና መነኰሳት ውርስ

ፍትሐ ነገሥት
ጠስ = ተጥላሳት

ኤጲስ ቆጶስ ኤጋጲስቆጶስነት ከመሾሙ አስቀድሞ ያጠራቀመውን ገንዘብ ያስተዳደርበትና ያገዘበት ዘንድ ለወደደው ሊሰጥ ይገባል። ከኤጲስ ቆጶስነቱ በኋላ ያጠራቀመው ገንዘብ ግን ለቤተክርስቲያን ይሁን ከእርሱ በምንም ያገዘ ዘንድ ለእርሱ ትእዛዝ አይገባውም ከወላጆቹና ወንድሞቹ ወይም ከአባቶቹ ወንድሞች ርስት ካመጡለት ገንዘብ ካልሆነ በቀር ።

ልጆች እያሉት የመነኰሰ ሰው ከምንኲስናው በኋላ ገንዘቡን ሁሉ ለልጆቹ ሊያካፍል ይገባዋል ። ለገዳሙ የሚሆን ለራሱ አንድ ዕጣ ካከፈለ በኋላ ትእዛዙን — ኑዛዜውን ሳይጽፍ ቢሞት ያን ጊዜ ልጆቹ ያለ ትእዛዝ የሚገባቸውን ይውሰዱ ። እነርሱም ወራሾች ይባላሉ ። እሱም አውራሽ ይባላል ። የቀረውን ግን ለገዳሙ ይስጡት ። ልጆች ባይኖሩት ገንዘቡም ለገዳሙ ቢያገባ ግን እርሱም ግንዛቤ ይግባ ቢል ወደ ገዳም ከመግባቱ አስቀድሞ እርሱ እንዳዘዘ ገንዘቡ ለገዳሙ ይሁን [1468]

Procheiros Nomos

ከኤጲስ ቆጶስናው በፊት የነበረውን ንብረት የመስጠት ወይም የፍላጎቱ መጠን የማዋል መብት አለው ። ከሲመተ ኢጶስቆጶስና በኋላ የተፈራ ንብረት ግን ከዚሁ ይለያል ። ለራሱም ሊውል አይችልም ። ከወላጆቹ ከጌቶቹና እኅቶች ወይም ወንድሞች ለእርሱ ከመጣለት ንብረት በስተቀር[1469]

1468. ጠስ 24—ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 42 ቁጥር 1383 ፣ 1385
1469. Procheiros Nomos Tit. 24 Jus Graecoromanum. TII ገጽ 188
Ντιμπεκούλου Ζέουντε, Αἱ σχέσεις εκκλησίας καί πολιτείας έν Αιθιοπία κατά το σύνταγμα του 1955
Dibekulu Z, Relations Between State And Church in Ethiopia According to the Constitution of 1955 ገጽ 161 የግርጌ ማስታወሻ 171

2· መክ— ቀኖናተ ነገሥት ካልእ

ባለፈው ክፍል እንደተወሳው ቀኖናተ ነገሥት በመባል ከሚታወቁት የፍትሐ ነገሥት በተለየ የሥጋዊ ክፍል ምንጮች አንዱ ሁለተኛው ቀኖናተ ነገሥት ሲሆን "መክ" በሚል ምኅፃረ ቃል ይጠቀሳል[1470] ።ይህም ምኅፃረ ቃል አንድ በአንድ ቃላቱ ሲታዩ "መ" ከዐረብኛ ቃል "ማሉክ" ንጉሥ የመጀመሪያው ፊደል ነው ሁለተኛው ፊድል "ክ" በማይረዳ ሁኔታ ግን 2 ቁጥር (ሁለተኛን) የሚተካ "ብ" ማለት ነው ። ምክንያቱም በዐረብኛ ቋንቋ ሁለት በሁለተኛ ፊደል "በ" ይወክላል በ"ከ" ግን እይሆንም በአጠቃላይ "ከ" ምንም ማለት ሳይሆን የ"በ" መለወጥ — መተካት ሆኖ ነው የሚታየው ። እንደማንኛውም ቋንቋ በዐረብኛ ቋንቋም ፊደሎች አሐዞችን ቁጥሮችን ተክተው ወይም ሁነው እንዲያገለግሉ በሚያስፈልግበት ጊዜ አሌፍ ፡ ቤት ፡ ጋሜል ፡ ዳሌጥ ፡ ሂ ፡ ዋው ፡ ዛይ ፡ ሔት ፡ ጤት ፡ ዮድ ፡ ካፍ ፡ ላሜድ ፡ ወዘተ· በሚል ተራ ተቀምጠው የሚገኙ ፊደሎች ወደ አሐዝ ሲለወጡ ወይም አሐዞችን ተክተው ሲነበቡ 1·2·3·4·5·6·7·8·9·10·20·30· ወዘተ· ሁነው ይገኛሉም ።

ስለዚህም "ካፍ" (ከፍ) 20ኛ ቁጥርን ተክቶ የሚገኝ እንደ መሆኑ መጠን "መክ" ማለት ቀኖናተ ነገሥት 20ኛ የሚለውን ስም ነው የሚሰጠው ። ከዚህም የተነሳ በስሕተት ተቀርጾ—ተያይዞ የመጣ መሆኑን መገመት ይቻላል ። ለምሳሌ ከአምስቱ ብሔረ አሪት ሁለተኛው መጽሐፍ ዘፀአት ትቤ ሁለተኛ መጽሐፈ አሪት ተብሎ እንደተሰየሙ ሁሉ ይዘም በ"መክ" "ፋንታ" "መብ" ሆኖ ሁለተኛ ቀኖናተ ነገሥት ተብሎ መሰየም ነበረበት [1471]

"መክ" በሚባል የሚታወቀው ሁለተኛው ቀኖና — መጽሐፈ ነገሥት እንደ ጀርመናውያን ተመራማሪዎች E. Sachau-G.Bruns[1472] ና W. Riedel[1473] በ325—534 መካከል በግሪክ ቋንቋ እንደተጻፈ ከሚቆጠረውና ሶርያዊ—ሮማዊ ተብሎ ከሚታወቀው የሕግ ሰነድ እንደ ተወሰደ ተረጋግጧል ። ይህም ሕጋዊ ሰነድ በእነዚሁ Sachau-Bruns በጀርመንኛ ትርጉም ታትሟል።[1474] ይህም የሕግ ሰነድ በምሥራቅ ልዩ ፖለቲካዊና ቤተክርስቲያናዊ ቦታን ይዞ የነበረ ሕግ ነበር። ይህም ሕግ 130 አርእስት ኑረውት ሲገኝ ከእነዚህም የመጀመሪያዎቹ 44 አርእስት የትልቁ ቆስጠንጢኖስ ፣ የቀሩት 86 አርእስት ከዩስጢኒያኖስ በፊት የነበሩት ነገሥታት ለምሳሌ ቴኦዶስዮስ ፣ ቆስጠንጢኖስ ፣ እና ሊዮን Statuta Imperatorum ወይም Leges Constantini Theodosii et Leonis እንደሆኑና የሕጋዊ ትምህርት ሰነድ እንደነበረ ይታመናል[1475]

· ስለዚህ መክ በምሥራቅ ሰፍነው ይገኙ ከነበሩት ሁኔታዎች—ልምዶችና ባህሎች ጋር በመጣጣም የሚያገለግሉ ሕገጋት ለመሆን ይችሉ ከነበረ ዓላማ አንጻር እንደተዘጋጀ ሶርያዊ — ሮማዊ የሕግ ሰነድ ሲሆን በመጀመሪያ በሱርስጥ ቋንቋ[1476] ቀጥሎም በዐረብኛና አርመንኛ ትርጉሞች መገኘቱ አላጠራጠረም ፣ ሱርስጡ ሰነድ መጀመሪያ በ1864 በብሪቲሽ ሙዚየም ከሚገኝ [1477] ከአንድ የሰባተኛው ምዕተ ዓመት የእጅ ጽሑፍ በ M. Land ሊታተም ሲችል [1478] ቀጥሎም በዚሁ ሰው "Leges Saeculares et Sermone Romano Translate በሚል ርእስ በላቲን ትርጉም ታተመ።[1479] ቆይቶም Sachau-Bruns (በበርሊን የሕግ አስተማሪዎች) በመተባበር በሦስቱም ቋንቋዎች ትርጉሞች ፣

1470· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2 ከዚሁ ገጽ 80 105 የግርጌ ማሳታወሻ 5

1471· Guidi, Fetha Nagast ገጽ 1 የግርጌ ማስታወሻ 15 ገጽ 5—6 የግርጌ ማስታወሻ 10 P. Tzadua, Fetha Nagast ገጽ 8 የግርጌ ማስታወሻ 52 Riedel, Die Kirchenrechtsquellen ገጽ 146 የግርጌ ማስታወሻ 1

1472· E. Sachau— . Bruns: Syrisch— Römisches Rechtsbuch Aus Dem Füntem Jahrhundert Herausgegeben Übersetzt und erlänter Leipzig 1880 TI ገጽ 67 94 TII ገጽ 114 ፡ 160 ፡ 177 180

1473· Riedel: Die Kirchnrchtsquellen. ገጽ 297· W. Selb; Zur dedeutung des Syrisch Römisches Rechtsbuch —München 1964.

1474. J. Stam. Episcopacy on the Apostolical tradition, Basel. 1936. ገጽ 133—134.

1475. As Handbook, Probably of didactic character intended to explain the ancient Roman ius Civile in the light of the Ius Novum" P.Tzadua. Fetha Nagast ገጽ XVI

1476. M. Land: Anecdota Syriaca 1864. T.I. ገጽ 30—64.

1477. M.Land: Anecdota syriaca T.I ገጽ 128—283

1478. B.L. ADD 14528 ገጽ 192 - 228

1479· ይህ ሰነድ በሦስት ክፍሎች ሱርስጥ ዐረብኛና አርመንኛ ትርጉሞች ሲከፈል የሁሉም ጀርመንኛ ምላሽ አላቸው ሀ—Die Firläuternung ገጽ 151 180ለ—Erklarunh ገጽ 181—316

ሱርስጥ ፡ ዐረብኛና አርመንኛ በየበኩላቸው ከጀርመንኛ ምላሽም ጋር ይህን ይዘቱ ከብሪቲሽ ሙዚዬም ቁ· 1458 የእጅ ጽሑፍ ጋር የሚዛመድ ሁለተኛ ቀኖናት ነገሥት (መክ) አሳተሙ ማለትም [1480]

I ሀ· 127 ምዕራፎችን ያየዘ ሱርስጡን ሰነድ [1481] ከጀርመንኛው ትርጉም ጋር [1482]

ለ· አንድ መግቢያንና ሁለት ምዕራፎችን [1487] ይዞ በብሪቲሽ ሙዚዬም የተገኘ [1484] ሱርሰጥ ሰነድ የተወሰኑ ክፍሎችን ከጀርመንኛ ትርጉማቸው ጋር [1485]

ሐ· 83 ምዕራፎችን ይዞ [1486] በBibliotheque Nationale De Paris የሚገኝ [1487] ሱርሰጥ ሰነድ ከጀርመን ትርጉም ጋር [1488] እንደ ገና በአዲስ መልክ አሳተሙ።

II/ በ130 ምዕራፎች ተከፍሎ [1489] በBodleian Library[1490] የሚገኝ ዐረብኛ ትርጉም ሰነድ ከጀርመንኛ ትርጉም ጋር[1491] ለመጀመሪያ ጊዜ [1492]

III. 149 (150) ምዕራፎችን ይዞ በKöniglichen Bibliothek in Berlin የሚገኝ[1493] አርመንኛ ትርጉም ሰነድ ከጀርመንኛ ትርጉም ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ አሳተሙ[1494]።

ስለዚህ Syrisch–Römisches Rechtsbuch ተብሎ የተሰየመው ሕጋዊ ሰነድ በተጠቀሱት ሦስት ቋንቋዎች ትርጉሞች - ሱርሰጥ ፡ ሀረብኛና አርመንኛ የተሰያዩ አሐዞች ሀ. 127 ወይም 83 ለ 130 ፡ ሐ 149

1480. Syrisch— Römisches Rechtsbuch T.I. ገጽ 3—36
1481. B.L. ADD 14528 ገጽ 192—228
1482. Syrisch—Römisches Rechtsbuch T.II ገጽ 3—40
1483. Syrisch — Römisches Rechtsbuch T.I. ገጽ 37—38
1484. B.L.ADD 18295 148A—148e
1485. Syrisch — Römisches Rechtsbuch T.II. ገጽ 41—42
1486. Syrisch — Römisches Rechtsbuch T.I. ገጽ 39—67
1487. Syrisch — 1128 ገጽ 263—376
1488. Syrisch — Römisches Rechtsbuch T.II. ገጽ 44—73
1389. Syrisch-Römisches Rechtsbuch. T.T. ገጽ 68—94
1490. Thome Roe 26 B.L.C. 339A-356
1491. Syrisch–Römisches Rechtsbuch T. II ገጽ 74—114
1492. Syrisch–Römisches Rechtsbuch T.I ገጽ 95—145
1493. MSS. Orient 278 ገጽ 10—59
1494. Syrisch–Römisches Rechtsbuch T. II ገጽ 114—150

(150) ተጠብቆ ሲገኝ በይዘትም ቢሆን የተወሰኑ ልዩነቶች ያጋጥማሉ ለምሳሌ ሀረብኛውና አርመንኛው ሰነድ በሚከተለው ሐረግ ሲጀምር ሕገ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ቴዎዶስዮስ ወሊዮን [1495] በሱርሰጥ ሰነድ ይሀ ሐረግ አይገኝም ።

ወደ ፍትሐ ነገሥት ይዘት ስንመለስ የምናገኘው 130 ምዕራፎችን ይዞ የሚገኘውን ዐረብኛ ትርጉም ሰነድ ነው[1496] ። ምክንያቱም በፍትሐ ነገሥቱ ቅንብሩ እብነ እል አሳል እንደ ምንጭ የተጠቀመበት ይህን 130 ምዕራፎችን ይዞ የሚገኘውን ዐረብኛ ሰነድ ነው[1497] ።

ስለዚህ ይህን ለማረጋገጥ የተወሰኑ ድንጋጌዎችን ከፍትሐ ነገሥት መከነታቸው ጋር ለማሳየት ይሞክራል ።

ርእስ

ለአካለ መጠን ስለ አልደረሱ ልጆች ሞግዚትነት

ፍትሐ ነገሥት =

ምክ ፡ቀኖናተ ነገሥት ካልዕ

ወንድ ልጅ ዕድሜው 14 ሴት ልጅም ዕድሜዋ 12 እስኪያልፍ ድረስ በሞግዚት ሥር ይሁኑ ። ይህ ጊዜ ካለፈ ከሥልጣኑ ይወጡ ። ከዚያም በኋላ 25 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ በሹም እጅ ይሁኑ ያን ጊዜ በሥራቸው ላይ መብት ይኑራቸው ።

ሹመትን መተው በ2 ነገር ይሁን ። ከእነርሱም አንዱ አምስት ወንዶችና ሴቶች ልጆች ያሉት

Syrisch–Römisches Rectsbuch

አካል መጠን ያልደረሰች ሴት 12 ዓመት እስኪሞላት ድረስ አስተዳዳሪ ተብሎ በሚጠራ ሞግዚት ስር ትሆናለች ። 12 ዓመት ሲሆናት ይህ የሞግዚትነት ጥበቃ ይቆማል። በዚህ ጊዜ በሹም (Curator) ሥር ትጠበቃለች ። በዚያን ጊዜ የውልን የመዋዋል መብቶች ይኖራታል ።

ይህም ሁኔታ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ወንድም ይሰራል ። ስለ

1495. Syrisch—Römisches Rechtsbuch T. II ገጽ 74 115
1496. Syrisch-romisches Rechtsbuch T. II ገጽ 74 114. 68-94
1497 ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

ሰው ከትእዛዝ ሹመት እንዲድን ለባዕድና ለዘመድ ድሃ አደግ ልጆች አስተዳዳሪ እንዳይሆን ቢወድ ይህ ይገባዋል ፡፡ ከ5 ልጆች የሚያንሱ ቢሆኑለት ግን ከመዘዶቹ ወይም ከሌሎች ቢሆኑ ለድሃ አድጐች ልጆች ሞግዚት ወይም ሹም ይሆን ዘንድ ዳኛ ይከፋል ፡፡ ዳግመኛም ለድሃ አደጐች ልጆች መጋቢ የሆነ ሰው ቢኖር ከደብዳቤ ትእዛዝ በገንዘባቸውም ከታዘዙለት ሥራ ሊድን አይገባውም አዘዙን ደብዳቤ ከተቀበለና ያንን ገንዘብ ድንገት አደጋ ካገኘው ይከፈለው የድሃ አደግ ሹም ገንዘባቸውን ስለ መጠበቅ ሰው ሊሾም ይገባዋል ፡፡ ነገር ግን በዳኛ ትእዛዝ ይሁን[1498] ፡፡

ዚህ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወንድ 14 ዓመት እስኪሞላው በሞግዚት ነት ስር ይሆናል 14 ዓመት ሲሞ ላው ከዚህ ሞግዚትነት ይወጣል ፡፡ በሹም (curator) ጥበቃ ስር ይሆ ናል ፡፡ በዚህ ጊዜ ውል የመዋል መብት ይኖረዋል ፡፡ ወንዶችም ሴቶች 25 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ በሹም (curator) ጥበቃ ስር ይቆያሉ ፡፡ ይህ ጊዜ ሲሞላ ወንድም ሴትም ሁለቱም ለተሟላ አካለ መጠን የደረሱ መሆናቸው በማንኛ ውም ጉዳይ ሙሉ መብትን ያገ ኛሉ፡፡[1499]

ርእስ
ስለሞግዚትነት

ፍትሐ ነገሥት መከ ቀኖና ነገሥት ካልእ

በትእዛዙ ውስጥ የሚያዝለትን ሰው ስምና የሚያስተዳድረውን ስም የጻፈ ሰው ቢኖር ንብሮቶችን ተቀብለው ለልዶቹ ያካፍሏቸው ፡፡ ሹሙም ከእርሱ አይወሰድ፡፡ አዛዥ የትእዛዝ መጽሐፍ ባይጽፍ፡ የሕፃን

Syrisch –Rr'o'misches Rechtsbuch

አንድ ሰው ልጆች ትቶ በሚሞ ትበት ጊዜ የልጆቹን ሞግዚት ስሞች ጠቅሶ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ ሰዎች መያዣ በማስያዝ ግዴታ ሳይኖርባቸው በልጆች ስም የሟ ቹን ሰው ንብረት ያስተዳድራሉ

1498· መክ 2 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 41 ቁጥር 1301—1304 P. Tzacdua: Fetha

1499. Syrisch-Römisches Rechtsbuch T. II 78—79

ነቱ ወራት ያለፈው 25 ዓመት የሆነው ያዘዘላቸው ወንድም ቢኖር እርሱ አስተዳዳሪ ይሁን፡፡ታላቅ ወን ድም ባይኖራቸው ከአባታቸው ወንድሞች አስተዋይ የሆነው አስ ተዳዳሪ ፈራጅ ይሁን ፡፡ አባታቸው ከተወው ገንዘብ እንደሚገባ ለእ ነሱ ያውጣጣ ፡፡ አባታቸው የተወ ውን ሁሉ ይጻፍ፤ በመዝገብ የተጠ በቀ ይሁን ፡፡ አስተዋዮች የሆኑ የአባት ወንድሞች ባይኖሯቸው ከአባታቸው ወንድሞች ልጆች ወገን አስተዋይ የሆነው በሙኑ ከ25 ያለፈ ያስተዳድራቸው ፡፡ ለአባታ ቸው ወንድም ልጆች ባይኖሯቸው የልጆቹ እናት ሥራቸውን (ገንዘባ ቸውን) ልታከናውን ብትወድ እን ግዲህ ለዳኛ ትንገረው ፡፡ ዳኛውም ልጆቹን እስከታሳድጋቸው ድረስ ባል እንዳታገባ ባደትም ጊዜ ርስታ ቸውን እንድትሰጣቸው የመሐላ ቃል ይቀበላት ፡፡ እርሷ ባትወድ ግን ያገር ዳኞች ለድሃ አደጐች አስተዳዳሪዎችንና አሣዦችን ይሾ ሙ ዘንድ ሕጎችን ታዝለት ፡፡ እንደ ተተወችው የርስት ገንዘብ መጠን በታወቀች ደመወዝ ይስማሙላ ቸው ፡፡ ሹማምቱም የሰጧቸውን ሁሉ ከእነርሱ ይቀበሉ ፡፡ ለአካለ መጠን በደረሱ ጊዜ እስኪሰጧ ቸው ድረስ የድሃ አደጐችን ገንዘብ በፍጹም ትጋት ይጠብቁ አዛዥ

ነገር ግን ያለ ኑዛዜ ልጆችን ትቶ ቢሞትና ግን 25 ዓመት የሞላው ልጅ ቢኖረው ይህ ልጅ ዋስትናን የማስያዝ ግዴታ ሳይጠየቅ የሚች አባቱን ንብረት ማስተዳደር ይች ላል ፡፡ በሌላም ሁኔታ አንድ ሰው ሳይናዘዝ ልጆችን ትቶ በሚሞት በት ጊዜ ግን ወንድሞች ከአሉት ከእነሱ እምነት የሚጣልበት አንዱ በአንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ሞግዚትና ጠባቂ ሆኖ ይሾማል ፡፡ እሱም ለልጆቹ ጥቅም አስፈላጊ በሆነው ዘዴ የውርሱን ንብረት ያስተዳድራል ፡፡ ንብረቱን ይመዘግ ባልና ይጠብቃል ፡፡ በመጨረሻ ሟች በሕይወት ያለ ወንድም ሳይ ሆን የወንድ ልጆች ካሉት ከወንድ ልጆች 25 ዓመት የሞላው ይሆን

ሞግዚትና ሹም ካደረገው ሰው በሾመበት ገንዘብ ላይ ዋስ አይፈልግ ፡፡ የገንዘቡ ጌታ እስኪያድግ ድረስ አስቀድሞ በገንዘቡና በልጁ ላይ አስተዳዳሪ ያደረገው እርሱ ነውና፡፡ [1500]

ንብረት የማስተዳደር መብት ይኖረዋል[1501]

ርእስ
የይርጋ ዘመን

ፍትሐ ነገሥት = መክ ካለእ ቀኖናተ ነገሥት

ከሌላ ዘንድ ገንዘብ ያለው ሰው እስከ 30 ዓመት ባይፈልገው ከዚህ በኋላ እርሱም ቢሆን ልጁም ቢሆን ተመልሶ ሊጠይቅ አይገባውም ፡፡ በአስተዳደሪነትም ሥራ እንደዚሁ ይገባል ፡፡ በከሳሽም እጅ መያዣ ቢኖር ከእጁ ወደ ሌላው እጅነት ባይወጣ ለእርሱ ገንዘቡን ሊጠይቅ ወይም የያዘውን መያዣ ሊይዝ ይገባዋል ፡፡ መያዣው ከእጁ ወደ ሌላው ቢወጣ ሊጠይቅ አይገባም ፡፡ ዕዳን ለመፈላለግ ሁሉ እንደዚህ ነገር ይገባል የርስትና የዳኝነት የሕግና የአንድነት ንግድ የቅሚያ የምድር ድንበር የጉድጓድ በቤትና በሀገር ከተክልም ቦታ ያለ የውሀ ቦይ ይህን የመሰለውም ለአንድ ሰው ከ30 ዓመት በላይ

Syrische–Römisches Rechtsbuch

ከሌላ ዘንድ ገንዘብ ያለው እስከ 30 ዓመት ባይፈልገው ከዚህ በኋላ እርሱም ቢሆን ልጁም ቢሆን ተመልሶ ሊጠይቅ አይገባውም ፡፡ በአስተዳደሪነቱም ሥራ እንደዚሁ ይገባል ፡፡ በሳሻም እጅ መያዣ ሲኖር በእጁ ወደ ሌላው እጅነት ባይወጣ ለእርሱ ገንዘቡን ሊጠይቅ ወይም የያዘውን መያዣ ሊይዝ ይገባዋል ፡፡ መያዣው ከእጁ ወደ ሌላው ቢወጣ ሊጠይቅ አይገባም ፡፡ ዕዳን ለመፈላለግ ሁሉ እንደዚህ ነገር ይገባል፡፡ የርስትና የዳኝነት የሕግና የአንድነት ንግድ የቅሚያ የምድር ድንበር የጉድጓድ በቤትና በሀገር ያለ የውሀ ቦይ ይህን የመሰለ

1500· መክ 3 ፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 41 ቁጥር 1298 1130፡፡ P.Tzadua, Fetha Nagast ገጽ 233

1501. Syrisch–Römisches Rechtsbuch T. II ገጽ 78—79

ሊጠይቅ አይገባውም ፡፡ ሊከራከር ቢወድም በዚህ አይፍረዱለት[1502]

ውም ለአንድ ሰው ከ30 ዓመት በላይ ሊጠይቅ አይገባውም ሊከራከር ቢወድም በዚህ አይፍረዱት[1503] (ልዩነትም እምብዛም ስለሌለው እንደ አለ ተገልብጧል)፡፡

በአጠቃላይ በተመለከቱት ሰነዶች ማለት ከፍትሐ ነገሥት ተቀርጾው በሚገኙት መክ/ቀኖናተ ነገሥት ትእዛዛት/ ካልእ Syrich-Romisches Rechtsbuch በታተሙት ሰነዶች መካከል የተከሰቱት (የሚታዩት ልዩነቶች) ለመመልከት ቢቻልም "መክ" ከSyrisch-Römisches Rechtsbuch አልወጣም ወደ ማለት መደምደሚያ አያደርስም ፡፡

በፍትሐ ነገሥት ምንጭነት የ"መክ" አጠቃቀም በጣም በስፋት የተካሄደ ሆኖ ይገኛል፡፡ ራሱ እብን እል አሳል እንደሚናገረው በተለይ ስለ ብድር ፡ ዋስትና—መያዣ ፡ ውርስ ፡ ስለ ርስት ፡ ዳር ድንበር ፡ ስለ ማኅበራት የሚደነግጉ የፍትሐ ብሔር ሕጋጋት ፡ ስርቆትን ፡ ቅሚያና ዝርፊያን ፡ ወዘተ· የሚመለከቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጋጋት በርከት ያሉ ቀኖናት—ድንጋጌዎች ከ130 ምዕራፎች መካከል [1504] በ45ኛው ምዕራፍ በዝርዝር ተይዘው ይግኛሉ[1505] ማለትም Syrish-Römisches Rechtsbuch መክ 130 ምዕራፎችን በያዘው በዐረብኛው ትርጉም ተገኝተው ለማነጻጸር ያስቀመጣቸውን አርእስት የሚመለከቱ ትእዛዛትን በ45ኛው ምዕራፍ ይዞ ይገኛል ፡፡

"መክ" ቀኖናተ ነገሥት ካልእ በዚህ ዐረብኛ ትርጉም አማካይነት በመለካውያንና በግብጻውያን ዘንድ የታወቀ ነበር[1506] ሆኖም በሕግ ሰነድነቱ ሳይሆን በቤተክርስቲያን ሕይወት ክልል ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ብቻ ነበር፡፡ የቀኖናተ ነገሥት ካልዕም በሱርስጥ ትርጉሙ በንስጥሮሳውያንም ዘንድ የታወቀ ነበር Ebedjesus)

1502· መክ 45 = ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 27 ቁጥር 1000

1503 . Syrisch-Römisches Rechtsbuch T. II ገጽ 20—91

1504· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 1 P. Tzadua, Fetha Nagast ገጽ 1

1505. Syrisch-Römisches Rechtsbuch T. II ገጽ 90-91

1506. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2 P. Tzadua: Fetha Nagast ገጽ 28

3·መጅ—ቆኖናተ ነገሥት ማልስ

ከቀኖናተ ነገሥት 3ኛው መጽሐፍ — 3ኛው ቀኖናተ ነገሥት በፍትሐ ነገሥት "መጅ" በሚል ምኅፃረ ቃል — ይጠቀሳል (ይታወ ቃል [1507]

ከላይ ስለ "መክ" እንደተነገረው አሁንም "መ" የመጀመሪያው ፊደል ዐረብኛ ቃል ማሉክ ነገሥት የመጀመሪያው ፊደል ሲሆን "ጅ" የሚለው ሁለተኛው ፊደል በዐረብኛ ቋንቋ ሦስተኛው ፊደል ነው ። በፊደል አሐዛዊ ቁጥር አሌፍ ቤት ጋሜል "ጀ" 3ኛ ማለት ስለሆነ "መጅ" ማለት ቀኖና ነገሥት 3ኛ ማለት ነው [1508]። 3ኛ ቀኖና ነገሥት "መጅ" ማለት ቀኖናተ ነገሥት 3ኛ ማለት ነው። 3ኛ ቀኖናተ ነገሥት ክፍሉ ምንጩ ሲሆን ትልቁ ቆስጠንጢኖስን በአስተዳደር ሥራው ለመርዳት በ318 የኒቅያ ሲኖዶስ አባቶች ሳይጻፉ ግን እንደተጻፉ ተቆጥረው የመጡ ቀኖናትንና ትእዛዛትን Canones et Constitutiones) ከያዘ አንድ የጥንት ሰነድ መዝገበ ሕግ የመጣ እንደሆነ ይታመን ነበር ።[1510]

27ን ሳይሆን 25ን አርእስት (ቀኖናት) ይዞ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ ተተርጉሞ የሚገኘው ይህ ሰነድ (መዝገበ ሕግ በ Abrhamus ማሮናይት ኢጸስቆጸስ ወደ ላቲን ተተርጉሞ ታትሟል ።[1510]

በተቃራኒው ዛሬ ይህ ሰነድ የቢዛንቲን ነገሥት ሊዮን 3ኛ ዘኢሳብ ሮን እና ቆስጠንጢኖስ 5ኛ ዘቆጵሮኒሞስ ምእለደ ሕገጋት ሁኖ በሚታወቀው አንድ የቢዛንቲን ሮማ ቅንብራዊ ሕግ—ዐረብኛ ትርጉም ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ሕግ መሆኑ ይደግፋል ።[1511] ቢሆንም Nallino ይህ

1507· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1508· ከዚሁ· 282

1509· ከዚሁ· ገጽ 58

1510. Abrhamus Echellensis Eorumdem Sanctorum Patrum (Nicaenorum) CCCXVIII Sanctones et decretá alia ex Quatuor Regum ad Constantinum Libris Decerpta: Mansi: T. II ገጽ 1029—1054

1511. P. Tzadua: Fetha Nagast ገጽ XVI የግርጌ ማስታወሻ 6 Riedel: Die Kirchenrechtsquellen... ገጽ 42—297 Constanzo: L'ecloga Araba... ገጽ 8 costanzo, IL Fetha Nagast... T.I. ገጽ 253

የቤዛንቲን — ሮማ ነገሥታት መድበለ ሕገጋት ሕጋዊ ሰነድ ለእብን እል አሳል ያልታወቀ እንደነበር በመደገፍ ተቃራኒ አቋምን ወስደዋል[1512] ። ሆኖም "መጅ" ከEcloga Leonis et Constantini ተወልዷል የሚለው አስተሳሰብ ድጋፍ አግኝቷል። እንግዲህ የአጽራረ ሥዕል ሊዮን 3ኛና ቆስጠንጢኖስ 5ኛ መድበለ ሕገጋት በመጀመሪያ በC.E.Zachariae von Lingenthal የታተመ ሲሆን[1513] በአቴንስ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ከሚገኝ ግን ዘካርያስ ካልተጠቀመበት የእጅ ጽሑፍ ላይ በመሥረት በአንጦንዮስ Mompheratus ሊታትሞ ችሏል ።[1514] በሌላም በኩል ይህ የዘካርያስ ሕትመት ሰነድ በዜፖስ ታትሞ እንደተሰራጨ ይታወቃል። [1515]

ከዚህም ጋር አብሮ ሌላ በዘካርያስ Ecloga Privita የሚል ርእስ መድበለ ሕግ ይገኛል[1516]

ይህም መድበለ ሕገጋት II Ecloga Privita Aucta et ecloga ad Procheiron Mutata በሚሉ አርእስት በተከታተሉት ዓመታት ለውጡ ሕገጋት መሠረት ሊሆን ችሏል። እነዚህም የተጠቀሱት ሕጐች በZachariae Von Lingethal ታትመው ተሰራጭተዋል[1517] አሁንም እነዚህ ሕትመቶች እንደገና በዜፖስ ሊታተሙ በቅተዋል ።[1518] Ecloga Leonis et Constantini በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጕመው ከሐተታ ጋር በFreshfield የታተሙ ሲሆኑ[1519] ወደ ፈረንሳይ ቋንቋ ተተርጉመው

1512· C.A Nallino. libri Giuridici Byzantini ...R.R.A.L. Serie IV. T.I. 1925 ገጽ 196 የግርጌ ማስታወሻ 4

1513. Collectio librorum Juris Graecoromanum ineditorum 'Lipsiae 1962 ገጽ 9—52

1514. Ecloga Leonis et consttantini cum appendice Athens 1983

1515. Jus Graecoromanum T. II ገጽ 11—62

1516. Zachariae procheiros Nomos...LXVII: Zachariae Historia Juris Graecoromani Delineatio Cum Appendice Ineditorum Heiedelbeg 1839 ገጽ 68—69

1517. Zachariae Jus Graecoromanum...Paris IV Lipsiae 1855 ገጽ 7—48 55—70

1518. Graecoromanum...T 4 ገጽ 12—47፣ 223—318

1519. F.Freshfield. A manual of Roman Law. the Ecloga Published by the Emperors Leon III and Constantinc V of Isaurin A.P. 726. (1926)

በC.A. Suplber ታትመዋል[1520]።

እንግዲህ "መጅ" ተብለው በፍትሐ ነገሥት የተያዙትን የተወሰኑ ቀኖናትና ተቀድተውባቸዋል — ተወስደውባቸዋል የሚባሉትን ሶርያዊ—ሮማዊ ሕግ Ecloga Leonis et Constantini እንጻራውያን ቀኖናትን በምሳሌነት እነጻጽሮ በማስመስከር "መጅ" ከ Ecloga Leonis et Constantini — Syrisch—Römisches Rechtsbuch በርግጥ እንደመጣ መቀበል ይቻላል ።

ርእስ
ስለ ድኃ አደጎች ልጆች መተጫጨት

ፍትሐ ነገሥት = መጅ
ቀኖና ነገሥት ሣልስ

የሚጋቡ ልጆች ድኀ አደጎች አካለ መጠን ያለደረሱ ቢሆኑ ከእነርሱ ወገን ለአንዱ አባት ወይም እናት ሞግዚት ባይኖረው ፤ ራሳቸው በሰው ፊት ቢተጫጩ ስለዚህም ቢያዝኑ 15 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ይቆዩ ከእነርሱ ወገን ለአንዱ አስተዳደራቸውን ባለማወቅ ሁለተኛው፣ ሊመግብ ባይችል የዚህን ዓመት ቁጥር ቢፈጽሙ እእምሮአቸውም ትክልል ቢሆን አብረው ቢኖሩም ቢለያዩም የወደዱትን ሊያደርጉ ይገባቻዋል።[1521]

Ecloga Leonis et Constantini

ወላጆች የሌላቸው ልጆች ወንዶች ወይም ሴቶች ዕድሜአቸው ሳይፈቅድ የመተጫጨት ቃል ኪዳን ቢገቡና ቆይተውም 15 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ቢጸጸቱ ጉዳትን በሚያስከትልና ጥቅሞችን ሳይነካ የጠባቂዎችን ፈቃድ ያገኛሉ። ዕድሜያቸው ሲደርስ ግን
ያለምንም ፈቃድ በፍላጐታቸው መሠረት የሚፈልጉትን ማከናወን ይችላሉ ።[1522]

1520. L'ecolgue des Isauriens Text–traduition Histoire

1521 — "መጅ" 1— ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ቁጥር 876

1522. Antonius Mopheratus: Ecloga Leonis et Constantini. T.II. I 18

ርእስ
ስለቤተክርስቲያን ጥገኝነት
Lex Asyli

ፍትሐ ነገሥት = መጅ
ቀኖናተ ነገሥት ሣልስ

በቤተ ክርስቲያኑ አገልጋይ ላይ የተደፋፈረውንም ይግረፉት ፤ ያባርሩትም ፤ በቤተክርስቲያን የተማፀነውንም ሰው ተደፋፍሮ በኀይል ከእርሱ ያወጣው 12 ጊዜ ይገረፍ ። በእርስዋ የተማፀነውም ስለ ኮበለለ በሚገባ ይያዝ ። ነገር ግን ካህኑና ከሕዝቡ ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ተቀብለው የሸሸበትን (የደ.ወለበትን) ምክንያት ይገለጡ ሕግም እንደሚያዘው ይፍረዱለት[1523]።

Ecloga Leonis Et Constantini

ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተማሕጽኖን የጠየቀ ሰውን ማንም አያውጣው ነገር ግን የተማጸኖውን ምክንያት ለካህኑ ይንገር ። እሱም ተማፃኙን በደኅንነት ይጠብቀልና ያስተዳድራል ። በቤተክርስቲያን ጥገኝነትን በጠየቀው ሰው ላይ እጁን ያነሳ ሕግን ይተላለፋል ። 12 አካላት — ቅጣት ይጣልበታል ። በቅድስት ቤተክርስቲያን የተጠጋን ሰው አስገድዶ ያወጠ ተጽፋቶና ተገርፎ ለዘለዓለም ይሰደድ[1424]።

ርእስ
ስለውርስ
Jus Hereditarium

ፍትሐ ነገሥት = መጅ
ቀኖና ነገሥት ሣልስ

የተተወው ገንዘብ ብድር ለመክፈል የማይበቃ ቢሆን ግን ወራሽም

Ecolga Leonis et Constantini

የተተወው ገንዘብ ብድር ለመክፈል የማይበቃ ቢሆን ግን ባይወ

1523. መጅ 14 ፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 50 ቁጥር 1794

1524. Antonius Mompheratus Ecloga Leonis et Constantini TIT T. A. TIT. II ገጽ 74

ባይወስድ ዕዳውንም ብድሩንም መክፈል አይገባውም ። እርሷን ቢወስድ ግን ለይቶ ቁጥሯን ይጻፍ ። ለአበዳሪዎችም ልኩን ይግለጽ። ለሁሉም ለየአንዳንዶቹ በገንዘባ ቸው ግምት ይስጥ ። እርሷን ተቀ ብሎ በመስጠትና በሚመስለው ቢያወጣጣት ወይም አበዳሪዎችን ስለገንዘባቸው ባዶ ሊያስቀራቸው ወድዶ ቢሸሽግ እርሷንም ባይገልጽ እኩሌታዋንም ቢሰጣቸው በእውነ ተኞች ምስክሮች ከተረጋገጠ በኋላ ምስክሮች ገንዘባቸውን ሁሉ ሊከፍ ላቸው ይገባዋል ።

አምላካዊ ከሆነ ዕዳ ወገን በመ ዋቲ ላይ ያለው ይህን የሚከተል ነው። ይኸውም እንደ ብፅዓትያለ ነው ። ከዚህ በኋላ የሕጉን ትእዛዝ ያደርጉ ።እነሆ ስለ አዛዥም ከገንዘቡ ከእኩሌታውና ከአራተኛው እጅ በገንዘቡ ትእዛዝ ያዝዝ ዘንድ እንዳ ይገባው አስቀድመን ተናግረናል ። አራተኛ እጅ ሊወርስ ለሚገባው ሰው ይቅር በዚህ ማዘዝ የለም ።[1525]

ስድ ዕዳውንምና ብድሩን መክፈል አይገባውም ። እርሷን ቢወስድ ግን ለይቶ ቁጥሯን ይጻፍ ለአበዳሪዎ ችም ልኩን ይግለጽ ። ለሁሉም በገንዘባቸው ግምት ይስጥ ። እር ሷን ተቀብሎ በመስጠትና በሚመ ስለው ቢያወጣጣት ወይም አበዳሪ ዎችን ስለ ገንዘባቸው ባዶ ሊያስቀ ራቸው ወድዶ ቢሸሽግ እርሷንም ባይገልጽ እኩሌታዋንም ቢሰጣ ቸው በእውነተኞች ምስክር ከተረ ጋገጠ በኋላ ገንዘባቸውን ሁሉ ሊከ ፍላቸው ይገባዋል ።

አምላካዊ ከሆነ ዕዳ ወገን በመ ዋቲ ላይ ያለው ይህን የሚከተል ነው። ይኸውም እንደ ብፅዐት ያለ ነው ። ከዚህ በኋላ የሕጉን ትእዛዝ ያደርጉ እነሆ ስለ አዛዥም ከገንዘቡ ከእኩሌታውና ከአራተኛው እጅ በገንዘቡ ትእዛዝ ያዝዝ ዘንድ እንዳ ይገባው አስቀድመን ተናግረናል ። አራተኛ እጅ ሊወርስ ለሚገባው ሰው ይቅር ። በዚህ ማዘዝ የለም ፣[1526]

ርእስ

ኑዛዜ ማድረግ ስለ አለመቻል

ፍትሐነገሥት = መጅ

ቀኖናተ ነገሥት ሣልስ

ዲዳ ወይም ደንቆሮ ሆኖ የተወለ

1525· መጅ 12 ፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 42 ቁጥር 1313—1314 መከ 95· 123·125

1526· Antionius Momipheratus Ecloga Leonis et Constantini TIT. 6 H.IA. TI ገጽ 33—34

ደም ትእዛዝ የለውም ። ዲዳና ደን ቆሮ ግን ይህ ደዌ ድንገት ያገኛቸው ቢሆኑ መጻፍ ከተቻላቸው ትእዛዛ ቸው ይጸናል ። ለባዕድ ግን ትእዛዙ አይጸናም ።[1527]

Ecloga Leoniset Constantini

ዲዳ ወይም ጀሮው የማይሰማ ሆኖ የተወለደ ትእዛዝ የለውም ።

ዲዳነት ወይም የጆሮው አለመስ ማት ደዌ ድንገት ያገኛቸው ከሆነ መጻፍ ከተቻላቸው ትእዛዛቸው ይጸናል ። ለባዕድ ግን አይጸ ናም[1528]።

በአጠቃላይ እንደገና ለማለት የሚፈለገው መጅ Ecloga Leoni set Constanini ዐረብኛ ትርጉምን አልያዘም ግን የቀኖና ነገሥት ሦስተኛ መጽሐፍ ጸሐፊ ይህን መጽሐፈ ሕግ ሲያዘጋጅ Eclogaleonis etr Constantini እነደ ወና ምንጭ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው ።

ስለዚህ መጅ በከፍተኛ ደረጃ Ecloga Leonis et constantini ላይ ተመሥርቶ ይታያል ።

1527· መጅ 22 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 41 ቁጥር 1252

1528· Antonius Mompheratus: Ecloga Leonis et Constantini TIT -So' Tus Graecrum: T. II 29-30

4 መግ— ቀኖና ነገሥት ራብዕ

"መግ" በሚል ምኅፃረ ቃል በፍትሐ ነገሥት የሚጠቀሰው ሰነድ፡ የቀኖናተ ነገሥት Leges Imperatores ወይም Basilica አራተኛ መጽሐፍ — ቀኖናተ ነገሥት ነው ። [1529]

ከላይ እንደተመለከተው አሁን "መ" የሚለው የመጀመሪያው ፊደል የዐረብኛ ቃል ማሉክ ነገሥት የሚባለው ቃል የመጀመሪያው ፊደል ሲሆን "ግ" የሚለው ሁለተኛው ፊደል ደግሞ የመጽሐፉን ቁጥር አራተኛ ቁጥርን ሚያመለክተው ፊደል ነው።

ነገር ግን የዐረብኛ ፊደሎች ወደ ቁጥሮች ተለውጠው በሚታዩበት ጊዜ አራተኛው ፊደል አሌፍ፣ ቤት፣ ጋሚል ዳሌጥ እንደመሆኑ መጠን "ደ" ነበር አራትን ቁጥር የሚተካው (አ·በ·ገ·ደ· 1·2·3·4·) በዚህም መሠረት ቀኖናተ ነገሥት አራተኛ ለማለት በመግ ፋንታ መድ ነበር መባል የነበረበት[1530] አሁን ግን በአለበት መልኩ ቀኖናተ ነገሥት አራተኛ የሚለውን ትርጉም ነው የሚሰጠው ።

መግ — መጅ — ቀኖና ነገሥት አራተኛ 35 አርእስት (ምዕራፎች) ሲኖሩት በ208 ንዑሳን ክፍሎች — ቀኖናት ተክፍሎ ከእነዚህም ንዑሳን ክፍሎች — ቀኖናት 85ቱ የመጀመሪያውን ክፍል የቀሩት 123 ሁለተኛውን ክፍል ይዘው ይገኛሉ ።

የዚህ ቀኖናተ ነገሥት አራተኛ — መግ ምንጭን በሚመለከት በአንድ በኩል በአብዛኛው ክፍል ከአምስቱ ብሔረ ኦሪት የተወሰዱ ሥርዐተ ቤተ መቅደስና ሥነ ምግባራት ትእዛዛትን ከያዘ በዓለ 35 ቀኖናት መእላድ በሌላ በኩል 'ከ318 የኒቅያ አባቶችና" ከታላቁ ቆስጠንጢኖስ በፊት ከነበሩ የሮማ ነገሥት ውሳኔዎች ውጹእን ክፍሎች የመነጨ፡ በዓለ 26 ቀኖናት ምእላድ የተቀነባበረ — የተሳበ ሰነድ ነው። [1531] በአሁኑ

1529. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2
1530· ከዚሁ ገጽ 85 216
1531 . Stan, l'Eglise d'Ethiopie Nouveau Patriarchat. Abba Selama T.II 1971
ገጽ 84 Sachau-bruns; Syrich–Romisches Rechtsbuch. T II ገጽ 77-144 Nallino: Libri Guiridici Byzantini Versione Arabe Christane del Secoli XII E XII R. R.A.L.Ser VI. T.I.ገጽ 105 W. Reidel: Die Kirchenbrechtsquellen ገጽ 43

ጊዜ የአይሁድ ልምዶችና ባህሎች ከፍተኛ ተፅዕኖ ባሳደሩባቸው ክርስቲያኖች (ግብጻውያንና ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች) መካከል የሚነሱ ጉዳዮችን ለመፍታት ዓላማ በሙሴ ሕጋጋት የተወሰኑ ትእዛዛት ላይ ተመሥርተው የተደነገጉ ሕጋጋት በዐረብኛ ቋንቋ መገኘታቸው ይታወቃል ። እነዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

1. Lex Dei ሕገ እግዚአብሔር[1532]

2. Lex Mosaicum ሕገ ሙሴ በሙሴ ከአምላክ ለእስራኤላውያን የተሠጠ ትእዛዝ ሕግ[1533]

በሙሴ ከአምላክ የተሰጠው ትእዛዘ ሕግ እንደ Riedel [1534] በሁለት ክፍሎች የተካፈለ ሆኖ ሲገኝ [1535] ከእነዚህም የመጀመሪያው ክፍል ከኦሪት ዘፀአት 21—22 ምዕራፎች ላይ ተመርኩዞ የተነሱ 18 ምዕራፎችን ይዞና ተዘጋጅቶ የሚገኘው ክፍል ሲሆን [1536] ሁለተኛው ደግሞ ከኦሪት ዘሌዋውያን 12— እስከ ኦሪት ዘዳግም 27 ምዕራፎች ላይ

1532. Lex Dei በFr. Bluhme በ1933 ታትሞ ሲገኝ
1533. Lexis Mosaicum Εκλογή του πορό του θεού διά του Μωϋσή δοθέντος Νόμου τοίς Ιοροηλίτοις. በ J.B. Cotelerius ታትሟል ። Ecclesiae graccaeMonumenta Paris 1677 ገጽ 1 27
1534. Riedel: die Kirchenrechtsquellen ገጽ 298።
1535. W. Riedel: Kirchenrechtsquellen ገጽ 298
1536 ዘፀአት

1	ምዕራፍ	ቁጥር
2	21	1 6
3	21	7 11
4	21	12
5	21	15
6	21	18
7	21	19
8	21	20
		22
10	21	28 32
11	21	32—34
12	21	35—36
	21	
13	22	5
14	22	6

ተመሥርቶ — ተነስቶ 35 ምዕራፎችን ይዞና ተዘጋጅቶ የሚገኘው ክፍል ነው· [1537]

ይህንም ግንኙነት ወይም ልዩነት ማለትም Lex Mosaicum እና በተመሠረተባቸው (በመነጨባቸው) በተጠቀሱት መጻሕፍተ ኦሪት መካከል ያለውን ግንኙነትና የሚከሰተውንም ልዩነት በብሪቲሽ ሙዚዬም — ብሪቲሽ ቤተ መጻሕፍት የሚገኘውን የCotelerius ሕትመት Ecclesiae Graecae Monumenta Lex Mosaicum (ከእምላክ በሙሴ ለእስራኤል የተሰጠ ሕግ በተጠቀሱት የሙሴ መጻሕፍተ ኦሪት ምዕራፎች ጋር በማነፃፀር ለማሳየት ይቻላል ።

15	22	8
		15
16	22	17 18
18	22	24
	22	

1537 ሀ· ዘሌዋውያን

	ምዕራፍ	ቁጥር	
1	12	2	(88)
2	15	16	(89)
3	18	22·19·11·13	(90)
4	21	1 6	(91)
5	21	7 15	(92)
6	21	16	(93)
7	22	18	(94)
8	25	14	(95)
9	25	3	(96)
10	25	35	
11	25	2 29	(77)
12	27	2	(98)

ለ· ዘኍልቁ

	ምዕራፍ	ቁጥር	
13	5	11	(100)
14	6	1	(101)

ሐ· ዘዳግም

	ምዕራፍ	ቁጥር	
15	19	4	(102)
16	20		(103)
17	21	10	(104)

የንጽጽር ሰሌዳ

ሕገ ሙሴ Lex Mosaicum

ቁጥር	ርእስ ስም	ምዕራፍ	ቁጥር
1	ዘፀዐት	61	
2	ዘሌዋውያን	93	
3	ዘፀዐት	63	
4	ዘፀዐት	68	
	ዘሌዋውያን	119	
	ዘዳግም	36	
	ዘዳግም	78	
	ዘዳግም	78	
4	ዘሌዋውያን	99	
5	ዘፀዐት	68	
	ዘዳግም	22	
6	ዘፀዐት	68	
7	ዘፀዐት	68	
8	ዘፀዐት	120	
	ዘፀዐት	68	
9	ዘሌዋውያን	101	
10	ዘኍልቁ	119	

አምስቱ ብሔረ ኦሪት
(ምንጮች — ምዕራፎች)

ስም	ምዕራፍ	ቁጥር
= ዘፀአት	28	1 8
= ዘዳግም	16	18
= ዘሌዋውያን	19	15 16
= ዘፀአት	20	2— 17
= ዘዳግም	5	61—
= ዘፀአት	22	11— 17
= ዘሌዋውያን	25	35—37
= ዘዳግም	15	7—10
= ዘዳግም	23	19—20
= ዘዳግም	24	10—13
= ዘሌዋውያን	19	13
= ዘዳግም	14	14
= ዘፀአት	22	7—11
= ዘዳግም	6	1 4
= ዘፀአት	22	10— 13
= ዘፀአት	22	14 15
= ዘፀአት	30	2 10

18	21	15	
19	22	13	(105)
20	23	6	(106)
21	23	18	(107)
22	23	19	(108)
23	23	25	(109)
24	23	26	(110)
25	23	1	(111)
26	21	5	(112)
27	24	6	(113)
28	24	14	(114)
29	24	19	(115)
30	25	4	(116)
31	25	4	(116)
32	25	5	(117)
33	26	13	(118)
34	26	14	(119)
35	26	15	(119)

11	ዘፀአት	68	= ዘፀአት	12	22—24
12	ዘፀአት	68	= ዘሌዋውያን	19	33—36
13	ዘፀአት	68	= ዘሌዋውያን	24	13—16
14	ዘፀአት	68	= ዘኍልቍ	27	4—11
15	ዘፀአት	68	= ዘፀአት	22	5
16	ዘፀአት	68	= ዘፀአት	22	6
17	ዘሌዋውያንን	93	= ዘፀአት	21	33, 34
18	ዘዳግም	87	= ዘፀአት	22	1 4
19	ዘፀአት	68	= ዘፀአት	21	28 36
	ዘሌዋውያንን	94	= ዘሌዋውያን	19	32
	ዘሌዋውያንን	55	= ዘዳግም	24	28 36
20	ዘፀአት	67	= ዘፀአት	21	15
	ዘዳግም	59	= ዘሌዋውያን	20	9
21	ዘሌዋውያንን	120	= ዘዳግም	21	18 21
22	ዘዳግም	57	= ዘፀአት	21	16
23	ዘዳግም	61	= ዘዳግም	14	7
24	ዘኍልቍ	68	= ዘዳግም	25	39 43
25	ዘዳግም	93	= ዘዳግም	21	10 14
26	ዘሌዋውያን	60	= ዘዳግም	22	13 21
	ዘዳግም	65	= ዘፀአት	21	22 23
27	ዘፀአት	68	= ዘዳግም	25	11 12
		22	= ዘሌዋውያን	20	10
28	ዘሌዋውያንን	90	= ዘዳግም	22	22
29	ዘሌዋውያን	90	= ዘፀአት	22	16 17
30	ዘሌዋውያን	94	= ዘፀአት	23	24
31	ዘሌዋውያን	90	= ዘሌዋውያን	18	6 7
32	ዘሌዋውያን	94	= ዘሌዋውያን	20	11
33	ዘሌዋውያን	94	= ዘሌዋውያን	18	10
34	ዘሌዋውያን	94	= ዘሌዋውያን	20	17
35	ዘሌዋውያን	94	= ዘሌዋውያን	20	12
36	ዘሌዋውያን	90	= ዘሌዋውያን	20	24
37	ዘሌዋውያን	90	= ዘሌዋውያን	21	14
38	ዘሌዋውያን	90	= ዘሌዋውያን	21	14
39	ዘሌዋውያን	94	= ዘሌዋውያን	18	11
40	ዘሌዋውያን	95	= ዘሌዋውያን	18	18
41	ዘሌዋውያን	94	= ዘሌዋውያን	18	14
42	ዘፀአት	68	= ዘሌዋውያን	20	20
43	ዘሌዋውያን		= ዘሌዋውያን	21	9
44	ዘፀአት		= ዘሌዋውያን	20	16
	ዘፀአት		= ዘፀአት	22	19
45	ዘፀአት	67	= ዘሌዋውያን	20	15
46	ዘፀአት	68	= ዘሌዋውያን	20	13
—	ዘኍልቍ	136	= ዘፀአት	21	26 27
47	ዘሌዋውያን	111	= ዘፀአት	21	12 14

48	ዘኍልቍ	137	= ዘኍልቍ	35	16 25
49	ዘዳግም	44	= ዘዳግም	19	3 7
	ዘዳግም	52	= ዘሌዋውያን	24	17 19
50	ዘፀአት	68	= ዘኍልቍ	35	30 33
(51)	ዘሌዋውያን	94	= ዘዳግም	19	6 7
			= ዘዳግም	22	18
			= ዘፀአት	19	31
			= ዘሌዋውያን	20	6 27

ሆኖም የእያንዳንዱ ምዕራፍ (ርእስ) ይዘቶችን ለማስፈር አልተሞከረም ምክንያቱም በቀላሉ የተመለከቱትን የአምስቱ ብሔረ ኦሪት ምዕራፎች በሚመለከት ለመረዳት ስለሚቻል ነው ። ምን ዓልባት ቀላል ላይሆን የሚችለው Lex Mosaicum አግኝቶ ማመሳከሩ ሊሆን ይችል ይሆንም ቢሆን አሁንም እነዚህን ምዕራፎች በሚመለከት በንጻሩ መረዳት ይቻላል ።

ፍትሐ ነገሥትን በሚመለከት ግን በውስጡ የተያዙት ድንጋጌዎች አራት ድንጋጌዎች ሲሆኑ እነዚህንም አራት ድንጋጌዎች ከመነጩባቸው መጽሐፍተ ኦሪት ጋር ማስተያየት ይቻላል ።

1) መግ (መጽ) 100 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 18 ቁጥር 682 — ዘዳግም 23·22 24

2) መግ (መጽ) 108 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 18 ቁጥር 679 ዘሌዋውያን 27 1 8

3) መግ (መጽ) 42 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 931 ዘኍልቍ 5 11 23

4) መግ (መጽ) 105 — ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 930 ዘዳግም 13·21

ርእስ
ስለ ተገባ ስዕለት መጠበቅ

ፍትሐ ነገሥት — መግ	Lex mosaicum ከእምላክ
ቀኖናተ ነገሥት ራብዕ	በሙሴ ለእስራኤል የተሰጠ ሕግ

ለጌታችሁ ለእግዚአብሔር የተሳላችሁት ስእለት ቢኖር ቸል አትበሉ ስለ እርሱ በእናንተ ላይ ኃጢአት እንዳይሆንባችሁ ለመፈጸም አትስነፉ...ልትሳሉ ባትወዱ ግን ኃጢአት የለባችሁም በአፋችሁ

የወጣውን ግን ሥሩ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔር እንደተሳላችሁት አድርጋችሁ ፈጽሙ በእንደበታችሁም ቆርጣችሁ የተናገራችሁትን [1539]

ልጅን መሳል ከልጆቹ ውስጥ ወንዱን ወይም ሴትዋን ለእግዚአብሔርና ለቤተመቅደስ አገልግሎት እሰጣለሁ ብሎ የተሳለ ሰው ቢኖር እግዚአብሔር እንዲህ አለ ለእግዚአብረሔር የነፍስ ዋጋ የሚሆን ስዕለትን የተሳለ ሰው ቢኖር ከ20 ዓመት ጀምሮ እስከ 60 ዓመት ድረስ ያለ ወንድ ልጅ ዋጋ በቤተ መቅደሱ ሚዛን ከብር ወገን 50 የብር ሰቅል (ወቄት) የሴት ልጅ ዋጋ 30 የብር ሰቅል (ወቄት) ይሁን አለ ። ከአንድ ወር ጀምሮ እስከ 5 ዓመት ድረስ የወንድ ልጅ ዋጋ አምስት የብር ሰቅል (ወቄት) የሴት ልጅ ዋጋ ሦስት የብር ሰቅል (ወቄት) ይሁን ። ከ60 ዓመት ጀምሮ እስከ 5 ዓመት ድረስ የወንድ ልጅ ዋጋ አምስት የብር ሰቅል (ወቄት) የሴት ልጅ ዋጋ 10 የብር ሰቅል (ወቄት) ይሁን አለ ። የተሳለውን ዋጋ መክፈል የማይቻለው ድኃ ቢሆን በመከራው ጊዜ ይህን ተሳለ እንጂ ችግሩን እንደሚያውቁ መጠን ዋጋውን ያቅልሉለት ዘንድ ወደ ኤጲስቆጶሱ ወይም ቄሱ ይሂድ ። የተሳለው ሰው መንጋ ከብት ሁሉ ያለው ከባለጸጎች ወገን ቢሆን ባለቤቱም በዋጋ ሊያስቀረው ቢወድ እግዚአብሔርን በመፍራት ካህኑ የገንዘቡን ዋጋ መወሰን ይገባዋል ። ስለ ቤተክርስቲያን አያድላ እግዚአብሔር ባለጸጋ ነውና የሚያመልኩትንም ያከብራቸዋል ። እርሱ ወርቁንና ብሩን መንጋውን በምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ ይሰጣቸዋል ። ካህኑ የተሳለውን ሰው ፊቱን አይመልስበት እርሱንም ፈርቶ አያቅልለት ዋጋውን ሁሉ መገመትህ በቤተ መቅደስ ሚዛን ይሁን እንጂ አንዱ ሚዛን ግን 20 አቦሊ ነው እንደዚህ ባለ መለኪያ ስዕለት ሁሉ ሊመጠን ይገባል [1540] ነገር ግን በፍትሐ ነገሥት መጣ በመግነቱ አዘውትሮ አይገኝም ምክንያቱም የመጣ ድንጋጌዎች መጅ ሁነው ነው የሚገኙት [1541] ስለዚህ መጣ መጣ ሁኖ የምናገኘው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው [1542]

1539· መጣ 100—ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 18 ቁጥር 882 Lex Mosaicum ምዕራፍ 8 ዘኁልቁ 23·22–24 እንደ ፍትሐ ነገሥት ትዳ (ዘዳግም) 13

1340· መጣ 100—ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 18 ቁጥር 679 Lex Mosaicum ምዕራፍ 12 ፣

1341· ለምሳሌ መጅ 4 መጅ 8 እና መጅ 24– ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥሮች 946· 950 እና 963

1342· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 930–931– መጣ 100 እና መጣ 108

እነዚህ የተዘረዘሩት ቀኖናት ከብሔረ አሪት መጥተዋል ምክንያቱም ፍትሐ ነገሥትን ለመተርጐም ሞክረን ቢሆን ኖሮ በመሠረቱ እነዚህ ሰነዶች ነበሩ የሚመለሱት

እንግዲህ እነዚህ ሁለት ሰነዶች በፍትሐ ነገሥት በተሳሳተ መንገድ እንደሚጠቀሱ ማለት በ"መጣ" ፈንታ "መጅ" እየተባሉ ይጠቀሳሉ ምክንያቱም በመሠረቱ Les Mosaicum- ከሕገ ሙሴ ጋር ግንኙነት ያለው መጣ እንጂ መጅ አይደለምና ነው ።

በአጠቃላይ የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ እብን እል አሳል ፍትሐ ነገሥቱን ለማቀነባበር ከ"መጣ" የተወሰዱ ቀኖናት የተወሰኑ እንደነበሩ ይናገራል ። ይህም ቀኖናተ ነገሥት ተብለውና በተለየ ለፍትሐ ነገሥት ሁለተኛው ክፍል– ሥጋዊ ሕግ መሠረታውያን ምንጮች ሁነው ከተጠቀሙት የሕግ ሰነዶች መካከል እንደተመለከተው ቀኖናተ ነገሥት 3ኛ መጣ (ሕገ ሙሴ ከእምላክ በሙሴ ለእስራኤል የተሰጠ ሕግ) የአምስቱ ብሔረ ኦሪት ሥርዐተ ቤተመቅደስ ፣ ሥነ ምግባራት ትእዛዛት እና የተወሰኑ ክርስቲያናውያት ትእዛዛት ምእላድ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ ይዘቱ አንጻር ለፍትሐ ነገሥት ሁለተኛው ክፍል– ሥጋዊ ሕግ እንደፊተኞቹ ሦስት የሕግ ሰነዶች– ቀኖናተ ነገሥት– "ጠስ" ፣ "መክ" እና "መጅ" ፣ መጠን ሆኖ አለመገኘቱ መልስ ሊሆን ይችላል ።

ቀጥሎም የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ እብን እል አሳል ፍትሐ ነገሥት የመነጨባቸውን ምንጮች ቁጥሮች በሚመለከት በተለየ ልዩነቶችን ያመለከታል በተለየ ሐዋርያውያት ቀኖናትና ሲኖዶሳውያት ቀኖናት ወደ አንድ ወይም ወደ ሌላ ቋንቋ ሲተረጐሙ የይዘቶች መናጋት ብቻ ሳይሆን የቁጥሮች መለያየቶችም በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም ለምሳሌ በመለካውያን ፣ ንስጥርሳውያን ፣ ያዕቆባውያን– ሶርያውያንና ግብጻውያን በተካሄዱ ዐረብኛ ፣ ሱርስጥና ቅብጥ ትርጉሞች ከዚያም በተለያዩ መድበላተ ቀኖናት በተለየ ግብጥ የአሐዝ ልዩነቶች ተመልክተዋል [1543]

እንግዲህ በተጠቀሱት ቀኖናት ወይም ሌሎች ሰነዶች ከላይ እንደተባለው [1544] የቁጥሮች ልዩነቶች የተከሰቱት ሁል ጊዜ ሁለትን ወይም የበለጡ ቀኖናትን ወደ አንድ ቀኖና ወይም ወደ አነሱ ቀኖናት በመጭመቅ ወይም አንድን ቀኖና ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቀኖናት ወይም ጥቂት ቀኖናትን ወደ ብዙ ቀኖናት በመበተን ወይም የተወሰኑ ቀኖናትን በመዝለል ወይም ሌሎችን በመጨመር ሊፈጠሩ እንደቻሉ

1543· ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2

1544· ከዚሁ ገጽ 148–149

መገንዘብ ይቻላል ።

ይዘቶችን ምንጮችን በሚመለከት ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት የመጡ የተወሰዱ ትእዛዛት ቃል በቃልና የተወሰኑ ብቻ በነፃ ምላሽ የተወሰዱ ሲሆኑ ከቤተክርስቲያናውያት ቀኖናት ከመጡት ከተወሰኑት በስተቀር ግን ፈጽሞ በነፃ ምላሽ ተወስደዋል [1545] ሆኖም በፍትሐ ነገሥት የሰፈሩትን ቀኖናት በአጠቃላይ ገጽታዎች በፅንሰ ሐሳብና በይዘቶችም ከሚጣጣሙት (በሌላ አነጋገር ከምንጮች) ማለት ሐዋርያውያትና ሲኖዶሳውያት ቀኖናት ጋር በማነጻጸር ማመልከት ከፍተኛ ትርጉም ይኖረው ነበር [1546] ቢሆንም ይህ ራሱን የቻለ ሌላ ሙከራ የሚያስፈልገው ሆኖ ነው የሚታየው ። በመጨረሻ እብነ አል አሳል ቀኖናት በፍትሐ ነገሥት በሰፈሩበት መልካቸው በአፈጻጸም ሂደት ርስ በርሳቸው የሚጋጩበት ወይም የሚፋለሱበት ሁኔታ ቢፈጠር ከዚሁ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚስማማውና ይበልጥ ለሥነ አእምሮ ቅርብ ሁኖ የሚገኘው ቀኖና ተፈጻሚነት እንዲኖረው እንደሚመረጥ ይደመድማል [1547]

በሌላ በኩል በአንድ ግብፃዊ ዮሴፍ አሴማኖስ Assemaus ተዘጋጅቶ በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ አንድ ዐረብኛ ምዕላደ ቀኖናት Collectio Sacrorum Canonum Abu- Isaac II Ben-Assamani[1548] በሚል ርእስ በዐረብኛ ትርጉሙ አንድ የፍትሐ ነገሥት የእጅ ጽሑፍን ይዞ ይገኛል ። ይህም የእጅ ጽሑፍ በማመርመር ላይ ከሚገኘው ፍትሐ ነገሥት ሰነድ ጋር በይዘት አይለይም ነገር ግን የበለጠ ዝርዝር ምንጮችን ይዞ ስለሚገኝ በዚህ በኩል ይለያል ።

ስለዚህ በዚሁ Collectio Sacrorum Canonum Abu Isaac II Ben Assemani እጅ ጽሑፍ መግቢያ የተመዘገቡ ምንጮች እስከ አሁን ከተዘረዘሩት ምንጮች

ሀ· ቅዱሳት መጻሕፍት [1549]

ለ· ሐዋርያውያት ቀኖናት [1550]

1545· ከዚሁ ገጽ 91–92

1546· STAN L' Église... ገጽ 335

1547· በዚሁ ገጽ 95–96

1548· A Maio. Scriptorum... TIV ገጽ 283 284

1549· በዚሁ ገጽ 97–101

1550· በዚሁ ገጽ 102

ሐ· ቤተክርስቲያናውያት — ሲኖዶሳውያት ቀኖናት [1551]

መ· ቀኖናተ አበው [1552]

ሠ· ቀኖናተ ሊቃነ ጳጳሳት [1553]

ረ· ሥጋውያን ሕጎች — Statuta imperatorum ወይም Canones Basilicorum[1554] በስተቀር የሚከተሉትን ምንጮች ይዞ ይታያል ።

1/ ሲኖዶሳውያት ቀኖናት

ሀ/ የቁስጥንጥንያ (ሁለተኛው ዐቢይ ሲኖዶስ)[1555]

ለ/ የኤፌሶን (3ኛ ዐቢይ ሲኖዶስ)[1556]

2/ ቀኖናተ አበው

ሀ· ዘጎርጎርዮስ ገባሬ ተአምራት (ቀኖናዊ መልዕክት) [1557]

ለ· ዘኤጲፋንዮስ ዘቁስጥንጥንያ [1558]

ሐ· ዘአትናቴዎስ ዘእስክንድርያ [1559]

መ· ዘሚዛኤል ዘድምያጥ [1560]

3/ ቀኖናትና ውሳኔያት ዘሊቃነ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ

ሀ· ዘቄርሎስ ኢብን ላቅላቅ [1561]

ለ· ዘገብርኤል ኢብን ቱራይቅ [1562]

4/ የአፍሪቃ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ቀኖናት[1563]

ነገር ግን ከዚህ የምንጮች ዝርዝር

ሀ· ቀኖናት ዘዲዮናስዮስ

ለ· መልዕክተ ጴጥሮስ ተዘለዋል

1551· በዚሁ ገጽ 252–266

1552· ከዚሁ ገጽ 257–259

1553· ከዚሁ ገጽ 280–287

1554· ከዚሁ ገጽ 288–322

1555. Riedel : Die Kirclhenrechtsquellen ገጽ 313

1556. Riedel: Die Kirchenrechtsquellen ... ገጽ 313

1557. Χριστοφιλοπούλου, Ελληνικόν Εκκλησιαστικόν Δίκαιον 45

1558. Riedel: Die Kirchen rechtsquellen ገጽ 313

1559. Riedel: Die Kirchenrechtsquellen ... ገጽ 246,336

1560. Riedel: Dic kirchenrechtsquellen ... ገጽ 352

1561. Riedel: Die Kirchenrechtsquellen ... ገጽ 354

1562. Riedel: Dic Kirchenrechtsquellen ... ገጽ 350

1563. Α. Αλιβιζάτου, Οἱ Ιεροί Κανόνες ገጽ 217 - 218

በመጨረሻ አጠራጣሪም ቢሆን አሁን ከአለው የበለጠ ዝርዝር ይዘት ያለው የግእዝ ትርጉም ፍትሐ ነገሥት እንደ አለ ይወራል ።

ስለዚህ የተጠቀሱት ዜናዎች ቢረጋገጡ ምንዓልባት ይህ የበለጠ ዝርዝር ይዘት ያለው ፍትሐ ነገሥት አሁንም ከሚታወቁት የበለጡ ዝርዝር ምንጮችን ይዞ ይገኝ እንደሆነ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ።

ነገር ግን ስለ አለመኖሩ ፍጹም ርግጠኛ ነን ለማለት ባንችልም ጥያቄው በቀረበበት መልኩ ይቆያል ምክንያቱም ይህን መሰል ሰነድ ጽሑፍ ማግኘቱ ካለም "ምን አልባት" ነው

ክፍል አራት
ምዕራፍ አሥራ አንድ
የፍትሐ ነገሥት ምንጮች መጠቃለልና ይዘት

1 እስከ አሁን በዝርዝር እንደተመለከተው ፍትሐ ነገሥት (ብሔረ ሕግ ወቀኖና) ከተለያዩ ትጉባት መጻሕፍት ፡ ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናትና ሥጋውያን ሕገጋት መመንጨቱ ታውቋል

ሆኖም ሁሉም ቀኖናውያንም ሆነ ሥጋውያን ሕገጋት እነሱም የፈለቁባቸው ምንጮችና የተዘጋጁባቸው— የታወጁባቸው ጊዜያት ጥያቄዎች እንደተጠበቁ ሆነው ግን አንድ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በተለየ ሁኔታ በራሱ በፍትሐ ነገሥቱ ይደናገራሉ

በመጀመሪያ ከላይ እንደተባለው ፍትሐ ነገሥት የኒቅያ ሲኖዶስ 318 አባቶች ሥራ እንደ ሆነ ይተረካል ። ስለዚህም ከልዩ ልዩ ቀኖናውያንና ፖለቲካውያን– ሥጋዊያን ምንጮች የተወሰዱትንና በፍትሐ ነገሥቱ የተያዙትን ሁሉንም ምንጮች በግድ ለ300 አባቶች ይሰጣሉ ።[1564]

ከዚህም በመነሳት አንድ ዓይነት መፍትሔ የሚሹና ቀኖናዊም ሆነ ሥጋዊ ፖለቲካዊ ባሕርይ ያላቸው ችግሮች ምንጊዜም ቢፈጠሩ (ሲፈጠሩ) ይህን መፍትሔ እንዲሰጥ የሚገባው – የሚሻው አግባብ ሥልጣን ያለው አካል (ለምሳሌ ዳኛ) እንደነገሩ ሁኔታ በፍትሐ ነገሥት ውስጥ በተገቢው ቀኖናዊም ሆነ ሥጋዊ ትእዛዝ በመደገፍ ለተፈጠረ ችግር መፍትሔውን ለመስጠት በመምከር ነበር ። ስለዚህም አንድ የተፈጠረ ጉዳይንም የሚመለከት አግባብነት ያለው ድንጋጌ ሙሉ ሰነዱ ያለባቸውን ምንጮች ፍለጋ ለመሄድ አይገደድም ማለትም የጉዳዩ መፍትሔ የሚፈለግበት ፍትሐ ነገሥት በባሕርዩ መሠረት የተወሰኑ ምእላዳትን ወይም ጥቅሶችን ይዞ እንደመገኘቱ መጠን እንደ ሁኔታው ወደ ምንጭነቱ ከመሄድ ፈንታ በራሱ ብቻ ተወስኖ ውሳኔውን መስጠት ልምድ ሆኗል ለምሳሌ በኢትዮጵያ የፍትሐነገሥት መሠረታዊ ምንጭ ሲኖዶስ ከፍትሐ ነገሥት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ መኖሩ እያተወቀ

1564- ስለ 318 አባቶች በሚጠተሰበት ጊዜ ሁል ጊዜ የተለመደው ሙሉ ቁጥር 300 መጠራት

በመጨረሻ አጠራጣሪም ቢሆን አሁን ከአለው የበለጠ ዝርዝር ይዘት ያለው የግእዝ ትርጉም ፍትሐ ነገሥት እንደ አለ ይወራል ።

ስለዚህ የተጠቀሱት ዜናዎች ቢረጋገጡ ምንዓልባት ይህ የበለጠ ዝርዝር ይዘት ያለው ፍትሐ ነገሥት አሁንም ከሚታወቁት የበለጡ ዝርዝር ምንጮችን ይዞ ይገኝ እንደሆነ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ።

ነገር ግን ስለ አለመኖሩ ፍጹም ርግጠኛ ነን ለማለት ባንችልም ጥያቄው በቀረበበት መልኩ ይቆያል ምክንያቱም ይህን መሰል ሰነድ ጽሑፍ ማግኘቱ ካለም "ምን አልባት" ነው

ክፍል አራት
ምዕራፍ አሥራ አንድ
የፍትሐ ነገሥት ምንጮች መጠቃለልና ይዘት

1 እስከ አሁን በዝርዝር እንደተመለከተው ፍትሐ ነገሥት (ብሔረ ሕግ ወቀኖና) ከተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ፣ ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናትና ሥጋውያን ሕገጋት መመንጨቱ ታውቋል

ሆኖም ሁሉም ቀኖናውያንም ሆነ ሥጋውያን ሕገጋት እነሱም የፈለቁባቸው ምንጮችና የተዘጋጁባቸው— የታወጁባቸው ጊዜያት ጥያቄዎች እንደተጠበቁ ሆነው ግን አንድ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በተለየ ሁኔታ በራሱ በፍትሐ ነገሥቱ ይደናገራሉ

በመጀመሪያ ከላይ እንደተባለው ፍትሐ ነገሥት የኒቅያ ሲኖዶስ 318 አባቶች ሥራ እንደ ሆነ ይተረካል ። ስለዚህም ከልዩ ልዩ ቀኖናውያንና ፖለቲካውያን— ሥጋዊያን ምንጮች የተወሰዱትንና በፍትሐ ነገሥቱ የተያዙትን ሁሉንም ምንጮች በግድ ለ300 አባቶች ይሰጣሉ ። [1564]

ከዚህም በመነሳት አንድ ዓይነት መፍትሔ የሚሹና ቀኖናዊም ሆነ ሥጋዊ ፖለቲካዊ ባሕርይ ያላቸው ችግሮች ምንጊዜም ቢፈጠሩ (ሲፈጠሩ) ይህን መፍትሔ እንዲሰጥ የሚገባው – የሚሻው አግባብ ሥልጣን ያለው አካል (ለምሳሌ ዳኛ) እንደነገሩ ሁኔታ በፍትሐ ነገሥት ውስጥ በተገቢው ቀኖናዊም ሆነ ሥጋዊ ትእዛዝ በመደገፍ ለተፈጠረ ችግር መፍትሔውን ለመስጠት በመምክር ነበር ። ስለዚህም አንድ የተፈጠረ ጉዳይንም የሚመለከት አግባብነት ያለው ድንጋጌ ሙሉ ሰነዱ ያለባቸውን ምንጮች ፍለጋ ለመሄድ አይገደድም ማለትም የጉዳዩ መፍትሔ የሚፈለግበት ፍትሐ ነገሥት በባሕርዩ መሠረት የተወሰኑ ምእላዳትን ወይም ጥቅሶችን ይዞ እንደመገኘቱ መጠን እንደ ሁኔታው ወደ ምንጭነቱ ከመሄድ ፈንታ በራሱ ብቻ ተወስኖ ውሳኔውን መስጠት ልምድ ሆኗል ለምሳሌ በኢትዮጵያ የፍትሐነገሥት መሠረታዊ ምንጭ ሲኖዶስ ከፍትሐ ነገሥት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ መኖሩ እያተወቀ

1564· ስለ 318 አባቶች በሚጠቀስበት ጊዜ ሁል ጊዜ የተለመደው ሙሉ ቁጥር 300 መጠራት

አንድም ጊዜ ሲጠቀስ አያጋጥምም ለምሳሌ ስለ ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት ከሐዋርያውያት (መስማተ ሐዋርያውያት) 81 ቀኖናት ቀኖና 81[1565] ወይም ከ 56 ቀኖናት ቀኖና 56 [1566] ሳይሆን ቀኖናቱ ተጠቀሰውበት የሚገኘው የፍትሐ ነገሥቱ አንቀጽ 2 ነው የሚጠቀሰው ።

2· ፍትሐ ነገሥት 51 አንቀጾች ሲኖሩት ከእነዚህም የመጀመሪያዎች 22 አንቀጾች ሕገ ቤተክርስቲያንን- መንፈሳዊ ሕግን የያዙ ናቸው ። የሚከተሉት 29 አንቀጾች 52ኛ አባሪ- ተቀጽላ አንቀጽን ጨምረው ሥጋዊ ሕግ (ማኅበራዊ ግለዊ ሕግ) የተቀነባበረባቸው ክፍሎች ናቸው[1567] ሰነዱ - ፍትሐ ነገሥቱ በመስመ ቅድመ መቅደም ይጀምራል[1568] ከዚህም በሁለት ክፍሎች ተከፍሎ[1569] የሚታይ መቅድም ሲኖረው ፍትሐ ነገሥቱን ወደ ግእዝ የመለሰው ሰው መደምደሚያ- መዝጊያ ይገኛል [1570]

የመጀመሪያ ክፍል ይዘት

1· ስለ ቤተክርስቲያን
2· ስለ ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት
3· ስለ ጥምቀተ ክርስትና
4· ስለ ሊቃነ ጳጳሳት
5· ስለ ኤጲስ ቆጶሳት
6· ስለ ቀሳውስት
7· ስለ ዲያቆናት
8· ስለ ሌሎች ላዕከነ ቤተክርስቲያን
9· ስለ ካህናት ሁሉ
10· ስለ መነኩሳትና መነኩሳይያት

1565· ከዚሁ ገጽ .137-166
1566· ከዚሁ ገጽ 197
1567· ሥጋዊ ሕጉ በግላዊ ሕግነቱ በአንድ በኩል ግላዊ ሕይወትን (ምግብ ፣ ልብስ ፣ ወዘተ) እንደዚሁም ግለሰብአውያን ግንኙነቶችን ጋብቻን ፣ ልጅነት ፣ ወዘተ· ይመለከታል በማኅበራዊ ሕግነቱ ማኅበራውያን ግንኙነቶችን ፤ የንግድ ልውውጥን ፣ ብድርን ዋስትናን ፣ ወዘተ· ይመለከታል
1568· ከዚሁ ገጽ 70
1569· ከዚሁ ገጽ 65-68
1570· እየአንድአንዱ አንቀጽ በምዕራፎች ወይም ክፍሎች ሲከፈል እየአንድአንዱ ምዕራፍ በክፍል ወይም በሐረጎች ይከፈላል ።

11· ስለ ሕዝብ ትእዛዝና ተግሣጽ
12· ስለ ቅዳሴ
13· ስለ ቁርባን
14· ስለ ጸሎት
15· ስለ ጾም
16· ስለ ምፅአት
17· ስለ ምጽዋት እደላ ኃላፊነት
18· ስለ አሥራትና በኩራት ፣ ስእለትና ጉልት
19· ስለ እሑዶችና በዓላት
20· ስለ ሰማዕታት-አማንያንና ከሐዲያን
21· ስለ ድውያን
22· ስለ ሙታን

የሁለተኛው ክፍል ይዘት

23· ስለ ምግብ ልብስ ቤትና ተግባረ እድ
24· ስለ ማጨትና ጋብቻን ማጽናት
25· ስለ ከዕቁባት መከልከል
26· ስለ ስጦታ
27· ስለ ብድር ፣ ዋስትና ፣ መያዣ ማስተዳደር
28· እንደ ልብስና እንስሳ ያሉትንና ሌሎችንም ስለ መዋስ
29· ገንዘብን በአደራ ስለ ማስቀመጥና ስለመሳሰለው
30· በአስተዳዳሪነት ስለ መሾም
31· ስለ ባርነትና ነፃነት
32· ስለ ሕፃናት ሞግዚትነት
33· ስለ መሸጥና መግዛት
34· ስለ ሽርክናና ስለሚመስለው
35· ስለ ማስገደድና ስለ ቁጣ
36· ስለ ቤት ማከራየትና የመሬት ግምት ስለመስጠት
37· ስለ ቤት ግንባታና ስለሚመስለውም
38· ስለ ብድር
39· ኃጢአትን ስለ ማመን
40· ከእንስሳት ወገን የጠፋን ስለማግኘትና ስለሚመስለው
41· ስለ ገንዘብ ማዘዝ ኑዛዜ

42· ስለ ርስት
43· ስለ ዳኛና ረዳቶች
44· ስለ ነገሥታት
45· ስለ ብሉይና አዲስ (መጻሕፍት)
46· ስለ ክሐዲያን ቅጣት
47· ስለ ነፍስ ገዳዮች
48· ስለ ዝሙት ቅጣት
49· ስለ ሌቦች ቅጣት
50· ስለ ኃጢአት ቁጥር
51· ስለ ልዩ ልዩ ሥራዎች ቁጥር
52· ስለ ውርስ (አባሪ ተቀጽላ)

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

የፍትሐ ነገሥት በግብጽና በኢትዮጵያ ተግባራዊነት

ስፋትና ኃይል

1·<u>በግብጽ</u>

ፍትሐ ነገሥት እንደሕጋዊ ቀኖና ለቤተክርስቲያናውያን ፍርድ ቤቶች የተዘጋጀ እንደሆነ ይቆጠራል ፡ እነዚህ ቤተክርስቲያናውያን ፍርድ ቤቶች በክርስቲያን ማኅበረሰቦች መካከል በተለየ ግን እስልምና በስፈነባቸው በግብጽና ሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ክርስቲያኖች መካከል የሚነሱ ሃይማኖት ነክና የፍትሐ ብሔር ትእዛዝ ፡ ሕገ ቤተክርስቲያንንም መተላለፍ ማለት የወንጀል ጉዳዮችን ጨምሮ ልዩነቶችን ለመፍታት የሚቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ናቸው ።

"Some Authors are of Opinion That it ought to be Considered as one of the works prepared for use by the Episcopales Audientiae, Church Institutions of Judicial nature which were Permitted to Adjudicate certain Disputes among the Christians by the Muslems Conquerers of Egypt and other Areas of Middle east" [1571].

ሆ· ከዚያም በመነሳት በቱርክ ሥልጣን በኦቶማን ግዛት አጼ ሥር በሚኖሩ ክርስቲያኖች መካከል የሚነሱ ሲቪል ጉዳዮችን ለመዳኘት ለቁስጥንጥያ ሊቀ ጳጳሳት – ፓትርያርክ የተሰጠው መብት–ሥልጣን ለግብጽ ቤተክርስቲያን ተሰጥቶ ይኖር እንደነበር ሊያጠራጥር ይችል ይሆናል[1572] ነገር ግን ከቤተክርስቲያን ጉዳዮች ውጪ ለነበሩ ችግሮች መፍትሔ የሚያስችል ሥልጣን ለእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት–ፓትርያ

1571. P. Tzadua. Fetha Nagast ገጽ XVI ። ከዚህም የቀደሙ ተመሳሳይ ሥራዎች ነበሩ ለምሳሌ ዐረብኛ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ዘሚካኤል ዘድምያጥ እና ቀኖናዊ መድበል ዘመቃርዮስ ፡ ሱርስጥ ብሔረ ሕግ ወቀኖና H.Gegorius Adbulphargius Bar-Hebraeus እና ብሔረ ሕግ ወቀኖና H. Ebediesus Mitropolitiae Sorac ከዚሁ ገጽ

1572· በክርስቲያኖች መካከል የሚከሰቱ ችግሮችን የመፍታት ሥልጣን ከቁስጥንጥንያ ውድቀት በኋላ ለክርስቲያኖች ሊቀ ጳጳሳት ፓትርያርክ በሡልጣን ምእመት ሁለተኛ ተሰጥቶ ነበር ።

ርክ ተሰጥቶ ስለነበር ይህ ለፍትሐ ነገሥት ቅንብር መነሻ ዓላማ ነበር ለማለት አያስችልም ። ስለዚህም ፍትሐ ነገሥት Episcopales Audientiae ውሳኔ አሰጣጥ የሚረዳ ሕግ ሆኖ ተዘጋጀ ብሎ ለመበቀል አያስችልም ምክንያቱም በአንድ በኩል ፍትሐ ነገሥትን ለማቀነባበር እንደ መጀመሪያ ምንጭ

ሆነው የተጠቀሙት ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናትና የግብጽን ቤተክርስቲያን ጨምሮ በጥንት አብያተ ክርስቲያናት በሥራ ላይ የነበሩት ቀኖናውያን ሕገጋት ነበሩ በሌላም በኩል በሁለተኛው ክፍል የተያዙት አብዛኞቹ ቀኖናት ድንጋጌዎች በግብጽና በሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ እስላማውያን አካባቢዎች ክርስቲያኖች መካከል የተፈጠሩ ሕጋውያን ልዩነቶችን ወይም ግንኙነቶችን ለመፍታት— ለመወሰን ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ አልነበሩም ።

ስለዚህ በርግጥ ሥልጣን ከነበሩት ሥልጣናት መካከል በተለየ የማይቻሉት ተቆርሰው ለእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት— ፓትርያርክ ተሰጡ ማለቱ ያስቸግራል ለምሳሌ ሕገ ቤተክርስቲያንን ጥሰዋል ተብለው በሞት የመቀጣት ሥልጣን እንደገናም በሥጋዊ የወንጀል መቅጫ ሕግ ለምሳሌ በጠንቋዮች ላይ ቅንጣት የመወሰን ሥልጣን ለምሳሌ በደንጋይ ተወግሮ እንዲሞት የመፍረድ ሥልጣን[1573] ተሰጥቷል ብሎ መቀበሉ ችግር ነው ።

እንግዲህ የግብጽና ሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢዎች አገሮች በእስልምና ከተያዙ 400 ዓመታት በኋላ (640–13ኛው ምዕተ ዓመት) በዚያ አካባቢ ተፈጻሚነት ሊኖራቸው የሚችሉ ድንጋጌዎች ለምሳሌ ከክርስቲያኖች ነገሥታት ወደ አሸናፊዎች እስላሞች እጅ ሥልጣነ መንግሥት ከተዛወረ በኋላ ስለ ሥልጣነ ንጉሥ የሚናገር ድንጋጌ ለቤተክርስቲያን መሪዎች ተሰጠ ማለትን ሥነ አእምሮ የሚበቀለው አይሆንም[1574]

1573· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 43 ቁጥር 1447

1574· እብን አል አባባል ፍትሐ ነገሥትን እንደ መደበኛ ሕጋዊ ሰነድ ሳይሆን ነገር ግን ለእምነቱ ተከታዮች የሕግ ሰዎች ረዳት ሕግ አድርጐ እንደአዘጋጀው Guidi ይደግፋል IL Synodos Etiopico ገጽ 41–48 በሌላ በኩል Marger Perham, the Government of Ethiopia ገጽ 134· D' Emillia: Ifflussi Diritto Mussulmano Nel Capitolo XVIII Den NomoCanonc Arabo Chrisstiano d IBN al-Assal R.S.O. 19/1946. T.I ገጽ 1 15

በርግጥ ስለ ነገሥታት በሚናገረው አንቀጽ ሥልጣን ከእግዚአብሔር እንደሚመነጭና የሚከተሉት የእምነት ዓይነት ከግምት ሳይገባ ይህን ሥልጣን ለያዙ ሰዎች መታዘዝ እንደሚገባ የሚያዘው ጳውሎሳዊ ቃል ግን ይታወሳል[1575]

ሆኖም ግን ከዚህ ከጳውሎስ ቃል ጋር አብረው የማይሄዱ ትእዛዛት ይገኛሉ ለምሳሌ የማያምኑና የማይዘመዱ ሰዎችን አለማንገሥ[1576] ስለ ኦርቶዶክስ ዳኛ አስፈላጊነት ፣ ወዘተ· ። ስለዚህ ፍትሐ ነገሥት ሥልጣነ መንግሥትን የጨበጠ ሰው እምነት ከአገር ቤተክርስቲያን እምነት ጋር ተመሳሳይ መሆን እንደሚኖርበት ያስተምራል ። ስለዚህ ፍትሐ ነገሥት በግብጽ ቤተክርስቲያን ፍርድ ቤቶች Episcopales Audientiae ጥቅም ይውል ዘንድ ሊዘጋጅ አይችልም ነገር ግን በመልክዐ ምድራዊ ክልል ሳይወሰን

ለምሳሌ ይህ ዓይነቱ የቤተክርስቲያን ሲቪል ሕጋዊ ሰነድ (ምእላደ ሕገጋት) የክርስትና እምነት መሠረታዊ እምነት ለሆነባትና የእምነቷ ተከታዮች ከዙፋን ላይ ለሚወጡባት አገር ኢትዮጵያ አስፈላጊ ነበር ።[1577]

ስለዚህ በርግጥም ፍትሐ ነገሥት ለዘመናት በኢትዮጵያ ተከብሮ የኖረ ምእላደ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕግ ነበር ። አሁንም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ምእላደ ሕገጋት ቀኖናውያን መሆኑ እንደተጠበቀ ሁኖ በኅብረተሰቡም ዘንድ መሠረታዊ የሕጐች ምንጭ ሆኖ ያገለግላል

2·በኢትዮጵያ

ፍትሐ ነገሥት ወደ ግእዝ እንደተተረጎመ እስከ ተተረጎመበት ወቅት ድረስ የሕዝብን አጠቃላይ ተቀባይነት አግኝተው በተፈጻሚነት ላይ ከነበሩት ትውፊታውያን ሕጎች ጎን በተወሰኑ ጉዳዮች ደግሞ የበላይነት ኑሮት በሥራ ሜተርጎም እንደጀመረ ይታወቃል ምክንያቱም ይህች አገር ምንም እንኳን እምስቱ ብሔረ ኦሪት ሕገጋተ ሙሴ ቤተክርስቲያናውያት፣ ሐዋርያውያትና ሲኖዶናውያት ቀኖናት አስቀድመው ገብተውና በተወሰኑም ጉዳዮች የሕግ ኃይል እንደነበራቸው

1575· ሮሜ 13·1

1576· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 44 ቁ· 1530

1577· Π. Φούγιαη Είσοδος του Ισλάμ έν Αιθιοπία, ΑΘΗΝΑΙ:1971 እስላምና ወደ ኢትዮጵያ ስለመግባትና ሥርጭት

የሚገመት ቢሆንም እንደ ፍትሐ ነገሥት—ምእላደ መንፈሳዊ ወሥጋዊ ሕግ/ቀኖናዊና ሥጋዊ ሕጋዊ ጽሑፍ—ሰነድ አልነበራትም በተለየ የሲቪል ሕገጋትን በሚመለከት ይህ ዓይነት ሕግ አለመኖር የበለጠ ችግሩ ይሰማ ነበር። በሕግ ልማዳዊ (ትውፊታዊ ሕግ) መሠረት የሚሰጠው የሕግ ውሳኔ—ፍትሕ ጥርጣሬ ሊኖርበት ስለሚችል ይህን ዓይነት ጥርጣሬ—ቅሬታ ለመፍታት—የመጨረሻ መፍትሔ ለመስጠት የመጨረሻው መፍትሔ የይግባኝ ዘዴ ፍትሐ ነገሥት ነበር።

እያንዳንዱ በፍትሐ ነገሥት ተይዞ ይገኝና በኢትዮጵያ ይሠራ የነበረ ወይም ምንአልባት የሚሠራ ርእስ መመርመር ወይም አለመመርመር በዚህ ጽሑፍ መሠረታዊ ዓላማ ውስጥ ሊስተጋባ የሚችል አይሆንም ነገር ግን ፈጽሞ ደግሞ መተውም አልታየም። ስለዚህም ቢያንስ በአለፉት ዘመናት ተግባራዊ ተፈጻሚነት በግልጥ ከነበራቸው ሥርዐቶች መካከል አንዱን መመልከት እንችላለን።

2·1·የጥገኝነት መብት ሥርዐተ ሕግ—ወደ ቤተክርስቲያን ገብቶ ደወል ደውሎ ተማሕፅኖን የማግኘት መብት

ሕግን ጥሶ በሚገኝበት ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ሂዶ ደወልን ደውሎ ጥገኝነትን የጠየቀ—ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ሸሽቶ ሂዶ የተማፀነ ማንም ሰው ጥገኝነትን የማግኘት መብት ይኖረዋል። በሌላ አነጋገር ሕግን ጥሶ ተገኝቶ በሕግ አስከባሪዎች አካላት ለሚሰደድ ሰውና ወደ አንድ ቤተክርስቲያን ክልል ሸሽቶ ለተጠጋ—ለተማፀነ ሰው ቤተክርስቲያን ጥገኝነትን — መማፀንን የመስጠት መብት ሥልጣን (Juris Asylum) አላት—ነበራት [1578]

በታሪክ ቤተክርስቲያን ይኖራት የነበረው ጥገኝነት የመስጠት — የመማፀን መብት Lex Asylum በየጊዜው የሮማ — ቤዛንቲን ንጉሠ ነገሥት በቤተክርስቲያን ላይ ከሚኖረው አቋም የሚመነጭ ነበር [1579]

ስለዚህ እንደ ሁኔታው የዚህ መብት ኃይል የሚዋልል ሆኖ ነበር

1578· መጅ 14— ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 50 ቁጥር 1794 Basilicorum,E'.A.'1A'.. Cod. Theod.IX.40.15.x1.36.31.1x 45.2.45.4 (ሁሉም 322 ዓ·ም) Cod.Just.1.12.14.7

1579. Novellae Iustinianus T.V.17 Ράλλη-Ποτλής Σύνταγμα Τ.Ε: ገጽ 210

የሚገኘው ሆኖም ግን ይህን ለቤተክርስቲያን የተሰጠ መብት በመተላለፍ ተማሕፀኖን ከቤተክርስቲያን የጠየቀውን ሰው ከቤተ መቅደስ አውጥቶ የተገኘ ሰው በግርፋት ይቀጣል፡ ጠጉሩን ተላጭቶ ይሰደዳል። በቅድስት ቤተክርስቲያን የተማፀነውን ሰው በራሱ ሥልጣን ቀምቶ ከእርሷ ቢያወጣው 12 ጊዜ ይግረፉት ፀጉሩንም ላጭተውም ይስደዱት… [1580] ነገር ግን ዘመድ የሆነ ደም ተበቃይ ነፍስ ገዳዩን ይህን ጥገኝነት ከመጠየቁ—ከመማፀኑ በፊት የገደለው እንደሆነ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት አይኖረውም ነበር [1581]። ወደ ቤተክርስቲያን ሸሽቶ የተማፀነው ሰው በቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ተመርቶና ወደ ቤተ መቅደስ አስተዳደር

ተወስዶ በሕግ መሠረት ለፍርድ ይቀርባል[1582] ምክንያቱም በሌላ በኩል በሕግ የሚታወቀው የጥገኝነት መብት ሊከብር የሚችለው ያለ ፍላጎት ለተፈጸመ ነፍስ ግድያ Homicidium Casuale Culporum ሲሆን በዕቅድ ታስቦ ለተሠራ ወንጀል—ነፍስ ግድያ Voluntarium አይሰራም [1583] ያለ ፍላጎቱ ነፍስ ግድያን Homicidum Causale Colporum የፈጸመ ሰው የተማፀነበትን የቤተክርስቲያን ጥገኝነት ያገኛል። ከዚያም ምንአልባት ከደም ተበቃዮች በኩል አደጋ እንዳይደርስበት የቤተ መቅደሱ አለቃና የሌሎች ኃላፊዎች ጥበቃ ይደረግለታል። በተለይ ግን የምንኩስናን አስኪማ ተቀብሎ ለነፍሱ ደኅንነት ወደ ንስሐ ለመግባት ከሆነ ወደ ቤተ መቅደስ የመጣው የተለየ ጥንቃቄ ይደረግለታል [1584]

ያለ ውድ በግድ Homicidium Casuale Culporum ነፍስ ገዳዮች የማመፀኛ ከተሞችም እንደነበሩ በብሉይ ኪዳንም ይታወቁ ነበር። “ወደ ከነዓን ምድር ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ በስሕተት ነፍስን

1580· መክ 39= ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 47 ቁጥር 1701 Procheiros Nomos 38·7 ·

1581· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 47 ቁጥር 1699 ዘኁልቁ 35 12—28

1582· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 50 ቁጥር 1781 ዘፀአት 21·17· ስምላሴ ኢሳይያስ 10·3

1583· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 47 ቁጥር 1775 በደረቅ ሕጎች ከዚያም አልፎ በቤተክርስቲያን አባቶች ትምህርት በቂም በበቀል ነፍስን መግደል ከባድ ቅጣትን ሊያስከትል ቢችልም ያለውድ በግድ የተፈጸመ ግን ቀላል ቅጣትን እንደሚያስከትል ተስምሮ ይገኛል ቀኖናት ዘአንቀራ 22·23 ቀኖና ዘጎርጎርዮስ ዘኒሲስ ፡ በንዝህላልነት ነፍስ ግድያ ቀኖና ባስልዮስ

1584· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10 ቁጥር 353 አንቀጽ 47 ቁጥር 1781 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 47 ቁጥር 1776

የገደለ ሰው ወደዚያ ይሸሽ ዘንድ የመማፀኛ ከተሞች እንዲሆኑላቸው ከተሞችን ለእናንተ ለዩ። ነፍስ ገዳይ በማኅበሩ ፊት ለፍርድ እስኪቆም ድረስ እንዳይሞት ከተሞች ከደም ተበቃይ የመማፀኛ ከተሞች ይሁኑላችሁ...[1585]"

ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሸሽቶ ጥገኝነትን የጠየቀው—የተማፀነው ሰው የነፍስ ግድያ ወንጀል የፈጸመው በቂም በቀል Homicidium Voluntarium ከሆነ ይህ የተጥገኝነት መብት—የማመፀን መብት አይሰጠውም ። ስለዚህ ይህ መብት ተነፍጎት ከቤተ መቅደሱ ይባረራል ፤ ለባለደም ተበቃዩ ተላልፎ ይሰጣል ። ነፍስ ግድያም ይፈጸምበታል [1586] ደግሞም ለአገር ጠላት መረጃን የሰጠ [1587] ወይም ለአገር ድል መነሳት ዕቅዶችን የገለጠ [1588] ሰው ይህን የጥገኝነት መብት አያገኝም ። ተመሳሳይ ድንጋጌዎች ከዘመኑ የወንደለኛ መቅጫ ሕጎች የማይታለፍ ድንጋጌዎች ናቸው [1589]

ይህን አስመልክቶም ምሳሌዎችን ማስቀጠመጥ ይቻላል ለምሳሌ በዘመነ ኢያሱ ዳግማዊ አድያም ሰገድ (1730—1755) የሆነውን መጥቀስ ይሆናል።

አንድ ሱራሔ ክርስቶስ የተባለ በንጉሡ ላይ ያመጸ ሰው ወደ እጨጌው ሄዶ ተማፀነ ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ወንጀለኞች በእጨጌ ፤ ኤጲስ ቆጳሳት ወይም በአንድ ቤተክርስቲያን አበምኔት መማፀንና ጥገኝነትን ማግኘት ይችሉ እንደሆነ የሚያዙ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶችን አውጥተው እንዲያሳዩት የፍትሐ ነገሥትን ሊቃውንት ሰብስቦ ጠየቀ። በዚህም ሲኖዶስ የሚከተሉት የፍትሐ ነገሥት ሊቃውንት ሊከፈሉ ችለዋል [1590] ሊቁ ተክለ ሃይማኖት ፤ ሊቁ ነጮ ፤ ሊቁ ኮከበ ልዳ ፤ ሊቁ ኢሳይያስ ፤ ሊቁ በትሬ ፤ አዛዥ ቴዎዶስዮስ ፤ አዛዥ ባሕርይ እና አዛዥ

1585· ዘኁልቁ 35፡11—12 ዘዳግም 19፡2—5

1586· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 47 ቁጥር 1675 ዘፀአት 21፡12 -14

1587· ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 42 ቁጥር

1588· በአብያተ ክርስቲናያናት የመማፀን ሥርዐት/የጥገኝነት መብት ሥርዓት በመጀመሪያ ትውፊት ሆኖ የገባ ሲሆን ቆይቶ የሕግ ቅርጽን ሊይዝ ችሏል Cod. Theod.1x.45.1. ለምሳሌ በዩስጢኒያኖስ አዲስ ሕግ (Novellae. 17) ይህም መብት ለነፍስ ገደዮች፣ አመንዝሮች፣ አፋኞች ለመንግሥት ንብረት ባለዕዳዎች አይሰጥም ነበር

1589· ለምሳሌ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 103

1590· "ሊቁ" የሚለው ኃይለ ቃል—ማዕርግ ለፍትሐ ነገሥት አዋቂዎች—ሊቃውንት የሚሰጥ ርእስ ሲሆን በላቲን Jurisconsultus ይተካል

ፋሲሎ [1591]

በዚህም ጊዜ እነዚህ ሊቃውንት ያለፈ ቂም በቀል ሳይኖረው በድንገት አጋጣሚ ሁኔታ ወንጀልን የፈጸመ (Homicidium Casuale) Culporum ለምሳሌ ነፍስ የገደለ ሰው የመማፀን መብት እንደሚኖረው ከቅዱሳት መጽሐፍት ጥቅሶችን በማውሳት ሲወስኑ [1592] በተቃራኒው ደግሞ ግን በነበረ ቂም በኩል ተነሳስቶ ወንጀልን የፈጸመ ለምሳሌ ፈልጎ ነፍስን የገደለ ሰው (Homicidium Voluntarium) ወይም በአገሩ ላይ የክሕደት ወንጀልን የፈጸመ ሰው ይህን የማመፀን መብት ዕድል ማግኘት እንደማይችል አረጋገጡ [1593] Conti Rossini ንጉሡ ነገሥቱ በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ወንጀል የፈጸመ ሰው ከቤተክርስቲያን መሪዎች ዘንድ መማፀን ይቻል እንደሆነ እንዲመልሱለት የፍትሐ ነገሥትን ሊቃውንት ከጠየቀው ጥያቄ ላይ በመመሥረት ፍትሐ ነገሥት በሥራ ላይ የነበረ ሕግ እንደ አልነበረ ተጠራጠረ ቢሆንም የሕግ ልዩነቶችን ለመፍታት ለዳኞች የሚረዳ የሕግ ሰነድ እንደነበር ይደገፋል ።

ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ በትክክል በጻውሎስ ጻድዋም ሰነድ ውድቅ ሆኗል ምክንያቱም ፍትሐ ነገሥቱ ለብዙ ዘመናት በኢትዮጵያ ይፋ የሕግ ሰድ ሆኖ መኖሩ ርግጠኛ ነውና [1595]

በኢትዮጵያ የመማፀን መብት ጥገኝነት የማግኘት መብት—ዕድል በገዳማትና አድባራት ተጠብቆና ተከብሮ በኖረ መብት መሠረት አንድ ሕገ ወጥ ተግባርን የፈጸመ ሰው ወደ አንድ ገዳም ወይም ደብር ሄዶ በመደወል ይማፀን ነበር።

በደንብ ግን ተማፃኙ ሰው ወደ ቤተክርስቲያኑ ክልል ውስጥ ከገባበት ደቂቃ ጀምሮ ከሲቪልና የፍትሕ አካላት ወይም ከባለ ደም ተበቃዩ ከመሰደድ መያዝ ወይም ከመታሠር የሚጠበቅበትን የጥገኝ

1591· "አዛዥ" የሚለውም ኃይለ ቃል ማዕርግ በንጉሡ ነገሥቱ አጠገብ ለሚገኙ የፍትሐ ነገሥት ሊቃውንት የሚሰጥ የማዕርግ ስም ነው በቃቤ ሰዓት፡ ጸሐፊ ትእዛዝ፡ ወዘተ፡ ማለት ነው

1592·ዘኁልቁ 35·11··· ዘዳግም 19፡2 5፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10 ቁጥር 353

1593·ዘኁልቁ 35·16 ዘዳግም 19·11፡ መዝሙር 104·15 2ኛ ነገሥት 20·5፡ 3ኛ ነገሥት 1·50 12·2·፣ ማቴ 22·21፡ ሮሜ 13·1 -2፡ 6·4፡ 1ኛ ጴጥሮስ 1·17፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 47·ቁጥር 1710—1711

1594. Contini Rossini: Diritto Consuetudinario Etiopico... ገጽ 303

1595· P.Tzadua:Fetha Nagast...ገጽ XXVI

ነት መብት ያገኘ ነበር። ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት ይህ የጥገኝነት መብት—ዕድል በሕግ ባይታወቅም—ባይረጋገጥም በሥነ ምግባራት ድንጋጌዎች መሠረትና ለተቀደሱ ቦታዎች ከአለው አክብሮት የተነሳ ይህ መብት አይጣስም ነበር ማለትም በትውፊት ለገጠር አብያተ ክርስቲያናትም የጥገኝነት መብት ታውቆ ነበር።

በመጨረሻ በአብያተ ክርስቲያናት ክልል የጥገኝነት/የመጠበቅ—ያለመደፈር መብት ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለሥነ ፍጥሮችም የተጠበቀ ነበር ለምሳሌ ርግብ

2·2 በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥርዐተ ሕግ የፍትሐ ነገሥት ስፍራ

በአጠቃላይ "ትውፊት" ከሕግ ኃይልነት ወይም ከሕግ ሥርዐ ምንጩነትና ተፈጻሚነት አንጻር ሳይሆን ከጊዜ—ትውልድ አንጻር ብቻ የሕግን የመጀመሪያ ምንጭነት ይይዛል ምክንያቱም ያልተጻፈ ሕግ በጊዜ የተጻፈ ሕግን እንደሚቀድም ግልጥ ነውና....

"ትውፊት" የሕግን በሰነድነት መቀረጽ ከሚቀድመው ስለ ሕግ ግንዛቤ—ማኅበራዊ ስሜት ሌላ አይደለም። የጥንት ሰው ጽሕፈትን ካለማወቁ የተነሳ ፈጽሞ በትውፊታዊ ሕግ ገዢነት ሥራ Gewohnheits-recht Consuetudo ይኖር እንደነበር ይታወቃል ቆይቶ ግን የሰው ልጅ የመጽሐፍና የማንበብ ዕውቀት ብርሃንን ለማስገኘት በመቻሉ እንደ አመችነቱ በሁሉም የሕግ ገጽታዎች ትውፊታውያንና ቅርጻውያን Gesetzrecht ሊመራና ሊተዳደር ችሏል።

በለዚህም የጽሕፈት ፍልስፍና ከመፈጠሩ ጋር የትውፊታውያት ሕጋዊያት ቀኖናት ቅርጻዊ አላዴን ይያያዛሉ ። በታሪክ የታወቀው ጥንታዊ ቅርጻዊ ምእላደ ሕገጋት የባቢሎን ንጉሥ ሐሙራቢ ምእላደ ሕግ (2279 ቅ·) ነው [1596]

1596. W.Eilers:Dic Gesetzesstele Hamurabi 1932 Ch. Ecwards:The World's Earliest Laws 1914 Cruveilhier Introduction au code 'd Hummurabi 1932. Νικολαΐδου-Σκορδύτης Ο Κώδιξ τής Αρχαίας Βαβιλώνας 1951

1597 · Η. LEVY-BRUCHL-Σάββας Καινωνιολογία Δικαίου ገጽ 12-60

Δασκαλάκη Γ.: Η Οικουμενική διακήρυξις τών Ανθρωπίνων Δικαιωμάτων 1952-1955 ገጽ 12-90

ከዚያም የሙሴ አሠርቱ ቃላት (15ኛው ምዐተ ዓመት ቀ·ክ) የሮማ 12ቱ ቃላት (5ኛው ምዕተ ዓመት) የሕንዳዊ ማኑስ ሕጎች የ3ኛው ምዕተ ዓመት [1597] ብዙም ምሳሌዎችንም መጥቀስ ይቻላል ግን ለማሳየት የተፈለገው ማንኛውም ሕግ ቢሆን ወደ መቀረጽ ከመድረሱ በፊት በትውፊትነት እንደሚዳብር ነው።[1598]

ስለዚህ የዘመኑ የኢትዮጵያ ሥርዐተ ሕግ በሁሉም ሥርዐተ ሕገጋት (ትውፊታውያንና ቅርጻውያን) ተዕዕኖ ሥር የሚገኝ ሥርዐተ ሕገጋት ነው ።

እንግዲህ ትውፊታውያት ቀኖናተ ሕግ በጥንት ጊዜ ብቻም ሳይሆን እስከ ዛሬም እንደ አልተጻፉ ሕገጋት አንድ አንድ ጊዜ የበለጠ ኃይል ኑሮአቸውም በተፈጻሚነት ላይ ይገኛሉ [1599] በሌላ በኩል ፍትሐ ነገሥት እንደ ቅርጻዊ ሕግ ተቆጥሮ ሲጠበቅ ኖሮዋል።

ፍትሐ ነገሥት ዛሬም በተወሰኑ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ ዳኛው ወደ ሌሎች ሕገጋት መሄድ ላያስፈልገው ወይም መሄድ እንደማያስፈልገው በገመተበት ጊዜ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ሆኖም ግን ይህ የፍትሐ ነገሥቱና በሥራ ላይ ያሉት ሕጎች ድንጋጌዎች እስከ አልተጋጩ ድረስ ሲሆን ልዩነት ከተከሰተ ግን በርግጥ የሕጎች የተፈጻሚነት ቅድሚያ ይጠበቃል

ሁሉም በግን ለአንድ ጊዜ ትውፊታውያን ሕገጋትን አስመልክቶ አጠቃላይ ብሔራውያን ወይም አካባቢያውያን ሁነው ሲገኙ የአፈጻጸም ችግር የሚያጋጥማቸው ሁኔታዎች ይኖራሉ ቢሆንም የአካባቢዎች ልምዶችም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ [1600]

1598. C.Rossini:Diritto Consuedioario Etiopico R.G.M.E O.G.O. SER.1937 ገጽ 302 C.Rossini.Principi Di'Diritto Consuedinario De Eritrea Rome 1916.

1599. Cerulli, Il Nouvo Codice Penale Etiopico O.M. T.12 No. 80 ገጽ 392፡ A. L. Gardiner. La Juridiction concernant les éntrangers en Ethiopie R.G.D.P. Paris T.44. ገጽ 90

1600. Stini: Diritto Consuedinario Adkeme Melga Law Code Tigrinya-Italia-na Asmara 1944. Consuetudini Giuridiche del serre Tigrinya-Italiana T 2· ሕትመት c. Rossini. L.Ricci, Roma. 1948. — 1953 ዐዚያም Logo Towa Law Code Tigrinya

ይህ እንደ<u>ተጠበ</u>ቀ ሆኖ በዘመኑ ሕገጋትም ቢሆን እየተቀረጹ የሚገኙት ትውፊታውያን ሕጎች ብዙዎች ናቸው። የፍትሐ ብሔር ድንጋጌዎች እንደ ኑዛዜ —ውርስ፣ ጋብቻ ወዘተ· የፍትሐ ነገሥት ውርሶች ናቸው ማለትም የዘመኑ የኢትዮጵያ ሕገጋት በአንድ በኩል ከሕጋዊ ትውፊት ተጽፈው ብቻ ሳይሆን በልምድ ሲያያዝ ከመጣ—ሥርዐተ ሕግ/በሌላ በኩል ከተጻፈ ቅርጻዊ ሕግ ፍትሐ ነገሥት የመነጩ—የተሳቡ ሕገጋት ናቸው።

በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ የራሱ አመለካከት ቢኖርም ከትውፊቶችና ሕጎች/ ሕጎች ተቀርጸውም ሆነ አልተቀረጹም/ ጋር የሚጋጩ ሕጎች ሊቀረጹ ወይም ትውፊቶች በገዝምታ ሊዳብሩ አይችሉም።

ስለዚህም ፍትሐ ነገሥትን ለማሻሻል ወይም ለመተካት የነበረው አስፈላጊነት ሊታይ የቻለው የአገሪቱ ዘመናዊ ፍላጎትና የሕዝብ ጥያቄ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጥሮ ስለተገኘ ነበር። ከጊዜ ሂደትም በኋላ መንግሥት ቀኖናተ ሕገጋትን የፍትሕ ብሔርና የወንጀልኛ መቅጫ ሕገጋትን ለማለድና ለማወጅ ሲገደድ የእነዚህ ሕገጋት ቢጋሮች አርእስቶች በሚመለከቷቸው የፍትሐ ነገሥት ድንጋጌዎች ላይ እንደሚመሠረቱና እንደሚመረኮዙ የሚያስገድድ መመሪያ ነበር።

የዘመኑ የሕግ ማውጣት ሥራ ሕገጋት ጊዜው ከሚጠይቀው የማኅበራዊና ግለሰብአዊ ሕይወት ፍላጎት ጋር መጣጣም እንደነበረባቸው ከተገነዘቡት አፄ ምኒልክ ጊዜ (1892 1905) ጀምሮ ነበር መንቀሳቀስ የጀመረው[1601]

አፄ ኃይለ ሥላሴ ገና እንደራሴ በነበሩበት ጊዜ በኢትዮጵያውያንና በውጪ የሕግ ሊቃውንት አማካሪዎች በመታገዝ በ1923 የወንጀለኛን መቅጫ ደንብ (ሕግ) አወጁ። ቆይቶ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በ1949 እና የፍትሐብሔር ሕግ በ1952 ተሻሽለው ታወጁ፣ አሁንም በሥራ ላይ ይገኛሉ።

እነዚህም ሕጎች ከታወጁ ወዲህ ፍትሐ ነገሥት በቀጥታ የነበረውን ተፈጻሚነት ያቆማል። ቢሆንም የሕጎች ምንጭነቱ እንደተጠበቀ ነው። በርግጥ ፍትሐ ነገሥት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ አሁንም እንደገና ሕግ ሆኖ

1601· ገብረ ሥላሴ ዜና ምኒልክ (1917) የአፄ ኃይለሥላሴ የፍትሐ ብሔር ሕግ (1952)፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ (1949) እና የፍትሐ ነገሥት እንግሊዝኛ ትርጉም (1968 እ·ኤ·አ·) መቅድሞች

ሲታይ በአንድ በኩል በሌላ በኩል በተዘዋዋሪ መንገድ አሁን ለአሉት የአገሪቱ ሕጎች ምንጪ ሆኖ ተጠቅሟል። በጊዜ ሂደት ከጊዜ ማለፍ የተነሳ ግን በተለየ በዝቅተኛ ፍርድ ቤቶች እየራቀ እየሄደ ሲገኝ በከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለየ በንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ችሎት ፍትሐ ነገሥት ከሌሎች ሕጐች የበለጠ ተደማጭነት ነበረው ።[1602]

ከዙፋን ችሎት ሥርሀት መሠረዝና የንጉሠ ነገሥቱ የዳኝነት ሥልጣን መነፈግ በኋላ ፍትሐ ነገሥት ራሱ ሁለተኛውን ክፍል በተመለከተ ታሪካዊ ትርጉም ነው ያለው [1603] ነገር ግን ይህ ለረዥም ዘመናት ከአገሪቱ ነዋሪዎች ማኅበራዊ ሥነ ልቦና ላይ ተፅዕኖን ያሳደረ ሕጋዊ ሰነድ ሆኖ የኖረ እንደመሆኑ መጠን አሁን በሥራ ላይ በሚገኘው ሥርዐተ ሕግ ያለው ቦታ ከፍተኛ ትርጉምን ይዞ ተገኝቷል [1604] አንደኛውን ክፍል መንፈሳዊ ሕጉን በሚመለከት በሌላ በኩል ሊተላለፍ የማይችል ሕገ ቤተክርስቲያን ነው።

1602· በሁለቱ አዳዲስ ሕጎች (የፍትሐ ብሔር ሕግና ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ) እና ፍትሐ ነገሥት መካከል ስለ አሉ ግንኙነቶች Graven: The Penal Code of The Empire of Ethiopia. J.E.L.T.1 1964. ገጽ 273. S.Lowenstein: The Penal System of Ethiop- ia.J.E.L.T.2 1965 ገጽ 384. J.Vanderlindem, an Introduction to The Sources of Ethiopian Law.J.E.L.T.1 1964.ገጽ 247 N.Singer, The Disolution of Religious Marriage in Ethiopia. J.E.L.T. 4 1967 ገጽ 205·Norman Bentiwich The New Code of Ethiopia Contemporary Review May 1944 ገጽ 269 70· CH.Stanford: Ethiopia Under Haileselassic ገጽ 8·M. Perham: The Government of Ethiopia ገጽ 134

1603· በንጉሠ ነገሥቱ ከዙፋን መውረድ የዙፋን ችሎት ተሠርዟል ቢሆንም በ1966 ተነድፎ ግን ባልጸደቀው ረቂቅ ሕገ መንግሥት ፍትሕ በንጉሠ ነገሥቱ ስም በፍርድ ቤቶች ወደ ፊት እንደሚሰጥ ይመለከት ነበር። ይህም ረቂቅ ሕገ መንግሥት ወደ ፊት የሚተረጎመው ሕገ ሕዝብ እንደራሲዎች በወጣ ሕግ ብቻ መሆኑንም ያመለክት ነበር።

1604· የተያያዘው አባሪ ገጽ

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

መደምደሚያ

በዚህ ጽሑፍ የፍትሐ ነገሥት ችግሮችን በአጠቃላይ መስመሮች በተለየ ታሪካዊ አመጣጡንና ከእነሱም በመነሴ የቤተክርስቲያንና መንግሥት ግንኙነቶችን በሚመለከት የሚቻለው ጥረት ተደርጓል ።

በመደምደሚያ በአጪሩ እንደሚከተለው በየጊዜው ፍትሐ ነገሥትን በሥራ መተርጐም እና እሱም በሥነ ሃይማኖትና ሥነ ሕግ ጥበብ ክልል ያለው ሥርዐተ ትርጉም የሚመለከቱ ጉዳዮች ሊመለከቱ ይችላሉ።

1· ከታሪካዊ አመለካከት አንጻር

ፍትሐ ነገሥት ወደ ግእዝ ከተተረጐመና በሥራ ላይ ከመዋሉ በኋላ (ነገር ግን ከተዘጋጀበት ጊዜ ጀምሮ በግብጽ) በሙሉ—በምልዓት ተፈጻሚነት ሊኖረው አልቻለም ነበር ። ስለዚህም በመጀመሪያ የተወሰኑ ድንጋጌዎች ከኢትዮጵያ ማኅበረሰብአዊ ሕይወት ሁኔታዎች ጋር የማይሄዱ ወይም ከዚሁ መንፈስ ጋር የማይጣጣሙ ሁነው በመገኘታቸው በሥራ ሊተረጐሙ አልቻሉም/አይችሉም ነበር ምክንያቶችም ሆነው ሊነሱ የሚችሉት የይዘቶቹ አመራረጥና አሰጣጥ ያለፈበት እንደነበር ነው።

ሌሎች ድንጋጌዎች ለተወሰኑ ጊዜያት በሥርዐት ተፈጻሚነት ከኖራቸው በኋላ ጊዜ ከወለዳቸው ማኅበራዊያን ለውጦች ጋር የማይጣጣሙ ሁነው እየተገኙ ከመፈጸም የቆሙ ሁነው ይገኛሉ ። በመጨረሻ ሁለተኛው የፍትሐ ነገሥት ክፍል በአዳዲስ ሕጎጋት ፤ የፍትሐ ብሔር ሕግ (1952) እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ (1949) ተተክቷል ። የመጨረሻዎቹን የወሰድን እንደሆነ ዛሬ ፍትሐ ነገሥት በአገሪቱ በየጊዜው በሚወጡ ሕጎጋት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ከማኅበራውያንና ፖለቲካውያን ለውጦች የተነሳ እየተዳከመ በመሄድ ላይ ይገኛል ምክንያቱም ፍትሐ ነገሥት የተቀነባበረበትን ጊዜ ብቻ ሳይሆን የተቀነባበረባቸው ምንጮች ሲፈጠሩ የነበሩት ሁኔታዎች በጊዜአያችን ካሉት ሁኔታዎች ጋር ሲተያዩ በጣም የተራራቁ ነገሮች ናቸው ።

2· ከኪነተ ሕግ አንጻር

ፍትሐ ነገሥት በሚመረመርበት ጊዜ ወደ አስቸጋሪ መስመር ይጐትታል ምክንያቱም የፍትሐ ነገሥቱ ቅርጸት ቀላል የሥነ ጽሑፍ ባሕርይን ሥርዐትን እንጂ የሕግንና የኪነተ ሕግን ሥርዐትና ቅርጽ ይዞ አይታይም ። የይዘቱ አመዳደብና የአንቀጾች አከፋፈል የኪነተ ሕግን ሥርዐት ተከትሎ ያልተደላደለ ይዘት ያለውን ምእላዳዊ ቅርጽን ይዘው ይታያሉ ነገር ግን አንድም ከአዘጋጁ እጅ እንደገባ አንድ አጋጣሚ ቅደም ተከተልን ወስደዋል/ይዟል ወይም አንድ ጊዜያዊ ቢጋርን ተከትሎ ተደልድሏል ። በእርግጥ ትርጉም ያለው ፍሬ ነገር መንፈሳዊ ሕጉ ሥጋዊ ሕጉን ይቀድማል ለዚህም እንደ ምክንያት የተወሰደው በጸሐፊው እብነ እል አሳል የነፍስና ሥጋ ግንኙነት ሲሆን ነፍስ ቀድሞ አካል–ሥጋ መከተሉ ነው ።

3· ከሥነ ትርጉም ሥርዐት አንጻር

3·1 ከሥነ ሥልጣናዊና ሥነ ጥበባዊ ትርጉም አንጻር

በመንፈሳዊ ሕግ ክፍሉ – የመጀመሪያው ክፍል በተለይ ከ1–3 አንቀጾች የጉዳዮችን ሥነ ሥርዐታዊ ቅደም ተከተል ሲከተል በሁለተኛው ሥጋዊ ክፍሉ ተቃራኒውን መንገድ መርጦ ይገኛል ።

በመመርመር ላይ የሚገኘው ፍትሐ ነገሥት ግልጥነት ሲያስፈልግ በሃይማኖታዊ ሥነ ትርጉም በአንድምታና በኀብር ማለት በአሊጐርክና ሜታፎሪክ በተለይ ሁለተኛ ክፍል በሥነ ሕጋዊ ትርጉም ማለት በሥነ ሥልጣናዊና ሥነ ጥበባዊ ትርጉም ሳይተረጎም መዋቷል ። በመጀመሪያ ደረጃ ፍትሐ ነገሥት በሥነ ሥልጣናዊ ትርጉም ሥርዐት ለመተርጐሙ ይህ መሰል ሥልጣን ያለው አካል አይኖርም ፍትሐ ነገሥትን በሥልጣኑ ለመተርጐም ወይም አግባብነት ያላቸውን የሥነ ትርጉም ዘዴዎችን ለማስቀመጥ ችሎታ ባለው አንድ ዓይነት አካል ተቀነባብሮ አልታወጀም ነገር ግን ከጊዜ አንጻርም ሆነ ከቦታ አንጻርና ከምንጮች አንጻር ከተለያዩ ምንጮች ከመጡ–ከነበሩ ምንጮች የተቀነባበረ ሕጋዊ ሰነድ በመሆኑ እንዴት ይቻላል? ሊባል ይችል ይሆናል ።

እስከምናውቀው ድረስ ሥልጣናዊ ትርጉም የሚባለው አንድ ሕግ በራሱ ባወጣው አካል በዚያው ዘዴ በተቋቋመው አካል ግን በሌላ አዲስ ቀኖና ሕግ /መተርጐም ሕግ/ የሚሰጠው–የሚብራራበት ትርጉም ነው ። "Eius Est Interpreter, Legem Cuius Est Conder" ሕግን የማውጣት ሥልጣን ያለው ይህን ሕግ የመተርጐም ሥልጣን አለው ።

በርግጥ የቤተክርስቲያን አለቆች በተለይ ሊቃነ ጳጳሳት — ፓትርያር ኮች ያሉት ሕጐችን የመተርጐም ፣ የመሠረዝና ከጊዜው ሁኔታዎችም አንጻር አዳዲስ ሕጐችን የመደንገግ ሥልጣን እንደአላቸው የሚመለከት ድንጋጌ ይገኛል ፣ ሆኖም ይህ ዓይነቱ ድንጋጌ ዕድል ስለ እግዚአብሔር ያለ እምነትን እስከ መሰረዝና ማሻሻል አይደርስም ። ስለ ሁለተኛ ክፍል ግንሊሠራ ይችል ነበር ።

3·2 ከሥነ ሰዋሰዋዊ ትርጉም አንጻር

• በሁለተኛ መንገድ ፍትሐ ነገሥት በሥነ ሰዋሰዋዊ ትርጉም ዘዴዎች መሠረት መተርጐም ይችላል ። ሆኖም ግን በሃይማኖት ሥነ ትርጉም ሥርዐት መሠረት ከመሆን መራቅም አይኖርበትም ።

3·3 ከሥነ አእምሮአዊ ትርጉም አንጻር

ፍትሐ ነገሥትን ለመተርጐም ሥነ አእምሮአዊ ትርጉም ሥርዐተ–ዘዴ መጠቀም አያስኬድም ለማለት ይቻል ይሆናል የመጀመሪያውን ክፍል በሚመለከት ። ሆኖም ፍትሐ ነገሥትን በሥነ አእምሮአዊ ትርጉም ሥርዐተ–ዘዴ የተረጐሙም ሊቃውንት አልፈዋል ።

ይህ ዋነኛ የፍትሐ ነገሥት ትርጉም ዘዴ ነው ። ፍትሐ ነገሥት ቀደም ብሎ እንደተገለጠው ከንባብ አንፃር ግልጥነት የጐደለው ከመሆኑ የተነሣ አብዛኛውን ክፍል ለመርዳት በሐሳብም Ad Sensum ነው ።

ስለዚህ ለፍትሐ ነገሥት የተሻለ ግንዛቤ ሥነ ሰዋሰዋዊ ትርጉም ከፍተኛ ድርሻ አለው ። የሥነ አእምሮአዊ ትርጓሜ ክልል ከሕግ ይዘትና ቅርጽ ግልጥ ካለመሆን የተነሳ የሚከሰቱ ልዩነቶችን ለመፍታት ዳኛ ወይም ሌላ ሕግ ተርጓሚ አካል ጥረት የሚያደርግባቸውን ሥነ ጥበባዊያን ዘዴዎችን ይከላላል ።

የፍትሐ ነገሥት የሥነ ዓላማዊና ሥነ ግባዊ ትርጓሜ ቀኖናት–ዘዴዎች የዳኛን ወይም የሌላ ሕግ ተርጓሚ ችሎታንና ሥነ ጥበባዊ ዝግጅትን ይጠይቃሉ ። የሥነ አምሳል ትርጉም ዘዴዎች–ቀኖናት የፍትሐ ነገሥት ተተርጓሚ ድንጋጌ ከአዲስ ሕግ ጋር የሚጋጭ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ትርጉም አይኖራቸውም ። ይህን መሰል ችግር ቢፈጠር የተሻለው—የሚመረጠው ዘዴ በትውፊታውያን ቀኖናተ ሕግ ልዩነቱን መፍታት ነው።

ስለዚህ ሁል ጊዜ ከሥነ መለኮታዊ ትርጉም ዘዴዎች–ቀኖናትና መሰል ዘዴዎች በስተቀር የሥነ ጥበባዊ ትርጉም ዘዴዎች ከፍትሐ ነገሥት ሰነድ በጣም ርቀው ነው የሚገኙት ምክንያቱም በአንድ በኩል ፍትሐ ነገሥት በአብዛኛው ክፍሉ ከቤተክርስቲያናውያን ምንጮች የተወሰደና በሌላ በኩል በቤተክርስቲያን ጉያ ሥር የተዘጋጀ በመሆኑ በጥቅሉ ሥነ መለኮታዊ ቀለምን ብቻ ተቀብቶ ተገኝቷል ስለዚህም እየአንዳንዱን ጉዳይ የሚተረጉሙ ወይም ከሥራ ላይ የሚያውሉ የቤተክ ርስቲያን ሊቃውንትና መተርጉማን ነባቢያነ መለኮት ናቸውና ።

4· ከሥነ ትምህርት አንጻር—ሥርዐተ ትምህርት አንጻር

ፍትሐ ነገሥት በኢትዮጵያ ልማዳዊ–ባህላዊ ትምህርት ዘርፎች ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ባህላዊ ሥነ መለኮታዊ ትምህርት በሚከተሉት አራት ጉባኤያት እንደሚከፈል ይታወቃል ሀ· ትርጓሜ ብሉይ ኪዳን ለ· ትርጓሜ ሐዲስ ኪዳን ሐ· ሊቃውንት ፍትሐ ነገሥትን ጨምሮ የአባቶች ሥነ ጽሑፎች እና መ)· መጻሕፍተ መነኮሳት

እየአንዳንዱ ጉባኤ የተለያየ ይዘትና ቅርጽ ስለአለው ብዙ ጊዜ የሚያጋጥመው የአንድ ወይም ቢበዛ የሁለቱ ጉባኤያት ሊቅነት ወይም ከእየጉባኤዎቹ የተወሰኑ የትምህርት መስኮች ሊቅነት ተገኝቶ ሲሆን ግን ረጅም ጊዜንና ብዙ ድካምን የሚጠይቅ ቢሆንም አልፎ አልፎ አራቱን ጉባኤያት ያጠናቀቁ ሊቃውንትም ያጋጥማሉ ። እነዚህም ሰዎች "አራት ዓይናች" በመባል ይታወቃሉ/ይጠራሉ ለምሳሌ ከዓመታት በፊት የነበሩ አራት ዓይና ጐሹ[1605]

1605. Ντιμπεκούλου Ζέουντες Εκποίδευσις εν Αιθιοπία,\"Χριστιανική Αγωγή" Dibekulu.Z ፣ ትምህርት በኢትዮጵያ 1967 ገጽ 12

እንግዲህ ወደ ታሪክ ስንመለስ በአጠቃላይ የፍትሐ ነገሥት መተርጉማን–የፍትሐ ነገሥት አዋቂዎች ከሌሎች ጉባኤያት መተርጉማን ወንድሞቻቸው መካከል በሚከተሉት ምክንያቶች ልዩ ሆነው ይተዩ–ይገመቱ ወይም ይቆጠሩ ነበር ።

የፍትሐ ነገሥት መተርጉማን ቁጥር የተወሰነ ነበር ምክንያቱም የፍትሐ ነገሥት ትምህርት ለብዙ ዘመናት ለኅብረተሰቡ በስፋት እንዳይታወቅ በሚል ዓላማ በምሥጢር ይጠበቅ–ይያዝ ወይም ይሰጥ ነበር ማለትም የፍትሐ ነገሥት ትምህርት – ትርጉም ሥልጠና ይሰጥ የነበረው በጠባብ ክልል ለሚገኙ ሰዎች በተለይ በሥልጣነ መንግሥት – በትውልድ ቦታ የማግኘት መብት – አገር የመግዛት – ሥልጣን Exofficio ለሚኖራቸው የመሳፍንትና መኳንንት ልጆች ብቻ ስለነበር ነው ይባላል

ስለዚህም ይህ ትምህርት ይሰጥ የነበረው የተራው ኅብረተሰብ አባል ሊጠጋበት በማይችልበት ቦታ በተለይ በስገነት ተደብቆ ነበር ።

በዚህ ሁኔታም ቢሆን ግን የፍትሐ ነገሥት ዕውቀት ለሌሎች ዜጐች ፈጽሞ ተከልክሎ ነበር ለማለት ባይቻልም በአንጻሩም አገርን ለመግዛት የትውልድ–የውርስ መብት አላቸው የሚባሉት ሁሉ ፍትሐ ነገሥትን መማርና ማወቅ ነበረባቸው ማለቱ አዳጋች ነበር–አይቻልም ነበር ።

ይህም የራሱን ሂደት በሚከተለው መልክ ፈጥሮዋል ።

አንድ አገረ ገዥ ፍትሐ ነገሥትን መተርጐም የማይችል ሆኖ ግን አንድን ክፍለ ሀገር ለማስተዳደር በሚሾምበት ጊዜ ከፍትሐ ነገሥት መተርጉማን — Jurisconsultus አንድ ፍትሐ ነገሥት አውጪ–አማካሪ ባጠገቡ ያስቀምጥና ችግሩ ሲፈጠር ፍትሐ ነገሥትን በማውጣት/በመተርጐም በፍትሐ አስተዳደር ሥራ እንዲረዳው ያደርጋል ።

ስለዚህ ለተነሳው ከፍተኛ የሕግ ጥያቄ በመጀመሪያ የፍትሐ ነገሥቱ አውጪ ትርጉም ይሰጥ ነበር ቢሆንም የአገረ ገዥው የግድ በዚህ የፍትሐ ነገሥተ አውጪ ሐሳብ ታስሮ እንዲወሰን አይገደድም ነበር።

ምዕራፍ አሥራ አራት

የፍትሐ ነገሥት ፣ ብሔረ ሕግ ወቀኖና አባሪዎች

